እንዲህ እንዲህ እያለች ሳታስበው በደመ ነፍስ ነድታ ቤት ስትቆም ነው መድረሷን ያወቀችው። ደመ ነፍስ እንግዲህ ከንቁው አእምሮአችን ሥር ያለው የተንጣለለው ከፊል ንቁና ድብቁ አእምሮአችን ነው የሚባለው። አንዳንዴ በደመ ነፍስ ኖረን በደመ ነፍስ መሞትም አለ። ደመ ነፍስ ስንል በርግጥ አንዳንዴ የሰውን እንስሳዊ የፍላጎት ግፊትንም ለመግለጽ እንጠቀምበታለን። እዚህ ጋ ግን ሰሎሜን ነድቶ እቤት ያደረሳት እንስሳዊዉ ሳይሆን፣ ረቂቁ ከስሜትና ካስተሳሰብ ሥር የተወሸቀው ሌላው የፊታድ መዘውር፣ ስፋቱ የማይታወቀው የአእምሮ ክፍል ነው። ነቅቶ የሚንከላወሰውን አእምሮአችንን በጥልቅ የማንነታችን ውቅያኖስ ውስጥ ተወሽቆ እሱ ነው አሉ የሚያሾረው፣ የሚያሽከረክረውም።

ደመ ነፍስ የነፍስ ደም ነው፣ መልኩ ግን ቀይ አይደለም፣ የነፍስ ነገሮች በቀለም ሳይሆን በሐሳብ ደርዝ ነው የሚገለጹት። ደመ ሥጋ የሥጋ ህልውና እንደሆነ ሁሉ ደመ ነፍስም የነፍስን አኗኗር ይወስናል። ደመ ሥጋ ለሰውነት ሁሉ የሚያስፈልገውን ምግብና ኦክሲጅን ያዳርሳል። ብሎም ካንዱ ክፍል ወደ ሌላው ጠቃሚ መልእክተኛ ንጥረ ነገሮችንና ተወጋጅ ቆሻሻዎችን በልብ እየተገፋ ያመላልሳል ቀን ከሌት። እሱ በቆመበት ቀን ሕይወትም ትቆማለች። ደመ ነፍስም በነፍስ ዓለም ያንኑ ሳይሠራ ይቀራል? ቀን በውን ... ሌት በህልም... አውቀን በንቃት... ሳናውቅ በፍዘት... የቀዳነውን ሐሳብ አመላላሽ ... ባቡራችን ... ቧንቧችን ነው። ሰሎሜ ሥዕሉን ቸኩል ቸኩል እያለች ከመኪናዋ አውርዳ ይዛ ወደ ቤት ስትገባ፣ ቤቱ ዘመዱ ራት ሲያቀራርቡ ነበር የደረሰችው። እህሉ ተጋግሮ እንጀራው፣ ሟችም ተሰናብቶ ምስሉ ነው የቀረው። እንዱ ተሥሎ ሌላውም ተጋግሮ።

ሶፊያም ለብቻዋ ወደ አንድ ክፍል አፓርትመንቷ ነበር የሄደችው። ዊቶን ወደሚባለው ምዕራባዊ ቺካጎ ውስጥ ወደሚገኝ መኖሪያ ቤቶች ወደሚበዙበት ሰላማዊ የከተማው ክፍል ነው የተከራየችው። ሙሉ በሙሉ ዕቃው የተሟላለት ሲሆን፣ ኪራዩ ወደድም ቢል የተከራየችው ለአንድ ወር ብቻ ነው። ወደ ኢትዮጵያ ልትሄድ ስለሆነ ዕቃዋን ሁሉ መልክ መልክ እያስያዘች ነው። የተወሰኑ ዕቃዎቿን መርጣ የዕቃ ማስቀመጫ ክፍል በመከራየት እዚያ አድርጋ ለመሄድ ነው ያሰበችው። የተረፈውን ደግሞ ለበጎ አድራጎት ድርጅት ለመስጠት ለይታዋለች። ሶፊያ ለሰሎሜ የነገረቻት ታሪክ ከሶለን ጋር በነበራቸው ግንኙነት የተፈጠረውን ሁኔታ ለማስረዳት የሚያስችላትን ብቻ ነው። ሶፊያ ለማንም የማትነግረው ታሪክና ገና ብዙ ሥራ የሚያስፈልገው እድንጋይ ላይ ወድቆ እንደተሰባበረ ብርጭቆ ስብርብሩ የወጣ ማንነትም አላት። አንዳንዱን እዚሁ አሜሪካ ትታው ልትሄድ ብትወስንም፣ አብዛኛው ግን እንደጥላዋ አብሮአት መሄዱ አይቀርም። ሲፌልም እየጠፋ፣ ሲነጋ እየመጣ። አንዴ እያጠረ፣ አንዴ ደግሞ እየረዘመ፡፡ ሲለው እየደበዘዘ፣ ሲያሻው ደግሞ እየደመቀ። ሁለተኛው የኢትዮጵያ ጉዞዋ ግን ምን እንዳዘጋጀላት ምንስ እንደሚያደርጋት ማን ያውቃል? ደግሞስ ሶፊያ ለሰሎሜ ከነገረቻት ውጪ የተለየ ዐይነት ሰው ብትሆንስ?

ወጥመድ

መላኩ በማግስቱ ወደ ዱባይ ሊሄድ ዝግጅቱን ጨርሷል። ኮንፈረንሱ የሚጀምረው ሰኞ ሲሆን እሱ እሑድ ለመጓዝ ነው ያሰበው። ማራም ትንሹ ልጇ ጉንፋን እሞት ስለነበር ላለፉት ሶስት ቀናት ከቤት አልወጣችም። ዛሬ ግን ሻል ብሎት እሷም አረፍ ብላለች። ሌሎቹ ሁለቱ ልጆቿ ካባታቸውና ካያቶቻቸው ጋር ወደ ደብረማርቆስና ባሕርዳር ለአንድ ሳምንት ቆይታ ከሁለት ቀን በፊት ስለሄዱ በአንድ በኩል ትንሽ እፎይ ብላ ነው የሰነበተችው። ቅዳሜ ከሰአት በኋላ ከዘጠኝ ሰአት ጀምሮ ከመላኩ ጋር ሸራተን ነበር የቆዩት። ለአንድ ሰዓት ያህል ከዋኙ በኋላ ሳውና ባዝ ወስዷ፣ ማሳጅ አድርጋ ስለነበር ነው መሰል የድካም ስሜት ቢኖራትም እንኳ፣ ለራት ሲወጡ የረጋ ሰውነቷ ሁሉ ተፍታቶአል። ልጁም ያለወትሮው ተኝቶ ቆይቶ ስለነበር አላስቸገረም። ቢያንስ እስካሁን አልተደወለላትም። ምናልባት ሌሊት እንቅልፍ ሊኖራት እንደማይችል በማሰብ ፈርታለች። ከዚህ ዐይነቱ ጥሩ ቀን በኋላ ግን የማትችለው ነገር አይኖርም። ማራና መላኩ አሜሪካ ከመሄዱ በፊት ስለነበራቸው መልካም ትዝታ እያወሩ ሁለቱም ርቧቸው ስለነበር ወደ አንድ የሚያውቁት ፒዛ ቤት ሄዱ።

ማራ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉትን የአእምሮ ህክምና አገልግሎቶች ሁሉ ጎብኝታለች። በተለይ ከሕፃናትና ወጣቶች አንጻር ያለዉን ከፍተኛ ጉድለት ለመቅረፍ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባት እያሰበች ነው። አንድ የሕፃናት የአእምሮ ማእከል ከፍታ እዚሁ አገር ለመሥራትም ልቧ በጣም ተነሣሥቷል። የራሷንም ልጅ ጨምሮ እንደ ኦቲዝም ባሉ የአእምሮ እድገት መዛባትና ዝግመት ላላቸው ልጆች ክብካቤ የሚያደርግና የሕዝቡን ንቃት የሚጨምር ሥራ ለመሥራት ቆርጣለች። ሐሳቧን ለመላኩ ስታጫውተው ሙሉ ድጋፉን ነበር የሰጣት። ደግሞም የትዳሯ ጉዳይ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ተጨንቆ ጠይቋታል። ምክንያቱም ምንተስኖትም ሆነ የሱ ቤተ ሰቦች በጥብቅ የሚቃወሙት ሐሳብ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። ትዳሩ ቢኖጋ ደግሞ የልጆቹ ጉዳይ አሳሳቢ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ ስለ ኦቲዝም የተወሰነ ቢያነብም አሁንም ብዙ ጥያቄ አለው። እናትም የሙያውም ባለቤት ስለሆነች ከማራ የተሻለ ስለዚህ ጉዳይ ማንም ሊያስረዳው አይችልም።

"ግሪ በናትሽ ላደርቅሽ ነው እንግዲህ።"አለና መላኩ ጥያቄውን የጀመረው። "የባቢ ሕመም ኦቲዝም ነው አይደል ያልሽኝ። ለማንበብ ሞክሬ ነበር ግን ያን ያህል አልገባኝም። ምን ዐይነት በሽታ ነው? ማለቴ ስሙ ራሱ አይገባኝም እኮ!" አላት ለማወቅ ያለው ጉጉት በአጠያየቁ እየታየበት።

"እም ... ም ምን መሰለህ መልዬ ... ኦቲዝም አንድ በሽታ ነው ማለት አይቻልም። በአጠቃላይ ተመሳሳይ መገለጫ ያላቸው ከአእምሮ እድገት መዛባት ጋር የተያያዙ ችግሮች የጋራ ስም ነው። ኦቲዝም የሚለው ስም 'አውቶ' ማለትም የአንድ ሰው እኔነት (ራስ) ከሚለው ቃል የወጣ ሲሆን፣ ኦቲዝም የተባለበት ምክንያት ይህ ችግር ያጋጠማቸው ሕፃናት አብዛኛው ዓለማቸው በራሳቸው ውስጥ ስለሚሽከረከር ነው። አሁን እየህ አእምሮው በትክክል የሚሠራ ሰው ውስጣዊውንና ውጫዊውን አለም አመጣጥኖ ነው የሚኖረው። ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት ግን ልክ ሳጥን ውስጥ እንዳለ ሰው ብዙውን ጊዜ የሚያሳልፉት በራሳቸው ጭንቅላት ውስጥ ነው። ከዚህም የተነሣ ለሰው ግሬ የሚያጋባና ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነ የባሕርይ፣ የቋንቋና የማኅበራዊ ግንኙነት ጉድለቶች ይታዩባቸዋል። ደግሞም በአብዛኞቹ ላይ የአእምሮ ዝግመት ይከሠታል። እንደ ባቢዬ በጣም የከፋ የአእምሮ ዝግመት ያለባቸው ከሆነ፣ ሕመሙን የበለጠ የከፋ ያደርገዋል። ሁሉም ልጆች በሁሉም አቅጣጫ በተመሳሳይ ደረጃ ጉድለት ስለማይኖራቸው፣ ኦቲዝም ያለበት እያንዳንዱ ልጅ አንድ ዐይነት ሊሆን አይችልም።" ብላ እየቀዘቀዘ የነበረውን ሻይዋን ፉት አለች።

"ቆይ እኔ ምልሽ ለምሳሌ ባቢዬ እንደ ሌላ ልጅ ስትይዢው ደስ አይለውም ወይም በቃ ግድም አይሰጠው። ደግሞም ሁሌ ከጁ የማትለየው ኳስ አለችው፣ ለምንድነው ነው እንደ ሌላ ልጅ እሷን ጥሎ በሌላ ነገር የማይጫወተው? አንዳንዴ እኮ ጭንቅ ይለኛል ትንሺዬ ነገር ይዞ በዛች ስንት ሰዓት ሙሉ ሲጫወት፣ ከተንካችበት ደግሞ እንዴት እንደሚበሳጭ!" አለ ጥያቄውን መቋጨት እያቃተውና የተቀመጠበት መቀመጫ እንዳልተመቸው ሁሉ ለመስተካከል እየሞከረ።

"ምን መሰለህ ባጠቃላይ ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች ለውጥ አይወዱም፣ ውጫዊ ለውጥ ውስጣዊ ዓለማቸውን ስለሚያውኩባቸውም ሊሆን ይችላል። ስሜታቸው ደግሞ በጣም ስስና ስል ነው። ለምሳሌ ብርሃን፣ ድምፅ፣ ሽታ፣ ጣዕም ወይም ያንድ ነገር ልስላሴና ሻካራነት ለውጥ ለነሱ የመቆንጠጥ ወይም ከፍተኛ የሆነ ድምፅና ብርሃን እኛን የሚረብሸንን ያህል ነው የሚረብሻቸው። አንዳንዴ ደግሞ በራሳቸው ዓለም ውስጥ ገብተው ስለሚጠፉ በቃ እስከ መኖርህም ነው የሚረሱህ። ሌላው ቀርቶ ራሳቸውን እንደ ሦስተኛ ሰው የሚቆጥሩበት ጊዜም አለ። ለምሳሌ ባቢዬ መጥቶ ባቢ ካካ መጥቶበታል ሊለኝ ይችላል። ከሰው ይልቅ ከእንስሳቱና ግዑዛን ከሆኑ ነገሮች ጋር መጫወት ነው ደስ የሚላቸው። ምናልባት

ከሰው ይልቅ እንስሳቱና ግዑዛን ነገሮቹ የነሱን ፍላጎት ስለማይጫኗቸው ሊሆን ይችላል። ከሌሎች ልጆች ጋር አብረውም ሆነ እየተወዳደሩ መጫወት አይችሉም። በቀላሉ ሊጐዱም ስለሚችሉ ሁሌም ጥንቃቄና የተለየ ሥልጠና ሳትታክት ልትሰጣቸው ይገባል" አለች፡፡

"ምግብስ ላይ አሁን ባቢዬ ከተፈጨ ሙዝና ገንፎ በቀር ምንም አይበላልሽም፣ ይህ ለምን እንደሆነ ይታወቃል?"

"ምን መሰለህ ቅድም እንዳልኩህ አንደኛ ለውጥ ፈጽሞ አይወዱም፣ በጣም ነው የሚረብሻቸው። ሁለተኛ ደግሞ ለጣዕም፣ ለሽታና በማንኛውም ነገር ልስላሴና ሻካራነት ውስጣቸው በቶሎ ነው የሚረበሸው። ከለመዱት ውጪ የሆነ ሁሉም ነገር ከምታስበው በላይ ነው የሚያውካቸው። በዚያ ላይ ደግሞ አሁን በባቢዬ ሁኔታ የአእምሮ ዝግመቱም ስላለ በቃ የሚፈልገውን ማወቁም ከባድ ነው።"

"ግን መንስኤው ይታወቃል? ማለቴ ምንድነው የሚያመጣው? አንድ አንድ ሰዎች ክትባት ነው የሚያመጣው ይላሉ፣ በዘርስ ይተላለፋል?" አለ መላኩ አሁንም የጥያቄው ቋት ገና ሳይጎድል።

"እም..ምም ይሄ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል አንድ መንሥኤ አለው ማለት አይቻልም እስካሁን ባለው ጥናት መሠረት። ደግሞ እንዳልኩህ አንድ ዐይነት ሕመምም ነው ለማለት አዳጋች ነው። ከዛ በተጨማሪ ብዙ አጨቃጫቂና ግር የሚያሰኙ ቲዎሪዎችና መንሥኤ ተደርገው የሚወሰዱ ጉዳዮች ቢኖሩም፣ አንዱም ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠ ነው ለማለት ይከብዳል። ሕክምናውን አዳጋች የሚያደርገውም እሱ ነው። የክትባቱ ጉዳይ ገና የተረጋገጠ አይደለም። እስካሁን ያሉ ጥናቶች አሉታዊ ምልከታ ነው ያላቸው። ያው ለክትባት ካምፓኒዎችም ትልቅ ቢዝነስ ስለ ሆነ ብዙ ሰዎች ያሉትን ጥናቶች ከልብ አይቀበሉዋቸውም። ብዙ 'ጀነቲክ' የሆኑ መንሥኤዎችና ጠቋሚ ነገሮች ቢኖሩም፣ አንድ የታወቀ 'ጂን' ነገሩን ያመጣዋል ብሎ ለማስረዳት አልተቻለም። በዘር የመሄዱም ጉዳይ ያንን ያህል የታወቀና የተረጋገጠ መልክ ያለው ሆኖ አልተገኘም። ከምግብ ጋር የተያያዙ ማጻበሪያ፣ ፀረ አረምና ፀረ ተባይ መርዞች፣ ምግብ ሲታሽግ ሳይበላሽ እንዲቆይ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውል ኬሚካል . . . ወዘተ የሚወንጀሉበት ሁኔታ አለ። እናት በርግዝና ጊዜ ወይም ሕፃኑ በጣም ትንሽ በነበረ ዕድሜው ወቅት በተለያዩ ቫይረሶች ተጠቅቶ ሊሆን ይችላል የሚል መላ ምትም አለ። ግን ያው አሁንም እንዳልኩህ ይሄ ነው ተብሎ በርግጠኝነት ሊጠቁም የሚችል መንሥኤ ግን ገና አልተገኘም።" አለች ረጅም ማብራሪያዋን ገታ አድርጋ።

"ሕፃኑ ስንት ዓመት ሲሆነው ነው ነገሩን በርግጠኛነት ማወቅ የሚቻለው? ምንድነው አንድ ሕፃን ኦቲዝም አለበት ለማለት የሚያስችለው? አንቺ በስንት

ዓመቱ ነው ባቢ ይህ ችግር እንዳለበት ያወቅሽው?" አለና እቃ የሚሰበስበውን አስተናጋጅ ሌላ ሻይ እንዲያመጣለት ነገረው

"ትልቁ ችግር ምን መሰለህ? ማንም እናት ወይም ወላጅ ይህንን ችግር በቀላሉ አምኖ መቀበል ስለማይፈልግ ችግሮቹን እንኳ እያየ እንዳላየ ነው የሚሆነው። ሲነገረውም አይቀበልም። እኔ እንኳን አስበው ራሴ የሕፃናት አእምሮ ሃኪም ሆኜ በቃ ዝግጁ አልነበርኩም። የመጀመሪያ ልጅህ ካልሆነ ነገሩን ቶሎ ለማወቅ ይቀልላል። የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን ግን ከባድ ነው ማነጻጸሪያ ስለማይኖርህ። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ልጅ ላይ የምታየው ምልክት ስለሚለያይ አንዳንዴ አስቸጋሪ ያደርገዋል። ከዚያ በተረፈ ግን አንዳንድ ልጆች ላይ ደህና ማደግ ጀምረው ስድስት ወርና አንድ ዓመት ሲሆናቸው ነው ነገሩ የሚጀምረው። ይህ ደግሞ አልፎ አልፎ የሚታይ የኦቲዝም ዐይነት ነው።

"በአጠቃላይ ግን ብዙ ወላጅ ነገሩን በትክክል ለይቶ ወደ ህክምና ሲመጣ ሦስት ዓመትና ከዚያም በላይ ይሆናል። ከሁለት ዓመት ጀምሮ ነገሩን ልብ ካልከው ከሚታሰበው በላይ ግልጽ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ምልክቶቹ ሕፃኑ አንድ ዓመት ሲሆነው ጀምሮ በደንብ ይታያሉ። ልጆቹ ለመታቀፍና ለመያዝ አንድም ግድ የሌላቸው ይሆናሉ ወይም እሪ ብለውም ሊያስቸግሩ ይችላሉ። አፍ ቶሎ ላይፈቱ ወይም በትክክል ላይፈቱ ይችላሉ። የምግብ አመጋገብና እንቅልፋቸው የተዛባ ይሆናል። አንዳንዴ በቃ በራሳቸው ዓለም ውስጥ ገብተው ይጠፋሉ። ለድምፅም ሆነ ጤነኛ የሆነ ሕፃን በቀላሉ መልስ ለሚሰጥህ ነገር መልስ አይሰጡም። በቋንቋ፣ በግንኙነትና በባሕርይ ዙርያ ወይ የዘገዩ ወይ የተለዩ ነው የሚሆኑብህ። አለበለዚያ ለውጪው ዓለም ደንታ ቢስና ቁጡ ዐይነት ይመስሉሃል። ከአራት ሦስቱ ታማሚዎች ወንድ ሕፃናት ናቸው። አእምሮአቸው ዘገምተኛ ከሆኑ ደግሞ ችግሩ የባሰውን ለወላጅ ከአቅም በላይ ሊከብድ ይችላል። የአእምሮ ዘገምተኛነት ደግሞ በብዙዎቹ ላይ ይታያል።"

"ዋው! የሚገርም ነገር ነው። ቶሎ ማወቁና አለማወቁ ለውጥ አለው? ማለቴ ግን በአጠቃለይ ህክምና አለው ወይስ ሁሌም እንደዚሁ ነው የሚኖሩት?" አለ አሁንም ጥያቄዎቹ እየበዙበት በውስጡ፡፡

"አዎን ... በጣም ለውጥ አለው... ነገሩን በጊዜ ማወቁ ሕፃናቱን በቋንቋም ሆነ በሌሎቹ ማኅበራዊና አእምሮአዊ እድገቶች ለመርዳትና ቶሎ ወደ መንገድ ለመመለስ ቁልፍ ነገር ነው። በጣም ካደጉ በኋላ ወደ ህክምና ለሚመጡ ልጆች ሊደረግ የሚችለው ነገር በጣም ውሱን ነው። ህክምናው ዘርፈ ብዙና የብዙ ባለሙያዎችን ድጋፍ የሚፈልግ ከመሆኑም በላይ ወላጆችንም ማሳተፍ ይኖርበታል። እንደ ወባና ሳንባ ነቀርሳ የሚድን ሕመም አይደለም። ብዙ ሕፃናት ከችግሩ ጋር ምናልባት ዕድሜ ልካቸውን መታገላቸው አይቀርም። ህክምናው

በልጆቹም ሆነ በቤተ ሰባቸው ላይ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ ሲሆን ያልታከሙ ሕፃናትና ወላጆች ሥቃይ ግን በጣም ልክ የለውም።" አለች ከቦርሳዋ ውስጥ የእጅ ማጽጃ ፈሳሽ እያወጣች።

"ህክምናው ትምህርትን፣ ለኑሮ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ችሎታዎችን፣ ማኅበራዊና ግንኙነታዊ ዐቅምን ማዳበርንና አስቸጋሪ የሆኑ ባሕርያትን ማረቅንም ያጠቃልላል። በመድኀኒት የሚደረገው ነገር በጣም ውሱን ነው። ነገሩን መከላከል የሚቻልበት መንገድ ገና አልታወቀም። ለዚህም ነው መንሥኤውን ማወቅ የሚያስፈልገን። የባሲ ግን ከፍተኛ የአእምሮ ዝግመትም ስላለበት በጣም ከባድ ነው። ምናልባትም የዕድሜ ልክ እገዛ ያስፈልገዋል። የተወሰኑ ነገሮችን ለራሱ ማድረግ ከቻለ እንኳ ትልቅ ድል ነው።" ብላ እንባዋ እያቀረረ ትክዝ ብላ እጇን እንዳጣመረች ማውራቷን አቆመች። የሻዩን ስኒ እየነካካችና በጣቷ መታ መታ እያደረገች ሳታስበው እንባዋ ዱብ ዱብ አለ።

መላኩም ግራ ገባው ምን ማለት እንዳለበት። "አ ይቅርታ... ማሪ.... እምም... " ብሎ ምን ማለት እንዳለበት እርግጠኛ ስላልነበረ ጀርባዋንና ትከሻዋን ማሻሸት ጀመረ፡፡

"አይ መሌ ... እንዲያው እናት መሆን እንዴት ከባድ መሰለህ? ብዙ ነው ያለቀስኩት። አንዳንዴ ራስህን ትኰንናለህ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከፈጣሪ ትጣላለህ። ከዚያ ደግሞ ቁጣ ቁጭት.. ምን ልበልህ!... ሃኪም መሆንህም ምንም አይጠቅምህም። ደግሞም እንደገና ለምን እኔ የሚለውን ጥያቄ ይዘህ ሳትጨርስ የባሰ ብዙ ችግር ታይና... ለምን ሌላውስ ትላለህ። ፈተና ነው ብቻ" ብላ በረጅሙ ተነፈሰች።

"አይደል ማሪ... በጣም ከባድ መሆን አለበት መቼም። አንቺ ግን ስንት ዓመቱ ላይ ነው መጀመሪያ ያወቅሽው?" አለ አሁንም ከመጠየቅ በቀር ምን ማድረግ እንዳለበት ስላላወቀ።

" አሁን ወደ ኋላ ሳየው ስድስት ወሩም ላይ ብዙ ምልክቶች ነበሩት። በቃ እንደ ሌሎቹ ልጆች አይሥቅም፣ ስታቅፈው ወይ ይነጫነጫል ወይም ደግሞ መኖርህንም አያስብም። በቃ ሁሉም ነገሩ ደግሞ የዘገየ ነበር። በመጨረሻም አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሲሆነው ጨክኜ ወስጄ ሳስመረምረው ሃኪሞቹ ትልቅ ጥርጣሬ ቢኖራቸውም ገና ሕፃን ስለሆነ ትንሽ እንድንታገሥ ነገሩኝ። መጨረሻ ላይ ግን ሁለት ዓመት ከስምንት ወር ሲሆነው በትክክል ኦቲዝም እንዳለበት ተነግሮን ህክምናውን ጀመርን። እሱ ብቻ ሳይሆን የምንተስኖትም እኅት የመጀመሪያ ልጇ እንደሱ ባይከፋም፣ ተመሳሳይ ችግር እንዳለበት ነው የተረዳነው። ያው ችግሩ ሲኖርብህ ዐይነህ ስለሚከፈት በየቦታው ይታይሃል።" ብላ የቀረውን ውሃ ከጠርሙሱ ወደ ብርጭቆው ሞላችው።

"እኔ ምልሽ ግሬ የሲቲ ስካን ወይም ኤክስ ሬይ ምናምን ምርመራ ሲደረግ አንጎላቸው ላይ ኦቲዝም ከሌለባቸው ሕፃናት የተለየ ነገር ይገኛል?" አለ መላኩ።

"እም ... ም... የተወሰኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአንጎላቸው ውስጥ ያሉ የነርቭ ሴሎች ያላቸው ትስስርና ግንኙነት በትክክል ያልዳበረና የሳሳ ነው የሚባለው። በአጠቃላይ የኔትወርክ ችግር ነው እንደ ማለት ነው። ግን ይህም ገና ብዙ ሪሰርች እየተሠራበት ያለ ነገር ነው። አንዳንዴ ደግሞ እኮ ያስገርሙሃል። በጣም ከደኅና ልጆችም በላይ የዳበረ የአእምሮ ክፍልም አላቸው። ወይ በሙዚቃ ወይ በሂሳብ ወይ በሥዕል የተለየ ችሎታ የሚያሳዩ ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች አሉ። ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ቡድኖች ኦቲዝም በሽታ ሳይሆን የሰብእናና የአእምሮ ልዩነት ነው ብለው ይሟገታሉ። ልጆቹ መታከም ሳይሆን፣ እንደ ማንኛውም ሰው ታይተው እገዛ በሚያስፈልጋቸው ነገር ላይ ብቻ ነው መረዳት ያለባቸው ብለው ያምናሉ። የሆነው ሆኖ ችግሩ በቤቱ ያለበት ሰው ብቻ ችግሩን ያውቀዋል።" አለች ሰዓቷን እያየች።

"መሽ አይደል? ኧረ እንሂድ... ዛሬ መቼም አስለፈለፍኩሽ።" ብሎ አስተናጋጁን ጠራ ሂሳቡን ለመክፈል። "እኔ ምልሽ ግሬ... በተለይ አበሻው ላይ ኦቲዝም እየበዛ ነው የሚባለው እውነት ነው? በተለይ በአሜሪካ አገር?"

"ሰው እንደዚያ ይላል። ነገሩ አበሻ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ አሜሪካን አገር ባጠቃላይ እየበዛ እንዳለ የሚያምኑ ብዙ ሰዎች አሉ። ግን ደግሞ አሁን ነገሩን የበለጠ ስላወቅነውና ትኩረት ስለተሰጠውም ነው የበዛ የሚመስለን የሚሉም አሉ። እርግጠኛ ነኝ እዚህም አገር አገልግሎቱ ቢኖርና ህክምናው ቢያድግ፣ ነገሩ ከምናውቀው በላይ ብዙ እንደሚሆን። አብዛኛው ሰው እኮ ስለሚያፍርና አቅሙም ስለማይፈቅድ በቃ ልጁን እቤት አፍኖና አስሮ ነው የሚያስቀረው። ብዙ መንገድ ላይ ወድቀው የሚለምኑ ሕፃናትም ይኖሩ ይሆናል። እርግጠኛ አይደለሁም።" አለች ግሬ ዕቃዋን እየሰበሰበች። ከዚያም ሂሳባቸውን ከፍለው ወደ መኪናቸው አመሩ።

ከዚህም በላይ ግሬን ያስለቀሱ ያሣቁና ግራ ያጋቡ ብዙ ጥያቄዎችንም ነበር መላኩ የጠየቃት። የሚገርመው ግን ከቀኑ ሳውናና ዋና ይልቅ እራት እየበሉ የተጫወቱት ጨዋታ ነበር ከላይዋ ላይ አንዳች ሸክም የተነሣላት ያህል ለነፍሷ ዕረፍት የሰጣት። መላኩ ግን በመስኮት አሾልቆ እንዳየው አስፈሪ እስር ቤት ያህል ነው የተጫወቱት ነገር ልቦናውን የተጫነው። ግሬ እናትና ሃኪም ሆና ሌላው ሌላው ሕመም ሳይቆጠር ከኦቲዝም ጋር ብቻ የምታደርገው ትግል ምን ያህል ሸክም ተሸክማ እንደምትኖር አሳይቶት ከልቡ ነው ያሳዘነችው፣ ደግሞም ያደነቃት። በዚህ ላይ እንደ ምንተስኖት ያለ ባል ሲጨመርበትማ አይጣል!

እቤት እንደገቡ ነበር ባቢ ከእንቅልፉ የነቃው። ማንም ሊያባብለው

አልቻለም፣ ምን እንደሚፈልግም ማወቅ አልቻሉም። ግሬም ለሊሊቱ ስራ ራቷን እያዘጋጀች አቅፋው ለማባበል ወዲያ ወዲህ ማለት ጀምራለች። በግራ ደረት ላይ ሆኖ ተመሳሳይ ማባበያ መዝሙር እየዘመረችለት ስታወዛውዘው ረጋ ይላል። መላኩም መሸቶ ስለነበር ጠጋ ብሎ ጉንጩ ላይ ሳም አደረገና፣ "ግሬና በይ ሰላም እደሪ። ያው ምንም ነገር ቢያስፈልግሽ ማርቆስ አለ። እንደገባሁ እንደውላለሁ። በጣም ነው ደስ ያለኝ ጥሩ ጊዜ ነበረን። እንግዲህ በርቺ ..አይዞን" ብሎ ወጣ።

ወደ ቤቱ ሲመለስ ደግሞ ነገሩን ሁሌም ከሚበላው ሀገራዊና ማኅበራዊ አስተሳሰብ አንጻር ማሰቡ አልቀረም። በትክክል ካላደገና ካልዳበረ አንጎል የተነሣ በኦቲዝም ሕፃናት ላይ የሚታየው ችግር፣ በኅብረተሰብ ደረጃም ሳይታይ አይቀርም የሚል መላምታዊ አሳብን ትንሽ አውጠነጠነ። በማጥን ውስጥ ያለ ጭንቅላትና ከራሱ ውጪ ላለው ዓለም ዝግ የሆነ። ውስጡና ለማንም የማይገባ ቋንቋ፣ ተደጋጋሚና ትርጉም የለሽ ባሕርይ፣ የተዛባ አስተሳሰብና ማኅበራዊ ግንኙነት ኦቲዝም ያለበትን አእምሮ በትክክል ይገልጸዋል። ዝግመተ አእምሮ ሲጨመርበት ደግሞ ነገሩ ይወሳሰባል ያለችውም ትዝ አለው። ቶሎ ተደርሶበት በብዙ ባለሙያዎች ካልታገዘ ደግሞ የሌላ ሰው ጥገኛ መሆንና አስቸጋሪ የሆነ ኑሮ ነው ውጤቱ ያለችውም እንደገና አንቃጨለበት።

በእርግጥ በአፍሪቃውያን ድምር አስተሳሰብም ላይ ከኦቲዝም ያልተለየ ዝብርቅርቅ ያለ እድገትና የአስተሳሰብ መዛባት ያለ መሆኑ አይካድም። አኗኗራችንም የኦቲዝም አእምሮ ከሚፈጥረው አኗኗር ብዙም ርቆ አልታየው። በርግጥ ኦቲዝም ያለበት ልጅ ችግሩን ማወቅም ማመንም እንደማይችል፣ የኛም ማኅበረ ሰብ ለዚህ ከኦቲዝም እጅግም ለማይለየው የአስተሳሰባችን በሽታ የነቃ አይመስልም። የሕዝብ አስተሳሰብና አመለካከት በትክክል ካልዳበረና ካልተቃኘ ማኅበራዊ ኦቲዝም ሊከሠት እንደሚችል ገመተ። ለለውጥ ዝግ የሆነና የግንኙነት መሥመሩ የተምታታበት አስተሳሰብ።

መላኩ ነገሩን ሙሉ በሙሉ አዳብሮ ጥርት ያለ መላ ምት ለማውጣት አልቻለም እንጂ እንደ አገር ለመለወጥ የምናደርገው ትግል ከማኅበራዊ ኦቲዝም ጋር ሳይሆን እንደማይቀር ግን ሰግቷል። የተጫወቱት ጉዳይ ከአእምሮ አኳያ ሊሠራ ባለው ሥራ ላይ ትልቅ ሞዴልና ምሳሌ የሚሆን ነገር ሆኖ አግኝቶታል። ለጉዞው የሚሆን ሻንጣውን እያዘጋጀም ይሄንኑ ሲያስብ አመሸ።

በማግስቱ ወደ ዱባይ ሲሄድ አየር ማረፊያ ያደረሰው ማርቆስ ነበር። ወደ ውስጥ ገብቶ ሲለያዩ "ማርክ አደራ የግሬን ነገር። ሰዎቿም አገራቸው ሄደዋል። በቻልከው ጊዜ ሁሉ አግኛት። እሷ ምንም ነገር መጠየቅ አትወድም፣ ሰው ማስቸገር ነው የሚመስላት። እነሶሲም ያንተው ኀላፊነት ናቸው። ከፍያው ከዱባይ እኔ ነኝ ያለ ...ምን መሰለህ?" አለ እየሳቀ።

"እ ... ዱባ ብቻ እንዳትለኝ። በል አትፈላሰፍ። እንደገባህ ደውል። ስማ ሰውዬው ደግሞ እዚያ ቀላል ነው ወዳሜሪካ መደወል። ስሎሜን ልታገኛት ሞክር። ኀዘኑ በጣም ስለጐዳት ባትመልስልህም ተስፋ ሳትቆርጥ ደጋግመህ ሞክር። ታውቃለህ ምን ያህል ምስኪን እንደሆነች? እዚህ ያለውን ለኔ ተወው። በል ጉድ ላክ እሺ." ብሎ ማርቆስም እየሳቀ ተለየው። አውሮፕላኑ ውስጥ ከገባ በኋላ ነበር ዓለም አቀፍ በረራ ካደረገ ምን ያህል እንደቆየ ያስተዋለው። ደክሞት ስለነበር ለመተኛት ቢሞክርም፡ ብዙም ሳይቆይ አጠገቡ ተቀምጣ የነበረች አንዲት ወጣት አበሻ ዕረፍት አልሰጥ ብላው እንቅልፉን አጠፋችበት። እሷ የለመደች የዱባይ ነጋዴ ስትሆን ከሰው ጋር ካላወራች የአውሮፕላኑ መንገድ አያልቅላትም። መተኛቱ የማይሆን ሲሆንበት የምታወራለት ወሬ እምብዛም ስላልጣመው ላፕቶፑን አውጥቶ ካየው ብዙ ጊዜ የሆነውን የጋንዲን የሕይወት ታሪክ የሚተርከውን ፊልም ማዳመጫዉን ጆሮው ውስጥ ሰክቶ ማየት ጀመረ።

መታጠቢያ ክፍል ደርሳ ስትመጣ እሱም ፊልሙ ላይ ተጥዶ ስለ ነበር ከግራዋ ያሉትን ዕድሜያቸው ጠና ያሉትን ሰው ማናዘዙዋን ተያያዘችው። መላኩ ሁሌም የሚገርመው በሄደበት ሁሉ አብዛኛው ፈረንጅና ሌላው የውጪ ሰው አውሮፕላን እስኪገባም ሆነ አውሮፕላን ውስጥ ሆኖ የሆነ ነገር ያደርጋል። ወይ ንባብ ወይ ዕረፍት። የኛ ሰው ግን በአብዛኛው ወይ ወሬ ነው ወይ አየሩ ላይ አፍጥጦ ነው ጊዜው የሚያልፍለት። ዱባይ ደርሰው ሲወርዱ አውሮፕላን ጣቢያው መቼም አሜሪካም ሆነ አውሮጳ ካየው ሁሉ የበለጠ ሆኖ አገኘው። ትልቅነቱና ውበቱ።

የተባበሩት ዐረብ ኤምሬትስ እንደ አገር ከተመሠረተች አርባ ዓመት ያልሞላት ቢሆንም፡ እድገታቸው ይሄ ነው የሚባል አይደለም። እንደ አውሮጳና አሜሪካ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝት መጥቀው፡ በትምህርት ልቀው ያገኙት እድገት እንዳልሆነ ያስታውቃል። እንደ እስያውያን በጥረትና የምዕራቡን ሥልጣኔ በመቅዳትም የመጣ አይመስልም። እዚህ ትልቁ የሥልጣኔ መቅጃ የሆናቸው የነዳጅ ዘይት ይመስላል። ግን ደግሞ ገንዘብ በትክክል ካልያዙት ያጋድላልም ያቆረቁዛልም። የመሪዎቻቸው ባለራእይነትና ገንዘቡን በሕዝባቸውና በአገራቸው ላይ ማፍሰሳቸው የፈጠረው ተአምር ሳይሆን አይቀርም። ብዙ የአፍሪቃ አገሮች በተለይ እንደ ዛየርና ናይጄሪያ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል የሀብት ደኻ አልነበሩም። የመሪዎቻቸው የገንዘብ ፍቅርና የሰዉን በተለይም የዜጎቻቸውን ክቡርነት አለማወቅ ዛሬም የስዊዝን ባንክ አደላቢና የሠለጠኑትን አገሮች የጦር መሣሪያ ሸማች አድርጎ በድኽነት እንዲማቅቁ አድርጎአል። መላኩን የገረመው እዚህ አገር ያሉ መሪዎች እንዴት በትልቁ እንደሚያስቡ ነው። በዓለም ረጂሙ ሕንጻ፡ በዓለም ትልቁ የገበያ አዳራሽ፡ ትልቁ ሰው ሰራሽ ደሴትና ሌሎችም ቱሪስቶችን የሚስቡና ትውልዱን በዓለም መድረክ ከፍ ብሎ ራሱን እንዲያስብ የሚያደርጉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ከብዛትና ከትልቅነት ባሻገር ጥራትንም ቢሆን እዚህ አገር ባህላቸው ለማድረግ ተግተው እየሠሩ እንዳለ ያስታውቃል። ከጥንት የነበሩት የአገሬው ሕዝብ በብዛቱ ከሃያ በመቶ ቢሆንም የሃገሬ ዜጎች የሀብቱ ሁሉ ተጠቃሚና የምቾቱ አጣጣሚ እንዲሆኑ ነው የተደረገው። ቢዝነስ እንኳ የውጪ ዜጋ ሲከፍት እስከ 50 በመቶ ያለው ድርሻ በሀገሬ ዜጎች እንዲያዝ ነው የሚያደርጉት። ምድረ በዳውን ያለሙት በእስያውያንና በሌሎች አገር ዜጎች ነው። እንደ አሜሪካና ፈረንሳይ ያሉ አገሮችን ለከለላነት ነው የሚጠቀሙት። መቶ ሺህ አካባቢ እንግሊዛውያንና ሌሎችም እጅግ የተማሩ ያውሮፓና ያሜሪካ ዜጎች እንዲኖሩ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል። እንደዚህ ባይሆን ይህ አገር በረሓና ለምንም የማይሆን ነበር። የኛ ሃገር ሰዎች ግን ከጥቂት በንግድ ከተዋጣላቸው ሰዎች በቀር መብታቸውን ያጡ የቤት ሠራተኞችና ተሯሩጦ አደር ናቸው። ብዙ የመብት ገፈፋና ግፍ ይፈጸምባቸዋል። የድኻ አገር ሰው መሆን አበሳው የትም ቢሄድ አለመከበሩ ብቻ ሳይሆን አለሁ ባይም የሌለው መሆኑ ነው። የኑሮው ምሬት ሲብስባቸው አጠር ያለ አቋራጭ ፍለጋ አያሌ ሴቶቻችን ሴተኛ አዳሪነቱን ተቆጣጥረውታል ነው የሚባለው። እዚህም በሌላም ዐረብ አገሮችም።

መላኩ ይህንን ሁሉ ያጤነው ባጭር ቆይታው ሲሆን፡ እንደምንጊዜውም የአገሬውን ሰዎች አስተሳሰብና አመለካከት ለመረዳት ሞክሮ ነበር። በምንም መለኪያ የሠለጠኑና በአእምሮአቸው የበለጸጉ ሕዝቦች ናቸው ማለት አይቻልም። ያንን ግን እውን ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ በትምህርት፡ በባህልና በሳይንስ አገራቸው ላይ ገንዘባቸውን እያፈሰሱ ስለሆነ፡ ከአንድ ትውልድ በኋላ በዚህ ከቀጠሉ ሥልጡን ከሚባሉት አገሮች መደዳ መመደባቸው አይቀርም። ሰው በሰውነቱ የማይከበርበት አገር አይደለም። ሃይማኖትና ከየት አገር ነው የመጣው የሚለው የሰውን ዋጋ ይወስናል። አገሬዎቹም እንደ ብዙ ዐረቦች በገንዘብ ውስጥ የተደበቁ ኋላቀር ባለጌዎች ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ነገር ግን ትልቅ የሚያስብና ጥራት ላይ አተኩሮ የወደፊቱን በሰፊው የወጠነ መሪ ያለው ሕዝብ መለወጡ አይቀርም።

የሥልጣኔ ትልቁ መለኪያው ገንዘብ ሳይሆን ለሰው ልጅ ያለን ክብርና እውነተኛ ሰብአዊነት ነው። አፍሪካውያን ግን ገና የራሳችንንም ሕዝብ ያላከበርን ዓለማችን ኪሳችን፡ መለኪያችን ድሎታችን የሆነን ስለሆነ፡ ብዙ መንገድ መሄድ ሳይኖርብን አይቀርም። መሪዎቻችንም የኛው ውጤት ስለሆኑ ምርጫን አሸንፈው እስከ ቤተ መንግሥት ቢደርሱም፡ ራሳቸውን ማሸነፍ ሳይችሉ በሌላ ይተካሉ። ከራሳቸው በላይ ሕዝባቸውን፡ ከምቾታቸውም በላይ መጪውን ትውልድ ማስበለጥ እስኪችሉ ያለወታደር አደባባይ መውጣት የማይችሉ እንደባነኑ የተኙ፡ እንደ ተጀሩ የመሰኪኑ ነገሥታት ሆነው ይቀራሉ።

መላኩ በዱባይ ጉዞው የሕይወትንና የሰዎችን አስተሳሰብ ሌላ ገጽታ ያየበት ጊዜ ነበር። ሥልጠናው ብዙም አድካሚ አልነበረም። ብዙ ትርፍ ሰዓት

ስለነበረው ዱባይንና አቡዳቢን ዞር ዞር ብሎ ማየት ችሎ ነበር። የማርቆስ ጓደኛ የሆነው ሳምሶን እዚህ ዱባይ ስለሚኖር ብዙ ነገር ነው አዙሮ ያሳየው። ተጫዋችና ሰው የሚወድና ደግ ሰው ስለሆነ ለመላኩ ብዙም አልከበደውም። በተለይ ደግሞ የኮምፒዩተር ፕሮግራመር የሆነችው ሚስቱና ሁለት ሕፃናት ልጆቹ የመላኩን ቆይታ የማይረሳ እንዲሆን አድርገውለት ነበር። ልጆቹ ሰው እጅግ ስለሚርባቸውም ይሁን የመላኩ ልጅ መውደድና ማጫወት መቻል፣ ተጣብቀውበት እንለቅም ነው ያሉት። የማርቆስ ጓደኛ ሚስትም በጥልቀት የማሰብና የመፈላሰፍ ነገር ስላለባት የጠፋባትን ጓደኛ ያገኘች ያህል ነው ከመላኩ ጋር ሲያወሩ የሚያመሹት። ሌሊት ስምንት ሰዓት ገደማ ነበር ሆቴሉ የሚያደርሱት።

ስለ አእምሮ ሁልጊዜም ሊጽፈው ለሚያስበው መጽሐፍ የጅማሬ ሐሳብ ወይም ደግሞ ቢያንስ የመንደርደሪያ አጭር ጽሑፍ ለመጻፍም አስቦ ነበር እዚህ ባለው ቆይታ። ሆኖም አብረውት የሄዱት የቢሮ ልጆች፣ የማርቆስ ጓደኛ ቤተሰቦችና እዚህ ኮንፍረንሱ ላይ የተዋወቃቸው ሰዎች ሁሉ ተደማምረው ፋታም አልሰጡት። ያቀረበው ጽሑፍ የተሰብሳቢዎችን ብቻ ሳይሆን ያዘጋጆቹንም ቀልብ የሳበ ነበር። እዚያው ዱባይ ያሉ ካምፓኒዎችና ሌላ ከሆንግ ኮንግ የተሳተፈ ድርጅት ወኪሎች በከፍተኛ ደሞዝ ቀጥረው ሊወስዱት እንደሚችሉ ቢነግሩትም፣ መላኩ ላስብበት ብሎ ነው ነገሩን የዘጋው።

መላኩ በዚህ ሁኔታ እንዳለ ነበር ስንክሳር የደወለችው። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ "እኔ ምልሽ ስንኪ ሰሎሚ እኮ ጠፋችብኝ። ስልኬንም አትመልስም። የዱባይ ቁጥሬንም ኢሜይል አድርጌላት ነበር። ደህና ናት? ቤትስ እንዴት ናቸው?" አለ መጨነቁን በሚገልጽ ድምፅ፡፡

" እኔም ሰሞኑን ብዙ አላገኘኋትም። እቤትም ስሄድ እናቷን ነው የማገኘው። ትዝ ይልሃል ስለ ክብሮም ነግሬህ ነበር። አብረው ነው ያደጉት፣ የቅርብ የቤተሰብ ጓደኛም ነው። ያው ከሱ ጋር ነው ብዙ የጊዜ የምትሆነው። ምናልባት ለዚያም ሊሆን ይችላል መሰለኝ። በጣም ጥሩ ልጅ ይመስላል። በቃ ሶለንም ታጥቦ ካጠገቧ አይለይም ነበር። እንጃ እሱ ባይኖር ሰሎሚ ነዙ እንዴት ያደርጋት እንደነበር! የሆነ ደግ ልጅ ነው... ከሰሎሚ ጋር ያላቸው ቅርርብ ትንሽ ግራ ስላጋባኝ ነው እንጂ እውነቱን ንገሪኝ ካልከኝ ለራሴም ከጅዬው ነበር" ብላ ሣቋን ለቀቀችው። መላኩ ግን ውስጡ እየበገነ ነበር።

"እና አሁን ቺካጎ ናት ወይስ ? ማለቴ ባለፈው ኒውዮርክ እንደምትሄድ ኢሜይል አርጋልኝ ነበር።" አለ ንዴቱ እንዳይታወቅበት እየጣረና ርእሱንም ለመቀየር እየሞከረ፡፡

"አይ አልሄደችም። ግን ነገ ምናምን ነው የምትሄደው እስኪ ደውዬላት

ነበር። ከመሄዷ በፊት እኔም ቺካጎ ሄጄ አገኛታለሁ ብዬ። በነገራችን ላይ ይሄ ሁሉ የራሴ መላምት ነው እንጂ ከክብሮም ጋር ምንም ነገር አለን አላለችኝም እሷ። አለ አይደል ብዙ ጊዜ አብረው ስለሚሆኑ ነው። ላንተ ስለ ክብሮም ምንም አልነገረችህም?" አለች ሌላ የጥርጣሬ ዘር እየዘራችበት፡፡

"እም ም... ምንም የነገረችኝ ነገር የለም። አይ እንግዲህ በቃ እስኪ እኔም እደውላለሁ። ካገኘሻት ሰላም በይልኝ። አሁን እኔም ልተኛ እስኪ።" አለ ከዚህ በላይ ለማውራት እንዳልፈለገ እያስታወቀበት። ወዲያው ቻው ብሏት ስልኩን ዘጋው።

የዚያን ለታ መላኩ እንቅልፍ አልወሰደውም። ለምን ሰሎሚ ስለ ክብሮም ምንም እንዳልነገረችው ሊገባው አልቻለም። ከሄደች በኋላ ደግሞ እየቀዘቀዘችበት የመምጣቷ ምስጢርም የሶለን መታመምና መሞት ብቻ ሳይሆን፣ ክብሮምም ሊሆን እንደሚችል ለማሰብ ተገደደ። ካንዴም ሁለቴ የነሶስናን ጉዳይ በእሱ ላይ ለዚህን ያህል ረጅም ጊዜ መሜኗ እንደከበዳት ነግራዋለች። አክስቷ ልትረዳው ስለምትችል ብዙም ራሱን እንዳይወጣጥርም የነገረችው ከዚህ ጋር የተያያዘ ይሆን ወይ የሚል ሐሳብም አእምሮው ላይ ደወለበት።

ናፍቆት ቅናትና ፍቅር ግራ በገባው ልብ ውስጥ ተደባልቀው ሲንተከተኩ የሚፈጠረው ጣዕም ልብን የሚሰንፍጥ፣ ነፍስንም የሚሸነቁጥ ሳይሆን አይቀርም። ከዚያ በኋላ ሰሎሚ ጋ ለመደወል አልፈለገም፣ ደግሞም ለአንድ ሰዓት እንኳ ከአእምሮው ሊያወጣት አልቻለም። ስለ አእምሮ ሊጽፈው የፈለገውን አጭር ጽሑፍ አሁን እንኳን ሊጨርሰው ዞር ብሎም ማየት ነው ያስጠላው። የሚያቀርበውንም ጽሑፍ ከዚያ በፊት ማቅረቡ ነው የበጀው። ሰሎሚን ይህንን ያህል እንደሚወዳት ለሱም ግልጽ አልነበረም። ክብሮምን ባያውቀውም ጠምዶታል። ምን ማድረግ እንዳለበት ግን አልገባውም። ወትሮውንም የወደደውን መንጠቅ የመላኩን ደካማ ገጽታ የሚፈትን ገና በቅጡ ያላለፈው ፈተና ነው። አሁን ደግሞ በቅርቡ ከተደበቀችበት የብቸኝነት ዋሻ ወጥታ መውደድና መወደድን ለመለማመድ ድክድክ ለምትለው የመላኩ ልብ ይሄ ሁኔታ ቀላል አይሆንም።

ልቦናችንን ከእውነቱ ይልቅ እውነት ነው ብለን የያዝነው፣ ያመንነው ጉዳይ ይገዛዋል። የውሸት ኀይል ደግሞ እውነት መስሎት በተቀበለው አእምሮ ላይ ነው። ምድር በውሸታሞች የተሞላች ከመሆኗም ባሻገር ውሸትን በቀላሉ እውነት አድርገው የሚቀበሉ ሰዎችም ከዚያው አይተናነሱም። ስሜታችን የተጠመደበት ጉዳይ ሲሆን ደግሞ የበለጠ ለውሸት የተጋለጥን ያደርገናል። ይህም ምናልባት ስሜት ከምክንያትና ከማስረጃ ይልቅ በእምነትና በግንኙነት ላይ ስለሚደገፍ ይሆናል። ያመንነውና የተጠጋነው ሰው ደግሞ የስሜታችን ሹፌር መሆኑ አይቀርም። ስንክሳርም በነመላኩ ሕይወት ውስጥ መረጃንና ምክንያትን ሳይሆን፣ በጥንቃቄ የፈጠረችውን እምነትና የግንኙነት መሥመር ተጠቅማ ስሜታቸውን

እየኰረኰረች ወደምትፈልገው አቅጣጫ እየጠመዘዘቻቸው ይመስላል። ግን ለምን?

የብዙ ሰው አስተሳሰብ ለስሜታዊው የልቡና ክፍል ማይም ነው። ሦስት፣ አራት ዲግሪ ይዘውና ስልሳ ሰባ ዓመት ኖረው እንኳ ቢሆን የራሳቸውን ስሜት በመረዳትና በመምራትም ሆነ የሌላውን ሰው የስሜት ዓለም በማንበብ ችሎታ ከዜሮ ክፍል ፈቀቅ ያላሉ ሰዎች አያሌ ናቸው። እንደ ስንክሳር ዐይነቶች ደግሞ ስሜትን በማሾር ሰዎችን ወደ ፈለጉበት አቅጣጫ የመንዳት ችሎታውን እንዴት ይሆን የተማሩት ያስብላል። ይህን ስናስብ አንዱ ጕልቶ የሚታየው እውነት ስንክሳር እንደ እናቷ መሆኗም ነው። ከልጅነቷም የፈለገችውን ለማድረግ የሰውን ስሜት ከፍና ዝቅ እያደረገች የሰዎችን የውስጥ ፍላጎት ማሾር ታውቅበታለች፤ ራሷን የሌሎች ፍላጎት አስፈጻሚ አሽከር በማስመሰል በመጨረሻ የምትፈልገውን ነገር ፈልቅቃ የራሷ በማድረግ የተካነች ናት።

እናቷም ቢሆኑ ያገቧቸውን ባሎች ሁሉ አንድ ባንድ የሚፈልጉትን ካገኙ በኋላ በሚገርም ሁኔታ ነው ያሰናበቷቸው። ሁሉም የሚታዘንላቸውና እንደተበደሉ የሚቆጠርላቸው ለእርሳቸው ነበር። በዚህም ከድኅነት ወለል ተነሥተው ነው ባለጸጋ የሆነው ብዙ ሀብት ለልጆቻቸው ትተው የሞቱት። ለስንክሳር ግን ሀብት ብቻ ሳይሆን የሌሎችን ሰዎች ፍላጎትና ህልም የራሷ ምኞት ማስፈጸሚያ ለማድረግ የማይጸጸተውን ኅሊናና ስል የስሜት ራዳር አውርሰዋት ሳይሆን አይቀርም የሄዱት። የፊቷ ብቻ ሳይሆን የስብእናዋም መልክ ቁርጥ እናቷን ነው። ነገር ግን ደግሞ ይህ እናቷ የፈጠሩባት ተጽዕኖ ተደርጎ ብቻ መወሰድ የለበትም። ገና ከልጅነቷ ጀምሮ ይህ ችሎታ ሰዎችን ወደ ፈለገችው ለመጠምዘዝ ያለውን ኀይል በማወቋ እሷ ራሷም በጥረቷና ደጋግማ በመጠቀም ያዳበረችው ክህሎትም ነው።

የጭንቅላት ዕውቀት ሰውን ሊቅ ሲያደርገው፣ የልብ ዕውቀት ደግሞ ብልኅ ያደርገዋል። ታዲያ ለምሳሌ፣ ማርቆስም ቢሆን ከስንክሳር የማይተናነስ የልብ ዕውቀት አለው። ልዩነቱ ማርቆስ ለሰው የሚያስብና ራስ ወዳድ ያልሆነ ደግ ሰው መሆኑ ላይ ነው። ይህም የማርቆስ ዐይነቶቹን ብልኅ ሲያሰኛቸው የስንክሳር ዐይነቶቹን ግን ብልጣብልጥ ያደርጋቸዋል። የነመላኩ ዐይነቶቹ የልብ ዕውቀታቸው ትንሽ ባይባልም እንኳ፣ የጭንቅላት ዕውቀታቸው በእጅጉ የበለጠ ስለሆነ ምክንያትንና መረጃን ሳይዙ ማመንና መቀበል ስለሚሳናቸው፣ አንዳንዴ የልብ ዕውቀታቸው የላቀ ሰዎች በቀላሉ ሊበልጧቸው ይችላሉ። በተለይ ስሜትን በሚያሳትፉ የግንኙነትና የኑሮ ጉዳይ በሆኑ ነገሮች ላይ። የከበሮምና የሕያው ዐይነቶቹ ግን ዕውቀታቸው በአመዛኙ የጭንቅላት ቢሆንም፣ በአብዛኛው ድርጊት ተኰርና ስኬት መር ነው። እንደነመላኩ የሕይወትን ጥልቅ ነገርና የአስተሳሰብን ውስጣዊ ምስጢር ለመመርመር እጅግም ፍላጎቱም ችሎታውም ስለሌላቸው ባለትልቅ ደሞዝና ባለትንሽ ደርዝ ሕይወት ይኖራሉ።

የሰሎሜና የሶፊያ ዐይነቶችን ደግሞ ልዩ የሚያደርጋቸው ከልቡም ከጭንቅላቱም መጥኖ የሰጣቸው መሆናቸው ነው። ሁለቱን በቅጡ አዋሕደው በሚያምር ስብእናና በተዋበ አካል ተከሽነው ስለሚቀርቡ ያወቃቸው ሁሉ በቀላሉ ይወዳቸዋል። የሕይወትን ሥቃይ የሚቀንሱትና ውበቷንም የሚያጐሉት እንደነሱ ዐይነቶቹ ፈርጦች ናቸው። ከብዙ ሚሊዮን አንድ የሆኑትን የሰለን ዐይነቶቹን ልዩም ብርቅዬም የሚያደርጋቸው የልብንና የጭንቅላትን ዕውቀት አትረፍርፎ ያደላቸው መሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሰለን በስብእናው ውስጥ የልብ ብልኅነትንና የጭንቅላት ልቀትን ያለማጕደል ያጣጣመ ማንነትን፣ ድፍረትንና ግልጽነትን የተሞላ ስብእናም ስለነበረው ነው።

የሆነውን ሁሉ ለስንክሳር የመንገር ልማድ እያዳበረች የመጣችው ሰሎሜ ያውላ ከሶፊያ ጋር ያወሩትን ሁሉ አጫውታታለች። በተለይም ስንክሳር ስለ ሶፊያ ያሰበችው ሁሉ ልክ እንዳልሆነም ለማስረዳት ዐስባ ስለነበርም ሊሆን ይችላል። እሷም ብትተዋወቃት እንደምትወድ ስለ ሶፊያ የተጸጸተች መስላ ነገረቻት።

ሰሎሜ በሚቀጥለው ቀን ወደ ኒውዮርክ እንደምትሄድና ሶፊያም ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ኢትዮጵያ እንደምትሄድ ለስንክሳር ነግራታለች። ከደወለችላት ከሁለት ሰዓት በኋላ ስንክሳር ለወንድሟ ኢትዮጵያ የምትልከው መድኀኒት ስላለ ሶፊያ ልትወስድላት እንደምትችል አስተዛዝና ጠየቀቻት። መድኀኒቱን ይዛላት መሄድ መቻል አለመቻሏን እንደምትጠይቅላት ስትነግራት ፈጣኑ የስንክሳር አእምሮ የታሻለ ሀሳብ አመጣ። ከኢንዲያናፖሊስ በጠዋት ነድታ መምጣት እንደምትችልና ለሶፊያ ዕቃውን ሰጥታ በዚያውም ሰሎሜንም ከመሄዷ በፊት ብታገኛት እንደምትወድ ነግራ አሳመነቻት። እሷም በሚቀጥሉት ሳምንታት ጊዜ እንደማይኖራት ነግራት ከዚህም የተሻለ ጊዜ እንደማይኖር ተስማምተው ነበር የተለያዩት። ስንክሳር ለወንድሟ የምትልከው መድኀኒት ሳይሆን ሶፊያን መተዋወቋ መላኩን እንደገና የራሷ ለማድረግ በምታደርገው ድብቅ ጥረት ውስጥ የምትጠቅም መሣሪያ ሳትሆን እንደማትቀር በማሰቧ ነው። ሰሎሜም ከመላኩ ጋር ልታስተዋውቃት እንዳሰበችም ስትነግራት፣ ስንክሳር ልቧ ሙሉ እየረገጠ ነው ሐሳቡን የደገፈችው። ባንዴ ለሶፊያ አፍኝ መሆኗ ሰሎሜንም ቢያስገርማትም፣ ያው የነገረቻት ታሪክ ሐሳቧን አስቀይሮአት ነው ብላ በቀና አሰበችው።

በሚቀጥለው ቀን ረፋዱ ላይ ስንክሳር ሁለት ጠርሙስ ቫይታሚንና የሕመም ማስታገሻ መድኀኒት ይዛ መጣች። በተጨማሪም የተለያዩ ቸኮሌቶችንና የሰሎሜ እናት የሚወዱትን ባቅላቫ አምጥታለች። የሰሎሜ እናት ስንክሳርን ወደዋታል፣ እናቷ በቅርብ ስለሞቱባትም ታሳዝናቸዋለች። አቶ አላና ግን ትንሽ ስለምትቸኩልና ወሬ ስለምታበዛ እምብዛም ግድ የላቸውም። ሲጫወቱ ቆይተው፣ ሰሎሜን ዕቃዋን ሻንጣዋ ውስጥ ለማስገባት ረድታት፣ ምሳ በልተው በዚያውም ሶፊያን አግኝተው ወደ ኤርፖርት ለመሄድ ወጡ። ሕያው እንደተለመደው ተረኛ

ስለነበር እቤት አልነበረም። ሰሞኑን ፈቃድ ላይ የነበረው ክብሮም ግን ከጠዋት ጀምሮ እዚያው እነሰሎሜ ቤት ነበር የቆየው።

የክብሮምና የስንክሳር መቀራረብና አብሮ ጊዜ ማሳለፍ ሰሎሜን ደስ ሳያሰኛት አልቀረም። የሰሎሜም እናት ምናልባት የስንክሳር መኖር ሰሎሜንና ክብሮምን ያቀራርብ ይሆናል የሚል ተስፋ ሳይፈጥርባቸው አልቀረም። እንዲያውም የልባቸውን ምኞት ሁሉ ለስንክሳር አጫውተዋታል። እሷም ልክ እንደሳቸው እንደምታስብ ነው የነገረቻቸው። እንግዳ ይጠብቁ ስለነበር የሰሎሜ እናትና አባት እቤት ሲቀሩ፣ ክብሮምና ስንክሳር ሰሎሜን ለመሸኘት ወጡ። ሰፊያ ምንም ጊዜ ስላልነበራት ለአጭር ደቂቃ ስንክሳርን ለመተዋወቅና ዕቃውን ለመቀበል፣ በዚያውም ሰሎሜን ለመሰናበት ቅርብ አካባቢ ያለ ስታርባክስ ካፌ ተገናኙ። አንድ አሥራ ዐምስት ደቂቃ ተገናኝተው ነበር የተለያዩት።

ሰሎሜን ኦሄር አየር ማረፊያ ካደረሱ በኋላ ስንክሳርና ክብሮም ቡና ለመጠጣት ተስማምተው ቦታ ለመምረጥ የተቸገሩ ይመስል ተፋጠጡ። ሁለቱም ለመተንፈስ ያሰቡት ጉዳይ ስለነበር ጭንቅላታቸው በሐሳብ ተወጥሮ ስለነበር ሳይሆን አይቀርም። በዚህ መሃል ስንክሳር ማቅ እያለች፣ "እንግዲህ አንተ ነህ the Chicago boy ... ጥሩ የሚባል ቦታ የምታውቀው... ጸጥ ያለ ካፌ ነገር ቢሆን ጥሩ ነው" አለች ስንክሳር ሰዓቷን እያየች። ወዳሚሪካ ስትመጣ እናቷ የሰጧት ሰዓት ነው። ስንክሳር ወደ ቺካጎ ስትመጣ ክብሮምን አንድ ጉዳይ ልታዋሪው እንደምትፈልገው በስልክ ነግራው ስለነበር ይህ ያጋጣሚ ቡና አይደለም። ክብሮምም ስንክሳር በሰሎሜና በቤተ ሰቡ ውስጥ ባጭር ጊዜ ያገኘችውን ተሰሚነት በማሰብ ሊነግራት የፈለገው ጉዳይ አለ። በተጨማሪም ለማናገርም የምትቀል ሰው ስለሆነች ልቡን ሲበላው የኖረውን ጉዳይ የሴት ብልኀት ቢጨመርበት ይሳካ ይሆናል በሚል እምነት የራሱ አጀንዳ ስለነበረው መገናኘታቸው ደስ ብሎታል። እሱ ተረቱን ባያውቀውም 'እሾህን በሾህ ሴትንም በሴት' የሚባል ተረት አለ ቢሉት 'እሱን ማለቴ ነው' ማለቱ አይቀርም ነበር። ስለዚህ የዛሬው ቡና ዝም ብሎ ቡና አይደለም።

"እም ... ኢቫንስተን አካባቢ ሄደሽ ታቂያለሽ? ወደ ምሥራቅ ቺካጎ አካባቢ ያለ ቆየት ያለ ከተማ ነው። በጣም አሪፍ የቡና ሱቆችና ካፌዎች አሉ። አካባቢውም ደስ ይለኛል፣ ነገረ ሁኔታው ሁሉ ከፊል አውሮፓ ከፊል አሜሪካ ነገር ነው..." ብሎ ወደሷ አየ።

"አንተ አሪፍ ነው ካልክ እንሂድ... ስለማላውቀው አካባቢውን ባየው ለኔም ጥሩ ነው..." አለች ወደ ኋላዋ እንደመንጠራራት ብላ ወንበሩ ላይ ሙሉ በሙሉ የመተኛት ያህል እየተደገፈች።

አንድ አርባ ደቂቃ ነድተው ነበር የባጥ የቆጡን እያወሩ ኢቫንስተን

አካባቢ የደረሱት። ሁለቱም አጀንዳቸውን የሌላውን ቀልብ በሚገዛና እሺ በሚያስብል መንገድ ማቅረብ እንዳለባቸው ነበር ውስጥ ውስጡን የሚያስቡት። ይህ ሰፈር የነጮች ሰፈር ሲሆን በቺካጎ ውስጥ የቆዩ ሰፈሮች ከሚባሉ አካባቢዎች አንዱ ነው። የቤቶቹም ሆነ የሕንጻው አሠራር ትንሽ ቆየት ያለ መሆኑ ያስታውቃል። መንገዶቹ ጥብብ ያሉ ሲሆኑ ዕድሜያቸው ገፋ ያሉ ሰዎችም በብዛት ይታያሉ። የሀብታም ሰፈር መሆኑ ግን ያስታውቃል። ትንሽ ዞር ዞር ብለው አካባቢውን ካዩ በኋላ አንድ ቀለል ያለና ብዙ ብርሃን የሚገባው የአውሮጳውያን ዐይነት ለዛ ወዳለው ካፌ ገቡ። ቤቱ ፈካ ያለ ሲሆን የኬኮቹና የቡናው ሽታ ተደባልቆ ደስ የሚል መዐዛ ይረጫል። ብዙ ጫጫታም ባይኖረው ቤቱ በስሱ በተከፈተው በጊታር ብቻ የተቀነባበረ ለስላሳ ሙዚቃና እጅግም ጫጫታ በማይባል የተስተናጋጆች የወሬ ጉምጉምታ ደመቅ ብሎአል። በዋናው መንገድ አኳያ ወደ ጥግ ላይ በመስኮቱ አጠገብ የሚመቹ ሁለት ሶፋ መሳይ መቀመጫዎች ባዶአቸውን አይተው እንደተነጋገረ ሰው ዐይናቸውንም እግራቸውንም ወደዚያው አቀኑ።

እውነትም ሶፋዎቹ ይመቻሉ። የሶፋዎቹ መጠን አነስተኛ ስለሆነና በመካከላቸው ያለችው የቡና ጠረጴዛም ትንሽ ስለሆነች ብዙም አልተራራቁ። ሁለቱም ካፌ ላቴ አዘዙ። ትንሽ ስለ ካፌውና አካባቢው ካወሩ በኋላ ክብሮም፡-

"እሺ ... ስንኪ ... ትናንት ከደወልሽልኝ ጀምሮ እኮ ለምን ይሆን የፈለገችን የሚለውን ጥያቄ ልገምት እንኳ አልቻልኩም። ለነገሩ እኔም እንደዚህ ቁጭ ብለን ቡና እንድንጠጣ ሙሺ ምናምን እንድናደይም ሁሌ አስብ ነበር። በተለይ ሰሊም ሒያዊም አንድ ላይ ሆነን" አለ በወረቀት ብርጭቆ ያለውን ላቴ እየነካካ።

"እም ... እኔን ለብቻዬ ማግኘት አትፈልግም ማለት ነው!" ብላ ስትሥቅ፣ ደንገጥ ብሎ፣

"እንዴ ኧረ አላልኩም... ግን ያው ያሰብኩትን ማለቴ ነው..."

"አይ ባክህ አትጨነቅ እየቀለድኩ ነው" ብላ አሁንም ፈገግ ብላ እጁን መታ መታ አድርጋ ሐሳቧን እንዴት መቀጠል እንዳለባት አዘጋጀች።

"አይ ምን መሰለህ... በርግጥ ከተዋወቅንም ያን ያህል ረጅም ጊዜ አይደለም። ግን አንተንም ሰሎሜንም የማውቃችሁን ያህል አውቄያችሁ ምን ያህል አብራችሁ ልትሄዱ እንደምትችሉ ሳስብ ያንተን ሐሳብ ምንም ስለማላውቅ ልጠይቅህ ብዬ ነው። ዝም ብዬ ሳስበው አንተም በጣም የምትወዳት ትመስላለህ። ቤተ ሰቦቿም አንተን እንዴት እንደሚወዱህ በጣም ግልጽ ነው። በተለይ እናቷ ቢችሉ አንጠልጥለው ወስደው ላንተ የሚያጋቧት ነው የሚመስሉት። ትንሽም አዋርቻቸው ነበር።" ብላ ልቡን አንጠልጥላ ነገሩን ባየር ላይ ተወችው። ሰዎች የልባቸውን ጕልጕለው እንዲያወሩና የሷንም ቋልፍ ሚና እንዲቀበሉ ይህ ሁነኛ

ዘዴ እንደሆነ ስለምታውቅ።

ከዚያ በኋላ ከልጅነታቸው ጀምሮ ወላጆቻቸው እንዴት ወዳጆች እንደነበሩ፣ አብረውም እንዳደጉና ከኮሌጅ ጀምሮ እንዴት እንደሚወዳት በስሜት እየተነዳ ተረከላት። በኋላም ከብዙ ፍርሀት በኋላ እሷ ኮሌጅ ጨርሳ ወደ ኢትዮጵያ ልትመለስ መሆኑን ሲያውቅ እንዴት ነፍሱ እንደተጨነቀች ገለጸላት። ያለ የሌለ አቅሙን አጠራቅሞ እንደሚወዳትና ያለሷ መኖር እንደማይችልም እያለቀሰ ሲነግራት አዝናለት እሷም አብራው ማልቀሷን አጫወታት። ግን እንደ ወንድሟ ብቻ እንደምታየውና የሷና የሱ ሕይወት ዐላማ ለየቅል ስለሆነ፣ እሱን ማግባትን የምታስበው ነገር እንዳልሆነ ስትነግረው፣ ለረጅም ጊዜ ታሞና ተደብቶ እንደቆየ ነገራት። በዚህ ጊዜ ዐይኑ እንባ ሞልቶ ስለነበር የስንክሳር ማጽናናትም አስፈላጊ ነበርና እጁን እያሻሸች በረድ አደረገችው። በኋላም እሷ ኢትዮጵያ በነበረችባቸው ዓመታት በሥራውና በትምህርቱ ቢሳካለትም፣ ሁሌም ወስጡ ባዶ እንደሆነና ከሷ ሌላ ሴት ለማሰብም ሆነ ለመመልከት እንደማይችል እጁን እያወናጨፈ፣ ድምፁንም ሳያውቀው ከፍ አድርጎ ነገራት።

"ኧረ ቀስ ልጅቷ ኒውዮርክ ሄዳለች ብለህ ነው እንዴ? እንዳትሰማህ ዋ!!" ብላ አሥቃው አሁን ሰሎሜ ከኢትዮጵያ ከመጣች በኋላ ስላለው ነገር ጠየቀችው።

እሱም ያው እንዴት ቀስ በቀስ በሶለን መታመምና በሱም እናት ሞት ሳቢያ እንደተቀራረቡ የምታውቀው ጉዳይ ቢሆንም እንዳዲስ ተረከላት። በተለይ ሶለን እንደገና ታሞ ሆስፒታል በገባበት ቀን የሱን ልደት ለማክበር ይዛው እንደወጣች ነገራት። የዚያን ዕለት የነበራቸው ቅርርብ እንዴት የጠበቀ እንደነበርና ቢጠይቃት እንኳ እምቢ የምትለው እንዳልመሰለው ፊቱ በርቶ ነገራት።

"ታዲያ ምን ከለከለህ?" አለች ስንክሳር ነገሩ በሰሎሜም በኩል ተመሳሳይ አይነት ግራመጋባት ዐዘል ስሜትን የፈጠረ ቀን እንደሆነ ሰሎሜ የነገረቻት ትዝ እያላት።

"ሶለን ድንገት ታሞ ሕያው ሲደውል ሁሉም ነገር ደፈረሰ። ከዚያ ቀን ጀምሮ ሁሉም ነገር ግራ ገባኝ። አሁን ደግሞ የሰሎሜ ወደ ኢትዮጵያ መሄጃ ቀን እየቀረበ ሲሄድ፣ ፍርሀትና ጭንቀት ወጥሮ ይዞኛል። ምን ማድረግም እንዳለብኝም አላውቅም። እንዲያውም እንገናኝ ስትይኝ ይህንንም ላማክርሽ እያሰብኩ ነበር። የውልሽ ይህንን አዘጋጅቼ ነበር።" አለና ከኪሱ ውስጥ ለሰሎሜ ያዘጋጀውን ቀለበት እያሳያትና፣ "ያበጠው ይፈንዳ ብዬ ለልደቷ ራት ጋብዤ ሳታስበው በድፍረት ለጋብቻ ልጠይቃት ወስኜ ነበር። ደግሞ አንድ ልቢ እምቢ ብትለኝስ ብዬ ... እኔንጃ ምን ይመስልሻል?" አለ በስሜት ድምፁ የበለጠ እየጋለ። ምንም መልስ ሳትሰጠው

አሁንም

" እኔ ሳስበው ይህ ብቸኛው አማራጩ ነው። ዕድሜ ልኬን እየቆጨኝ ከምኖር የመጨረሻ ዕድሌን ሞክሬ የሆነው ይሁን። ሰው በፍርሃት አይሞት። ሌላው ምናልባት ሶለን ሰሎሜ እኔ ጋር እንድትሆን እንደማይፈልግ አውቃለሁ። አሁን እሱም የለም። ብቻ I don't know! ... oh my God! ምን ይመስልሻል አንቺ? ብዙ ለፈለፍኩ መሰለኝ።" ብሎ ጸጉሩን እያሻሸ የምትለውን ለመስማት መጠበቅ ጀመረ። ነገሩ በቀላሉ በእጁ ዉስጥ እንደሚገባ ያወቀችው ስንክሳርም ረጋ ባለ ድምጽ

" ሁሉም ነገር ገብቶኛል ክብርሽ። ደግሞም ከሰሎሜ ጋር አብዛኛውን ነገር ስላወራን የምትለውን መረዳት አያቅተኝም። ግን እኔ ምልህ ሰሎሜ መላኩ ስለሚባል ልጅ ነግራህ ታውቃለች እንዴ?" አለቻው አሁን በቀጥታ ክብሮምን ወደምትፈልገው አቅጣጫ ለመንዳት ዝግጁ መሆኑን እርግጠኛ ሆና።

"እም .. አዎን .. ማለቴ ጓደኛ እንደሆኑና ከሶለን ጋር ብዙ እንደሚመሳሰሉ። ያው አሁንም እዚያ ያለውን ቤቷንና የምታሳድጋቸውን ልጆች እንደሚንከባከብላት። ሌላ ብዙ አላውቅም።" አለ ወዴት ለመሄድ እንዳሰበች እጅግም ሳይገባው። እሷም ስሜቱን የበለጠ ማጦዝ ብትችል ወደምትፈልገው አቅጣጫ ልትጠመዝዘው እንደምትችል በማሰብ ቦርሳዋን አውጥታ መላኩ ለሰሎሜ እንድታደርስ የሰጣትን ደብዳቤና ካርድ እንዲያነበው ፊቱ አስቀመጠችለት። እሱም ደብዳቤውን እያነበበ ግማሽ አካባቢ ሲደርስ ፊቱ መለዋወጥ መጀመሩን አየችና፡-

"ምናልባት ብዙ ሊገባህ እንደማይችል አውቃለሁ። አለ አይደል ደብዳቤውን እንዴት አገኘሽው? ይሄን ሁሉ ለማድረግ ለምን ፈለግሽ? አንቺ እንዴት መላኩን አወቅሽው? ... ከኔ የምትፈልጊው ምንድነው? ምናልባት ሌላም። አይደል?" አለችና ደብዳቤውን በጁ እየከለለችበት፡-

"ቆይ ታነበዋለህ፣ ይህን ብቻ ሳይሆን ሌላም ነገር ታያለህ። አሁን ግን እነዚህን ጥያቄዎችና ትንሽ ተጨማሪ ማወቅ ያለብህን ነገር ልንገርህ" አለችና ስሜቱ እየተገለባበጠ ግራ የገባውን ክብሮምን ሙሉ በሙሉ ቁጥጥሯ ሥር እንዳስገባችው በማወቅ ስሜቱን ለማርገብና አእምሮውን ለማንቃት ከፊል እውነት ከፊል ፈጠራ የሆነ ረጅም ዲስኩር አደረገችለት።

መላኩ የሷ የልጅነት ፍቅረኛዋ እንደሆነና አሁንም ልክ እሱ ሰሎሜን እንደሚወድ እንደምትወደው። ሆኖም ግን ኮሌጅ እያሉ እሷ በቤተ ሰብ ግፊት ተታላ በዕድሜው እጅግ የሚበልጣትን እዚህ አገር ብዙ የኖረ ሽማግሌ ፕሮፌሰር

አግብታ እንደመጣች። ሰውዬውም እዚህ አምጥቶ እንዴት እንዳሠቃያትና በቅናት አንገርግቦ መከራዋን እንዳበላት ሆድ በሚበላ ቃል ነገረችው። ሰውዬው በራሱ እርጅና ምክንያት ልጅ መውለድ ቢያቅተውም፣ እሷን ቁምስቅሏን እንዳሳያትና በኋላ እንደተረዳችውም ከሷም በፊት ብዙ ሴቶችን እያመጣ፣ መከራ እያሳየና እየፈታ የብዙ ወጣቶችን ሕይወት ያበላሸ መሆኑን ነገረችው። በዚህም የተነሣ ከአምስት የመከራ ዓመታት በኋላ ጥላ እንደጠፋችና በኋላም የሴቶች መብት ተከራካሪ ድርጅት ጠበቃ ቀጥሮላት እንደተገላገለችው ገለጸችለት። አሁን ደግሞ ማጽናናቱ የክብሮም ተራ ሆነ።

ልብወለድ ታሪኳን በመቀጠል በመጨረሻም ይሄ ሁሉ የደረሰባት ንጹሑን የመላኩን ፍቅር ለቤተሰብ ደስታ ብላ ረግጣ በመሄዷ መሆኑን ተገንዝባ ብትጸጸትም፣ መላኩ ከሌላ ሴት ጋር እንደሆነ ስላወቀች ምንም ማድረግ እንዳልቻለችና እየጸለየች ቀን ስትጠብቅ እንደነበር አጫወተችው። ከልጅቷ ጋር መላኩ ከተለያየ በኋላም እንደገና ማውራት እንደ ጀመሩና ስለ ሰሎሜ ግን ምንም ታውቅ እንዳልነበር አወራችለት። አሁን ግን እናቷ ሲሞቱ ለልቅሶ ሄዳ ሳለች መላኩ ከሰሎሜ ጋር በአዲስ ፍቅር ከንፎ ስታገኘው ህልሟ በድጋሚ ከንቱ ሊሆን እንደሆነ አውቃ ይህንን ነገር እንዴት ማቆምና ውስጥ ነፍሱን የጐዳችውን መላኩን እንዴት መካስ እንዳለባት ስታስብ፣ ወደዚህ ተመልሳ መጥታ እሱንም የሰሎሜንም ቤተሰብ እንደተዋወቀችና አሁን ባሉበት ቦታ እንዳለ ነገረችው።

“ክብሮሽ ምንም ባደርግ ላንተ ብዬ ብቻ እንዳይመስልህ። ልክ አንተ ሰሎሜን ማግባት እንደማትፈልገው ሁሉ እኔም መላኩን ማግባት አልፈልግም። ልክ ለሰሎሜ ከማንም ይልቅ አንተ እንደሆንክ የምትሻላት መላኩንም ከልጅነቱ ጀምሮ የማውቀውና ያለምንም ውጫዊ ምክንያት የምወደው እኔ ነኝ። ግባህ እሱን ደብዳቤ እንዳደርስላት ሲሰጠኝ ለሷ ያለውን ፍቅር በተወሰነ መጠን ነግሮኝ ስለነበር ደብዳቤውን አውሮፕላን ውስጥ አለማንበብ አልቻልኩም። ሳነበው ደግሞ አንተ ከተቃጠልከው በላይ ነው የተንጨረጨርኩት። በርግጥ ልክ አልሠራሁም፣ ግን ደግሞ ለፍቅር የማይሠራ ነገር የለም። ደብዳቤው ከሻንጣ ውስጥ ጠፋ አልኩት። እሱም ያው እንዳነበብከው፣ የደብዳቤው ይዘት ኀይለኛ ፍቅር ስለሆነ ግድ የለም ይቅር ወደፊት ስትመጣ ይደርሳል ብሎ እሮይ ነው ያለው። እነሱን ያጣመራቸው አገር መለወጥ ወገን መርዳት ምናምን የሚሉት ያገር ፍቅር ነው፣ እኛ ግን ተይዘን እየተሠቃየን ያለነው በሰው ፍቅር ነው። ስለዚህ አሁን ላንተም ለኔም ጥቅም አብረን መሥራት እንችላለን ወይ ነው ጥያቄው? ወይስ በሁለት ሳምንት ውስጥ ሰሎሜም ሄዳ በሦስት ወር ውስጥ ሲጋቡ ቆመን ማጨብጨብ? ምን ታስባለህ?” ብላ ግራመጋባት፣ ቅናትና ፍርሀት የተከመሩበትን የክብሮምን ፊት ማጥናቷን ቀጠለች።

ለኔ ግራ ነው የገባኝ። ማይ ጋድ ... ምን ማድረግ እንችላለን? አሁን

ሰሎሜም ትሄዳለች። በቃ ... ምን ታደርጊያለሽ? እስኪ ምን ይደረጋል? ገዛም ብዬ ነዋ ስለፋ የከረምኩት” ብሎ ብስጭትና ኀዘን ፊቱን ይወርሰው ጀመር።

“እንደዚህማ ባጭሩ ተስፋ መቁረጥ የለብህም። እኔ እኮ አልሬዲ ብዙ ሥራ ሰርቻለሁ። አየህ ለመላኩ ሰሎሜ ያንን ያህል ፍቅር ለሱ ያላት እንደማትመስል እንዲያውም ክብሮም ከሚባል ልጅ ጋር በጣም እንደምትገናኝና ቤተ ሰቡ ሁሉ እንዴት እንደሚወደው ነግሬው ልቡ ሲሻክር አይቼዋለሁ። ምክንያቱም ስልኳን፣ ኢሜይሏንም እንደማይ መልስና ብዙም እንደማይገናኙ ነው ሰሎሜ የነገረችኝ። እሷንም መላኩ እንዴት እንደ ንጹሕ እኅቱ እንደሚያያትና ከጥሩ ሰው ጋር እግዜር እንዲያገናኛት እንደሚጸልይ፣ እንደምታሳዝነውም እንደነገረኝና ነገሩን እንድታምን አድርጌ ግራ እንዲገባት ማድረጉ ትንሽ እየሠራ ነው። ቢያንስ ሁለቱም አሁን ልባቸው መራራቅ መጀመሩን አውቃለሁ። ግን አሁን ይህንን ነገር ሁለቱም እንዲያምኑና ተራርቀው እንዲቀሩ ወሳኝ ነገሮችን መሥራት አለብን።”

“ምን? ማለት እንዴት? አልገባኝም!” አለ ክብሮም ሳያውቀው፣ የስንክሳርን መሰሪነት ልቡ ብዙም አልወደደውም።ደግሞ እሱ ሰሎሜን ለማግኘት ምንም ለማድረግ እንደማይመለስ ሲያስብ የሷም ሥራ ለፍቅር የሚከፈል ዋጋ እንደሆነ ሊክድ እንዴት ይችላል? ለነገሩ እኮ ስንክሳርም መላኩን ትወደዋለች። ከሰሎሜ ቢለይ እሷ እጅና ልብ ላይ መውደቁ እንደማይቀር ነው የምታምነው። በተለይ ባሁኑ ለልቅሶ በሄደችበት ጊዜ ያሳያትን ክብካቤ ካገረሸ ፍቅር ጋርም ሳታምታታው አልቀረችም። ያነበበችው ደብዳቤ ደግሞ ህልሟን በከፊል አጨልሞታል፣ ቁጣና በቀልም ሳይሞላባት አልቀረም።

“የመጀመሪያው ነገር አንተና ሰሎሜን ማቀራረብ ነው። ለሱ ሙሉ ኀይላችንን ተጠቅመን መሥራት አለብን። ሰሎሜን እኔ የተቻለኝን ሁሉ ተጠቅሜ ልቧ ወዳንተ እንዲያዘነብል ለማድረግ ጥረት እያደረኩ ነው። ለዚህ ደግሞ እናቷንና ሕያውን መጠቀም እችላለሁ። ያንተም ጥረት ግን ያስፈልጋል። ሌላው ግን መላኩ ሰሎሜ ለሱ ስላንተ ምንም ስላልነገረችው፣ ልቡን በሰሎሜ ላይ የሚያጨልምና እምነቱን የሚያጠፋ ነገር ማሳየት አለብን። በሌላ በኩል ደግሞ የሰሎሜንም ልብ ከመላኩ እንዲሸሽ ማድረግ እንችላለን። እንዲያውም እቺ የሶለን ጓደኛ እቺ ጥቁሯ ማነች ሶፊያ አሁን ኢትዮጵያ ትሄድ የለም! ሁለቱን እንዲተዋወቁና እንዲቀራረቡ ማድረግ እንችላለን። ሁለቱ የተዋደዱ እንዲመስሉ ሁኔታዎችን እንፈጥራለን። ሰሎሜ ደግሞ የወንድሟን ገዳይና ፍቅረኛ በፍቅር የቀረበ ከመሰላት፣ መላኩን ብቻ ሳይሆን፣ እዚያ አገርም መኖር የምትፈልግ አይመስለኝም።”

“ኦ ማይ ጋድ አንቺ ጭንቅላትሽ እንዴት ነው የሚያስበው? ይሄን ሁሉ ከመቼው ነው እንዲህ ያሰብሽው? እሺ መላኩ ሶፊያን ባይቀርባትስ ወይ ደግሞ ሁለቱ የምር ቢፋቀሩስ ምን ልታደርጊ ነው፣ አንቺ?” አለ የራሱን ጉዳይ ትቶ የሷ

ጉዳይ እንዳስጨነቀው ሁሉ። ክብሮም የልቦለድ መጽሐፍ ታሪክ እንጂ እሱ ራሱ የሚተውነው የራሱ ሕይወት ያልመሰለውን ሴራ መስማቱን ቀጠለ። ገና የሚመጣውን መች አወቀ?

"እንደሚወዳት ምንም ጥርጣሬ የለውም። መላኩ አርትና ሥዕል እንደሚወድ አውቃለሁ። መልኳም ቢሆን መላኩ በቀላሉ ሊወደው የሚችለው ነው። ልጅቱም ደግና ተግባቢ ትመስላለች። ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ግን ይዛ የምትዞረውን ታሪክ በራሷ ላይ እንጠቀማለን። እሱን ለኔ ተወው። ሳይጣበቁ ማለያየት ይቻላል። አሁን አንተ ማድረግ ያለብህን ለማድረግ ፈቃደኛ ነህ ወይ ነው ጥያቄው?" አለች ኳሱን ወደሱ ሜዳ እየመለሰች።

"ምን ማድረግ እችላለሁ?" አለ አሁንም ግራ ገብቶት።

ስንክሳር ያሰበችውን በጥንቃቄ የተቀመረ ዕቅድ ስትነግረው፣ ክብሮም አስተሳሰቧ ከሚገባው በላይ ቢያስገርመውም ዕቅዱ በሆነ ምክንያት ቢከሽፍ የሚያመጣውን መዘዝና ቀውስ አስቦ በማመንታት ያለችውን ማድረግ እንደማይችል ሲነግራት

"አኬይ ... ምርጫው ያው ያንተ ነው። ከሁለት ሳምንት በኋላ ሄዶ መላኩ እቅፍ ስትገባልህ ሪስክ አለመሆኑ ነዋ? እና አንተ ቀለበቱን ምን ልታደርገው ነው የገዛኸው? ... ደስ እንዳለህ። እኔ አንተ ይህንን ፈርተህ ስላላደረግህ መላኩን የራሴ ማድረግን የማቆም ይመስልሃል? ኖ ኖ... የውልህ አንተ ሰሎሜን ማግኘት ከፈለግህ አብረን መስራት እንችላለን፣ ካልሆነ ግን እኔ ወደ ሌላው ዕቅዴ አመራለሁ። ሰሎሜን ማጣትህ ግን የዕድሜ ልክ ጸጸት እንደሚሆንብህ አንተም ታውቀዋለህ። ያው ይሄ በኔና ባንተ የሚቀር እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።" ብላ የሰጠችውን ደብዳቤ ወደ ፖስታው ማስገባት ስትጀምር አንዳች ፍርሀት ያዘው።

ከዚያም "እንዴ እኔ እኮ እምቢ ማለቴ አይደለም። እሺ የኔን ሥጋት እንዴት ነው የምትመልሺው?" አለ የቀዘቀዘውን ላቴ ፉት እያለ።

"እኔ ሴት ስለሆንኩ ልንገርህ። እሷ ላንተ ያላት ፍቅር እሺ ባያሰኛት እንኳ የሁኔታው ስሜት ቀስቃሽነትና ላንተም ያላት አክብሮት ከዚህ በፊትም ስሜትህን ስለጐዳችው እሺ ትላለች። ከወጣችሁ በኋላ ልታለቅስ ልትቆጣ፣ ውሎ ዐድሮም ቀለበቱን ልትመልስለህ ትችላለች። በመሃል ደግሞ እሷ እዚህ አሜሪካ እንድትቆይ ለማድረግ የተቻለውን እናደርጋለን። ያው ለኔም ያደረግኸውን መንገር ስለማይቀር። አንተም እግሯ ላይ ወድቀህ ይቅርታ ትጠይቃታለህ። እኔም ደግሞ ነገሩን በሴትኛ አለሳልሼ እነግራታለሁ። ከዚያም ነገሮች ይረግባሉ። በመሃል ደግሞ ከወዲያ ያለውን ነገር ስናከረው ወዳንተ መመለሷ አይቀርም። ሁሉም ነገር መፍትሔ አለው። ደግሞ የሰሊን ልብ ታውቀው የለም?" አለች ግዳይዋን እንደጣለች አንበሳ ዘና ብላ።

እሚለውን ያጣው ክብሮም ልቡ ነገሩን ሙሉ ለሙሉ ባይቀበለውም እያመነታም ቢሆን "እሺ ላስብበት። ሌላ የተሻለ አማራጭም ያለ አይመስልም። የምትገርሚ ሰው ነሽ አንቺ ግን። ከዚያስ? አንቺ ወደ ኢትዮጵያ ልትመለሺ ነው የምታስቢው ማለት ነው?" አለ አሁንም በመገረም እያያት፤

"እንዴ አሁን የተነጋገርነውን ካደረግንና ሰሎሜን ቢያንስ ላንድ ወር እዚህ ከቤተ ሰብ ጋር እንድትቆይ ካሳመንን እኔ ወደ ኢትዮጵያ እሄዳለሁ። እዚህ ያለው ነዳጅ ማደያና ሱቅ ያው ራሱ ነው የሚሠራው። ያክስቴ ልጆችም ስላሉ ችግር የለም። እኔ ጎዙሩን እንዳልቻልኩትና እዚያው ከቤተ ሰብ ጋር ትንሽ ማረፍ እንደምፈልግ ብዬ እሄዳለሁ። ከዚያ በኩል ያለውን ሥራ እሠራለሁ። አንተም ያው ሰሎሜን እዚሁ የማስቀረቱን ሥራ ታጠፋለህ። እምቢ ብላ እንኳ ከወር በኋላ ብትመጣ፣ መላኩንም፣ ሁኔታዎችንም ለውጠን ኢትዮጵያ መኖርን እንድትጠላ ማድረግ ይቻላል። አንተም በመሃል መጥተህ ተጨማሪ ማጠናከሪያ ትሰጣለህ። ይኸውልህ ዋናው ሁለት ሦስት ደረጃ ቀድሞ ማሰቡ ላይ ነው።" ብላ ዘና ብላ የሚለውን መጠበቅ ጀመረች።

"እንዳንቺ ዐይነት ጭንቅላት ያለው ሰው አይቼ አላውቅም። ፕሮፌሰሩ እንዴት እንዳታለሉሽ ገርሞኛል" አለ ነገሩ ከስንክሳር ብልጠት ጋር አልሄድ እያለው።

"የኔ ልጅ ነበርኩ። አየህ ኑሮ ብዙ ያስተምርሃል። ደግሞ ለእናቴ ፍቅር ብዬ እንጂ ሽማግሌውን ወድጄው ወይም የሆነ ነገር ጕድሎኝ ለራሴ ብዬ አላደረግሁትም። ከሁሉም በላይ ግን የምትወደውን ሰው ላለማጣት የማትፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም። ይህን ሁሉ ለማድረግ ዋነኛ ምክንያቴ መሌ ነው። ርግጠኛ ነኝ አንተም እንዲ ከገባህበት፣ ከኔ ብሰህ ነው ቁጭ የምትለው። ለማንኛውም ጊዜውም እየሄደ ነው መሰል። እኔም ነድቼ ወደ ቤት መመለስ ስላለብኝ መሄድ ሳይኖርብኝ አይቀርም" አለች ዕቃዋን እንደ መሰብሰብ እያለች። በሠራችው ሥራና ዕቅድ መርካቷ ፊቷ ላይ ይነበባል። ስንክሳር ሁሌም ያሰበችው ሲሳካላት ጥሩ ምግብ እንደቀረበለት ሰው ከንፈሯን መላላስና ምራቋን መዋጥ ይቀናታል።

"አይደል እንሂድ ኧረ እኔም ለነገ የማዘጋጀው ብዙ ነገር አለ። ሰሎሜም በሳምንት ውስጥ ትመጣለች። እንግዲህ ሁሉንም እየተማከርን እንደሚሆን እናደርጋለን።" ብሎ ተነሣ። ከካፌው ወጥተው መኪናዎን ካቆመችበት እነሰሎሜ ቤት እስኪደርሱ ባወሩት ዙሪያ እየተጫወቱና ስለ ክብሮም የማታውቃቸውን ነገሮች በመጠየቅ ነበር የደረሱት። መንገድ ላይ ሳሉ ሰሎሜም ደውላ ደኅና መድረሷን ነግራቸዋለች። እስከዚያ ሰዓት አብረው መሆናቸውም የተለየ ስሜት አልፈጠረባትም። እቤት ስትደርስ ራት ካልበላችሁ ተብለው ሲወራና ቡና ሲጠጣ መሽና የሰሎሜ እናት አድረሽ በጠዋት ብትሄጂ ስላሉ፣ ብዙም ሳትግደረደር ነበር እሺ ያለችው። ሰሎሜም ስልሌለች፣ ሕያውም ተረኛ ስለነበር ቤቱ ጭር ስላለባቸው

የስንክሳር መኖር ቤቱንም ደመቅ አድርጎት ነበር። ኀዘን የጐዳው ሰው መቼም ልቡ ስስና ቅርብም ነው። ስንክሳር መቼም በሁነኛ ጊዜ ነው እዚህ ቤት የገባችው።

ስንክሳር ከባሏ ከተለያየች በኋላ በተካፈለችው ገንዘብ የነዳጅ ማደያና አብሮትም ያለ ሱቅ ከፍታ የተደላደለ ኑሮ ነው የምትኖረው። ሰውዬው ሁለት ቤት ስለነበረው አንዱ ለሷ ተፈርዶላት፣ የምትኖረውም ከከተማው ወጣ ብሎ በሚገኝ መካከለኛ ገቢ ባላቸው የነጮች ሰፈር ባለአራት መኝታ ቤት ውስጥ ነው። አብረዋት አንድ ያክስቷ ልጅና በቅርብ ዲቪ ደርሶአቸው የመጡ የናቷ ዘመዶች ባልና ሚስቶች አሉ። ሁሉም እዚያው ነዳጅ ማደያ ውስጥ ነው ለጊዜው የሚሠሩት። ስለዚህም በፈለገችበት ጊዜ ተነሥታ ደስ ወዳላት ቦታ ለመሄድ ያን ያህልም ነጻነቷን የሚወስድባት ነገር የለም። ገንዘብም ችግር ሆኖባት አያውቅም አሜሪካ ከመጣች ወዲህ። የመጀመሪያ ዲግሪዋን በቢዝነስ የሠራች ሲሆን፣ ማስተርሷን ከጀመረች ብዙ ዓመት ቢሆናትም አሁንም የሚወሰዱትን ኮርሶች አልጨረሰችም።

ባሏን ከፈታች ወዲህ የተለያዩ ወንዶችን ለመቅረብና ለማየት የሞከረች ቢሆንም፣ ሁሉንም ጥቅም ፈላጊ ሥራ የማይወዱና የሚበልጣቸውን ሴት የሚፈሩ ‘አበሾች’ ናቸው እያለች ሰው አልበረከት ብሎአታል። ልጅ ለመውለድ ካላት ትልቅ ጉጉት የተነሣ ደግሞ ቶሎ ማግባቱን ሳትፈልገው አልቀረችም። በመጨረሻ የደረሰችበት እውነተኛ ቁምነገረኛና ከልቧ ልታከብረው የምትችለው ሰው መላኩ ብቻ መሆኑን ነው። ፍቅሯም እንደገና አገርሽቶባታል። እሱም ያን ሁሉ አድርጋው አሁንም ሳይቀየርባት ጥሩ ሰው ሆኖ በነዘንዋ ጊዜም አብሮአት ስለነበረ፣ ለሷ ያለው ፍቅር ከውስጡ ፈጽሞ ባይጠፋ ነው ብላ አስባለች። ይህም በተለይ ሰሎሜ የተባለችው ዕንቅፋት ከመንገድ ከተወገደች ከባድ እንደማይሆን ነው አሁን የምታስበው። ከብሮምም ቢሆን የዋህና ጥሩ ሰው ስለ ሆነ፣ ለሰሎሜም ቢሆን እሱ ስለሚሻላት እሷንም ቢሆን መርዳት እንጂ መጉዳት አይደለም ብላ ለዕቅዷ በጎ ገጽታ ትሰጠዋለች።

የሰሎሜ ወላጆችም ቢሆኑ ልጃቸው አጠገባቸው ኑሮው የተስተካከለና እንደልጃቸው የሚወዱትን ብረት መዝጊያ ባል አግብታላቸው ቢኖሩ፣ የስንክሳርን ውለታ ይረሱታል ብላ አታስብም። የሰው ልጅ መቼም ሊሠራ ያሰበውን ክፉት የደግነት ቀለምና የቅድስና ቅባት ቀብቶ ራሱን ሲያታልል የልቡናው ዐይን መታወሩን እንኳ አያውቅም። ስንክሳር ግን ነገሩ ተሰውሮባት ሳይሆን፣ የፈለገችውን ነገር ለማግኘት ኅሊናዋን የፈለገችውን ቅርጽና መልክ እንዲይዝ በማድረጉ የተካነች ስለሆነች ነው። ኅሊናውን አሽከሩ ያደረገ ሰው ክፋቱ ጌታው መሆኑ አይቀርምና።

ፍልሚያ

መላኩ ዱባይ ሆኖ ስንክሳር ከደወለችለት በኋላ ሌሊቱን ሲገላበጥና ሲቅበጠበጥ ነበር ያደረው። አልፎ አልፎም ደስ የማይሉ ቅዠቶች ሲረብሹት ነበር። ሰሞኑን ለሰሎሜ ደጋግሞ ቢደውልም ስልኩን ስላላነሣች ከብሮም ከሚባለው ልጅ ጋር ሆና የሱን ስልክ እያየች እንዳላየ ስትሆን ባይኑ ህሊናው ይታየው ጀምሯል። ደግሞ ሰሎሜ ፈጽማ ታደርጋለች ብሎ ለማመንም ከብዶታል። ሰሎሜ ከሰው ሁሉ የተለየች፣ እንከን የለሽ፣ ደግና ክፋት የማታውቅ ናት ብሎ ነው የሚያስበው። አሁን ስንክሳር ደውላ እንደነገረችው ከከብሮም ጋር ግንኙነት ጀምረው ከሆነ መቼም ከሚያስበው በላይ ነው። ስንክሳርም ለሰው ብላ ብዙ የማታደርግ ሰው መሆኗን ስለሚያውቅ የሷ ከወትሮው የተለየ አሳቢነትና በየጊዜው ደዋይነት ስስ ጥርጣሬ ዘርቶበታል። በማለዳ ተነሥቶ የሆቴሉ መዋኛ ቦታ ሄዶ ላንድ ሰዓት ከዋኘ በኋላ ሻወር ወስዶ ወደ ክፍሉ ተመልሶ ለመተኛት ቢሞክርም እንቅልፍ ባይኑ አልዞር አለ። ሰሎሜንም ከአእምሮው ሊያወጣት አልቻለም። ቀኑን ሙሉ ከመኝታ ቤቱ ሳይወጣ ዋለ።

ወደ አዲሳባ ለመመለስ ገና ሦስት ቀን ስለሚቀረው ጊዜው እንዴት እንደሚሄድለት ግራ ገብቶታል። ከዱባይ ውጪ ያለውን አገር ለማየት ከተቻለም ወደ በረሓውና ባሕሩ ላይ ያሉትን ደሴቶችና ሌሎች የሚጐበኙ ስፍራዎች ለማየት ዐቅዶ ነበር። አሁን ግን ለሁሉም ነገር ያለው ፍላጎት ጠፍቶበታል። አልጋው ውስጥ ገብቶ ኢንተርኔት ሲያሥሥ ቆይቶ ኮምፒዩተሩን ከመዝጋቱ በፊት ኢሜይሉን ከፍቶ ሲያይ ከሰሎሜ የተላኩ ኢሜይሎች አገኘ። ሁለቱም ዛሬ ጠዋትና ከጥቂት ሰዓታት በፊት የተጻፉ ናቸው። ብዙ ጊዜ ብትሞክርም ልታገኘው እንዳልቻለችና ከቻለ ቶሎ በቻለው ፍጥነት ኢሜይል እንዲያደርግላት ወይም ምልክት እንዲያሳያት ነው የጠየቀችው። ወዲያው የተሟሟነው ስሜት በመጠኑ ቀንሶለት አልጋው ላይ ተቀመጠ።

“ወይ አምላኬ... ሰው መውደድ እኮ ዕዳ ነው። ለምንድነው የሰው ሰው ልቡ ውስጥ ጨምሮ ሰው የሚሠቃየው? ሰሎሜ ሰሎሜ ምን እንደምትፈልጊ ማወቅ እንዴት ነው የምችለው?” ብሎ ለራሱ እያጉተመተመ የተንጨበረረውን ፀጉሩን እያሻሸ ይባስ አንጨበረረው። ትንሽ ክፍሉ ውስጥ ዘወር ዘወር አለና በቀዝቃዛ ውሃ ፊቱን ከታጠበ በኋላ ላፕቶፑን ይዞ ሶፋው ላይ ሄዶ ቁጭ አለ። ከዚያም ሰሎሜ

የጻፈችውን ኢሜይል እንደገና አንብቦ መልስ ጻፈላት የሆቴሉን ቁጥርና ማርቆስ በስልክ ያስተዋወቀው የማርቆስ ጓደኛ ሳምሶን የሰጠውን ጊዜያዊ ሞባይል ቁጥር ጨምሮ። ስልኮቹ ክፍት መሆናቸውን አረጋግጦ የጅ ስልኩን እንደያዘ በክፍሉ ባልኮኒ ደጅ ተቀምጦ መሬት ላይ ወዲያ ወዲህ የሚሉትን ዱባያውያንን ካንገት በላይ በሆነ ፍላጎት ማጤን ጀመረ።

ከግማሽ ሰአት በኋላ ሞባይል ስልኩ ሲጮህ ሰሎሜ ናት ብሎ በማሰብ ከኪሱ አውጥቶ ሲያየው የሳምሶን ሚስት ነበረች። ስልኩን አንሥቶ ትንሽ ጥሩ ስሜት ስላልተሰማው ሆቴል እንደዋለና መውጣትም እንዳላሰኘው ነገራት። ምግብ ምናምን ሠርተው ሊያመጡለት እንደሚችሉ ወይም ይዘውት ወጥተው ቀለል ያለ ቤት ሊያመሹ እንደሚችሉ ምርጫ ቢሰጡትም፣ ዛሬን እዚሁ ሆቴል ለመቆየት መረጠ። ከዚያም ሕፃናቱም ካላወራነው ብለው ትንሽ አሳስቀውት እየጠበቁት እንደሆነ ቢነግሩትም አማሥቆ ነገ አያችኋለሁ ብሎ ስልኩን ዘጋው። በማግስቱ ሙሉ ቀን አብረው ለመዋል ቢያስቡም በዚህ ስሜቱ እንዴት አድርጎ ከነሱ ጋር ቀኑን እንደሚገፋው ሐሳብ ሆነበት። ከልጆቹ ጋር ከተሟሟቀ በኋላ መንፈሱ ቀለል አለው። ልጅ ቢኖረው ተመኘ፣ ግን ገና ሚስትም የለውም። ጓደኛስ የት አለኝና ብሎ አሰበ።

ሰሎሜ ከሁለት ሰዓት በኋላ ደወለችለት። መነፋፈቃቸው ከልባቸው የገባውን መራራቅ ለማቅለጥ ግለቱ በቂ ነበር። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ "መሊ አይ ኖው በጣም እንደ ጠፋሁብህ። በቃ ሰሞኑንም ከልቅሶው በኋላ በተለይ ሁሉም ነገር ዞሮብኝ ነበር። ሁልጊዜም ነው የማስብህ ግን በቃ ጭንቅላቴም በትክክል የሚሠራ አልመሰለኝም።አንተ እንዴት ነህ በናትህ? ደግሞ ወርክሾፑስ እንዴት ሄደ? ጥሩ ነበር አንተ ያቀረብከው?" አለች አነጋገሯ የሰሎሜን በማይመስል አይነት።

"ሰሊ ደኅና ነበር። ቤተ ሰብ ተጽናና? በጣም ከባድ ነው የሚሆነው መቼም። ያው ሰንክሳርም ትናንት ማታ ደውላ ነግራኛለች ወደ ኒውዮርክ እንደምትሄጂ። እኔም እዚህ ተወጠርኩ መሰለኝ በቃ በጣም የተራራቅን ነገር ሆኖ ነው የሚሰማኝ። አንቺ ግን ደኅና ነሽ?" አለ እሱም እንዴት ማውራት እንዳለበት እንዳላወቀ ሁሉ። ልብ ሲሻክርና ሲራራቅ የሚዋደድ ሰው የሚያወራው ሁሉ አሸዋ ያለው ቆሎ በተራበ ሰው አፍ ውስጥ እንደ መጨመር ይሆናል። ወይ አይቆረጥሙት ወይ አይተፉት።

"ደኅና ነኝ መሊ ያው ደኅና ከተባለ። ያው ከቢቢ ሞት በኋላ ሁሉም ነገር ነው ዝብርቅርቅ ያለብኝ። እቤትም በጣም ነው የተጎዱት። አሁን እንዴት ጥያቸው እንደምመጣም ግራ ገብቶኛል። ኒውዮርክም መሄድ የፈለግሁት ትንሽ ራሴን አረጋግቼ ማሰብ ለመቻል ነው። በቃ ሐሳቤ እንደዚህ ሆኖ እኮ ከማወራህ ብዬም ነው የጠፋሁት።" አለች ላለመደወሏ በቂ ምክንያት ለማቅረብ የተቸገረች እያስመሰለባት።

"አይ ይገባኛል ሰሊ አትጨነቂ። ግን እኮ በዚህ ጊዜ ነው ጓደኛ የሚያስፈልገው። የግድ የሚወራ ነገር አያስፈልግንም እኮ። እኔ የምለው ኒውዮርክ እኅትሽ ጋ ብዙ ትቆያለሽ ወይስ"? አለ አሁንም ወሬው ፍሰት እያጣበት ለመጠየቅ ያህል።

"አይ አንድ ሳምንት ምናምን። ደግሞ ሶለን የሠራቻቸውን ጽሑፎች ሰጥቶኛል። እሱንም መጽሐፍ ሆኖ እንዴት እንደሚወጣ እያሰብኩ ነው። ለዚያ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ እየሰበሰብኩ ነው። በጣም ጥሩ ነገሮች ናቸው። አንተ ካልሆንክ ማንም ጥሩ መጽሐፍ ያደርጋቸዋል ብዬ አላምንም። እስኪ አንዴ ልሰብስባቸውና እዚያው ስመጣ እናያቸዋለን።" አለች የሱን አስተያየት ለመስማት።

"እህ ሪሊ…? በጣም አሪፍ ነው ሰሊ። ስለዚህ የመጀመሪያውን መጽሐፍ ለመጻፍ እየተንደረደርሽ ነዋ?" አለ ፈገግ እያለ፡፡

"አትቀልድ ባክህ መሊ እኔ እንኳን መጽሐፍ ደብዳቤም መጻፍ አልችልበት። ግን ደግሞ በጣም ከልቤ ነው የምልህ ጽሑፎቹን ብታያቸው አንተም መጽሐፍ ይሁኑ ነው የምትለው። ደግሞ ከልብ ወንድሜ ስለሆነ አይደለም ሶለን ብዙ ነገር መሥራት የሚችል ልጅ ነበር…"ብላ ዝም አለች። አዲስ ልቅሶ እንዳይጀመር ስለፈራ፣ "አይዞሽ ሰሊ የምትችዪውን ሁሉ ሰብስቢ። እስኪ የበለጠ እናወራውና መልክ መልክም እናስይዘዋለን። ስንኪንስ ታገኛታለሽ?" አለ ርዕሱን እየቀየረ፡፡

"አዎን ያው በስልክ በተለይ። እሷ ናት ኤርፖርትም ያደረሰችኝ።" አለች።

እንዲህ እንዲህ እያሉ አንድ ዐሥራ አምስት ደቂቃ የባጥ የቆጡን ከተጨዋወቱ በኋላ በሁለቱ ዓለም ሲካሄድ ስለሰነበተው ነገር እየተማማቁና እየተቃለዱ አወሩ። ከዚያም ሌሎች ጉዳዮችን ጨምረው ወደ ግማሽ ሰዓት ያህል በተለይ ስለ መጽሐፍ ፕሮጀክቷ ተነጋገሩ። ሰሎሜም አንድ ሳምንት ያህል እኅቷ ጋ ኒውዮርክ ቆይታ ወደ ቺካጎ ተመልሳ ቶሎ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ እንዳቀደች ነገረችው። ከዛም ስለ መላኩ ቤተ ሰቦች ብዙ አወሩ። ስለሱ ቤተሰቦች ሲያወሩ ሰሎሜ ደስታዋና ስሜቷ ያስታውቅ ነበር። የሚገርመው ሁለቱንም ያብሰለስላቸው የራሳቸው ግንኙነት ጉዳይ ቢሆንም፣ 'የውሾን ነገር ያነሳ' እንደሚባለው ይመስል ላይ ታች ሲረግጡ ጊዜው አለቀ። ፍቅር እኮ አንዳንዴ ይገርማል! አፍ የሚለጉም አንዳች ምትሃት አለው። ምናልባትም ሰንክሳር እንዳሰበችው መጠነኛ ግድግዳ በመካከላቸው ሳትሠራ አልቀረችም፣ ባለፉት ወራት የቦታ ርቀትና ሁኔታዎች ከፈጠሩት ርቀት በተጨማሪ። የቦታ ርቀትና መለያየት እንኳን በጅምር ፍቅርና በሰነበተውም ትዳር ላይ ይህ ነው የማይባል ጫና መፍጠሩ አይቀርም። ቢሆንም ስልኩን ሲዘጉት የተወሰነ ያህል ጭንቀታቸው የረገበ ይመስላል። መላኩ ወደ ታች

ወርዶ ለብቻው ትንሽ ከተንሸራሸረ በኋላ አነስ ያለች በአካባቢው ባለች የዐረብ ምግብ ቤት እራቱን በልቶ ወደ ክፍሉ ገባ።

መላኩ ዱባይ ከሄደ ጀምሮ ማርቆስ ነበር ለእነማራም ለእነሶስናም የሚያስፈልጋቸውን የሚያደርግላቸው። መላኩ በሄደ በሦስተኛው ቀን ነበር ምንተስኖት ከጎጃም ሳይመለስ ማራ ያልጠበቀችውን ዱብ ዕዳ የሰማችው። ከሁለት ዓመት በፊት ባለቤቷ ምንተስኖት ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ ለአጭር ጊዜ አብራው የምትወጣ ልጅ ነበረች። ወላጆቿ የመንግሥት ሠራተኞች ሲሆኑ፣ አባቷ ኀይለኛና አጥባቂ ሃይማኖተኛ ናቸው። ለቤተሰቧ ብቸኛ ሴትና የመጨረሻ ልጅ ናት። ሰፈራቸው ከምንተስኖት ወላጆች ቤት ቅርብ ባይባልም፣ በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚገኝ ነው።

አንድ ቀን በዝናብ ወደ ቤት ስትሄድ አግኝቶ ሊፍት ሰጥቶአት የጀመሩት ትውውቅ ነው አድጎ ባሥራምስት ቀን ውስጥ ምላጭ በሆነው ምላሱ ያሜሪካንን ተስፋ እንደ ከረሜላ እያሳየ እጁ ውስጥ ያስገባት። የቤት ልጅ ስለ መሰለችውም መከላከያ አይጠቀምም ነበር። አንድ ቀን በጥድፊያ ዕቃ ረስቶ እቤትም ይዞአት ሄዶ ስለነበር የወላጆቹን ቤት አይታው ነበር። ከሄደ በኋላ እንዳረገዘች ስትነግረው ፈጽሞ እንደማያውቃት ሆኖ የዘጋት። ለወላጆቹ ነገሩን ልትነግራቸው ብትሞክርም አጠገባችን እንዳትደርሺ የምናውቀው ነገር የለም ብለው ፊት ነስተዋታል። ከቤትም ተባርራ አሁን ካክስቷ ጋር ኬክ ቤት እየሠራችና ማታ እየተማረች ነው ልጁን የምታሳድገው። በምንተስኖት ቤተሰቦች ቤት ለረጅም ጊዜ የምትሠራውን ጽጊን ቀርባት ነገሩን አጫውታት ወዳጆች ሆነዋል። እሷ ናት ባለትዳር መሆኑንም የነገረቻት። አሁንም ከነቤተሰቡ መምጣቱን ደውላ ነግራት የማራንም ስልክ የሰጠቻት እሷው ናት።

ማራ መጀመሪያ ወሬውን ስትሰማ አንዳች ነገር ነው የነዘራት። ምንተስኖት አያደርገውም ብላ ማሰብ ባትችልም፣ በልጅቷ ላይ የተፈጠረባትን ንዴቷን ልትቆጣጠረው አልቻለችም። በስልኩ ውስጥ እያለቀሰች ነገሩን የምትነግራትን ልጅ ምን እንደምትላት ማራ ነበር የገባት። የምታደርገው ስላጣች መልሳ እንደምትደውልላት ነግራት ስልኩን ዘጋችው። ከዚያም አንዴ ቁጭ፣ አንዴ ደግሞ ቁጣና ቅናት እየተፈራረቁ ጠበሷት። ብቻ ከዚያ በፊት ሊሰማኝ ይችላል ብላ የማታስበው ስሜት ሁሉ ተፈራረቀባት። መታጠቢያ ቤት ገብታ እያለቀሰች ብዙ ቆየች። ፊቷን እያየች ለምን ሌላ ሴት ጋ መሄድ አስፈለገው? እኔ አረጀሁበት ወይስ ምኔ ነው ያስጠላው? ብላ ራሷን ለመወንጀል ከጀላት። ከዛም በሩን አፌኝ ዘግታ አልጋዋ ላይ ተጠቅልላ ለመተኛት ሞከረች። አልቻለችም። ልጅቷን እንዴት ብላ እንደምታገኛትም ግራ ገባት። ባልሽን ከኔ የወለደውን ልጅ ማሳደግ እንዲረዳኝ አማጥኚኝ ብላ ነው የደወለችላት። የሆነ ማንነቷ ነገሩ እውነት እንዳይሆን ተመኘ። የልጅቷ ልቅሶና አነጋገር ግን ውሸት እንዳልሆነ እንድታምን

አድርጎአታል። የምታደርገውን ስላጣች ማርቆስን ደውላ አሁኑኑ ከቻለ እንዲመጣ ጠየቀችው። ነገሩ ስላስደነገጠው እሱም ሲከንፍ ወዲያው ነበር የደረሰው። ማርቆስ እቤት ሲገባ እሪታዋን ለቀቀችው።

"እንዴ ማሪ ምንድነው ነገሩ? ሰላም ነው? ምን ልጆቹ ደኅና አይደሉም?" ብሎ ግራ ገብቶት ትከሻዋን ይዞ መጠየቁን ቀጠለ። "ተወኝ ባክህ የኔ መከራ ማለቂያም የለው። አንዲ ደግሞ አሁን ደውላ ነበር" ብላ አሁንም ልቅሶዋን ቀጠለች፡፡ "እሺ ምን ሆነ? ማናት የደወለችው?" አለ ማርቆስ ማራን እንዲህ ስትሆን አይቷት ስለማያውቅ ግራ ግብት እያለው፡፡

"የውልህ ደውላ ባልሽ ልጅ ወልጄለት ከዳኝ ነው የምትለኝ። ዕፍረትም የላት እና አንድ በይኝ ባልሽ እንዲያምን እርጂኝ ነው የምትለኝ። አሁን እኔ ምንድነው የማደርገው። ይሄ ሰውዬ እኮ ሊያሳብደኝ ነው። አሁንስ በቃ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም..." ብላ እንባ በሞላው ዐይን ቀና ብላ አየችው።

"እስኪ ቆይ ማሪ... በመጀመሪያ ደረጃ ነገሩ እውነት ነው ወይ? ከሆነስ እንዴት ነው የምናምነው... ማለቴ ያው ሰው ካሜሪካ መጣ ስለተባለ ብቻ ልጅ ወልጄለታለሁ ማለት የሚወዱ ብዙ ሰዎች እኮ አሉ።" አለ ነገሩን ለማርገብ ልቡ ነገሩ እውነት ሊሆን እንደሚችል ቢጠረጥርም።

"አይ ማርክ... ሰውዬውን እኮ ስለማታውቀው ነው። እኔ አሁንስ በቃኝ እዚያው እንደፈለገው መሆን ይችላል እሱ ከዘመዶቹ ጋር። እኔ ግን በቃኝ ድሮም የቤቱ ሰቦቹን ምክር ብሰማ ኖሮ እዚህ ሁሉ ውስጥ ባልገባሁም ነበር። እስካሁን ለልጆቼ ብዬ ብዙ ነገር ችያለሁ አሁን ግን በቃኝ..." ብላ ተነሥታ ወደ ጓዳ ገባች።

ማርቆስም ተከትሎአት እየሄደ፣ "እና ምን አልሻት ታዲያ?" አለ በጉጉት።

"ምን እላታለሁ ማርክ... እደውልልሻለሁ ብዬ ስልኩን ዘጋሁታ። እሷ በዚያ በኩል ታለቅሳለች። እኔ ደግሞ እዚህ ጭንቅላቴ ይዞራል። እናቱ መሰልኳት እንዴ ስትማግጥ ቆይታ በኋላ እኔ ጋ የምትደውለው?" ብላ ምሬቷን ገለጸች። ለወትሮው ማራ አዛኝና ለሰላሳ ሰው ብትሆንም ይሄንን ግን መሸከም አልቻለችም።

ከዚያም ማርቆስ ስልኳን ከማራ ተቀበለና ደውሎ አብረው ሊያገኟት ቀጠራት። ማራንም አረጋግቶ ልጅቷን ማግኘት እንደሚያስፈልግ አሳመናት። ጉዳዩ እውነትም ሆነ ውሸት መደረግ ያለበትን ነገር በርጋታ ነገራት። እሱም አብሯት እንደሚሄድና ያለውን ነገር ተረጋግተው ማጣራቱ እንደሚሻል ገለጸላት። ትንሽ ከተረጋጋች በኋላ ማታ ተመልሼ እመጣለሁ ብሏት ወደ ጉዳዩ ሄደ።

በቀጠሮው ሰአት ከልጅቷ ጋር ካፌ ውስጥ ነበር የተገናኙት። ልጂቱ ከአንድ ዓመት ብዙም የማይበልጥ ልጅ ይዛለች። እሷም ልጁም ድንበሽበሽ ያሉ

ሲሆኑ ኀዘን ያጠላበት ፊቷ ከየዋህ ዐይኖቿ ጋር ብልጣብልጥ አለመሆኗን ይመስክራል። ማርቆስ ማኪያቶ የቀሩት ደግሞ ሻይ አዘዙና የተፈጠረውን ውጥረት ማርቆስ ስለልጅቱ አጠቃላይ ነገሮችን በመጠየቅ ካረገበ በኋላ ወደዋናው ጉዳይ ገብተው መወያየት ጀመሩ። የሆነውን ሁሉ ነገር እንደገና ነግራቸው ስትጨርስ "እኔ ከሱ ምንም አልፈልግም ቢያንስ ልጄን ያለ አባት አያስቀረው። እኔንማ እንደ ተጫውቶብኛል። የራሴ ጥፋት ነው እሱን ማመኔ። ለማን እንደምነግረው ግራ ስለገባኝ ነው ላንቺም መናገር የፈለግሁት እንጂ... ይሄ የሚያሳፍር ነው። ትዳር እንደሌለውም ነበር የነገረኝ። ደግሞ ያሜሪካ ዜጋ ስለሆነ ባጭር ጊዜ ጨርሶ ሊወስደኝ እንደሚችል ነበር ቃል የገባልኝ። እዩው ይሄንን ሐብልና ቀለበት እንኳ ራሱ ነው የገዛልኝ። ማርገዜን ስነግረው ግን በቃ ከዚያ በኋላ ደውሎም አያውቅ። ቤት ስዐቱም ያው ምንም እንደማያውቁ ነግረው አመናጭቀው ነው ያባረሩኝ። እኔ አሁን ምን ማድረግ ነው የምችለው? ሰው በቃ ገንዘብ ካለው የፈለገውን አድርጎ እንደፈለገው መኖር ይችላል ማለት ነው?" አለች እንባዋ እየቀደማት። ከኪሱ ዉስጥ ምንም ናፕኪን ያላገኘው ማርቆስ አስተናጋጁን ጠርቶ እንዲያመጣላቸው አደረገ። ከዚያም የናቱ ለቅሶ በቁና ያደረገውን ልጅ እንዳያለቅስ ማጫወት አይሉት ማባበል የሚችለውን ማድረጉን ቀጠለ።

ግራ ንዴቱም፣ ቁጣውም፣ ለልጅቷ ማዘኑም በቃ ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት ጭንቅላቷን አጡዞት ስለነበር ድንጋይ ሆና ነው ስትሰማት የነበረው። ማርቆስ ድሮውንም ምንተስኖትን ተራ ዐይነት ሰው አድርጎ ስለሚያስበው አሁን ደግሞ የባሰውን ቀለበት። እሱም ምን ማለት እንዳለበት ስላላወቀ ግራን እየጠበቀ ዝም አለ። ምንስ ይባላል?

በዚህ መሃል ወዲያው ደግሞ ሕፃኑ እየተንገዳገደ ሄዶ ግራ ጉልበት ላይ ልጥፍ ብሎ እየሣቀ መጫወት ሲጀምር አንጀቷን በላውና እንሥራ ታቀፈችው። አፉ ላይ የተዝረከረከውን ለሃጭ በያዘችው ናፕኪን ጠራርጋለት ሳመችውና መልሳ ለእናቱ ሰጠችው። ሕጻኑ ጠረጴዛ ላይ ያሉትን እቃዎች ካልያዝኩ እያለ ስላስቸገረ አስተናጋጁን ጠርተው እቃውን አነሳስቶና ጠረጴዛውን ጠራርጎ ሄደ።

በዚህ መሃል ግራ እንደ ምንም ኀይሏን አጠራቅማ "እም ... ምን ልልሽ እንደምችል አላውቅም። ማድረግ የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለና። በተለይ ይህ ሕፃን ባላጠፋውና በማያገባው ጉዳይ መሠቃየት የለበትም። ያው የዲኤንኤ ምርመራ ስላለ የሱ ልጅ ከሆነ መካድ አይችልም። ያንቺንና የልጁን ፎቶ ይዘሻል እንዴ?" አለች አሁንም ውስጧ እንደተረበሸ፡፡

"አይ አልያዝኩም። ይቅርታ ግን ላንቺ ከባድ እንደሚሆን አውቃለሁ። እንዲያው የምገባበትና የማደርገው ባጣ ነው። ደግሞም በዚህ ካልተገታ ሌላ ሰውም ማበላሸቱን የሚያቆም አይመስለኝም።" አለች አሁንም ከፊል ዕፍረትና ከፊል ቁጣ እየተሰማት።

"እንቺ ከፈቀድሽ እኔ ካሜራ ይገኛያለሁ። ያው ፎቶውን አሳየውና መጀመሪያ እኔ ራሴ አነጋግረዋለሁ። አላውቅም ካለ ግን የዲ ኤን ኤ ምርመራውን ጉዳይ እንቀጥላለን።" አለች ግራ ካሜራ ከቦርሳዋ ውስጥ እያወጣች።

ሕፃን ሕፃን ነውና ከማርቆስም ከግራም ጋር ጨዋታውን ቀጠለ። በሱ ዓለም የትልልቆቹ ሰዎች ፖለቲካና አታካሮ ምንም ትርጉም የለውም። ሕፃን መሆን ደስ ሲል! ግራም ስላሳዘናት ትንሽ ተቀብላ ታቅፋ አጫወተችው። በዚያ ሰፍራ ያለውን ውጥረትና ውስብስብ የሰው ክፋት ያልተረዳና ያልተማረ እሱ ብቻ ነበር። ይህስ ምን ዐይነት ሰው ይሆን ሲያድግ? ፎቶ ካነሳቻት በኋላ ለታክሲና ላንዳንድ ነገር እንዲሆንሽ ብሎ ማርቆስ የተወሰነ ገንዘብ ሰጥቶአት እንደሚደውሉላት ተነጋግረው ተሰነባበቱ። ልክ እሷ እንደሄደች ግራ እዩዩዋን ለቀቀችው። ማርቆስም ፈጽሞ ሊያስቆማት አልቻለም። ለዓመታት በተሸከመችው የስሜት ፍም በዐይኖ... የእንባ ከረጢት ውስጥ የተረገዘውን እንባ ትኩስ ትኩሱን ታዘንበው ጀመረ። ማርቆስ ግራን አቅፎ ማባበሉ ብዙ ደቂቃ ነበር የወሰደበት። ከዚያም ቁጣዋና ንዴቷ ጦፎ

"የኔና የሱ ነገር አልቋል። ድሮውንም ቢሆን የራሴ ደንቆሮነት ነው። ቤተ ሰቤን ብሰማ ኖሮ እዚህ ሁሉ መቀመቅ ውስጥ አልወርድም ነበር። ወይኔ ግራ!" ብላ አዲስ እሽግ የእንባ ከረጢት እንደፈታች ሁሉ እንደገና ስቅስቅ ብላ ማልቀሷን ቀጠለች። በካፌው ውስጥ ወደ ጥግ አካባቢ ስለተቀመጡ ብዙም የሰውን ቀልብ አልሳቡም።

"የውልሽ ግሪ አሁን በጣም አስቸጋሪ ሰዓት ነው። ምንም አትወስኚ። ነገሩ እውነት ነው የሚመስለው። ግን ደግሞ አሁን በስሜት ብታደርጊው ብዙ ነገሮች ላንቺም ለልጆቹም ሊበላሹ ይችላሉ። መላኩም ይምጣና ተረጋግተን ተመካክረን ብናደርገው አይሻልም?" አለ ረጋ ባለ ድምፅ፡፡ ውስጡ ግን ስሜቱ ድብልቅልቅ ብሎ ለርሱም አስቸግሮታል። ነገሩ ግራ የገባው ሲያስተናግዳቸው የቆየው ልጅ መለስ ቀለስ ማለቱን ቀጥሏል።

"ማርክ ምን... ነው የምናስብበት ሰውዬው እኮ በሄደበት መዝለል መባለል ነው። እንስሳ እንኳን ከሱ ይሻላል። አያስብም እኮ። እይ ይቺ ልጅ አሁን የሱ ልጅ አትሆንም። ደግሞ ውሸቱ። ሲያዩት ትልቅ ሰው ይመስላል። እኔ ነኝ እሱማ ምን ያድርግ። አሁን ምንድነው ሚባለው።፡እኔ ኮ ለልጆቼ ብዬ እንጂ እሱን እዚያ እንደፈለገው መሆን እንዲችል ከሕይወቴ አሽቀንጥሬ መጣል አያቅተኝም ነበር። አሁን ግን በቃ ይሄ የመጨረሻው ነው።" አለች አሁንም ግራ መጋባትና ንዴት በተቀላቀለበት ስሜት። ቦርሳዋን ከተንጠለጠለበት አንስታ ከፊተኛና የያዘችውን ካሜራ የመወርወር ያህል ጣል አድርጋ በእግሯ መሬቱን እየጠበጠበች ዝም አለች።

ከብዙ ማጽናናትና ማረጋጋት በኋላ መላኩ እስኪመጣ ለመቆየት

ተስማምተው ነገሩን አረገቡት። ወደ መታጠቢያ ቤት ሄዳ ፊቷን ታጥባ ቀዝቀዝ ብላ ስትመጣ ተያይዘው ወደ ቤት ሄዱ። ማርቆስ ግራ ከምንተስኖት ጋር መኖር እንደሌለባት ቢያምንም ቀጥተኛ ምክርን ሊሰጣት አልፈለገም። ሁሉም ነገር ከስሜት ውጥረት ቢረግብ የተሻሉ አማራጮች ሊኖሩ እንደሚችሉም አሰቧል። እሱም የሚያውቃቸው ብዙ ውጪ የሚኖሩ ወንዶች ባለትዳሮችንም ጨምሮ አገር ቤት መጥተው መማገጥን እንደ ፋሽንና ሥልጣኔ ነው የሚያዩት። ሴቶቹም የተባሉትን ሁሉ አምነውና ጊዜያዊ መዝናናቱን ፈልገው ክብራቸውን እንደዚህ በዘቀጡ ዘልባሎች ላይ ራሳቸውን እንደ ዕቃ መጣላቸው አንድም የድኽነት ውጤት ነው፤ ደግሞም የስግብግብነትና ያለመብሰልም ምልክት ነው። ወላጅም ልጅ ስታረግዝ እንዴት ተነካሁ ብሎ ማባረር እንጂ ነገሩ ከመድረሱ በፊት በግልጽ በመወያየት እንደ ምንተስኖት ያሉ ተኩላዎችን እንዴት ማምለጥ እንደሚችሉ ለየዋህ ልጆቻቸው አያስተምሩም። አደጋው ከደረሰ በኋላ ዘራፍ ከማለት በሥቃይና በሠቆቃ ውስጥ ያለችውን ልጅ መርዳት እንደሚሻልም አያውቁም።

ከዕለት ወደ ዕለት እየወረደ ያለው ግብረገባዊ መፍረክረካችን፣ ሰብአዊ ክብራችንንም እንደ ጉልት ፍግ ማርከሳችን የአስተሳሰብ ድኽነት ውጤት ካልሆነ ምን ሊባል ነው? ዐረቡም ሌላው አፍሪካዊም መባለግ ሲያምረው እዚህ ኢትዮጵያ መጥቶ ቆሻሻውን አራግፎ ይሄዳል። ከነሱ የሚብሱት ደግሞ የሰው ደላሎች ናቸው። አንደኛውን ሴትኛ አዳሪ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን የቤት ልጆችንና ገንዘብ የጠማቸውን ችግረኛ ጉብሎች ለገበያ እያቀረቡ ይቸበችባሉ። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጉባኤዎችን የመሳሰሉ ዓለማቀፍ ስብሰባዎችማ ሲደርሱ ሴት እንደሸቀጥ ተቸብችቦ ዕጥረት አጋጥሞአል ሲባል መስማቱ ልቦና ላለው እንዴት የሚያሳፍር ነገር ነው! ቀን በስብሰባ ላይ ሲደሰኩሩ የሚውሉ ትልቅ ሰው መሳዮች ሁሉ በጨለማ በየሆቴሉና 'ማሳጅ' ቤት ተብዬዎቹ የሚያደርጉት ሥራ ሁሉ አሳፋሪነቱ ልክ የለውም።

* * *

ሰሎሜ ኒውዮርክ ስትሄድ የሶለን ማስታወሻ የሚል ርእስ የሰጠውን የወንድሟን ጽሑፍ እያነበበችው ነበር። 'አራቱ የፍቅር ፈርጦች' የሚለው ጽሑፉ የሚያሥቅ፣ የሚያሳዝን፣ ስሜቱንም ሆነ ሐሳቦቹን ግልጽ አድርጎ የጻፈበት የግል ማስታወሻው ነው። አንዳንድ ቦታ ጽሑፉ በጣም ግልጽ ከመሆኑ የተነሣ እያፈረች ነው ያነበበችው። ሶለን ይህንን ታሪኩን የጻፈበት ቋንቋ ደግሞ ወሬ የሚመስል ቀላል አጻጻፍ ቢሆንም፣ በውስጡ ብዙ ትርጉምና ቀዛም የበዛበት ስለሆነ ሳትወድ በግዷም ስትሥቅ ነበር። በተለይ ከህንዷ ጓደኛው ጋር የነበረው ግንኙነት በሣቅ ነው ያፈነዳት። ሲጣሉ እንዴት እንደምታኩርፍ፣ ወደር የሌለው ቅናቷ እንዴት መከራውን ያበላው እንደነበር፣ ህንድ አብረው ላንድ ወር በሄዱ ጊዜ ከቤተ ሰቦቿና ዘመዶቿ ጋር ያጋጠማቸው ነገር፣ ሶለን ቋንቋ ባለመቻሉና ባህሉን ባለማወቁ

የሠራቸውን ስሕተቶች፣ ከእርሱ ጋር ለመጋባት ጽኑ ፍላጎት ስለነበራት፣ ልትለቀው እንዳልቻለችና እሱ የፍቅር ዙረቱን አለመጨረሱ፣ መጨረሻ ላይም እሷን ለማራቅ የወሰደው ርምጃ ሁሉ የሚገርም ነው! ፕርያንካ አሁን ኮምፒዩተር ፕሮግራመር ሆና ሁለት ልጆችን ወልዳ ከህንዳዊ ባሏ ጋር ነው የምትኖረው። ኢሜይሏን ፈልጋ ልታገኛት ወስናለች ሰሎሜ።

ካርላ የመጀመሪያ ፍቅረኛው ስትሆን፣ ሳሮን ደግሞ ሦስተኛው ነበረች። የሁለቱም ታሪክ በሶለን አተራረክ አንድ የተካነ ደራሲ እንደ ጻፈው ልቦለድ ልብን እያንጠለጠለ በሣቅ እያፈረሳት ነው ሳታስበው የጨረሰችው። በተለይ ሶለን በሰው ጭንቅላት ውስጥ ገብቶ የማሰብና ብዙ ወንዶች የሌላቸውን ስሜትን በቀላል ቋንቋ ጥልቅ በሆነ መንገድ የሚገልጽበት መንገድ ሰሎሜን ከሌላ ሴት ጓደኛዋ ጋር የምታወራ እስኪመስላት ነው ያስገረማት። ስለዚህም ሳታውቀው ነበር ኒውዮርክ የደረሰችው። አጎቷ ተቀብሎአት መጀመሪያ የምትወደውን የኒውዮርክ ፒዛ በልተው ነው ወደ ማንሃታን አካባቢ ረጅም ፎቅ ላይ ወደአለው አፓርትመንቱ የሄዱት። ኒውዮርክን በተለይ ማንሃተንንና ሴንትራል ፓርክን እንደ ነፍሷ ነው የምትወዳቸው። ባጠቃላይ ኒውዮርክን የማትሰለች የማትተኛና የማታረጅ ከተማ ነው የምትላት። ትልቋን አፕል ልገምጥ መሄዴ ነው ነበር የምትለው በፊት ወደ ኒውዮርክ ስትሄድ።

እቤት እንደገቡ ሁሌም የለመደችውን መኝታ ቤቷን ተዘጋጅቶ ነው ያገኘችው። አጎቷ የአማካሪነት ሥራው ከፍተኛ ገንዘብ ስለሚያስገኝለት ማንሃታን አካባቢ ምቹ ኑሮ ለመኖር ለሱ ከባድ አይደለም። የሚኖርበት ባለሶስት መኝታ ቤት ቆንጆ አፓርትመንት ነው። ቤቱን የሟች ቤተ ሰቡ ፎቶ፣ ብዙ መጻሕፍትና ከፍተኛ ምቾት ያላቸው ውድ የቤት ዕቃዎች ሞልተውታል። በመስኮቱ በኩል ያለው እይታም ደስ የሚል ነው።

"ትንሽ አረፍ ትዪ ጢኒ?" አለ ቴሌቪዥንን ለመክፈት ሪሞቱን እየነካካ።

"አይ አንክል ትንሽ ቀዝቀዝ ስለሚል ልብስ ልቀያይርና ቡና ምናምን ፍለጋ ወጣ ብንልስ?" አለች እያወለቀ ያለውን ኮቱን እየተቀበለችው።

"ጥሩ በቃ ከፈለግሽም ትንሽ አረፍ በዪ። እኔም እዚህ ወይ ቲቪ እያየሁ ወይ ደግሞ ስልክ ምናምን እመላለሳለሁ" አለ ሸሚዙን ወደ ላይ እየሰበሰበ። ለምዶበት ሸሚዙን መሰብሰብ ከድሮውም ይወዳል። ሰውነቱ አሁንም ፈርጣማ ነው፣ ዕድሜውም ስልሳ አካባቢ የደረሰ አይመስልም። የሚያደርጋት ቀጭንና ፍሬም የሌላት ስስ መነጽር ለፊቱ ግርማና አጥልቆ አሳቢ የሚመስል መልክን ትሰጠዋለች። ዘናጭ ነው። ከዚያም ከወደ ጓዳ አካባቢ ማሪንጎ የሚለው ውሻው እየዘለለ መጥቶ ተጠመጠመበት። ከሱ ጋር ሲላፋ ሰሎሜ እየሣቀች፣ "እም ከፈለግህ ደግሞ የሆነ ጽሑፍ አለ። ቢቢ ነው ሆስፒታል እያለ ከኢሜይሉ ውስጥ የሰጠኝ።

አከችዋሊ ከሌሎች ሥራዎቹ ጋር ተደርጎ እንዲታተምም እንደሚፈልግ ነግሮኝ ነበር። እስኪ እየውና ስለሱም እናወራለን።" ብላ አንድ አምስት ገጽ ጽሑፍ ሰጥታው ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች።

'የሶለን ማስታወሻ' በሚል ሶለን በሰባት ዓመት ውስጥ በቀስታ በመጻፍ ያዘጋጀው አጫጭር ትዝብታዊ ጽሑፍ ነው። ሁሉም ስለ ተለያዩ ጉዳዮች ቢሆኑም፣ የአጻጻፍና አንዳች የመልእክት አንድነትም አያጡም። ሶለን ከዐሥራ ሦስት ዓመቱ ጀምሮ የኖረው አሜሪካ ሆኖ ይህንን ጽሑፍ ጽፎታል ማለት ፈጽሞ አያሳምንም። ምክንያቱም ጽሑፎቹ ጥሩ አማርኛና የጠለቀ ባህላዊ መረዳትን ስለሚያሳዩ። ሆኖም ሶለን ከልጅነቱ ጀምሮ ብዙ አማርኛ መጻሕፍትን ከማንበቡም በላይ፣ የክረምት ጊዜውን ወይ ኒውዮርክ አጎቱ ጋ ወይም ኢትዮጵያ ነበር የሚያሳልፈው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንደጨረሰም ኢትዮጵያ መጥቶ ለአንድ ዓመት ቆይቶ ነበር የሄደው። በዚህ ጊዜ የአማርኛ ችሎታውን በከፍተኛ ደረጃ ከማሻሻሉም በላይ አጫጭር ጽሑፎችንም መጻፍ ጀምሮ ነበር። መኝታ ቤቱ ውስጥ ከራስጌው የማይለየው በአዲሳባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ መምህር የሆነ አንድ ዘመዱ የሰጠው የአማርኛ መዝገበ ቃላት አለው።

የመጀመሪያ ዲግሪውን ከጨረሰ በኋላም ለስድስት ወር አዲስ አበባ በዓለም ባንክ ኢንተርንሺፕ ሠርቶ ነበር የተመለሰው። አንዳንድ ጊዜ የሚጽፈው ጽሑፍና የሚሰጠው ማኅበራዊ ትንተና አገር ውስጥም ዕድሜ ልኩን የኖረ ሰው የማይሰጠው ነው። ሁልጊዜም አዲሳባ ሲመጣ ገጠር ሄዶ ወደማያውቅበት አካባቢ መሄድም ደስ ይለው ነበር። ከልጅነቱ ጀምሮ ከአባቱ ጋር የሚያደርጋቸው ጥልቅና ሁለገብ ሙግቶችና ውይይቶችም ከፍተኛ ተጽዕኖ አድርገውበታል። ስለዚህም አሜሪካ በመኖሩ ፍጹም አሜሪካዊ ቢመስልም፣ ደሙ ውስጥ ግን ኢትዮጵያዊ ማንነቱ እንደሚበልጥ ጽሑፎቹም ይመሰክራሉ። ወደ ኋላ ላይ ነው አሜሪካ ያሉ የጥቁሮች ጉዳይና አጠቃላይ የአፍሪቃውያን ዝቅተኛ ኑሮና መናቅ ሲያንገበግበው፣ ከሃበሻነቱ ይልቅ አፍሪቃዊነቱ ላይ ማተኮር የጀመረው። የሰሎሜ አጎትም ሳያስበው ጽሑፉ ውስጥ ራሱን ነክሮ እያሰበ ማንበቡን ቀጠለ፤ አንዳንዱን ነገር ሁለቴና ሶስቴ እያነበበና እያሰበ።

ሁልጊዜም ውሃ ውስጥ መግባት የማይሰለቻት ሶሎሜ ከተዝናኑች በኋላ በተለይ ሻወር መውሰድ ልማዷ ነው። የአጎቷ ቤት መታጠቢያ ደግሞ ደስ ይላታል። ገንዳው ሰፊና ምቹ፣ የውሃ አሸንዳውም ቄንጠኛና የማሳሳ ያህል ነው። እየተርገበገበ ሰውነቷን ሲደበድበው ትደሰታለች። ስለዚህም የምትለብሰውን ልብስ ከመረጠች በኋላ ውሃ ውስጥ ገባች። የተለቀቀ ጸጉሯን እንዳይበላሽ አስራ ሸፈነችውና በመጀመሪያ ለሰስ ያለውን ውሃ ላይዋ ላይ ለቃ ጸጥ ብላ እንደ ቆመች አፈሳሰሱን እየቀየረች በውሃው መጫወት ጀመረች። ማስተካከያውን ስትነካካው ሳታውቅ ሙሉ በሙሉ ቀዝቃዛ አድርጋው ኖሮ እንደ በረዶ የቀዘቀዘው ውሃ

ሲቸለስባት "ማሚዬ ... ውሀ ሀ ሀ..." ብላ ለመሸሽ ስትል ልትወድቅ ነበር የሞጣ ማስቀመጫውን ባትይዝ። በተለይ ሳታስበው ከሆነ ቀዝቃዛ ውሃ በጣም ነው የምትጠላው። ከዚያም ቀስ ቀስ እያለች የሚመቻት ሙቀት ድረስ አስተካከለችና ወደ ውሃው ተመለሰች።

ሙሉ በሙሉ በሳሙና የተሸፈነው ሰውነቷ ውሃው ሲፈስበት ጠይም ገላዋ ተገለጠ። ጥሩ የሰውነት ቅርጽ ነው ያላት። የእግሮቿ ባቶች እስከ ቁርጭምጭሚቷ ድረስ ሞላና ወፈር ያሉ ስለሆኑ በተለይ ቁምጣ ወይም ጉርድ ልብስ ስትለብስ በጣም ነው የሚያምረው። የጣቶቿም ጥፍሮች ረዘም ያሉና ቅርጻቸው የሚያምር ነው። የጫማ ቁጥሯ ለቁመቷ ትንሽ አይባልም። የሰውነቷ አሰካክ የበለጠ እንዲያምር ያደረገው ከወገቧ በታች ያለው ቁመቷ በአንጻራዊነት ከወገቧ በላይ ካለው ስለሚረዝም ሳይሆን አይቀርም። በተለይ ቁምጣና እግሯን የሚያሳይ ልብስ ስትለብስ አቋሚን ያሳምረዋል። ቀጭን ባትባልም ዳሌዋ አካባቢ ሞላ ከማለቷ በቀር ሆዷ ለጥ ያለና በስፖርትና በዋና ብዛት በበቂ ጡንቻ የተደገፈ ስለሆነ፣ ስትጠግብ እንኳ አምልጦ የሚወጣ ሆድ የላትም። ሁሌም ሻወር ስትወስድ ራሷን ዞር ዞር እያለች ማየትና ሆዷን በእጆቿ መለካት ትወዳለች። እጆቿም ቢሆኑ ከሥብ ይልቅ በጡንቻ የጠነከሩ ስለሆኑ አጠቃላይ ቁመናዋ የተስተካከለ እንዲሆን የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል። ፊቷ ሞለል ያለ ሲሆን ወፈር ወፈር ያሉ ከንፈሮቿና ትንሽ ከማትባል አፍንጫዋ በላይ የተተከሉ ተለቅ ተለቅ ያሉ ቆንጆዬ ዐይኖቿ መልኳን ውብ ሊባሉ ከሚችሉ ሴቶች ጎራ ይቀላቅሉታል። ሰሎሜ ግን ቆንጆነቷን ብታውቅም፣ በቁንጅናዋ ተደምማ እዩኝ እዩኝ ባይ አይደለችም።

ከመታጠቢያ ገንዳው ወጥታ በመስተዋቱ ፊት ቆማ እየተቀባባችና ራሷን እያየች ትንሽ ቆየች። 'መላኩ ወይስ ክብሮም? ኢትዮጵያ ወይስ አሜሪካ? እነሶስና ወይስ ወላጆቿ? የሶለንንስ መጽሐፍ? የግድ መላኩ ማስፈለጉ አይቀርም።' የሚሉት አሳቦች ተደበላልቀውና ተግተልትለው በውስጧ ተተረማመሱ።

ሐሳቧን ከራሷ ላይ ለማራገፍ እየሞከረች ልብሷን ለባብሳ ስትወጣ አጎቷን ሲያለቅስ አገኘችውና "እንዴ ምነው ደኅና አይደለህም እንዴ? ምነው አንክል?" ብላ በፍጥነት አጠገቡ ተቀምጣ ዐይን ዐይኑን ማየት ጀመረች። እጁ ላይ ያለውን የሶለንን ጽሑፍ እንደያዘው ነበር።

"ጢጊዬ አነበብኩት... ታውቂያለሽ? እኛ እያለን ሽማግሌዎቹ ወይ ደግሞ ስንቱ የሀገር ሽክምና ሰው መሆንሽን የሚያስጠላሽ እያለ ሶለን አልነበረም መሞት የነበረበት። አስቢው ... ምናይነት ጭንቅላት ምን ዐይነት ፖቴንሺያል የነበረው ልጅ እንደነበር! ወይኔ ልጄ... እኔ እኮ ድሮም እሱ የተለየ ተልእኮ ያለው፣ ልዩ ችሎታ ያለው ሰው መሆኑን አውቃለሁ። ምናለ ፈጣሪ ትንሽ ዕድሜ እንኳን ቢሰጠው ኖሮ። ባልጠፋ ዕድሜ ስንቱ ሲቀልድበት።" አለ እንባውን ለመጠራረግ እየሞከረ፡፡

"እይ አንክል ያው እንግዲህ ፈጣሪ ለምን እንዲህ አደረግህ አይባልም። ደግሞ የፈጣሪ ብቻ ሳይሆን የሰውም ክፋት እኮ አለ። የሚገርምህ ሌሎቹንማ ጽሑፎቹን ብታነባቸው የሚገርም ነው። ግን እንግዲህ ምን እናደርጋለን? በቢኬ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ሰው የሚተርፍ ነገር ነበር የነበረው።" ብላ ካልወጣዉ የሚላትን እንባ እንደ ምንም አምቃ አስቀረችው።

"ኡፍፍፍፍ ... ብቻ ምን ይደረጋል?... ልክ ነሽ ... እስኪ መጣሁ። ፊቴን ትንሽ ውሃ ላስነካና እንወጣለን" ብሎ ወደ ጓዳ ገባ። ከዚያም ወረቀቶቹን እንደያዟቸው ወጥተው በአካባቢው ወዳለ ካፌ ገብተው ቡና ገዙና አየሩ ጥሩ ስለነበር ውጪ ዐላፊ አግዳሚውን እያዩ ተቀመጡ። የሶለንን ማስታወሻ እንደገና እያነበቡ በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ ተወያዩ፣ ተከራከሩም። በዚህም መሃል የሶለንን ታሪክና ሥራዎች በመጽሐፍ ለማውጣት እንዳሰበች ስትነግረው ደስታው ፊቱ ላይ እየተነበበ

"ጢኒ ትልቅ ሥራ ነው የሚሆነው። እኔም የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ የማግዝሽ ነገር ካለ ንገሪኝ። ከፈለግሽ እዚህ ቁጭ ብለሽ ልትጽፊ ትችያለሽ። ደስ እንዳለሽ። የማሳተሚያውን ዋጋ ሙሉውን እኔ ነኝ የምሸፍነው።" አለ ሳያስበው ፊቱ ፈካ ብሎና ሁለት እጆቹን በማወናጨፍ አይነት። እሷም ደስ ብሎአት ተነስታ ዕቅፍ አድርጋ ሳመችው። ከዚያም ወጥተው በቅርቡ የወጣ አንድ ፊልም አዩ። ሁሌም እንደሚያደርጉት ወደ ሴንትራል ፓርክ ሄደው ሲዘዋወሩ ቆይተው አመሻሹ ላይ ወደ ቤት ገቡ። በዚህ ትልቅ ከተማ መሃል ይህንን ያህል ስፍራ ለመናፈሻ ማስቀረታቸውና እንዴት እንደያዙት ስታይ ሁሌም ይገርማታል። በውስጡ ደግሞ መሮጫና የብስክሌት መጋለቢያ ጎዳናዎች፣ የመኪና መንገዶች፣ ተቀምጦ መዝናኛ ወንበሮች፣ ትንንሽ ኩሬ ሐይቆችና የተለያዩ ሐውልቶች አሉ። ዐልፎ ዐልፎም ውሾቻቸውን የያዙ ሰዎች ግማሾቹ በቀስታ እርምጃ፣ ሌሎቹም በሶምሶማ ሩጫ ያልፋሉ። መቼ ይሆን እኛስ አገር ዛፍ ስናይ ለመቁረጥ መጥረቢያ መሰንዘር፣ ውሻም ስናይ ወርውሮ መምቻ ድንጋይ ማንሣት የምናቆመው? ብላ ለራሷ ዐሰበች።

በማግስቱ አጎቷ ለአምስት ቀን ወደ ደቡብ አሜሪካ ከመሄዱ በፊት አንዳንድ ግራ ያጋቧትን ነገሮች አማክራው የተወሰኑ ምክሮችን ሰጣት። የመላኩንና የክብሮምን ነገር ግን ለማንሣት አቅም አላገኘችም። እሱ ከሄደ በኋላ ነው መላኩም ጋ የደወለችው። ከመላኩ ጋር ከዚያ በኋላ በየቀኑ ቢያወሩም፣ ልቧ ግን አሁንም በመካከላቸው የተፈጠረ ገደል እንዳለ ነው የሚሰማው። ምክንያቱን ልታውቀው አልቻለችም። በርግጥ የክብሮም ነገር ቶሎ መፈታት እንዳለበት አውቃለች። እንዴት እንደዚህ ዐይነት ግራ መጋባት ውስጥ እንደገባች ሊገባት አልቻለም። ክብሮም ያሳዝናታል፣ መላኩን ደግሞ ትወደዋለች። ልክ በሕያዉና በሶለን መካከል ምርጫ የማድረግ ያህል ነው የሆነባት። ጉዳዩን ከስንክሳር ጋር ለመመካከር አስባ ተወችው።ስንክሳር ደግሞ ክብሮምን ብታገባ ደስ እንደሚላት

እየገባት መጥቶአል፣ በግልጽም ነግራታለች።

በሚቀጥሉት ቀናት ሰፋ ያለ ጊዜ ስለነበራት የሶለንን ፋይሎች በሙሉ ከኢሜይሉ ላይ ልቅም አድርጋ ወደ ወረቀት ቀይራ ያዘቻቸው። ለመጻፍ ላቀደችው ሥራ ለሰዎች ቃለ መጠይቅ ማድረግ እንደሚኖርባት አሰበች።

አጎቷ እንደተመለሰ ሁልጊዜም ልታየው ወደምትመኘው ሜይን ግዛት ነድተው ሄደው አንድ ሁለት ቀን ቆይተው መጡ። ለካናዳ ቅርብ የሆነ ሰሜን ምሥራቅ ጫፍ ላይ ያለ በጣም የሚያምር ግዛት ነው። ክረምቱ ከባድ ቢሆንም በበጋው ጊዜ ልብ የሚሰርቅ ውበት አለው። በተለይ የባሕሩ ዳርና ያካባቢው ትናንሽ ከተሞች ልዩ ውበት ነው ያላቸው።

ሰሎሚ ወደ ቺካጎ የተመለሰችው ሳምንት ያህል ቆይታ ነው ። በተለይ የሶለንን ታሪክና ሥራዎች ወደ መጽሐፍ መለወጥ የሚለው ለአእምሮዋ አትኩሮትና ዐላማም ስለሆናት ኀዘኗን ቀንሶላታል። ኒውዮርክ ከርማ መምጣቷና ከአጎቷ ጋር ያደረገቻቸው ምክክሮችም በጣም ሳይጠቅሟት አልቀሩም። በሁለት ቀን ውስጥ ደግሞ ልደቷ ስለሆነ ገና ኒውዮርክ እያለች ክብሮም ለምሽቱ ሌላ ቀጠሮ እንዳትይዝ ነግሯታል። ክብሮም የምሽት ሽርሽር በሚደረግበት ትልቅ ጀልባ ላይ ነው ልደቷን ሊያከብርላት ስፍራ የያዘው። ይህ የስንክሳር ሐሳብም አለበት። ሰሎሜ ውሃ ስለምትወድና በጀልባ ላይም ያሉ ተንሸራሻሪዎችና አስተናጋጆች ልደት ማክበርን እንደ ትልቅ ነገር ስለሚያዩት፣ የሚፈጠረው ግርግር ስንክሳርና ክብሮም ላሰቡት እቅድ ሁነኛ ቦታ እንደሚሆን አምነዋል። ቤተሰቧም ከክብሮም ጋር ያላትን የራት ቀጠሮ ስላወቁ ምሳ ነው የጋበዟት። ሰሎሚ ሞርተን ስቴክ ከተባለች በደስታ እንደምትከንፍ ስላወቁ እዛ ነው የወሰዷት። ምግባቸው ውድ ቢሆንም የቤቱና የምግቡ ጥራት ግን ለዋጋው ይመጥናል። ጋባዡ ደግሞ ዶክተር ሕያው ነው።

"ታዲያ መቼ ነው እኛንም የልጅ ልጅ የምታሳዩን፣ ሰርግ የምታበሉን ሕያውዬ?" አሉ ወይዘሮ ሕይወት ሰሎሜንም እያዩና የቀረበላቸውን ውሃ ተጎንጭተው እያስቀመጡ።

"ማሚዬ እኔ እንዳንቺ ያለች ጥሩ ሴት ካገኘሁ ነገም አገባለሁ። ምን እኮ ሰውም ማግኘት አልተቻለም። በዚያ ላይ ሥራው፣ ማንን አውቀን ማንን እናገባለን ብለሽ ነው? ይልቅስ ሰው ከሞላበት አገር የመጡ አንዳንዶች ይናገሩ።" አለ የሰሎሜን እጅ ያዝ አድርጎ።

አቶ አላናም ፈገግ ብለው "የኔ ልጅ ጢኒማ እስካሁን መቼም አንድ ነገር ሳይጠነሰስ ይቀራል እንዴ?" አሉ ሌላ እጇን ለመያዝ እየዘረጉ።

"እዬ ዳዲዬ አሁን እኮ ሰውንም ማወቅ* ከባድ ሆኖአል። እኔ ግን በናንተ ጊዜ

ተወልጂ ቢሆን ጥሩ ነበር። እናንተ እኮ ነገር ሳታወሳስቡ በቃ ሰው በሚተማመንበት ዘመን ነው የተገላገላችሁት። አሁን እኮ በዚህ ፍቺው፣ በዚህ አለመተማመኑ መከራ ነው።" አለች ሰሎሜ። ለወትሮዋ ትዳርን ብሩህ አድርጋ እንጂ አጨልማ አታይም ነበር።

"እምነት አሁንም ድሮም ያው ነው። ምክንያቱም የምታምኚው ሰውን ሁሉ ሳይሆን የምታገቢው አንድ ሰው ነው። ለነገሩ ደግሞ ፍቅርና መተዋወቅ እያደር የሚገለብት ነገር ነው። ሰው በትዳር ውስጥ ይሠራና ያምራል እንጂ ለትዳር የተሠራ ያለቀለት ባልም ሆነ ሚስትም አይገኝም። እንደዚያ የሚመስል ሰው ካጋጠማችሁ ባብዛኛው ውሸት ነው። ዋናው ግን በመሠረታዊ ነገር ተስማምቶና ልባዊ ፍቅር መኖሩን አውቆ እግዜሩ የፈቀደው ከሆነ፣ የቀረው ተጋብቶ ነው የሚሠራው" አሉ አሁንም አቶ አላና ንግግራቸውን እያጠበቁ።

"አሁን ጢንዬ አንቺን ለመሰለች ልጅ ሰው ጠፍቶ ነው? ልጅም ትዳርም እኮ በልጅነት ነው የሚያምር። ሕያውዬ ግን እምቢ ካልክ እኔ ራሴ ነኝ ካገር ቤትም ቢሆን አምጥቼ የምድርህ።" ሲሉ እናቱ ማቁን ለቀቀው።

"ከሰማይ ቤት ካልሆነ እኔ ደግሞ አላገባም።" ሲል ሁሉም ሣቁ። ሕያው ቀልድ አይሆንለትም። የሶለን አለመኖር የፈጠረው ችሎታ መሆን አለበት እንጂ።

"እኔ እናትህ የመርጥኩልህ ከሰማይ ቤት የተመረጠች መሆኗን አትጠራጠር" አሉ አሁንም ፊታቸው እንደ ፈካ።

"አይ ማሚዬ እኔ ግን በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ ባገባ ደስ ይለኛል። እናንተም ጸልዩልኝ። ፕሊስ" አለች ሰሎሜ ሁሉቱንም ተራ በተራ እያየች።

"እኔ ግን አበሻ ከጠፋ ፈረንጅም ቢሆን ማግባቴ አይቀርም።" ሲል ሕያው፣ እናቱ ቀበል አርገው "የምን ፈረንጅ ልጄ.. አንተ እየው እንዲያውም ካገርቤት ከምንጩ የሆነችዋን አበሻ ነው ማግባት ያለብህ። ሕያውዬ አንተ አታውቀውም እንጂ እኮ አንተ ደንበኛ አበሻ ነህ። ምን አቃጠለህ ከሰው ሰው ጋር ልጄ?" አሉ እንደ ልጅነቱ ጉንጩን እያሻሹ፡፡

እንደዚህ እንደዚህ ሲጫወቱ ቆይተው ወደ ዐሥር ሰዓት ላይ ወደ ቤት አመሩ። ደስ የሚል ከሰዓት በኋላ ነበር። እነአቶ አላና የታመመ ሰው ለመጠየቅ፣ ሕያውም ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር እራት ስለነበረው ሲወጡ ሰሎሜም ለማታ ራት መዘገጃጀት ጀመረች። ለዐሥራ ሁለት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ክብሮም መጣና ተያይዘው ወጡ። እሱ እንደ ወትሮው ዝንጥ ያለ ሲሆን ሰሎሜ የሰጠችውን ሽቶ ነው የተርከፈከፈው። ፊቱ ሁሉ ሣቅ በሣቅ ሆኖአል። ለቅጽበት በክብሮም ልደት ቀን የሆነው ነገር ትዝ አላት። ትንሽ ውስጧን ቢረብሸውም ራሷን አረጋግታ መኪና

ውስጥ ገባች። ሰሎሜ ዛሬ ክብሮም የሚወደውን ልብስ ነው የለበሰችው። ይሄንን ልብስ ስትለብስ ሁሌም አድናቆቱን ሳይገልጽ አይቀርም። ይህም ልቡን ሞቅ አድርጎታል። ብዙ ጭንቅንቅ ስላልነበረ በጊዜ ደርሰው መኪናቸውን ኔቪ ፒየር ሥር ካለው መኪና ማቆሚያ ውስጥ አቁመው ወደ ጀልባ መሳፈሪያው ዴክ ሄዱ። ሽርሽሩ የሁለት ሰዓት ሲሆን የሚጀምረው ወደ አንድ ሰዓት አካባቢ ነው። ወደ ሐይቁ መሃል ደርሶ ነው የሚመጣው። የጀልባ ላይ ራት መሆኑ ራሱ ሰሎሜን አስደስቶአታል። ምክንያቱም ሰማዩ ዛሬ ጥርት ያለ ስለሆነ ፀሐይ ስትጠልቅ ማየት ስለሚችሉ ነው።

ኔቪ ፒየር እንደዚህ ባለው ፍንትው ያለ ቀን ሰው ይበዛበታል። ከሐይቁ ወደ ውስጥ ገባ ባለ ሰርጥ ላይ ሲሆን የተሠራው ብዙ መዝናኛዎችንና የምግብ ቤቶችን የያዘ ነው። ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ የመንሸራሸሪያ ጀልባዎችም መልህቃቸውን ጥለው ቆመዋል። አነስ አነስ ያሉት ደግሞ በየሰዓቱ ሰው እያሳፈሩ ያዝናናሉ። ውስጥ ገብተው ትንሽ ከቆዩ በኋላ ወደ ጥግ አካባቢ ሄደው ባለው መደገፊያ ላይ ደገፍ ብለው ሐይቁን ማየት ቀጠሉ። ጸጥ ያለ አየር ነው። ከነሱ ብዙም ሳይርቁ የሚዋኙትን ዳክዬዎች እያዩና ከባሻገር ያለውን ሳይትሃውስ የሚባለውን የመቆጣጠሪያ ቤት አልፎ ወደ ወደቡ የሚመጣውን ትልቅ መርከብ ከሩቅ አዩ። ዞረው ሲመለከቱ ደግሞ የከተማዪቱ ዋነኛ ክፍል አምሮና ደምቆ ይታያል። ባለፈው የሄዱበትም ጆን ሃንኮክ ሕንጻ ገዝፎ ከሩቅ ይታያል።

ጊዜው እስኪደርስ ድረስ የሆን ያልሆነውን ሲያወሩ ቆዩ። ጊዜው ደርሶ ቲኬታቸውን አሳይተው ወደ ጀልባው ገቡ። ጀልባዋ የምታምር ነጭ ዘመናዊ ጀልባ ስትሆን እስከ ሦስት መቶ ሰው ትይዛለች። ከማቆሚያው ተነሥተው እየራቁ ሲሄዱ ከተማዪቱን ይበልጥ ለማየት ቻሉ። ፀሐይዋም ወደ መጥለቂያዋ ስታሽቆለቁል በሐይቁ ላይ የፈጠረችው ቀለም ቀልብ ይሰርቃል። ደጋግመው ፎቶ ተነሱ። አሁን ክብሮምም ትንሽ ዘና ማለት ጀምሮአል። በጀልባው የላይኛው ክፍል ወጥተው ዙርያ ገባውን የበለጠ ተመለከቱ።

ከዚያም መቀመጫቸውን ይዘው የሚጠጣ ነገር ቀረርቦላቸው ለስለስ ያለ ሙዚቃ እየሰሙ ቺኪንንና ኒውዮርክን እያነጻጸሩ ማውራት ጀመሩ። ክብሮም ቺክጎን ሲያስበልጥ፣ ሰሎሜ ደግሞ የለም ኒውዮርክ ብላ ነጥቡን ዘረዘረች። ግን ያው ውበት በተመልካቹ ዐይንና በተከራካሪው አፍ ነው የሚወሰነው እንዲሉ አሸናፊ አልነበረም። መታጠቢያ ቤት ደርሼ መጣሁ ብሎ የምሽቱን ዕቅዱን ለነሱ ከተመደበው አስተናጋጅ ጋር ተነጋገረ። የልደቷን ኬክ መሸት ሲል ከራት በኋላ "እንዲያመጣና ለጋብቻም የሚጠይቃት በዚሁ ምሽት ስለሆነ፣ ፎቶ ካሜራውንም ሰጥቶት ሊያነሣው ተስማምተው ሁሉንም አቀነባብሮ ተመለሰ። ቀጥሎም ራት እየበሉ የተለያዩ ሙዚቃዎችንና ዳንሶችን ሲያዩ ቆዩ። በመሃል በዴኩ ላይ እየተዘዋወሩ ችካጎን ከሩቅ በመመልከትና የፀሐዩዋን አጠላለቅ አዩ። ብዙ

ፎቶዎችንም ተነሡ። ሰሎሜ ልቅቅና ዘና ማለት ችላለች። ውሃ ሁሌም ነው የሚያዝናናት ነፍሷን የሚያድሰው፣ እንኳን በሐይቅና በብርጭቆም ሲቀርብ።

ሰው ሁሉ ዲዘርት (የማሳረጊያ ጣፋጭ ምግብ) እየቀረበለት፣ ሙዚቃውም ጋብ ሲል፣ ከዐሥራ ዐምስት የማያንሱ የጀልባው አስተናጋጆች የሥራ ልብሳቸውን እንደለበሱ በተዘጋጀው ኬክ ላይ ሻማ እንደ በራ፣ "መልካም ልደት" የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ መጡ። የቁርጧ ሰዓት ደርሳለችና የክብሮምም እጆች ላብ አመነጩ፣ ያይኖቹ ቅንድቦችና ጀርባውም እንዲሁ ቀዝቃዛ ላብ አፈለቁ። ባንዱም ደመቅ ባለ ሙዚቃ ያጅባቸው ጀመረና ተንሸራሻሪው ሁሉ ቀልቡን ወደነሱ አዞረ። ሰሎሜ በዚህ መንገድ ያልጠበቀችው ስለነበር ድንግጥግጥ ብላለች። ጊዜውም ላይን ያዝ ማድረግ ጀምሮአል። ሻማውን አጥፍታ ኬኩን ስትቆርስ የሰዉ ጩኸት እንደናረ ያልጠበቀችው ነገር ተፈጠረ። ቀና ስትል ከፊቷ ቀለበቱን ከፍቶ ክብሮም ተንበርክኳል። ሁሉም ነገር ተደበላልቆባት የምታደርገውን ማሰቢያ ጊዜ እንኳ ሳታገኝ የሰዉ ፉጨትና ዙሪያ ከበባ የባሰውን ግራ አገባት።

እሱም በሚንቀጠቀጥ ድምፅ "የተወደድሽ ሰሎሜ ታገቢኝ ዘንድ ይህንን ቀለበት አቀርባለሁ፣ ታገቢኛለሽን?" ብሎ እንደ ፈረንጆቹ ደንብ ጥያቄውን ሲያቀርብ አሁንም ጭብጨባውና ፉጨቱ ጠዘ። የምታደርገውን ያጣችው ሰሎሜ በድንጋጤ ቀለበቱን ስትቀበል አካባቢው እንደገና በፉጨትና በሙዚቃ መማሪያ ደመቀ። ልክ ጣቱዋ ውስጥ ቀለበቱን ጨምሮ እንደጨረሰ "አይ ላቭ ዩ .." ብሎ ከንፈሩን ከንፈሯ ላይ አተመው። አሁንም የምትለው የጠፋት ሰሎሜ ሁሉም ነገር ዝብርቅርቅ ስላለባት፣ ክብሮም እንዳቀፋት ወንበሯ ላይ አረፍ አለች። በክብሮም ፊት ላይ ያለው ደስታ መደናበሩን ደብቆለታል። ሰሎሜ ደግሞ በአጭር ቅጽበት የሆነውን ነገር ወደ ልቧ መልሳ ለማሰብ እየሞከረች በደመነፍስ ብቻ "እንኳን ደስ ያላችሁ። እንዴት የሚያምሩ ጥንዶች!" ለሚሏቸው "አመሰግናለሁ" እያለች ትመልሳለች።

ክብሮም የባጥ የቆጡን ሲቀባጥር ሰሎሜ ግን አሁንም የገባችበት ድንዛዜ እየለቀቃት ስለሆነ ምንም ማለት አልፈለገችም። አጠር ያሉ መልሶችን ብቻ ነው የምትመልስለት።

"ሰሊ ይህ ቀን ለኔ ከቀኖች ሁሉ በላይ ነው። አላምንም የኔ ቆንጆ። እንዴት እንደምወድሽ እኮ አታውቂም። ቀለበቱን ወደድሽው?" ሲላት፣ "ቆንጆ ቀለበት ነው።" ብቻ ነበር ያለችው። ውስጧ ሳታውቀው የመታለልም ስሜት ስለተፈጠረ የበለጠ ስሜቷን ደበላልቆታል። ቀለበት ሲሰጥ እንደዚህ ነው የሚደረገው? ይህ ነው ሰርፕራይዝ የሚባለው? ደግሞ መሳሙስ ልክ ነው? ብቻ ምንም ሊገባት አልቻለም። እሱም ትንሽ ተደናብሮ ስላየችው ድንጋጤው የየዋህነት ይሁን ወይም እሱም እንደሷው ደንግጦ አልገባትም። ብዙም ሳይቆይ ጀልባው እየተመለሰ ነበርና

መውረጃ ቦታቸው ደርሰው ወደ መኪናቸው መጡ። ከዚያ በኋላ ግን ሰሎሜ ውስጧ መናደድ ሳይጀምር አልቀረም። ከፋ መናገር ግን አልፈለገችም። ክብሮም ለብቻው ሲያወራ ነው እዚያ የደረሱት። ቀለበቱ ለጋብቻ ጥየቃም የልደት ስጦታም ይመስላል። ክብሮምን የሚያስለፈልፈው ደስታው ብቻ ሳይሆን ሥራውንም ስለሚያውቅ ሳይሆን አይቀርም። አሁን ይህ ፍቅር ሊባል ይችላል? ቀለበቱስ ቃል ኪዳን ሊሠራ ይችላል? መሳሙስ ከመንከስ በምን ይለያል? ወደ ቤት እየሄዱ የሰሎሜ ደስታዋ ሁሉ ተሰርቆ ግራ ተጋብታና ስሜቷንም መረዳት አቅቷት ነው ዝም ያለችው።

"ምነው ሰሊ ችግር አለ እንዴ? ዝም አልሽ" አለ ነገሩ እሱንም እየከበደው ስለመጣ፡፡

"አይ ፈጽሞ ያልጠበቅሁት ስለሆነ ትንሽ አደናግሮኝ ነው። ደግሞ ብዙ ሰው ስለነበረ ፈጽሞ ለዚህ አልተዘጋጀሁም ነበር። ለዚያ ነው።" አለችና እጇን ጨበጥ ለቀቅ እያደረገች አሁንም ዝም አለች።

ዝም እንዳሉ ሰፈር ደረሱ። ከመኪና ከመውረዷ በፊት ቀጭ እንዳሉ፣ "የውልህ ክብርሽ እንዳልኩህ እኔ ፈጽሞ ያልጠበቅሁት ነገር ነው። እዚያ ደንግጬ ስለነበር ነው ሁሉንም ነገር ዝም ብዬ ያደረግሁት። መነጋገር ይኖርብናል። እስከዚያ ቀለበቱን ጣቱ ላይ አላደርገውም። ደግሞ ሕያውም ሆነ እነማሚ ከመነጋገራችን በፊት እንዲያውቁ አልፈልግም።" ስትለው ደንገጥ ብሎ፡-

"ሰሊና እኔ ይሄንን ሁሉ አላሰብኩትም። አንቺ ደስ እንዳለሽ እኔ ምንም የሚያስቸኩለኝ ነገር የለም። ይቅርታ ማታውን አበላሸሁት እንዴ?" አለ የነገሩ አካሄድ ያላማረው ክብሮም፡፡

"አይ ምንም አይደለም። ደግሞ በጣም አመሰግናለሁ ለራቱና ለክሩዙ። እንዳልኩህ ለማሰብ ጊዜ ያስፈልገኛል።" ብላ ስትወርድ እሱም ወረደ ሊሰናበታት። ሊስማት አፉን ሲያቀርብ ጉንጯን ጆሮዋ አጠገብ ሰጠችው። ቤት ስትገባ ማታ ሦስት ሰዓት ተኩል ነበረ። ደግነቱ ማንም እቤት ስላልገባ ስሜቷን ለማቀዝቀዝና ለመረጋጋት ጊዜ አግኝታ ነበር። የለበሰችውን ልብስ ወዲያ ጥላ ፒጃማ ቀየረች። ለማን እንደምታማክረውም ግራ ገባት።

ቀለበቱን እንደገና አውጥታ በደንብ ስታየው የምትወደውም ዐይነት ሆኖ አላገኘችውም። በጣቷ ልክ የሆነ ቀለበት እንዴት ሊገዛ እንደቻለም ሊገባት አልቻለም። ሕያው መቼም በዚህ ከሱ ጋር አብሮ ይሆናል ብላ አላሰበችም። ቀን ስለ ጋብቻ ሲወራ የነበረው የሚያውቁት ነገር ስላለ ይሆን የሚል ሐሳብ በጩረፍታ በጭንቅላቷ ውስጥ አለፈ። ለማንኛውም ቀለበቱን በከሮጀው ከትታ ቦርሳዋ ውስጥ ጨመረችውና ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። እናቷና አባቷ በዚያ መሃል ደርሰው ኖሮ መኪና ለማቆም ጋራጅ ሲከፍቷ ተሰማት። እነሱ ከመጡ በኋላ ስለምሽታቸው ትንሽ

አወሩ። ሁሉም ራት በልተው ስለነበር ሻይ እየጠጡ ትንሽ ተጫወቱ። ከዚያ ደክሞኛል ልተኛ ብላ ቶሎ ወደ መኝታ ቤቷ ገባች።

ሰሎሜ ደጋግማ የስንክሳርን ስልክ ብትሞክርም መያዙን ያሳያል። ስንክሳርና ክብሮም ስለ ጉዳዩ አስቀድመው እያወሩና እያናዘዙት ነበር። ፎቶዎቹን ወዲያው ነው ከካሜራው ላይ ኢሜይል ያደረገላት። ያሰበችው በዕቅዱ መሠረት ስለሄደላት እንጀቷ ቅቤ ጠጥቷል። ክብሮም ከስንክሳር ጋር እንደጨረሰ ደጋግሞ ሰሎሜ ጋ ቢደውልም ስልኩን አላነሳችውም። በመጨረሻም 'እኔ ራሴ እደውልልሃለሁ እስከዚያ ግን አትደውል' ብላ የጽሑፍ መልእክት ላከችለት። ጥቂት ቆይታ ስንክሳር ሰሎሜ ጋ ደወለች።

"ይቅርታ ሰሊ ከኢትዮጵያ ስልክ ላይ ሆኜ ስልክሽን እያየሁት ማንሣት አልቻልኩም ነበር። እንዴት ነው? ሁሉ ሰላም? አንቺ ልደትሽ መሆኑን እኮ ማምሻው ላይ ማሚ ናት የነገረችኝ። በውነት ያሳዝናል፣ ስጦታ ላለመቀበል ነው እንዴ የድብቅ ያረግሽው?" አለች ለሁሉ አዲስ መስላ።

"አዬ ዝም ብለው እኮ ነው፣ አሁን ካረጁ በኋላ ምን ያስፈልጋል። ትርፉ ሻማ መጨረስ ነው። እኔ እኮ ስሜትም አይሰጠኝ። ያው ይሁን ብዬ ነው።" አለች ቀዝቀዝ ብላ፡፡

"ኧረ ተይ ... ለዚህ ነዋ ቀን ምሳ፣ ማታ ደግሞ ራት" ብላ ሣቋን ጨመረችበት፡፡

"እንዴ ማን ነገረሽ እሱን ደግሞ? አንቺ በቃ ምንም አያመልጥሽም ማለት ነው? " አለች ክብሮም እንዳልሆነ የነገራት ተስፋ በማድረግ።

"ወሬ አይደበቅ... አሁን ማምሻው ላይ ማሚ ጋ ደውዬ እነሱ የታመመ ሰው ሊጠይቁ እንደሄዱና አንቺም ከክብሮም ጋር ለራት እንደምትወጡ ነገረችኝ።" አለች ነገሩን ሳታካብድ።

"አይደል ምን ባክሽ ድካም ነው"አለች እንዴት አድርጋ ያጋጠማትን መንገር እንደምትችል እያሰበች።

"እሺ ታዲያ እንዴት ነበር? የት ሄዳችሁ ከክብሮም ጋር? መቼም የዶክተር ብር ታየኝ" አለች አሁንም ወሬ እያነፈነፈች፡፡

"እም... ይልቅ ጠዋት ምን አለሽ ቁርስ ላይ? እዚህ ቺካጎ ነው የማድረው ብለሽኝ ነበር። መጥተሻል እንዴ?"

"አዎን መጥቻለሁ። ቁርስ ጥሩ ነው። በቃ ጠዋት ተደዋውለን እንገናኛ ሁለት ሦስት ሰዓት እንበል?" አለች በጥድፊያ ስሜት። በዛው ተስማምተው ስልኩን ዘጉት።

ሰሎሜ ብዙ ጓደኛች ቢኖሩዋትም፣ ስንክሳር እንዴት ባጭር ጊዜ የምስጢሯ ሁሉ ተካፋይ እንደሆነች አልገባትም። መላኩን ስለምታውቀውና እሱም የላከት ሰው ስለሆነች ሳይሆን አይቀርም ልቧን ሁሉ የከፈተችላት። በተጨማሪም ቤተ ሰቡን ሁሉ መቅረቧና በሶለን ሕመምና ሞት ጊዜ አብራቸው ስለቆመች ቤተኛ ለመሆን ጊዜም አልፈጀባት። እሷ ራሷም የምትፈልገው ነገር ስላለ ከመንገዱ ወጥታ የምታደርግላቸው ነገርና የምትሰጣቸው ጊዜ ከሆነችው በተቃራኒ መልእክ አስመስሎአታል። ሰው ጥሩ ሲሆንልን ጥሩ ለመሆን የሚያስገድድ አፀፋዊ ግዴታን የሚፈጥር ነገር በሰው ውስጥ ሳይኖር አይቀርም።

በማግስቱ ጠዋት ሲገናኙ ከሁለት ሰዓታት በላይ ነው ያጠፉት። የተገናኙበት ካፌ አይሆፕ የሚባል ሃያ አራት ሰአት የሚሰራ የፓንኬክ ቤት ነው። ብዙ ሰው ለቁርስ እዛ መገናኘት ይወዳል። በመጀመሪያ ለማሟሟቂያ ያወሩት ስለ ሰሎሜ የኒውዮርክ ቆይታ ነበር። ኒውዮርክ ሄዳ ስለማታውቅ በጉጉት ነበር የሰማቻት። በተለይ ስለ ሶለን ሕይወት መጽሐፍ ለመጻፍ እንዳሰበችና ያም ካሰበችው ጊዜ በላይ ሊያቆያት እንደሚችል ስትነግራት፡፡

"ታዲያ ምናለ ቆይቶ የተሻለ ሥራ መሥራት አይሻልም። ምን ያህል ያቆይሻል?" አለች የሚያዙትን ቁርስ ለመምረጥ ሜኑውን እየተመለከተች፡፡

"እም ምናልባት አንድ ወይም ሁለት ተጨማሪ ወራት ቢበዛ" አለች ሰሎሜ አፏን ጠመም አድርጋ እዚህ ቤት ስትመጣ የምታዘውን ስለምታውቅ ከፊታቸው የቀረበውን ቡና ለራሷም ለስንክሳርም እየቀዳች፡፡

"ኧረ ባክሽ አንቺ ቀልደኛ ነሽ። መጽሐፍ መጻፍ እኮ ዓመትም ሁለት ዓመትም ይፈጃል በተለይ እኮ ደግሞ ዝግጅቱ፣ ይመስለኛል ጊዜ የሚወስደው። ይሄ ደግሞ ልብ ወለድ አይደለም። ትምህርት ቤቱ፣ ጓደኞቹ፣ ዘመዶቹ ምናምን ስትይ ከዚያም በላይ ይፈጃል። በዚያ ላይ ደግሞ አስቢው ሕያው እንዴት ቢዚ እንደሆነ፣ ለነማሚም ምን ያህል ያንቺ መኖር እንደሚጠቅማቸው። ኢትዮጵያ የት ይሄድብሻል። መላኩም ቢሆን ከፈለገ መጥቶ ቆይቶ መሄድ ይችላል፣ መጥቶ ስለሚያውቅ ቪዛ የሚከለክሉት አይመስለኝም" አለች ነገሩን አሳማኝ ለማድረግ እየጣረችና በጁ አስተናጋጁን እየጠራች፡፡ የመረጡትን ካዘዙ በኋላ ሰሎሜ

"የኔ ዋና ጭንቀት ሶሲና ብርቄ ናቸው። መላኩ ላይ የጣልኩት ሸክም ካቅሙ በላይ ነው። የኔን ኀላፊነት ተሸክሞ እስከ መቼ መቆየት ይችላል? ኧረ በናትሽ እንዴት እንደማደርግ አላውቅም" አለች አሁንም መወሰን እንዳቃታት እያስታወቀባት።

"ኧረ እሱ አያስጭንቅሽ በናትሽ። አክስቶችሽ ጋ መሆንም ይችላሉ። ደግሞ ምናለበት ጓደኛ ለመቼ ነው? እኔም እኮ በቃ አገሩን ጥልት አድርጌው ልሞት ነው። ማታ ማታ እናቴ በህልሟ እየመጣች በቃ ሳለቅስ ነው የማድረው። ወንድም ጋሼም ወደ ውጪ ትንሽ ምርመራ ለማድረግና አየር ለመለወጥ ሳይወጣ አይቀርም። እኔም ሰሞኑን ልሄድ እችላለሁ። ስለዚህ የነሱ ነገር አያሳስብሽ። መጽሐፉ እኮ ለሶለን አይደለም ለመጭው ትውልድና ለአገር የሚተርፍ ነው። ስለዚህ በደንብ ቢሠራ ጥሩ ይመስለኛል። ግን አንቺ ያው ሁሉንም አመዛዝነሽና አስበሽ ወስኚ" አለች አሁንም ላለመቆየት ያቀረበቻቸውን ምክንያቶቿን እያሳነሰችና ራሷንም እንደ ምሳሌና እንደ አርዓያ እያቀረበች።

"እንዴ ስንኪ መቼ ነው ደግሞ ለመሄድ የወሰንሽው?" አለች የራሷን ጉዳይ ትታ ወደሷ እየገባች፡፡

"በቃ ትናንት ጠዋት ከወንድም ጋሼ ጋ ካወራን በኋላ እሱም ኀዘኑ እንደጎዳው ነው ያየሁት። እኔ እዚህ የሚጠብቀኝ ሥራ የለኝ። ዋናው ጤናና ሰላም ነው። ስለዚህ "ማታ ደውዬ እመጣለሁ ብዬዋለሁ ከቻልኩ በዚህ ሳምንት።" አለች ፊቷ ላይ የእፎይታ ስሜት እየታየባት። ከወንድሟ ጋ ካወራች ከሳምንት በላይ ቢሆንም አይኗን በጨው አጥባ።

"ኧረ ልጅቷ... በዚህ ሳምንት?..." አለች አይኗን አፍጥጣ፡፡

"እስኪ ቀኑ ገና አልተወሰነም ... ይታሰብበታል። እኔ ምልሽ ኧረ በኔ ጉዳይ ጠምጄሽ... ስለ ትናንቱ እኮ አልነገርሽኝም ራቱ እንዴት ነበር? ምን ሰጠሽ በናትሽ? የት ነበር የሄዳችሁት?" አለች ምንም እንዳለወቀ ሰው ቡናዋን ሁለቴ ፉት ብላ።

ሰሎሜ ከኪብሮም ጋር ያሳለፉትን ምሽትና የሆነውን ነገር ሁሉ ዝክዝክ አድርጋ አንድም ሳታስቀር ነገረቻትና፣

"እኔ እኮ በኋላ ሳስበው ነርቩ ላይ ነው የወጣው ኬኩን ቆርሼ ሚሚታውን ሰምቼ ቀና ስል አጅሬው ቀለበቱን ይዞ ፊቴ ተንበርክኮአል። ተደናብሬ ቀለበቱን ተቀብዬው ከመቼው ጣቴ ውስጥ አስገብቶ ከንፈሬ ላይ እንደተጣበቀ ነው። በጣም ነው ያናደደኝ። አላሳፍረውም ብዬ ነው እንጂ ከነቀለበቱ እዚያ ውሃ ውስጥ መጨመር ነበር።" ብላ እንዳዲስ ንዴቷ ጠፎ የያዘችውን ብርጭቆ ጥብቅ አድርጋ ቆየች፡፡

"እንዴ ሰሊ አንቺም እንደዚህ ትናደጂያለሽ እንዴ? እንደዚህ ሆነሽ አይቼሽ አላውቅም። ወንዶች እኮ አንዳንዴ ፍቅር ሲይዛቸው በጭንቅላታቸው ሳይሆን በራስ ቅላቸው ነው የሚያስቡት። በሱ ቤት እኮ በቃ ሰርፕራይዝ አድርጎሽ ሞቷል። ልጁ አሜሪካ ይደግ ይማር እንጂ እኮ ምንም የማያውቅ ገጠሬ ነገር ነው።"

አለች እንዴት ነገሩን ወደምትፈልግበት አቅጣጫ እንደምትቀይረው እያሰበች ስንክሳር።

"ኧረ በናትሽ አሁን ይሄ ጠፋቶት ነው። እንዴት ነው ከዚህ በፊት እምቢ ያለችውን ሴት ድንገት ተነስቶ ቀለበት ጣቷ ላይ ሰክቶ ለመሳም የሚንደረደረው? አይገባኝም። ሰርፕራይዝ ሌላ ጉዳይ ነው ይሄ ግን ድፍረት ነው።" አለች አሁንም ቁጣዋ ሳይበርድላት በጎደለው ስኒዋ ውስጥ ቡና ብቻ እየሞላችበት፡፡

"ቆይ ሰሊ የምር የምር አንቺ ምንም ሐሳብ የለሽም ለኪብሮም። ማለቴ ምንም ልብሽ ከጀል አያደርግም? ደግሞ ባለፈውም ለሱ ልደት ከዚያም በኋላ አሁን አንቺ ራስሽ ትንሽ ፍንጭ የሰጠሽው አይመስልሽም? እኔ ደግሞ ሳስበው ልጁ ለክፋት ሳይሆን በንጹሕ ልቡ የሚወድሽ ይመስለኛል። ግን ያው አንቺ የምትወጂው ዐይነት ፈላስፋ ቢጤና በንግግር የመጠቀ ላይሆን ይችላል። ደግሞም በራሱ መንገድ እሱም ስማርት ነው።" አለች በኪብሮም በኩል ሆና የተሟገተች እንዳይመስልባት ፈራ እያለች፡፡

"ስንኪ እኔ እኮ እጠላዋለሁ አላልኩም። ግን እሱን ለማግባትም ሆነ ከሱ ጋር ለመኖር ግን ዝግጁ አይደለሁም። ደግሞ አስበው አሁን እኔ ስንት ነገር እየመሳቀለኝ እያለ ከሱ ጋር ቀለበት ሳደርግ። ብቻ አሁን እንዴት እንደምነግረው እንድንመካከር ነው የፈለግሁሽ። ልጎዳው አልፈልግም፣ ይሁን እንጂ የማይሆን ተስፋ ልሰጠውም አልችልም።" ብላ እጇንም እግሯንም አጣምራ ተቀመጠች። ሰዎች እጃቸውንና እግራቸውን ሲያጣምሩ ሳያውቁት አእምሮአቸውም ባካባቢያቸው እየሆነ ላለው ጉዳይ ወይም ሐሳብ ፈቃደኛ አለመሆኑንና መዘጋቱን ያሳያል ይላሉ ሥነ ልቦናን ያጠኑ ሰዎች። የስንክሳር ሥነ ልቦና ይህንን ባይረዳም፣ ነገሩን ተረድታዋለች በራሷ መንገድ። በዚህ መሃል ያዘዙት ቁርስ ስለመጣ ትንሽ እረፍት ሰጣቸው። ስንክሳርም የመጀመሪያ ጉርሻዋን አጣጥማ

"ከባድ ነው በናትሽ፣ አንቺ ምን ልታድርጊ አሰብሽ?" አለች መጀመሪያ እሷ ያለችበትን ለመሰለል ፈልጋ።

"እኔ እስከምደውልለት እንዳይደውልልኝ ነግሬዋለሁ። በቃ መጀመሪያ ላይ ቀለበቱን ሰጥቼው ሁለተኛ እንዳያናግረኝ ልነግረው ነበር ያሰብኩት። ደግሞ አስቢው የሕያውዬ ቤስት ፍሬንድ ነው። እነማሚም እንዴት እንደሚወዱት ታቂያለሽ። መጥፎ ሰው እኮ አይደለም።ለዚህ ነው የቸገረኝ።" አለች ሰሎሜ። አስተናጋጇ ምግቡ እንዴት ነው ብላ ጠይቃ አዲስ ቡና ቀይራላቸው ሄደች።

"ለምን ቀለበቱን አንቺ ጋ አቆይተሽው፣ ረዘም ያለ ጊዜ ሳስብበት ያስፈልገኛል ብለሽው ሁሉ ነገር ሲረግብ ጨሳኔሽን አታሳውቂውም ታዲያ?" አለች መካከለኛ መንገድ ያገኘች መስሎአት ትንሽ ፈገግታ ብልጭ ብሎ ፊቷ ላይ።

"እም" ም.. አሳቡ ጥሩ ነው። ግን ቀለበቱ አሁኑኑ መመለስ አለበት። ሌላው ውሳኔ ጊዜ ይፈልጋል፣ በርግጥ ግን ተስፋ ልሰጠው አልፈልግም እኮ!" አለች በሐሳቡ ሙሉ በሙሉ ሳትረካ፡፡

"እኬይ ቀለበቱን መልሺለት አንድ ሦስት ቀን ጠብቀሽ። ነገሩ ረገብ ሲል ግን አሁን ምንም መወሰንም ማሰብም እንደማትፈልጊ ንገሪው። ላስብበት ማለትሽ እሺ አለመሆኑን ልትነግሪው ትችያለሽ። መልስሽ እምቢ ከሆነም በዚያ መንገድ ቀስ ብለሽ ዕቅጩን ትነግሪዋለሽ ወይም ያው ኢትዮጵያ ሄደሽ ትገላገዪዋለሽ" አለች ወደ ኋላ ደገፍ እያለችና ዘና ለማለት እግሮቿን በመጠቀም ጫማዎቿን እያወለቀች። ሰሎሜም ነገሩ የተሻለ ሐሳብ ሆኖ ስለተሰማት እንደዚያ ለማድረግ ወሰነች። ከስንክሳር ጋር ያደረገችው ጭውውት ያሰበችውን ያህል ባይረዳትም ስንክሳር ግን በነገሩ ውስጥ አለችበት ብላ ፈጽሞ አልጠረጠረችም። ሁለቱም መኪና ይዘው ስለነበር እዛው ተሰነባብተው ተለያዩ።

ከሰሎሜ ጋር ከተለያዩ በኋላ ስንክሳር የጭውውታቸውን ይዘት ለራሷ እንዲመች አድርጋና ምን ማድረግ እንዳለበት አስጠንቅቃ ለክብሮም ነገረችው። ይቅርታ መጠየቅ እንደሚኖርበትና እሷ የፈለገችውን ያህል ጊዜ መውሰድ እንደምትችልም እንዲነግራት መከረችው። በሚቀጥሉት ቀናት ሰሎሜ ክብሮምን አግኝታ በሆነው ነገር የተሰማትን ብስጭት ገልጻ ቀለበቱን መለሰችለት። ክብሮም ስንክሳር እንደነገረችው ይቅርታ ጠይቆ፣ ከፋም ደግም ሳይናገር ቀለበቱን ይዞ ሄደ። የሚያደርገው ግራ ስለገባውና ውጥረቱም ስላስጨነቀው ወዲያው የሁለት ሳምንት ዕረፍት ወስዶ ካሊፎርንያ ያሉ ዘመዶቹ ጋር ለመሄድ ወሰነ። እሷም እሱም ነገሩን ከስንክሳር በቀር ለማንም አልነገሩም። ስንክሳርም ክብሮም ለዕረፍት በሄደ በማግስቱ ወደ ኢትዮጵያ ሄደች። ሰሎሜም የሶለንን ታሪክ ለመጻፍ የሚያስፈልገውን መረጃ ለማግኘት መዳከሯን ቀጠለች።

አገር ቤት

መላኩ የዱባይ ጉዞውን ጨርሶ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። ከዱባይ አዲስ አበባ ረጅም መንገድ አይባልም። አዲስ አበባ ሲደርስ አየር ማረፊያ ፍተሻው ላይ ያየውና ያጋጠመው ነገር በጣም ነው ያሳዘነው። ሁሌም ወደ ውጭ መሄዱን የሚያስጠላው አንዱ ምክንያት እዚህ ፍተሻ ቦታ የሚያየው የሰውን ክብርና ማንነት የሚያጎድፈው አሠራር ነው። ኢትዮጵያውያን በውጪ የሚደርስባቸው እንግልትና መመናጨቅ ሳያንስ እዚህም አገራቸው እንኳን ደኅና መጣችሁ ሳይሆን ምን ይዛችሁ መጣችሁ የሚለው የጥርጣሬ መንፈስና እንደ ሌባ መታየቱ ያሳዝናል። የውጪ አገር ዜጎችና የምዕራባውያን አገሮች ፓስፖርት ያላቸው አበሾች ኮምፒዩተር፣ ካሜራና ያቅማቸውን ያህል ሽቶና ሻንጣዎችን ቢይዙም ተከብረው ያልፋሉ። ሌላው ኢትዮጵያዊ ደግሞ ሰርቆ የመጣው ይመስል ለቤተ ሰቡና ለወዳጆቹ የያዘውን ዕቃ እንኳ ከዕቃው ዋጋ በላይ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል።

የአገር ውስጥ ነጋዴዎች የዕቃውን ዋጋ ሰማይ ስለሚያደርሱት ለብዙ ሰው የማይቀመስ ይሆናል። ከስንት አንዴ ውጪ ሄደው እንደ የእጅ ኮምፒዩተርና መሰል ውድ የሆኑ ግን ጠቃሚ ዕቃዎች ይዘው ሲገቡ መከራቸውን የሚበሉ ባለኢትዮጵያ ፓስፖርት አበሾች ብዙ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉ ሲፈቀድ ሰው ሁሉ ነጋዴ ነው የሚሆነው። ካሜራና ላፕቶፕ ጭኖም ከመግባት አይመለስም። መብቱን በአግባቡ ስለማይጠቀም ክብሩን መገፈፉ ግን ችግሩን የሚፈታው አይደለም። ፍተሻውን የሚያደርጉት ሰዎች ራሳቸው ሁሉ ብርቃቸው ሲሆኑ ለራሳቸው ከሚኖሩት ኑሮ በላይ ማሰብ እንዴት ይጠበቅባቸዋል? ይህም ማን ምን ይዞ ቢያልፍ ተዝቢ እንደሆነና ማ ደግሞ መብቱን ከለላ አድርጎ እያጠፋ እንዳለ አስበው ለመወሰን አቅሙም ደንታው እንዳይኖራቸው አድርጓቸዋል። የሚያውቁት ሰው ከሆነ ዝሆንም ይዞ ቢገባ ጥንቸል ነው ብለው ያሳልፉሉ፣ በሌላ በኩል 'የዐይኑ ቀለም' እንኳ ያስጠላቸውን የያዛትን ትንሽ የሙዚቃ ማጫወቻ ኤሌክትሮኒክስ ኮምፒዩተር ነው ብለው ያለታክስ አያልፍም ብለው ሊይዙበት ይችላሉ። ይህ ሁሉ ግን ያንድዮሽ ችግር ሳይሆን የተንዛዛም የፈታሹም፣ የሕግ አውጪውም የአስተሳሰብ ደረጃና የአእምሮ ድርዝ የሚፈጥረው በሕግና በመመሪያ የማይቀረፍ ችግር ነው።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ የግራ ዘመድ የሆነች ልጅ በቀረጥ ፍተሻው ላይ

ነበረች። ስለዚህም መላኩ ዕቃው ሁሉ ያለችግር ነበር ያለፈለት። ማርቆስ ተቀብለት በቀጥታ ወደ ቤት ሄዱ። ከማራ ጋር በስልክ አውርተው ስለነበር የማራን ጉዳይ እንደገና ከማርቆስ ጋር ምን ማድረግ እንደሚሻል መመካከራቸውን ቀጠሉ። ማራም ድብት ብላ እንደከረመችና ወደ ውጪም ለመውጣት ብዙም ፈቃደኛ እንዳልነበረች ነው ማርቆስ የነገረው፤

"እኔ ምልህ ዱባይን ነው እንዴ እንዳለ ይዘህ የመጣኸው? እንዴት አሳለፍልህ ይሄን ሁሉ ጉድ ባክህ?" አለ ብዙ ጊዜ በተለይ ከዱባይ የሚመጡ መንገደኞች ላይ ጠበቅ እንደሚሉ ስለሚያውቅ።

"ፍተሻ ቦታ ላይ አንድ የማራ ዘመድ ነበረችና ያው እንዳለ ያለምንም ችግር ነው ያሳለፈችው። ያው ታውቀው የለ ሰው ካለ እዚህ አገር..." አለ መላኩ ነገሩን ቀለል ለማድረግ እየሞከረ፡፡

"ሙስና ነው በለኛ። ልክ አይደለህም አንተ ግን እንዴት ነው ታክስ ሳትከፍል? ... ይሄ ያስከስስሃል ..." አለ እየሣቀ የመላኩን ደካማ ጎን ስለሚያውቅ። ደካማ ጎን ከተባለ በሰውም በጉቦም የሚሠሩ ስራዎችን ሁሉ ይጠላል።

"በናትህ ማርክ ... ምን ላድርግ ... ዘራፍ ታክስ ካልከፈልኩ ልበል? ልጅቷ ደግሞ መርዳቷ ነው። በቃ ምን ማድረግ እንደነበረብኝ አላወቅሁም። አንተ ብትሆን ምንድነው የምታደርገው?" አለ ገበታውን እየገለበጠው፣ ደግሞም የምሩን የማርቆስን ሐሳብም ለማወቅ በማሰብ።

"እኔንጃ ... እኔ በዚያ በኩል ዕቃ ይገፉ አልገባም። ምክንያቱም እኔ የማስገባው ዕቃ ካርጎ ስለሆነና አሠራሩን ብዙም ስለማልወደው ነው። በመሠረቱ በሰው ወይም በሌላ መንገድ ሰዎች የተለየ መብት ማግኘታቸውን አልደግፈውም። እንዳልከው ግን በዛ ሰዓትና ቦታ ታክስ ካልከፈልኩ ብለህ መጋበዙ ፋይዳው አይታየኝም። ምናልባት ልጅቷን ሌላ ጊዜ ስላደረገችልህ ውለታ አመስግነህ አሳብህን ንገራት። ለሷም ቢሆን ከባድ ነው፤ አንተ እንዳዲህ አልክ እንጂ ሌላ ሰው እኮ ከቤት አስጠርቶ ሁሉ ሊሆን ይችላል እንድታሳልፍለት የሚለምናት። ቢያንስ አጋጣሚ እንጂ አንተ ጠይቀህ የተደረገልህ ስላልሆነ ... ብዙም መጨነቅ የለብህም። ሞንቀቱ አላስቀምጥ ካለህም ታክሱን ለኔ መክፈል ትችላለህ።" ብሎ ሣቀና ወደ ፍሪጅ ሄዶ የቀዘቀዘ ኮካ ይዞ መስኮቱ አካባቢ ባለ አንድ ከጠፍር በተሠራ ወንበር ላይ ተቀመጠ።

መላኩም ልብሱን ከቀያየረ በኋላ ማራ ጋ ደውሎ ሰላም መግባቱንና ለመምጣት ማሰቡን ነገራት። ከሰአት ወደ አስር ሰአት ለመገናኘትና ማርቆስም ከቻለ አብረው ሊመጡ ተስማሙ። ከዚያም ከማርቆስ ጋር ምሳ በልተው ለአንድ

ሁለት ሰዓት ቢያንስ እጣዳፊ ነግሮች ካሉ፣ ቢሮ ለመግባት ብሎ ቢደውል ፎዚያን አላገኛትም። ለማንኛውም የቻለውን ያህል ለመሥራትና የሚመለሱ ደብዳቤዎችን ለመመላለስ ብሎ ወደ ሥራ ገባ። መቂም ደውሎ ዘመዶቹን አዋርቶአቸው፣ በሰላም መግባቱንና ሥራውን ትንሽ ካረጋጋ በኋላ ከሰኞ መቂ እንደሚመጣ ነገራቸው።

ማራን የወንድሟ ጓደኛ ሚስት ነበረች ከቤት መጥታ የወሰደቻት። ማራ ኢትዮጵያ ስትመጣ መኪና መንዳት በጣም ስለምትፈራ ነድታም አታውቅ። የከተማይቱ መስፋት ደግሞ መንዳትን የግድ እያደረገው ነው። ግን ደግሞ ያለው የመንገድ ጥበትና የመለያ መሥመር አለመኖር ሰዉ እንደፈለገ መንዳቱና የእግረኛው ሕግ አክባሪ አለመሆንና የመሳሰሉ ነገሮችን ስታይ ሌላው ሰው እንዴት እነድሚነዳ ይደንቃታል። ብዙ ጊዜም የመለያ መሥመሩን በመኪናው መሃል ላይ አድርገው ስለሚነዱ የቀለሙ ከንቱ ብክነት ግራ ይገባታል።

ማራም የከሰአት በኋላ ቀጠሮዋ ከወንድሟ ጓደኛ ሚስት ጋር ነው። የወንድሟ ጓደኛ ስሙ አዱኛ ሲሆን ሚስቱ ደግሞ አብረኸት ትባላለች። በቅርብ ራሷን ለማጥፋት ሞክራ የተረፈችውን ልጃቸውን እንድታይላቸው ነው ቀጠሮው። ልጃቸው ዳናይት የአሥረኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን፣ አሥራ አምስት ዓመቷ ነው። መልኳ እንደናቷ ጠቆር ያለች ስትሆን ከሁለት ዓመት ወዲህ ባመጣችው አዲስ ያመጋገብ ጠባይ ከስታ ሣር አክላለች ማለት ይቻላል። አሥርና አሥራ አንድ ዓመት ላይ ድንቡሽቡሽ ያለች መሣቅ የምትወድ በትምህርቷ ሁሌም አንደኛ የምትወጣ ልጅ ነበረች።ዳናይትንም ፓንዳ እያሉ ነው የሚያበሽቋት። በውፍረቷና በጥቁረቷ ምክንያት። ልጆች እርስ በርሳቸው በጣም ክፉ ሊሆኑ ይችላሉ። የወፈረ፣ የጠቆረ፣ ያጠረ ወይም በጣም የረዘመ ልጅ፣ ዐይናፋር የሆነ ወይ ደግሞ መነጽር የሚያደርግ ከሆነ ከጓደኞቹ የሚደርስበት የስድብና የብሽሽቅ ናዳ ቀላል አይሆንም። በልጆች ዓለም ለየት ያለ ሁሉ መከራው ብዙ ነው።

የዳናይት እናት በባሕርይዋ ኀይለኛ በመሆኗ ሁሉን አንቀጥቅጣ ነው የምትገዛው። ልጆቿ ከሷ ፈቃድና ምርጫ ዝንፍ ማለት አይችሉም። ባንድ የመንግሥት ድርጅት ውስጥ የነበራትን ሥራ ትታ አሁን በንግድ ሥራ ውስጥ ገብታ የተሳካላት የአገር ባህል ልብስ ነጋዴ ስትሆን፣ ከሌሎች ጓደኞቿም ጋር በቡና ንግድ ውስጥ ገብታለች። ባሏ ደግሞ ዓለም ባንክ ውስጥ የሚሠራ፣ የሚስቱ ተቃራኒ ዝምተኛና በራሱ ዓለም ውስጥ የሚኖር ለስላሳ ሰው ነው። ብዙ ስለሚጓዝም አብዛኛው የሚስቱ ጅራፍና አገዛዝ ልጆቹ ላይ ነው የሚያርፈው። እቤት ቢኖርም የሌለ ያህል ስለሚቆጠር በተለይ ከእናቷ ጋር እሳትና ጭድ ለሆነችው ለዳናይት ምንም የሚፈይደው ነገር የለም። አብረኸት ከተንጣባት እሱንም ነው የምታርገበግበው። ልቧ ክፋት ባያውቅም አፏ ከመርዘኛ እባብ አይተናነስም።

"እኔ እኮ ምን ማድረግ እንደምችል ጸላውቅም፣ ለሷ ብዬ ያልሆንኩት ነገር

የለም። እኔ አሁንስ እናትም አባትም መሆን ሰልችቶኛል። እሱ እንደሆነ ከዕንቁላሉ እንዳልተፈለፈለ ጫጩት በራሱ ዓለም ነው የሚኖረው። ባለፈው ትልቁ ልጅ ሰክሮ ስለነበር ከሰው ጋር ተደባድቦ ከዩኒቨርስቲ ተባርሮ በስንት መከራ ነው መልሼ ያስገባሁት። አሁን ደግሞ ይቺ ይሄው ገና ከፍ ሳትል ...” ብላ ማልቀስ ጀመረች ባንድ እጇ መሪውን እየደበደበች። አብረኸት የምታደርገው ጠፍቶአት ነው የከረመችው። ለወትሮው ሁሉን መቆጣጠር የምትችለው የዳናይት እናት የልጇ ጉዳይ ግን ከአቅሟ በላይ እንደሆነ ተገንዝባለች።

“ይሄ የመጀመሪያዋ ነው ራሷን ለመጉዳት ስትሞክር?” አለች ማራ ዳሽቦርዱ ላይ ያለውን ናፕኪን እያቀበለቻትና ጀርባዋን እያሻሸችላት። ከእንባዋ ጋር እየገነፈለ የሚወጣውን ቁጣ ስታይ ማራ የአብረኸትን ሃይለኛነትና ምናልባት ይህም ለችግሩ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል መገመት ችላለች።

“ምን የመጀመሪያዋ ነው። ከየት እንዳመጣችው አላውቅም ከመዳፏ በላይ እጇን አንዴ በምላጭ፣ አንዴ በቢላ መቁረጥ ነው በከፋት ቁጥር። የማታየው ፊልም የለም ደግሞ ኢንተርኔት ላይ ተጥዳ ነው የምትውለው፤ ከዚያ የተማረችው ሙያ ሳይሆን አይቀርም። እንዴት ያለች ድንቡሽቡሽ ያለች ልጅ ማር አክላለች፣ አሁንም ወፍራም ነኝ እያለች ምግብ አትበላ! መታጠቢያ ቤት ካልተቆለፈባት ጣቷን እየሸነቀረች ያለ የሌለውን ማስወጣት ነው።” አለች ቀኝ እጇን ከመሪው ላይ አንስታ አመልካች ጣቷን ወደአፏ እንደማስጠጋት ብላና ፊቷን ጭምድድ አድርጋ። አነዳዷ ፈጣንና ድፍረት የተሞላበት ሲሆን ከፊታቸው አላሳልፍ ያላቸውን ታክሲ እንደምንም ብላ ስታልፈው የብስጭት ጡሩንባ ብታሰማውም ፊቱን አዙሮ ያላያት መሰለ።

ብዙ ጊዜ አብረኸት በሄደችበት ሁሉ ሰዎች ወድደዋት ሳይሆን ፈርተዋት የፈለገችውን ያደርጉላታል። የፈለገችውን በራሷ መንገድ ማግኘቷ ለጠባይዋ የበለጠ ድጋፍ ሳይሆነው አልቀረም። የመጀመሪያ ባሏ እንደሷው ኀይለኛ ስለነበር ከመጋደል ተርፈው ነው የተፋቱት። ከሱ የወለደቻቸው ሁለት ወንድ ልጆቻቸው ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ በመማር ላይ ናቸው። ካዱኛ የምትወለድ ልጃቸው ዳናይት ብቻ ናት። አዱኛን ባንድ የጋራ ጓደኞች ግብዣ ላይ ተዋውቃው ነው በዚያው ተቀራርበው ነገሩ ለጋብቻ የደረሰው። እሱ ሴት የሚፈራና ዐይናፋር ስለሆነ የሷን ድፍረትና ቅልጥፍና አይቶ ወዷት ነበር። እሷም የሱን ርጋታና ዝምተኛነት ልታልፈው አልቻለችም። ለጋብቻም እንዲጠይቃት ያደረገችው ወይም የጠየቀችው እሷ ነበረች ማለት ይሻላል። ትንሽ አብረው እንደኖሩ የቤቱ ሦስተኛ ልጅ ሆኖ አረፈው። የመረጠው መንገድ ራሱን ከሁሉ አግልሎና ሥራው ላይ ብቻ ተጠምዶ እሷ ባልም ሚስትም እንድትሆን መልቀቅን ነው።

“እም ... ባለፈው ሳምንት መድኀኒት ነው ወሰደች ያልሽን? ምን የሆነችው ነገር ነበር?” አለች ማራ አሁንም የአብረኸትን ስሜት ማርገቢያ መንገድን

በመፈላለግና እቤትም ከመድረሳቸው በፊት የቻለችውን ያህል ስለችግሩ ለመረዳት።

“ምን ትሆናለች ስትሞላቀቅ ነው እንጂ። እኛ እኮ እንዴት እንዳደግንና እዚህ እንደደረስን እያውቁ... ምን ያድርጉ የሰው ልጅ የማይበላው የለውም ... ብቻ ... ሁኔታዋ ስላላማረኝ በቃ ሳታየኝ የግል ማስታወሻዋን ወስጄ ሳነበው ራሴን ማመን ነው ያቃተኝ። ልጅቱ ለካ ስንት ነገር ውስጥ ገብታለች። አልሬዲ ከስንት ወንድ ጋ እንደወጣች አትጠይቂኝ። አልከሆል፣ ድረግ ሁሉ ሞክራልኛለች የኔ ጐረምሳ.. አላስቻለኝም በቃ ማስታወሻውን ይዤ ... እንዴት እንደሆነ ስጠይቃት ‘በገዛ ሰውነቴ ምንም አያገባሽም ... ደግሞ የግል ንብረቴን ያለኔ ፈቃድ ማንበብ አትችይም’ ብላ መንጭቃ ወደ መኝታ ቤቷ ስትሄድ ራሴን ነው የሳትኩት። ከዚያ ሠራተኛዋ ባታስለቅቀኝ ኖሮ አንቄ ልገድላት ነበር።” ብላ አሁንም መንዘፍዘፍ ጀመረች። ከወደፊት ያሉ ሁለት መኪኖች ስለተጋጩ መንገዱ ሁሉ ተዘጋግቶ ለመቆም ተገደዱ። ከዐሐይ መከላከያው ስር ያለውን የፊት መስተዋት ተጠቅማ በእንባ የራሰ አይኗንና ፊቷን ጠራርጋ ለማስተካከል እየሞከረች ከበፊቱ ትንሽ ረጋ ባለ ድምጽ

“እኔ እኮ ማይገባኝ እሑድ ቤተ ክርስቲያን አትቀር ሲያዩዋት ርግብ። ልጆቼ ምን እየሆኑ ነው። ስንት ከፍለን እኮ እዚያ ትምህርት ቤት እንደምንልካት አታምኚም። አባቷ ነገሩን ስነግረው ምንም እንዳልሆነ ሁሉ ትከሻውን ነቅንቆ ነው የሚሄደው። ማታ ላይ የጩኸት ድምፅ ሰምቼ እየሮጥኩ መኝታ ቤቷ ስሄድ የሆነ መድኀኒት ወስዳ ራሷን ስታ ትንፈራፈራለች። ያው ሆስፒታል ወስደናት ሦስት ቀኗ ነው ቤት ከመጣች። ያው አሁንም አታናግረኝም። አባቷም ደቡብ አፍሪካ ሄዶ ነገ ነው የሚገባው። አሁን ምን ማድረግ ይቻላል ዶክተር?... እኔ እኮ አንዳች አጋንንትም ከሆነ ብዬ ጸበልም ጸሎትም ወስጃታለሁ ... እኔ እኮ ላብድ ነው!” አለች ግራ መጋባቷንና አቅመ ቢስነቷን በሚገልጥ ድምጽ። አብረኸት በንጀራ አባትና በእስቼጋሪ እናት እጅ አድጋ ገና ያሥራ ሰባት ዓመት ወጣት ሆና ነው ከቤት ወጥታ ራሷን አስተምራ እዚህ የደረሰችው። በኑሮ ጉዳይ ጠንካራ ብትሆንም፣ እሷ የማታውቃቸው ምንም ያልተነኩ ካስተዳደግ ጋር የመጡ ብዙ ክፍተቶችና ችግሮች አሏት።

“እስኪ እናያለን ምን ማድረግ እንደምንችል። ያው ቀላል አይደለም። ግን ደግሞ ያው ገና ልጅ ስለሆነች ተስፋ መቁረጥ የለብሽም። እስኪ እሷንም ካዋራኋት በኋላ እንመካከራለን።” ብላ ትንሽ ዝም አለች። ወዲያው አብረኸት ይቅርታ ጠይቃ ወደቤት ስልክ ደወለች። እየመጣች እንደሆነና ዳናይት እቤት እንድትጠብቃት ለሰራተኛዋ ነግራ ስልኩን ዘግታ ወሬያቸውን ቀጠሉ።

ማራም በቀረው ጊዜ ስለ ራሷ ስለ አብረኸት አስተዳደግ፣ የመጀመሪያ ጋብቻ፣ ስለ አዱኛና ስላላቸው ግንኙነት፣ ስለ ዳናይትና ሌሎቹ ልጆቿ አስተዳደግና

ባሕርይ እና ሌሎችንም ጥያቄዎች እየጠየቀቻት እቤት ደረሱ። እቤት እንደደረሱ ወደ ሳሎን ገብተው ትንሽ ካወሩ በኋላ “አንቺም ሳትቸኩይ አትቀሪም እስኪ ልጥራትና አናግሪያት። እኔ አብሬያችሁ ባልሆን ይሻላል መሰለኝ። ምን ይምጣልሽ ቡናው እስኪፈላ?” አለች ከመቀመጫዋ እየተነሳች።

“አይ ግዴለም ለኔ ከሆነ ቡናው ይቅርብኝ። ይልቅ ቀዝቃዛ ውኃ ብትሰጭኝ። እንዴት ያምራል ባክሽ ያ የቤተሰብ ፎቶ!” አለች አይኗን ከባሻገር ካለው ትልቅ የቤተሰብ ፎቶ ላይ ወደ አብረኸት መልሳ። ትንሽ ስለፎቶውና ስለሌሎቹም ልጆቿ ነግራት ወደ ጓዳ ሄዳ ከዳናይት ጋር ተከታትለው መጡ። ዳናይት ድንቡሽቡሽ ያለች የጥቁር ጠይም ስትሆን ተጠርታ ስትመጣ የቤት ልብስ እንደለበሰች ነበር ። ሳራን ጨብጣት ከሷ ባሻገር ካለው ሶፋ ላይ አንገቷን እንደደፋች ዝም ብላ ተቀመጠች።

ዳናይት ግራ እጇ ላይ የታሸገ ቁስል ሲኖር የቀኝ ሌባ ጣቷም መተጣጠፊያው ወይቧል። ይህም ስታስታውክ ጣቷን በተደጋጋሚ አፏ ውስጥ ስለምትከተው እንደሆነ ሣራ ለማወቅ ችላለች። አከሳሷዋ የጤና አይደለም። ጉንጯ ላይም አበጥ ያሉ ዕጢዎች ይታያሉ። እነዚህም የምራቅ አመንጪ ዕጢዎች ሲሆኑ ከዚሁ ተደጋጋሚ ማስታወክ ጋር በተያያዘ ስለሚቆጡ ነው የሚያብጡት። ዐይኖቿ በከፊል የጐደጐዱ ናቸው፤ አንገቷ ቅጥን ብሎ ጭንቅላቷን እንዴት እንደተሸከመው ይገርማል። ለረጅም ጊዜ በመወፈር ፍርሀትና በራስ ምስል መዛባት ውስጥ የገቡ ወጣት ሴት ልጆች ምግብን ባለመብላት፣ ካቅም በላይ ያካል እንቅስቃሴን በማድረግ፣ ጣትን እየከተቱ በማስታወክና ሌሎች ነገሮችን በመጠቀም ለመክሳት ይሞክራሉ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን የአንጎላቸውና የአስተሳሰባቸው ሚዛን ይዛባና ነገሩ ከቁጥጥራቸው ውጪ ይሆናል። ችግሩ በሠለጠኑ አገሮችና በነጮች ላይ ቢበዛም፣ እኛም አገር አልፎ አልፎ ይታያል። የዳናይት ችግር ግን ከዚህም የጠለቀ ነው የመሰላት ለሣራ።

አብረኸት ትንሽ ተጫውታ ዳናይትንና ሣራን ለብቻቸው ትታቸው ወደሌላ ክፍል ሄደች። ዳናይት መጀመሪያ ላይ ሣራን ላለማዋራት ወስና ነበር። ትንሽ ካወሩ በኋላ ግን ቀስ ቀስ እያለች ማውራት ጀመረች። የንግግራቸውን አቅጣጫና መልክ ቅርጽ ለማስያዝ በማሰብ ወደ ዋና ጉዳዩ ከመግባቷ በፊት

“የውልሽ ዳናይት እናትሽ ናት እንዳነጋግርሽ የጠየቀችኝ። ግን አሁን እኔና አንቺ የምናወራው ነገር ሁሉ በኔና ባንቺ መካከል ነው የሚቀረው። ምናልባት ለሕይወትሽ የሚያሠጋ ነገር ብቻ ሲሆን ነው ለነሱ ልነግር የምገደደው። ያንንም ቢሆን እንደምነግራቸው ነግሬሽ ነው የምነግራቸው። ስለዚህ ምንም ፍርሀት ሳይሰማሽ የፈለግሽውን ነገር ልትነግሪኝ ትችያለሽ።” አለችና ሁኔታዋን በማጤን ለትንሽ ጊዜ ዝም አለች ሣራ። ዳናይትም መሬት መሬቱን እያየችና የጣቶቿን

ጥፍር እየበላች ዝም ብላ ቆየች። እፍረትም ፍርሀትም፣ ጥርጣሬም የተጫናት ትመስላለች። ሣራ ከተቀመጠችበት ባሻገር ካለው ሶፋ ተነሥታ አጠገቧ ሄዳ አንድ እጇን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ፡-

“ዳኒ አይዞሽ፣ .. ከባድ ነው በርግጥ። ግን እኔን እንደ ዶክተር አትይኝ። በቃ እንደ ጓደኛ ቁጠሪኝ። ምንድነው የምታስቢው የኔ ቆንጆ?” አለቻት የምርም አንጀቷን ስለበላቻት። የብዙ ዶክተሮች ችግር ሰው መሆን አለመቻላቸው ነው። ብዙ ሕመምተኞችን ደግሞ የሚፈውሳቸው ሰውነታቸውና ርኅራኄያቸው እንጂ ዶክትሬታቸው ላይሆን ይችላል።

ዳናይት በፈረፍታ ቀና ብላ ሣራን አየቻትና፣ “እኔ እኮ ማንም የማይወደኝ፣ ለምንም የማልጠቅም ሰው ነኝ። ለምን እንደተፈጠርኩ አይገባኝም። የምፈልገው መሞት ነው።” ብላ ዝም አለች፡፡

“ለምን የኔ ቆንጆ? እንዴት አወቅሽ ማንም እንደማይወድሽ?” አለች ጥያቄዎቿን እየመጠነች፡፡

“እኔ ምኔ ነው አሁን ቆንጆ? የገዛ እናቴና አባቴ ካልወደዱኝ ማን ሊወደኝ ይችላል? ትምህርት ቤት ፓንዳ ፓንዳ እያሉ በውፍረቴና በጥቁረቴ ይሥቁብኛል። ለምንድነው እግዚአብሄር እኔን እንደዚህ አድርጎ የፈጠረኝ?” ብላ መንሰቅሰቅ ጀመረች። ማልቀሷን እንደ ጥሩ ምልክት ያየችው ሣራ ዳናይትን እቅፍ አድርጋት እንደ ሕፃን ልጅ ስታባብላት ይባስ ለረጅም ጊዜ አለቀሰች። ሣራም ምንም ሳትናገር “አይዞሽ የኔ ቆንጆ” ብቻ ነበር የምትላት። ማንም ለረጅም ጊዜ እንደዚህ አቅፎአትም ብሎአትም የማታውቀው ዳናይት ከሣራ እቅፍ ውስጥ መውጣት አልፈለገችም። እናቷ እሷ ብትሆንም ተመኘች።

ለቅሶዋ ጋብ ሲል ፀጉሯን እያሻሸችላት “በጣም ቆንጆዬ ፀጉር እኮ ነው ያለሽ” አለቻት ከልቧ። ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግ ስትል የሚሰረጉደውን ጉንጯን ያዝ አድርጋ እሷም ፈገግ ብላ “ሄይ ዲምፕል ገርል ... በናትሽ እስኪ ሣቂልኝ። እኔ ዲምፕል ቢኖረኝ እንዴት ደስ እንደሚለኝ አታውቂም” ስትላት አሁንም የሚያምር የዋህና ንጹሕ ሣቋን ሳታውቅ ሣቀች። ከዚያ በኋላ ምንም ሳይቀር ነበር ከልጅነቷ ጀምሮ ሁሉንም ነገር የነገረቻት። ሣራም ምንም ነገር ሳያስደነግጣት፣ ፊቷንም ሳይለውጠው ሰማቻት። በርግጥ አንዳንድ የነገረቻት ነገሮች ራስ አስይዘው የሚያስጮኹ ናቸው። ሳይደነብሩና ለፍርድ ሳይጣደፉ ሰዎችን ረጋ ብሎ በጸጥታ መስማት ሙያዋ ካስተማራት ጥበቦች አንዱ ነው። ይህም የፈውሱ ዋና ክፍል ነው። ዳናይት ሰው ጉዷን ሁሉ ሰምቶ እንደዚህ ሳይፈርድባት ወይም ሳይቆጣት ሊሰማት እንደሚችል አታውቅም ነበር። አንዳንዱ አማካሪ አርጩሜ ቆርጦ ሁሉ መግረፍ ነው የሚቃጣው። ሣራ ግን ለመስማት የተከፈተ ልብ ነው ያሳየቻት ለዳናይት።

“ዳኒት መቼ ነው እንደዚህ ማድረግ የጀመርሽው? ለምንድነው እንደዚህ የምታደርጊው? ራስሽን ለማጥፋት ነው ወይስ?” ብላ ዐይን ዐይኗን ማየት ጀመረች፡፡

“እኔንጃ ዐሥራ ሦስት ዓመቴ ነበር መሰለኝ። አንድ የቀን ፓርቲ ላይ ጓደኞቼ ቤት ነበርኩኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር መጠጥ የጠጣሁት። ማሚም ዳዲም ውጪ ነበሩ ያን ጊዜ። ለዚያ ነበረ የመጠጣት ድፍረት ያገኘሁት፣ ደግሞም አንቺ ብቻ ከሆንሽ የማትጠጪ፣ ሁሉም እንደ ሞኝ ነው የሚያይሽ። ጓደኞቼም እነማሚ እንደሌሉ ስላወቁ በቃ ሲያደፋፍሩኝ ጠጣሁና ሰከርኩ መሰለኝ። ከዚያም ከኔ በሦስት ዓመት የሚበልጡ ሁለት ወንድ ልጆች ይዘውኝ አንዱ መኝታ ቤት ገብተን ከሁለቱም ጋር ሴክስ አደረግን። ወዲያው ባይታወቀኝም አሞኝ ቆየሁ አራት ቀን። ለማንም አልተናገርኩም። ከዚያ በኋላ ቤተክርስቲያን መሄድም አስጠላኝ። ቆሻሻ የሆንኩ ያህል ይሰማኝ ነበር።

“ከዚያ ግን በቃ ማሚም እሷ በትንሽነቷ ሴክስ ስለጀመረች ሕይወቷ ሁሉ እንዴት ተመሳቅሎ እንደነበር ሁሌም ትነግረኝ ስለነበር ፍርሀት አደረብኝ። ወንዶች እንዲወዱኝ ሴክስ ማድረግ ያለብኝ ስለሚመስለኝ ከብዙ ልጆች ጋር መውጣት ጀመርኩ። ትምህርት ቤት መታጠቢያ ቤት ውስጥ ሁሉ። ያ ደግሞ ራሴን የባሰ እንድጠላ አደረገኝ። ቤትም ዳዲ የለም ማለት ትችያለሽ። አንድ ቀን እንኳ አቅፎኝ ወይም ቆንጆ ብሎኝ አያውቅም። ስለዚህ በቃ በልጅነቴ ነው ቆንጆ ባልሆንና ባልወደድ ነው ብዬ ያመንኩት። ከዚያ በኋላ ዳና-ፓንዳ እያሉ ሲያበሽቁኝ እንዴት አድርጌ ላስወጣው። ስለዚህ እጄን ቆርጬው ደሙን ሳይ ትንሽ እፎይ እላለሁ። ራሴን ለመግደል አይደለም። አንዳንዴ እጄን ነክሼ ወይም ቆርጬ ካላደማሁት የምፈነዳ ነው የሚመስለኝ። እነማሚም ሲደነግጡና አትኩሮታቸውን ሲሰጡኝ ደስ ይለኛል። ያ ደግሞ የነሱን አዘኔታ ለማግኘት ቀላሉ መንገድ ሆኖ ነው ያገኘሁት።” ብላ የራሷን ረጅም ማብራሪያ ሰጠቻት።

“በጣም የሚገርም ነው። የሚገርምሽ በተለይ ውጪ አገር ብዙ ሰዎች አሉ፣ እንደዚህ የሚያደርጉ፤ የብዙዎቹ ምክንያት ተመሳሳይ መሆኑ ነው የገረመኝ። እስካሁን ብዙ አስቸጋሪ ነገር ውስጥ አልፈሻል። ግን በጣም ብዙ መልካም ነገርና ብዙ ትልቅ ነገር የሚጠብቅሽ ልጅ ነሽ። ጐበዝ ተማሪም እንደሆንሽ እናትሽ ነግራኛለች። ፈቃደኛ ከሆንሽ ደግሞ ከዚህ አይነት ችግርና አስተሳሰብ ውስጥ መውጣት ትችያለሽ። ቀላል አይደለም ግን ደግሞ ከዚህ የሚብስ አይሆንም...” ብላ የምትለውን መጠበቅ ጀመረች።

“አዎን .. እኔም ከ እየተሠቃየሁ ነው። እንደዚህ ሆኜ እስከ መቼ እኖራለሁ? ወይም በቅርብ ራሴን አጥፍቼ .. ለነማሚም ችግር ነው። ግን በቃ እንዴት ነው አስተሳሰቤን የምቀይረው? ሁለት ሦስት ቀን የተለወጥኩ ይመስለኝና የሆነ ነገር

ሲያጋጥመኝ የባሰ ነገር ውስጥ አገኘዋለሁ። ከማሚ ጋር መኖርም በጣም ከባድ ነው። ካንቺ ጋር እንዳየሻት ብቻ እንዳትመስልሽ። አንዳንዴ አውሬ ነው የሚያደርጋት። በቃ እኔ የሷ መሞከሪያ አይጥ የሆንኩ ነው የሚመስለኝ፡፡ የምለብሰውም እንኳ እሷ የፈለገችውን ነው። እሷ እኮ ናት እኔ ውስጥ ለመኖር የምትጥረው።” አለች ዳናይት አንዴ ሣራን አንዴ ደግሞ መሬት መሬቱን እያየች፣ ሣራም እንድትቀጥል አደፋፈረቻት።

“አባቴም ስለሚፈራት ራሱን ለማዳን ይሁን አይገባኝም ምንም አይረዳኝም። እናትሽን ጠይቂ ነው የሚለው። ለብቻዬ ደግሞ አልችላትም። እሷ ናት የሁላችንንም ዓለም የምታሽከረክረው። ወንድሞቼ አሁን በቃ እንዴት እንደሚጠሏት አታምኚም። ሐዋሳ ድረስ ሄዳ ኑሮአቸውን ለመኖር ትሞክራለች። ባለፈው አንዱ ወንድሜ ሰድቦ ነው ያባረራት። በእርሱ ላይ የነበራትን ንዴት እኔና አባቴ ላይ ነው የተወጣችብን። ምንም ምስጢር እንኳ እዚህ ቤት ሊኖረኝ አይችልም። እናቴ ናት እወዳታለሁ ግን ደግሞ እሷን መውደድ አይቻልም።” ብላ ተስፋ የቆረጠ ፊቷን ወደ መሬት ደፋችው።

“የውልሽ ዳኒ አሁንም ቀላል ነው አይደለም የምልሽ። እናትሽ አሁን ከምታደርገው የተሻለ ነገር ማድረግ አታውቅበትም። እሷ አንቺን እንደ ነፍሷ ነው የምትወድሽ። አታምኚም ቅድም ስንመጣ እንዴት ስታለቅስ እንደነበር። እሷም ምስቅልቅል ባለ አስተዳደግ ውስጥ ስለሆነ ያደገችው እናንተን ከዚያ ለማትረፍ ነው ጥረቷ ሁሉ። አባትሽም ባሕርዩ ሊሆን ይችላል ወይም እሱም ነገር ያቀለለ መስሎት። አሁን ማተኮር ያለብን አንቺ ላይ ነው፣ እንዴት ነው አንቺን የምንረዳውና ይሄንን ችግር እንድታሸንፊ የምናደርገው?” አለች ሙሉ መልስ እንደሌላት በሚያሳውቅ ሁኔታ።

ልጅን ማከም አስቸጋሪ የሚያደርገው ብዙ ጊዜ በሽታው ወላጅ ላይ ስለሆነም ነው። ወላጆች ደግሞ ችግሩ የነሱ መሆኑን ተረድተው ለመቀበል ይቸገራሉ። ሣራ ትንሽ እናቷን ለመምከር፣ ከተቻለም ዳናይትን እሷ ጋ ወስዳ አንድ ሁለት ቀን አብራት በማቆየት የበለጠ ጊዜ ወስዳ ልትመክራትና የፈራረሰውን ማንነቷን የተቻለችውን ያህል ለመጠገን ቆረጠች። በዳናይት ዕድሜ ያሉ ልጆች ከንግግር ይልቅ በቂ ጊዜ ዐብሮ በመሆን የበለጠ ይጠቀማሉ። ሣራ ትኩረትና ጊዜ ሰጥታ ያንን ማድረጓ ራሱ ከፍተኛ ጥቅም አለው። ለሁሉም ሰው ያንን ማድረግ አይቻልም እንጂ።

ለዳናይትም ዕቅዷን ነግራት ትንሽ ቀላልዳ እቅፍ አድርጋ ግንባሯ ላይ ስማት ተሰናበተቻት። ዳናይት የተለየ ፍቅር ነው ለሣራ ያደረባት። ፊቷም ፈታና በራ ብሎ ነበር ከሳሎን ወጥታ ወደ መኝታ ቤቷ የሄደችው። ይህንን ያየችው አብረኸት ነገሩ በጣም አስገርሞአት “እንዴ ልጅቷን ምን ብለሻት ነው ዶክተር...!

እንደዚህ ፊቷ በርቶ ካየሁዎት ስንት ጊዜ መሰለሽ?"

"አይ ትንሽ ተጫወትን፤ ተመካከርን። እንዴት የምትገርም ልጅ ነው ያለችሽ፤ ዕድለኛ ናችሁ።" አለች በደፈናው።

"አዎ ጥሩ ልጅ ነበረች። አሁንማ ተበለሻሽታ ነው ያየሻት አንቺ" ስትል ቀበል አድርጋ፤

"አይ .. ተቸግራ ነው እንጂ አሁንም የምትገርም ልጅ ነች" ብላ ያሰበችውን አጫውታት ለፂም አንዳንድ ምክሮችን ከሰጠቻት በኋላ አብረኸትም ዳናይት ከማራ ጋር አንድ ሁለት ቀን መቆየቷን በደስታ ተቀበለችው፤-

"ዶክተርዬ ምን እንደምልሽና እንደማደርግልሽ አላውቅም። በሌለሽ ሰዓት ይህንን ሁሉ ጊዜ ወስደሽ ስላየሽልኝ። ብቻ እግዚአብሔር ይክፈልሽ.." አለች የምሯን ውለታዋ ከብዶአት።

"ኧረ ምንም አይደለም። ደግሞ ዶክተር አትበይኝ፤ ማራ ብትዪኝ ደስ ይለኛል፡" አለች። አንዳንድ ሰዎች ዶክተር ካላሉዋቸው ልብሳቸውን የገፈፏቸው ያህል ይቆጣሉ ወይም ይቀየማሉ፤ ማራ ግን ሆስፒታል ካልሆነ በቀር ማራ ተብሎ መጠራት ነው የምትወድደው። ዶክተርነት ስም አይደለም፤ ሥራ ነው ትላለች። ማራ መላኩ እስኪመጣላት ድረስ እዛው ከአብረኸት ጋር ስለወላጅነትና እድሜያቸው በአስርት ወስጥ ያሉ ልጆችን በተመለከት ስላሉ ስነልቦናዊ ችግሮችና ለውጦች እያወሩ ቆዩ።

በትክክል ያላደጉ ልጆች እንዴት ጥሩ ወላጅ ሊሆኑ ይችላሉ? ሰዎች ሙዚቃና ስፖርት፤ እጅ ሥራና እርሻ ከልጅነታቸው ሲማሩ፤ ወላጅነትንና የትዳር አጋርነትን ግን በግምትና በመላ ምት የሚገቡበት መሆኑ አስገራሚ ነው። አውሮፕላን አብርሮ በማያውቅ ፓይለት በሚበር አውሮፕላን ውስጥ ማንም አይሳፈረም። ብዙ ልጆች የሚወለዱት ግን ትዳርና ቤተሰብ እንዴት እንደሚመራ በማያውቁ አዲስ ለማጆች ባቋቋሙት ቤት ውስጥ ነው። አብረኸትና አዱኛ ራሳቸውን በደንብ ሳይሠሩ ዕድሜያቸው ለትዳር ስለደረሰና መውለድ ስለቻሉ ብቻ ዳናይትን ሠሩ። ዳናይት ደግሞ ዕድሜዋ ላቅመ ትዳር ሲደርስ ካንዱ ካልተዘጋጀ ሰው ጋር ተቆራኝታ የምትወልዳቸው ልጆች ምን ዐይነት ይሆኑ ይሆን?

ከጐጆና ተዳዳሪው እስከ ሚሊየነሩ፤ ከገበሬው እስከ ሳይንቲስቱ፤ ከየኔ ቢጤው እስከ አገር መሪው አብዛኛው ያገባል ይወልዳል። ከዘጠና እጅ በላይ ግን ለትዳርም ሆነ ለወላጅነት ማይም ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በምድር ላይ ካሉ ሥራዎች እጅግ አስቸጋሪ ለሆነው ሥራ እንዴት ይሆን ሰው ሁሉ እንዲህ ደፋርና ግድየለሽ ሊሆን የቻለው? በዚህ በማይማን ኅብረት በተቋቋመ ተቋም ውስጥ

እንደሚወለዱ ልጆች ምን አሳዛኝ ፍጥረት ሊኖር ይችላል? እንደ ትዳር የዕድሜያችንንና የሕይወታችንን ብዙ ድርሻና ዘመን የሚወስድ ምን አለ? ሰውን የሚያህል ነገር ወልዶ እንደ ማሳደግስ ምን ከባድ ኀላፊነት አለ? ታዲያ የትዳርና የወላጅነት ማይማን የተመሳቀለ ኑሮ ኖረው ወደዚህ ዓለም ያመጡትንም ሰው ሕይወትና አስተሳሰብ ቢያመሳቅሉ ይገርማል? አስተሳሰብና አእምሮም በከፍተኛ ደረጃ የሚቀረጸውና የሚወሰነው ትምህርት ቤት ሳይሆን በልጅነት ዕድሜ በቤተሰብ ውስጥ ነው።

ለምሳሌ ያህል የማታፈናፍን ኀይለኛ እናትና የማይከላከል ፈዛዛ አባት ባለበት ቤት ተወልደው የሚያድጉ ሴት ልጆች ብዙ ጊዜ አንድም ዐመፀኛና መራር ነው የሚሆኑት፡ ወይም ራሳቸውን የሚጠሉና ስለ ራሳቸው ዝቅተኛ ግምት ያላቸው የፍቅር ረኀብተኞች። ሴት ልጅ ካባቷ ተወዳጅነትንና አፍቃሪነትን፤ ከናቷም ወዳጅነትንና ወላጅነትን ትወርሳለች ይባላል። ይህም ከምትክ እናትና አባት ሊገኝ ይችላል፡ ለምሳሌ፡ በአያት ወይም በማደጎ ቤት ያደጉ ልጆች ካሳዳጊዎቻቸው። እንደ አዱኛ ያሉ እያሉ የሌሉ ፈዛዛ አባቶች የሴት ልጆቻቸውን ልብ በፍቅር ረኀብና ስለ ራስ እርግጠኛ ባልሆነ ባዶነት ሲሞሉት፤ እንደ አብረኸት ዐይነት እናቶች ደግሞ ወይ ዐመፀኛና ማፍቀር የማይችሉ ተቧጫሪ ነብሮች፡ አለበለዚያም ፈሪና ድንጉጥ፡ እርግጠኛነት የሌላቸው ለእናትነት ብቃት የማይታይባቸው አሳዛኝ ፍጡሮች ነው የሚያደርጓቸው። ከሁሉም የሚያሳዝነው እንደ አብረኸትና አዱኛ ዐይነት ብዙ ወላጆች ቢኖሩም፡ በልጆቻቸው ላይ የሚፈጥሩትን ተጽዕኖና የሚተውትን አሻራ እንኳ አለማወቃቸው ነው። ለማስተካከል በሚያደርጉት ጥረትም ችግሩን ያብሱታል። በወንዶች ልጆች ላይ የሚፈጠረው ተጽዕኖ ደግሞ ለየት ይላል። ኀይለኛው አባት ፈዛዛዋ ደግሞ እናት ስትሆን በልጆች ላይ የሚፈጠረው ችግር ሌላ መልክ ይይዛል።

የነአብረኸት ቤት ከመላኩ መሥሪያ ቤት ብዙም ስለማይርቅ መላኩ ብዙም ሳይቆይ ስለመጣ ከማራ ጋር ተያይዘው ከማርቆስ ጋር ወደ ተቀጣጠሩበት ካፌ ሄዱ። እቤት ከሚገናኙ ካፌ ለመገናኘት ሐሳባቸውን ቀይረው ነው። ዱባይ ስለነበረው ቆይታና አንዳንድ ነገሮች እያወሩ ሳያውቁ ነበር ካፌው የደረሱት። ብዙም ሳይቆይ ማርቆስም ተቀላቀላቸው። ትንሽ ሲቀላለዱ ከቆዩ በኋላ ስለ ምንተስኖት አዲስ ልጅ ጉዳይ መወያየት ጀመሩ። ማራ ተረጋግታ ስለነበር ነገሩን እንዴት አድርገው ቢይዙት የተሻለ እንደሚሆን ነበር ዋና የውይይታቸው ዐላማ። ማራ ከምንተስኖት ጋር ለመኖር የነበራት ሙሉው ምክንያትም ውድም ብሎ ጠፍቷል።

"ቆይ አሁን እሱን መፍታት የሚከለክለኝ ነገር ይኖራል? ማለቴ በመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ መሠረት" አለች ማራ ብዙ ጥልቅ ዕውቀት ባይኖራትም፤ ከሷ ሁኔታ አንጻር ግን መፋታቱ የሚፈቀድ እንደሆነ ሳታውቅ ቀርታ አይደለም።

"ማሪ መፍታት መፈቀድ መካልከሉ ሳይሆን ዋናው ነገር ላንቺም ለልጆቹም የተሻለ የሚሆነው ማለቴ ባጠቃላይ ምንድነው የተሻለው አማራጭ የሚለው ይመስለኛል። መፍታትም ሆነ ሌላ ዕድል መስጠት ቢሆን ውሳኔሽ እንዴት ነው መደረግ ያለበት የሚለው የበለጠ ሊታሰብበት ይገባል። ከዚያ በፊት ደግሞ ነገሩ እውነት ነው ወይ? እሱስ ምንድነው የሚለው? እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ቢታዩ ጥሩ ይመስለኛል።" አለ መላኩ በምንትስኖት ስላልተናደደ ወይም ለማራ ስላልተቆረቆረ ሳይሆን በነገሩ ላይ በጣም ብዙ አስቦበት ስለነበር። እንደዚህ ያለውም በሚያደርጉት ውይይት ላይ ተቃራኒውን ወገን ይዞ በመቆም ሁኔታዎችን ለማየት እንዲቻል ነው። በተጨማሪም ማርቆስ እንዴት እንደተንጨረጨረ ስለሚያውቅና ማራም ማርቆስም ወደ ፍቺው እንዳዘነበሉ ስላወቀም ነው።

"ምንድነው ምትለው መላኩ? ... አንተ ኮ ልጁን ብታየው ትንሹ ምንትስኖት ነው። ምንድነው የሚረጋገጠው። ደግሞ ሰውዬው ልጅቷን እንዲህ መከራዋን እያበላት እያየህ የምን ዕድል ነው የሚሰጠው?" አለ ሳያውቀው ድምፁ ከፍ ብሎ ማርቆስ።

"መሌ የውልህ ባለፈውም ሐዋሳ ሄደው ሲመጡ ልብሱ ሊታጠብ ሲል የተገኝ ኮንዶም አለ። አሁንማ እኮ ምንም ደንታም የለውም፣ ቢታወቅ ባይታወቅ።" አለች ማራም የማርቆስን ሐሳብ ለማጠናከር በሚመስል አነጋገር።

"እኔ ግን አሁንም ፍቺ ወደሚባለው ጉዳይ ዝም ብሎ በጭፍኑ መንደርደሩ አይታየኝም። ላንቺም ቢሆን ጥሩ አይመስለኝም። ማለቴ ነገሩ እውነት ከሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር በዝሙት ሰበብ ሰው ሊፋታ ይችላል። ግን ሊፋቱ የሚችሉበት መንገድ አለ ማለት ይቅር ሊባባሉ ወይም ዕድል ሊሰጣጡ አይችሉም ማለት አይደለም።" ብሎ ማኪያቶውን ፉት ሲል፡-

"መሌ አንተ እኮ ችግርህ በመጽሐፍና በሕይወት መካከል ያለውን ልዩነት ትረሳለህ። አሁን የምናወራው ስለ እህትህ ስለ ማራ ነው። ሃሎ ... ደግሞ ታውቃለህ ምንትስኖት ስለሚባል አይ ዶና ... ምን እንደምል ስለሱ ... አንተ እንዴት እንደምታየው አላውቅም።" አለና ማርቆስ ወንበሩ ላይ ደገፍ ብሎ ጣራጣራውን ማየት ጀመረ።

"እኔ መፍትሔ የሚመስለኝ መጀመሪያ የቤተ ሰብ ስብሰባ ይጠራ፣ የሱም ወላጆች ይኑሩ። ከዚያም የልጅቷንና የሕፃኑን ፎቶ ተይዞ ችግሩ ይነገር። ካመነ ጥሩ ካካደም የ ዲ ኤን ኤ ምርመራ እንዲያደርግ ይጠየቅ.." ሲል መላኩ፣

"ምርመራውን እምቢ ቢልስ..? ታውቀዋለህ፣ ሥራውን ስለሚያውቅ እሺ የሚል አይመስለኝም.." አለ ማርቆስ።

ማራ ሁለቱ የሚያደርጉትን ክርክር መስማቱን ቀጥላለች ታዛቢ እንደ ሆነች ሁሉ። ይህም ማርቆስ የድርጊት፣ መላኩም የማሰብ ሰዎች የመሆናቸው ልዩነት የፈጠረው ነገር ነው።

"ካመነ ነገሩን ያሳጥረዋል። ማራ መወሰን ትችላለች ይቅር ለማለትና ዕድል ለመስጠት አልያም ለፍቺ። ለሁለቱም ነጻ ናት። ፍቺ ከተባለ እዚህ ሳይሆን አሜሪካ ከተመለሱ በኋላ ነው መሆን ያለበት። ካላመነ እና ለምርመራው ከተስማማ ውጤቱን መጠበቅ ነው። በዚያ መሠረት ይደረጋል። ምርመራውንም እምቢ ካለ ደግሞ አሁንም እምቢ ማለቱን እንደ መረጃ ወስዶ ማራ መወሰን ትችላለች። ዋናው ነገር ግን እዚህ መሆን የለበትም። ቀጥሎ ደግሞ ልጆቹን የማሳደግ ጥያቄ አለ። ሌላም ሌላም ቴክኒካል ነገር ። እሱ ግን በኋላ ይደርሳል። የቤተሰብ ስብሰባ መጠራቱ ደግሞ እውነቱን ሁሉም እንዲያውቅ ስለሚያደርግ፣ የሆነ ያልሆነ ወሬ ማውራት አይችልም ብዬ ነው የማስበው።" ብሎ ትከሻውን ወደ ላይ ሰበቅ አድርጎ መድረኩን ለቀቀ፡፡

ብዙ ተጨቃጭቀው ስብሰባውን በሦስት ቀን ሊጠሩና ምንትስኖት ቢስማማም ባይስማማም ማራ ከሳምንት በኋላ ወደ አሜሪካ ሄዳ የፍቺ ሂደቱን ልትጀምር ተስማሙ። ውይይቱ ለማራ ከባድ ነበር። በተለይ የልጆቹ ጉዳይ ብዙ ራተና መሆኑ አይቀርም። ከዚያም ተያይዘው ወደ ማራ ቤት ሄደው ራት በልተው ተጫውተው እነሱም ወደ ቤት ሄዱ። ምንትስኖትም እንደለመደው አምሽቶ ስለነበር እስከ እኩለ ሌሊት አልገባም። ማራ የፍቺው ነገር በውስጧ ስላለቀ ጉዳይም አልሰጣት። ሁለቱም መኪና ይዘው ስለነበር በቀጥታ ማርቆስ ቤት ሄደው እዚያው አድረው ነው መላኩም ወደ ሥራ የገባው።

ከሦስት ቀን በኋላ በነበረው የቤተ ሰብ ስብሰባ ላይ የምንትስኖት ወላጆች፣ መላኩና ማርቆስ፣ አንድ ሌላ ማራን በጣም የሚወዳት የምንትስኖት ታላቅ ወንድም እንዲሁም የማራ እከስት ተገኝተው ነበር። ማርቆስ እንዳለው ምንትስኖት ነገሩን ሽምጥጥ አድርጎ ክዶ ጭራሽ አራስ ነብር ሆነ።

"እዚህ ፎቶ ላይ ያለችውን ልጅ አታውቃትም?" ብላ ለሱም ለሌሎቹም ፎቶውን ሰጠቻቸው።

ትንሽ ድንጋጤ ፊቱ ላይ የታየበት ምንትስኖት እንዴ ሽምጥጦአልና አሁንም ድርቅ ብሎ አላውቅም አለ። ሁሉም የሕፃኑን እሱን መምሰል ግን ሳያውቁት አልቀሩም። አባቱ ከዚህ በፊት እቤት መጥታ ነገሩን ነግራቸው ያባረሩዋት ልጅ እንደሆነች ስላወቁ፡፡

"እንዴት አገኘችሽ አንቺን ልጄ? እዚህ እንዳላችሁስ እንዴት አወቀች?" አሉ ነገሩን ለማርገብም የምርም ግራ ገብቶአቸው።

"እኔ ስልኬን ከየት እንዳገኘችው አልጠየቅኋትም። ደወለችልኝ ቀጠርኳት ልጁን ይዛ መጣች። ሁሉንም ነገር ነገረችኝ። እናንተንም ለማግኘት ሞክራ ሰድባችሁ እንዳባረራችኋት ነግራኛለች።" አለች ማራ የሰውዬው እንዳለወቀ መሆን አንጀቷን ስላሳረረው።

ትንሽ አፈር ያሉት የምንተስኖት አባትም " ኧረ እኔ ትዝም አትለኝ። ምን ዘንድሮ ሰው አሜሪካ ከኖረ ሴቱ ሁሉ ወለድኩለት ነው እንዲህ ብሎ ቃል ገባልኝ ነው፣ ሰንቱ ትዝ ይለኛል ብለሽ ነው?" አሉ አሁንም የምንተፍረታቸውን እያስተባበሉ። የምንተስኖት ነገር ሆኖባቸው ትዳሩንም ማትረፍ ይቻል እንደሁ ብለው ነው እንጂ እሷም ትዝ ትላቸዋለች፣ ልጁም ልጃቸውን ቁጭ ነው!

"ቀላል እኮ ነው። ምንተስኖት እርግጠኛ ሆኖ እንኳን ሊወልድላት ልጅቷን እንደማያውቅ ነው የተናገረው። ስለዚህ አሁን እንደ ድሮ ዘመን አይደለም። የዲኤንኤ ምርመራ ማድረግ ነው እሱ ሁሉንም ይገልጸዋል። እሷም ከዋሸች የጁን ታገኛለች።" አለ መላኩ ነገሩ እያናደደው ስለመጣ። ነገሩ እንደ መብረቅ የመታው ምንተስኖት ዝም ብሎ ቆየና፡፡

"እና እኔ የማንም የመንደር ውርጋጥ ሁሉ የሱ ልጅ ነው ባለ ቁጥር ደም ምርመራ ልሮጥ ነው እብሬ? አላውቃትም፣ ምርመራም አላደርግም አለቀ። ማመን አለማመን የኔ ችግር አይደለም" አለ መውጫ መንገዱ ይህ ብቻ እንደሆነ እያሰበ።

እናቱም እሱን ተከትለው፣ "የምን ዴኔ ምናምን ነው የሰው ደኅና ትዳር ለመበጥበጥ ነው ሳጥናኤል የላካት። ልጄ እንዲህ በየመንደሩ የሚልከሰከስ አይደለም። ልጁን ታቅፋ እዚያ አባቱን ትፈልግ የማናት እቺ ውርጋጥ..!" አሉ የሱን ሐሳብ እያጠናከሩ።

"ምርመራው እኮ የሚደረገው ትዳርህን ለማዳን ነው እንጂ ስለ ሴትዮዋ ተብሎ አይደለም። ደግሞ ማንም ልብ ያለው ሰው ይሄ ልጅ አንተን አይመስልም ማለት አይችልም። እኔ ግን ምርመራውን ማድረግ ተገቢ ነው የሚመስለኝ ምንተስኖት። ችግርም ካለ ከዚያ በኋላ መነጋገር ይሻላል። ካሁን በፊትም ምርመራ የጠየቀህ የለም፣ በየጊዜውም የሚልህ ያለ አይመስለኝም።" አሉ የምንተስኖት አጎት። ብዙ በትምህርት ባይገፉም አስተዋይና ፍትሕ ወዳድ ናቸው። አሜሪካ ለጉብኝት ሄደው የምንተስኖትን ግፍ ስላዩ ሁሌም ለማራ ደጋፊና አዛኝ ናቸው።

"አንተ አይገባህም ጋሼ። በቃ ይሄ የራሴ ውሳኔ ነው። ትዳር ማዳን ምናምን የምትለውን አቁም" አለ ምንተስኖትም እየተናደደ።

"ኦ እንደሱ ከሆነማ ሁሉም ነገር ግልጽ መውጣት አለበት" አለች ማራ ንዴቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ፡፡

"እንካ ይሄንን ኮንዶምህን እዋሳ ሄደህ ከለበስከው ሱሪ ውስጥ ነው የተገኘው። እነሱም ይወቁት። በነገራችን ላይ አሊጋ ከለየንም ቆይተናል። እዚህ መጥተህ አንተና ጓደኞችህ ከየሴቱ ጋር ስትዘሉ ከርማችሁ እንደምትመጣ እኮ ዐውቃለሁ። ደግሞ አልመረመርም ያልከው ፈርተህ ነው እንጂ ሌላ አይደለም። ልጁ እኮ ያንተ ለመሆኑ ምርመራም አያስፈልገውም። እስኪ በደንብ እየው። ያቺን የመሰለች አንድ ፍሬ ልጅ ደግሞ እንኳን አንተን ማንንም የልጁ አባት ነው ብላ እንደዚያ እንባዋን እያዘራች አትከተልም። ጎሊና ያላት ሰው ናት ታስታውቃለች። አሁን ቤተ ሰቦችህ እንዲያውቁልህ ብዬ ነው እንጂ እኔ ያንተን ምርመራ የምፈልግልህ ይመስልሃል? ሁሉም ነገር አልቋል። ከዚህ በኋላ እዚያው የተጋባንበት በአሜሪካ ከጠበቃዬ ጋር ነው የምትነጋገረው። የተሰጠህን ዕድል መጠቀም ካልፈልግህ ከዚህ በኋላ እንደቀለድክ መኖር አበቃ። ድሮም የኔ ጥፋት ነው። ጨርሻለሁ። እናንተም ስለ መጣችሁ አመሰግናለሁ። ስብሰባው አልቋል። ሕፃን መሰልከህ እንዴ።" ብላ ድብልቅልቁን ስታወጣው ሁሉም ጸጥ አሉ።

"አይ ልጄ እንደዚህም አይሆንም፣ እኛንም ማክበር አለብሽ እኮ" አሉ አባቱ።

"አባባ ይቅርታ! እርሶንም በጣም ነው የታዘብሁዎት አሁን ይሄ ልጅ የእርሶ የልጅ ልጅ ለመሆኑ ምርመራ ያስፈልገዋል። ደግሞስ እሷን አሁን ረስተዋት ነው። ልጅዎት እንደሆነ አውቃለሁ። አሁን ግን አልቋል።" አለች ንዴቷ ሳይበርድ።

"እንዲያውም መላኩ ና እንሂድ እዚህ መቆየት አልፈልግም። እናንተ መሰብሰብ ትችላላችሁ። ይሄው አሉላችሁ እሳቸው ክቡርነታቸው። ሴቱ ሁሉ የልጄ አባት ነው እያለ የሚግተለተልላቸው ልዑሉ ... ምንተስኖት።" ብላ ተነሥታ ስትወጣ መላኩም ተከትሎአት ወጣ። ማርቆስ ግን ማራ እክስት ጎን እንደተቀመጠ ዝም ብሎአል።

"አንቺ ክፍታፍ አፍሽን አትክፈቺ። ዝም ስል ጊዜ .. ምን ልቅ አፏ ነች ባካችሁ! እዚህ አሜሪካ መሰለሽ እንዴ? እንዳላጋጭሽ!" አለ ምንተስኖትም ከመቀመጫው እንደመነሳት ብሎ።

"አንተ ቁጭ በል እንጂ ... ምን ልትሆን ነው?" ብሎ አጠገቡ ያለው አጎቱ እዚያው ሶፋው ላይ ቁጭ አደረገው። እሷ ዞር ብላ ሳታየው ከመላኩ ጋር ተከታትለው ወጡ። ከወጡ በኋላ ቤተ ሰቡ እንደ ምንም አግባብተውት ምርመራውን ለማድረግ ተስማማ። እሱም ጊዜ ለመግዛ እንዲ ሆነው ነው እሺ ያለው እንጂ ያሰበው ሌላ ተንኮል ነበር። እክስቷና የሱ አጎት ማራን ለማግባባት ተስማምተው ስብሰባው ተበተነ።

በማግስቱ ከጓደኞቹ ጋር የእርሻ መሬት ለማየት ወደ አሰሳ ለመሄድ የቆየ ቀጠሮ እንዳለውና ሲመለስ ምርመራውን እንደሚያደርግ ለማራ ተነግሯት እሷም ተስማማች። እሱ ወደ አሰሳ ለመሄድ ሳይሆን፣ ልጅቱን ከነልጁ ጠልፎ ገጠር አፍኖ አስቀምጦ እሷ ስትጠፋ ምርመራውንም ለማስቀረት ነው እቅዱ። ማምሻውን ከታች እላይ ብሎ ልጅቱን ሊያገኝ ቢሞክርም በመጨረሻ ደሴ አጎቷ ጋ ከልጁ ጋር እንደሄደች ሰማ። በሰው በሰው የአጎቷን አድራሻ በምልክት አግኝቶ እሷን ፍለጋ ደሴ ከጓደኛው ጋር በሌሊት ተነሥተው ወጡ። ማራም ለምርመራው እሺ ያለችው ጊዜ ለመግዛትና ጠርንቱን ጋብ ለማድረግ ብላ ስለነበር ለዚያኑ ማታ በረራዋን አስቀይራ ልጆቿን ይዛ ወደ አሜሪካ ተመለሰች። እሱ ደሴ ሲሄድ የልጁ እናት ደግሞ ወደ አዲሳባ እየመጣች ኖሮ፣ በመንገድ ተላለፉ። እዚያው ደሴ ወዲያ ወዲህ ሲሉ አረፋፍደው ወዳዲሳባ ሲመለሱ መኪናቸው መንገድ ተበላሽቶባቸው ደብረሲና ላይ ማደር ነበረባቸው። ሌሊት ላይ ስልክ ተደውሎ ከእንቅልፉ ነቅቶ ሲያየው ስልኩ ካሜሪካ ነው የተደወለው። ሃሎ ሲል ማራ "አታስብ በሰላም እኔም ልጆቼም አሜሪካ እንደ ገባን ልንገርህ ብዬ ነው። ካሁን በኋላ እንዳልኩህ ከጠበቃዬ ጋር ነው ጉዳዩን የምንጨርሰው። ምናልባት ግብርና ስለሆነ የሚሻልህ እዚያው አሰሳ እያረስህ ብትኖር ይሻልሃል። በል ቻው።" ብላ አንድም ቃል ሳያወራ ዘጋችው።

ደጋግሞ ሃሎ ሃሎ ቢልም፣ መልስ ቢደውልም ስልኳን አታነሣም። ዞረበት። ጓደኛውን ከሌላ ክፍል ቀስቅሶ የሆነውን ነገሮት፣ የሚያደርገውን አጥቶ ሳይተኛ ነጋ። አዲስ አበባ ሲደርስ ሐሳቡን ቀይሮ ልጅቱን ማግኘቱንም ተወው። መላኩ ጋ ደውሎ እየሮኘ የስድብ ናዳውን አወረደበት። መላኩም ዝም ብሎ ሰማው ሰማውና ዝም ሲል ስልኩን ዘጋው። ይሄም የበለጠ አንጨረጨረው። እቤት ሄዶ ዕቃውን ሊወስድ ሲል ዕቃውን ሁሉ ጠዋት አጎቷ መጥተው እንደወሰዱና ቤቱ ባዶ እንደሆነ፣ ላከራዮቹም እንደተመለሰ ዘበኛው ነገረው። ካልገባሁ ብሎ ሲያስቸግር የውጭ በሩን ቁልፍ ሊሰጠው እንደማይችል ቢነግረውም በጣም ተናዶ ስለነበር ለድብድብ ተጋበዘ። ዘበኛው ወጠምሻ ጐረምሳ ነበርና፣ በያዘው ዱላ ሊነርተው እንደሚችልና ሕግም በሱ በኩል እንደማይቆም በማሰብ እየተሳደበ ተመለሰ። አጎቱ ጋ ቢደውል ዕቃው እሳቸው ጋር እንዳለና ማራ ትናንት መሄዷን ሲነግሩት የባሰ በንዴት ጦፎ ስልኩን ጆሯቸው ላይ ዘጋባቸው።

*   *   *

ሶፊያ አዲሳባ ደግማ ስትመጣ ብዙ ነገር ተቀያይሮባታል። የአሁኑን አመጣጧን ከቀድሞው ጋር አንድ የሚያደርገው መጀመሪያ ስትመጣ አባቷን አጥታ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ በሕይወቷ ሁሉ ከወደደቻቸው ሰዎች በላይ የወደደችውን ሶለንን ማጣቷ ነው። ኢትዮጵያ ለሷ ማገገሚያዋ እንደሆነች ያሀል ነው የተሰማት። ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት የቆየችው ባለፈው ስትመጣ ካገኘቻቸው ቤተ ሰቦች ጋ ሲሆን፣ ከዚያም በኋላ እንድትሠራለት የቀጠራት ግብረ

ሠናይ ድርጅት ለሌሎች ሠራተኞቹ በተከራየው ትልቅ ግቢ ባለው የእንግዳ ማረፊያ ውስጥ ገብታ መኖር ጀምራለች። ግቢው ያለው ከብሥራተ ገብርኤል በታች የአፍሪካ አንድነት ዋና ጸሐፊ መኖሪያ ጀርባ አካባቢ ነው። ይህም ለፊስቱላ ሆስፒታልም ሆነ በሳምንት ሁለት ቀን ለምታስተምርበት ትምህርት ቤት እጅግም ሩቅ አይባልም።

በፊት የምታውቃቸው ሰዎች ስላሉና ለብዙ ነገርም እንግዳ ስላልሆነች መላመዱ እንደ በፊቱ አስቸጋሪ አልሆነባትም። መላኩ ስልኳን ከዱባይ ልኮለት ስለነበር አንድ ሁለት ጊዜም ከማርቆስ ጋር ተገናኝተው ነበር። ለመግባባት ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም። ሶፊያ በቀላሉ የምትወደድ ዐይነት ልጅ ናት። ማርቆስም ከሷ ጋር ለመግባባት አልተቸገረም። ብዙ ተመሳሳይ ፍላጎቶችና የሚያወሩት ነገር ስለነበረም በተገኛኙበት ጊዜ ረዘም ላለ ሰዓት አብረው ነበር የቆዩት። ማርቆስ አውሮጳ በነበረበት ጊዜ በአንድ ጓደኛው ተንኰል ተጣልተው የተለያትን የመጨረሻው የነበረችውን ጓደኛውን የሚመስል ብዙ ነገር አላት።

መላኩ ከዱባይ ከመጣ በኋላ ሶፊያን በስልክ እንጂ በአካል አላገኛትም። ከዚያም ሥራው፣ የማራ ነገርና ሌሎች ነገሮች ሁሉ ይዘውት ተወጥሮ ስለከረመ ጭራሽ ጠፍቶባት ነበር። ማራም ከሄደች በኋላ ከነሶስናም ጋር ናፍቆቱ እስኪወጣለት ጊዜ ማሳለፍ ችሎአል። ከሶፊያ ጋር ዛሬ ማታ ለእራት ሊገናኙ ነው ማርቆስንም ጨምሮ የተቀጣጠሩት። በማግስቱ ማርቆስም ወደ ቻይና ለሥራ ስለሚሄድ መቂ የመሄዳቸውን ሐሳብ ማርቆስ ሲመጣ ከዐሥር ቀን በኋላ ለማድረግ ነው ያሰቡት። ሊገናኙ የተቀጣጠሩት አምስተርዳም ሬስቶራንት ነው። የማርቆስ ምርጫ ነው። የምግቡን ዐይነትና ጥራትም ይወደዋል። በተለይ ግን የምግቡና የአገልግሎቱም ጥራት ሳይዛነፍና ከፍ ዝቅ ሳይል ደረጃውን የተጠበቀ መሆኑ ነው ማርቆስን የአምስተርዳም አፍቃሪ ያደረገው። አስተናጋጆቹ ሁሉ ናቸው የሚያውቁት፣ ተጫውቶ ቀልዶ ነው የሚወጣው። አንዳንድ ሰዎች እነማርቆስ ቤት እንገናኝ ሲሉ አምስተርዳም ማለታቸው ነው። መላኩ ስብሰባ ረዝሞበት ዐሥራ አምስት ደቂቃ አርፍዶ ነበር የደረሰው። ሶፊያን ከቤቷ ያመጣት ማርቆስ ነበር፣ የሞቀ ወሬ ይዘው ሲጫጫቁ ነበር መላኩ የደረሰው። የሆነ ሐሳብ በሐሳቡ በጨረፍታ አለፈበትና በራሱ ሣቀ።

በጣም ጥሩ እራት ነበር። መላኩና ሶፊያ ለመግባባት ጊዜም አልወሰደባቸውም። ማርቆስ ስለ መላኩ የነገራት ነገር ብቻ ሳይሆን የዚያን ለታ ማታ መላኩ በሁሉም ጉዳዮች ላይ የሚሰጣቸው አስተያየቶችና የቁምነገር ኮሮጆ የሆኑት ቀልዶቹም ሳታስበው ሶለንን ነበር ያስታወሳት። መልካቸው በርግጥ አይመሳሰልም። ግን መላኩ ደግሞ ከሶለን የተለየ የሰውን ልብና ቀልብ የሚገዛ ማግኔታዊ ሰብእና እንዳለው ነው ያስተዋለችው። ሻካራ ድምፁና ጐፈሬው ከሆነው በላይ ተሰሚነቱን ሳይጨምሩለት አይቀርም። የአስተያየቱ ይዘት ግን ሶለናዊ ሆኖባት አልፎ አልፎ ድንግጧ ስትል ነበር። በየመሃሉም ስሎሜ እንዴት ዐይነት

ጥሩ ልጅ እንደሆነች፣ መላኩም ሆነ ማርቆስ ባያውቁትም፣ የክብሮምን ደግነትና እንዴት እንደረዳት ማንሟ አልቀረም። የሁለቱ አንድ ላይ መነሣት ለመላኩ እንዳች ደስ የሚያሰኝ ስሜት ፈጠረበት። ስንክሳርንም ለአጭር ጊዜ አግኝታት ስለ መላኩ እንደነገረቻትና ለወንድሟ መድኀኒት እንደላከቻት ስታወራ ማርቆስ የስንክሳር እንዲህ ባንዴ አገሩን ሁሉ ማካለል ገርሞታል። ከዚያ ውጪ ስለ ሶለንና የስ ሞት ቤተ ሰቡን እንዴት እንደጐዳ በተለይ ሰሎሜን ኀዘኑ ምን ያህል እንደጎዳት አጫወተቻቸው። ከዚያ በተረፈ ሲማማቱና በማርቆስ ጉዞና ሥራ ላይ ሲያወሩ አመሹ።

የመላኩን መኪና እዚያው ትተው እርሷን በማርቆስ መኪና አድርሰዋት ተመልሰው ተከታትለው ወደ ማርቆስ ቤት ሄዱ። መላኩም ሶፊያን ምንም ሳትጨነቅ ምንም ነገር ብትፈልግ እንድትደውልለት አደፋፍሮአትና እንደሚገናኙም ተነጋግረው ነው የተለያዩት። ማርቆስ በረራው በጠዋት ስለነበር መላኩ እሱን ለማድረስም እንዲመቸው እዚያው አደረ። ለነገሩ ምክንያትም ባይኖር መለያየት አይወዱም። እቤት እንደገቡ ፒጃማ ቀያይረው ሳሎን ቤት ማርቆስ ሻንጣውን እያዘጋጀ ወሬያቸውን ቀጠሉ፡፡

"አንተ ይቺ ልጅ ዐይኔ ነው ወይስ የሆነ ማርታን የሚመስል ነገር አላት?" አለ መላኩ ስልኩ ላይ ያሉትን ያልተመለሱ ቁጥሮች እያየ። ማርታ ማለት ማርቆስ መጨረሻ ላይ እንግሊዝ አገር እያለ ባሳዛኝ ሁኔታ የተለያት ጓደኛው ስትሆን፣ መላኩ ከተለያዩ በኋላ ነበር ያያት። በዛ የተነሳ ማርቆስ በጣም ተጐድቶ ስለነበር ከፍተኛ ሱስ ውስጥ ገብቶ፣ ሕይወቱም ሁሉ ተበለሻሽቶ እያለ ነው ከመላኩ ጋር ጓደኛ የሆኑት። የማርቆስ ሕይወት ለመስተካከል ከሁለት ዓመት በላይ ፈጅቶበታል፡ መላኩ ባይኖር ከንቱ ሆኖም ይቀር ነበር። ለተሰበረ እግር መዳን ጀሶ እንደሚያስፈልግ የተሰበረ ልብንም ያለእውነተኛ ጓደኛ መጠገን አይቻልም።

"አይደል ... እኔም እንደዚያ መስሎኝ... ዝም ብሎ ዐይኔ ነው ብዬ አስቤ ነበር። አይገርምም። ነገር ግን ማርቴን የሚመስልም የሚያህልም የትም የለም። በናትህ ቁስሌ ነው የሚነካካብኝ ስለእርሷ ሲነሳ እኮ" አለ ትንሽ ፊቱ እየተለዋወጠበት። አሁንም በሱና በማርታ መካከል የሚያምነው ጓደኛው የሠራው ደባ ያንገሸግሸዋል። በማርታ ልክ የምትሆን ሴት የለችም የሚለው እምነቱ ነው አሁንም ድረስ ብዙ ሴቶችን እንዳይቀርብ የሚያደርገው። ይህም ከሌል እውነትነት ሲኖረው፣ አብዛኛው ግን በግፍ ያጣናቸውና በየዋህነት አእምሮአችን የወደድናቸው ነገሮችና ሰዎች ሁሌም የጻድቃን ሰማዕታትን ያህል በልባችን ፍጹምናን ስለሚላበሱ ነው።

ነገሩ ለማርቆስ ብዙም ምቾት እንዳልሰጠው የተረዳው መላኩ፣ "አይ እንዲያው ስለገረመኝ ነው አጋጣሚው። ጥሩ ልጅ ትመስላለች።" አለ ነገሩን ቀለል አድርጎ፡ "አይደል ... ትንሽ ከነገረችኝ ታሪኳም አሳዛኝ ነው። ደግሞ እዚህ መጥታ

ለመኖር መወሰኗና ለሰው ያላት ፍቅር በጣም የምትገርም ሰው ናት፣ ብዙም አትክብድም እኮ ደግሞ።"

"አይደል... ይገርማል የሰው ሕይወት የምትወስደው ጥምዝ መሥመር። እኔ ምልህ አሁን ሄደህ ኮንትራቱን ለመፈረም ነው ወይስ ማየት ያለብህ ነገር አለ?" አለ ርእሱን ፊጽሞ እየቀየረው፡፡

"እምም ዶክመንቱን አይቼዋለሁ፣ ከጠበቃ ጋርም ሕጋዊ አቅጣጫውን አይተነዋል። ግን እስኪ በመጀመሪያዎቹ አራት ቀናት ፋብሪካቸውንና ዋና መሥሪያ ቤታቸውን አይቼ ከዚያም ዋና ዋና ሰዎቻቸውን ለማግኘት እሞክራለሁ። ደግሞም ባብዛኛው የውክልና ሥራ ስለሆነ የምሠራላቸው መጀመሪያ ላይ ብዙም ሪስክ የለውም። ቀስ በቀስ እዚህ ማምረቻውን ለመትከልም ነው የሚያስቡት። ትልቅ ፖቴንሺያል ያለው ሥራ ነው። እስኪ እናያለን።" አለ ማርቆስ የቀሩትን ዕቃዎች ከመኝታ ቤት ሊያመጣ እየሄደ።

"በጣም አሪፍ ነው ማርክ ጀግናው። ከትንሽ ዓመታት በኋላ ደግሞ ካንተ ድርጅት ነው ወኪል ለመሆን ሰዎች ከየገሩ እዚህ የሚመጡት" ሲል ሪኮ ብሎ ማርቆስም በደማቁ እየሣቀ፣ "ቀልድ ምናለብህ አንተማ። እኔ ግን የቻይናና የህንድ ዕቃ ማራገፊያ ሆነን እንዳንቀር የራሳችንን ትልልቅ ኩባንያዎች አሁኑኑ መጀመሩ የሚደ ነው የሚመስለኝ። ለምሳሌ መቶ ዶላር በማይሞላ ገንዘብ የዛሬ ሰባ አመት በችርቻሮ ንግድ የተጀመረው ሳምሶንግ ዛሬ ዓለምን እንዴት እንዳጥለቀለቀ ተመልከት። የጃፓንና የኮርያ ካምፓኒዎችም ሆኑ ያሜሪካ ትልልቅ ካምፓኒዎች ባንድ ሰው አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ነው የተጀመሩት። ማይክሮሶፍት ብትል አፕል፣ ዴል ብትል ጉግል። ይመስለኛል ይሄ የኛ ጊዜ ነው። ኮርጀን ሳይሆን ፈጥረን ዓለምን የሚለውጥና የሚጠቅም ነገር መሥራት የምንችል ይመስለኛል። እስከዚያ ግን የነሱ ወኪልም ማራገፊያም ሆነን ቁም ነገሩን መማሩ ላይ ነው ቁምነገሩ። ምን ይመስልሃል ታላቁ የአፋር ፈላስፋ?" አለ አሁንም እየሣቀ።

"ልክ ነው ጋሽ ሮክፌለር" ብሎ እሱም ሣቀ።

"እኔ ምልህ አንተ ፈላስፋ ቢጤ ሰውዬ ለመሆኑ ሰሎሜን አግኝተሃት ታውቃለህ? እንዴት ናት? ምንድነው ስለሷ ማውራት ምናምን ቀንሰሃል?" አለ ፊቱን ቀጨም አድርጎ፡፡

"ያው እንዳልኩህ ዱባይ ሆኜ ብዙ አውርተን ነበር። ግን ያው ምንም ልብ ለልብ ማውራት የቻልን አልመሰለኝም። በቃ የሆነ ነገር አለ። ዝም ብሎ ወሬ ነው። ኢሜይሎቹም አጫጭር ናቸው 'ቀኑ ይሞቃል፣ መኪናው ይበራል፣ ደመናው ይገርማል' ነገር ናቸው። እስኪ እንግዲህ አንዴ ትምጣና እናያለን። ችግሩ እኔም ልሆን እችላለሁ። ደግሞ ኀዘኑም ምኑም ስላለ እሱም ሊሆን ይችላል ብዬ ነው ያሰብኩት።"አለ ብዙም እንዳላስጨነቀው በመምሰል፡፡

" እና መቼ ነው የምትመጣው?" አለ አሁንም ፊቱ ብዙም ሳይፈካ፤፤

"እኔንጃ ማርከ ... የሶለንን ታሪክና አንዳንድ የሱን ሥራዎች ወደ መጽሐፍ ለመቀየር ታስባለች።ታውቃለህ አይደል? እሷ እንዴት መጻፍ ላይ የተጠመደች ሰው እንደሆነች። ደግሞ ወንድሟን እንደ ነፍሷ ስለምትወደው እንኳን መጽሐፍ ሌላ ምንም ነገር ለማድረግ ብትፈልግ አይገርመኝም። ግን ዝም ብዬ ሳስበው ልቧን የሆነ የያዘው ነገር ያለም ይመስለኛል። ይሄ የኔ ግምት ነው።" አለ አሁንም ትከሻውን እየሰበቀ።

"ብራቮ መሊ መጠርጠርያሽን ማዳመጥ ጀመርሽ ማለት ነው። ከሙግት ወደ ስሜት ዓለም እንኳን ደኅና መጣህ!" አለ ነገሩን ለማቅለል በማሰብ፣ መላኩ ላይ ያየው ለውጥም እያስገረመው።

"እንዴ አንተ እኔ ስሜት አልባ የምክንያት ማሽን ነው የምመስልህ ማለት ነው? አንተ ልጅ ተበላሽተሃል እኮ!" አለ በያዘው መጽሔት ጭንቅላቱን መታ እያደረገው።

"አ ሰውዬው የኛ ፀጉር እንዳንተ ያሩር ጐፈሬ ጭንቅ አይችልም። ስንት ዋጋ ተከፍሎበት ከአርመን ድረስ እንደመጣ ረሳኸው እንዴ? የምር የምር አሪፍ ነው። ግን ገና ብዙም ስላልበሰለ ስሜትህን አትታመንበት እሱን ለኛ ተወው።" አለ አሁንም እየቀለደ።

"በል የኔ አርመናዊ ነጋዴ እስኪ እንተኛ። ነገ በጠዋት ስለምንነሣ። አይመስልህም?" አለ መላኩ እየተነጠራራ።

ጠዋት ላይ ማርቆስን አየር ማረፊያ ካደረሰው በኋላ በቀጥታ እቤቱ ሄዶ የዋና ልብሱን ይዞ ሂልተን ሲዋኝ ቆይቶ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ሲሆን ወደ ቤቱ ተመለሰ። ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦበት የነበረውን የቅዳሜውን የመላኩ ጊዜ ለመውሰድ ስልኩን አጠፋፍቶ ቀለል ያለ ልብስ ለብሶ ተሰየመ። የተወሰነ ሰዓት መጽሐፍ ቅዱሱን ሲያነብ ነበር የቆየው። ሐዋርያው ጳውሎስ ፊልሞና ለሚባለው ወዳጁ እስር ቤት ስላገኘው አናሲሞስ ስለሚባለው ሰው የጻፈው ደብዳቤ ነው። መጽሐፉ አንድ ገጽና አጭር ቢሆንም መላኩ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያጠና ማመሳከሪያ ይዞ ስለሆነ ከሁለት ሰዓት በላይ ነበር የወሰደበት። በመጨረሻም የተማረውንና ያጤነውን ነገር ሁሌም እንደሚያደርገው ላፕቶፑ ላይ ባለው ግለማስታወሻው ላይ በአጭሩ እንዲህ አሰፈረው።

በጊዜው ጳውሎስ ራሱ በእምነቱ ምክንያት በሮም እስር ቤት ታስሮ የነበረ ቢሆንም፣ ይህንና ሌሎች ደብዳቤዎችን ከዚሁ እስር ቤት ነበር የጻፈው። አናሲሞስም የፊልሞና ባሪያ የነበረ ሲሆን፣ ከጌታው ከሥልሎ ሳለ ነው ጳውሎስ ያገኘው። በዚያም ስለ ወንጌል ነግሮት ሕይወቱ ከተቀየረ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለበት መወሰን ነበረበት። አናሲሞስን እንደ ባሪያ ሳይሆን እንደ ልጁ ነበር ጳውሎስ የሚያየው። ምናልባትም መኰብለል ብቻ ሳይሆን ሲኰበልል ከጌታው ላይ የሰረቀው ነገርም ሳይኖር አይቀርም። በሮም ሕግ መሠረት ደግሞ ይህ እስከ ሞትም ሊያስፈርድበት ይችል ነበር። የሌላ ሰው ባሪያ ደግሞ ያለባለቤቱ ፈቃድ ማስቀረት ሕጉ አይፈቅድም። ለዚህም ነው ጳውሎስ ለፊልሞና ምንም እንኳን እኔን እንዲያግዘኝ ለራሴ ላስቀረው ብወድም፣ ላገዘ ሥልጣን ቢኖረኝም ያለፈቃድህ ምንም ላደርግ አልፈለግሁም የሚለው። ቀድሞ ምንም የማይጠቅም እንዲያም የጐዳህም ቢሆን አሁን ግን ከባሪያም ይልቅ የተወደደ ወንድምህን፣ ለኔም የሚጠቅመኝን ልጄን እንደእኔ ተቀበለው ነው የሚለው። ያጐደለብህ ነገር ወይም ዕዳ ቢኖርበት እኔ እከፍላለሁ ብሎ እማኝ ይሰጠዋል።

አናሲሞስ የሚለው የስሙ ትርጉምም 'ጠቃሚ ረዳት' ማለት ሲሆን ጳውሎስ የሚለው ደግሞ ምንም እንኳን ቀድሞ እንደስሙ መሆን ሳይችል ቀርቶ የማይጠቅም የነበረው እሽከርሀ አሁን ከመለወጡ የተነሣ እጅግ ጠቃሚ ሰው ሆኖአል ነው። በነበረው ሥርዐት አንድን ባሪያ ወስዶ ነጻ ማውጣት ብቻ ሳይሆን፣ ጠቃሚ የጌታው ወንድም እንዲሆን ማድረጉ ጳውሎስ ሰባኪም ከጊዜው የቀደመ የለውጥ ሐዋርያም እንደነበረ ነው የሚያሳየው። ጳውሎስ በራሱ የእስራት መከራ ተጠምዶ አሊያም የታወቀ ታላቅ ሐዋርያ በመሆኑ ተመክቶ ይሄንን ከጌታው ጠፍቶ የሚቅበዘበዝ ወጣት ተስፋቢስ ችላ ሊለው ይችል ነበር። ግን አናሲሞስን እንደ ልጁ አድርጎ ለመቀበልና ከገባበት ዐዘቅት ለማውጣት ያሳየው ትሕትናና የከፈለው መሥዋዕትነት አስገራሚ ነው።

ይህ ታሪክ ማንንም ቢሆን ሊለወጥ የማይችልና የማይጠቅም ነው ብዬ እንዳላስብ አስተምሮኛል። ደግሞም በምንም ዐይነት ችግርና እስራት ወይም በምንም ዐይነት ታዋቂነትና ታላቅነት ውስጥ ብሆን እንኳ ሰውን በተለይም ሰው ሁሉ አይጠቅምም ብሎ ተስፋ የቆረጠበትን ሰው ከመለወጥ የሚበልጥ ክቡር ሥራ እንደሌለ ተምሬበታለሁ። ዛሬም በየጐዳናውና በየእስር ቤቱ፣ በገጠርና በከተማው አያሌ ሰዎች የአናሲሞስን ዐይነት ሕይወት እየኖሩ ሲቅበዘበዙ በፍቅር ቀርቦና አቅርቦ ያጠፉትን እኔ እከፍላለሁ ብሎ የለውጥ ድምፅን የሚያሰማቸው ይፈልጋሉ። ከዚህች ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ የተማርኩት የለውጥ ሀግ ይህ ነው። ለውጥ ማለት 'አይጠቅምም የተባለን ሰውና ነገር ጠቃሚ የማድረግ ስራ ነው!' ለመማር ልቡን ለከፈተና ጊዜውን ለሰጠው ሁሉም ነገር ትምህርት ቤት ነው፣ ሁሉም ሰው አስተማሪ ነው።

በሚቀጥሉት አራት ቀናት መላኩና ሶፊያ ሦስት ጊዜ ተገናኝተው ነበር። ወደ አንድ የሥዕል ኤግዚብሽን ይዞአት ሄዶም ነበር። የሶፊያ አስተያየቶች የሥዕል ችሎታዋን ይገልጻሉ። ኤግዚቢሽኑን ያዘጋጀችውን ሠዓሊ መላኩ ያውቃት ስለነበር፡ ከሶፊያ ጋር አስተዋውቆአቸው አድራሻ ተለዋውጠዋል። ረዘም ላለ ጊዜ አውሮጳ አገር የኖረች ናት ሠዓሊዋ። ሶፊያ ከመላኩ ጋር በጣም ብዙ ነገሮችን ማውራት ችላለች። ታሪኳንም ከሞላ ጎደል አጫውታዋለች።

"አንተ እኮ አማካሪ ወይም ሳይኮሎጂስት ነበር መሆን የነበረብህ" ስትለው፣ "አይ እኔ ለሱ ተሰጥዎ የለኝም፤ ደስ የሚለኝ ሰው ማዳመጥ ነው። ሰው እያስለፈለፉ ማስከፈል አልወድም" ብሎ ነበር ያሣቃት። በየመሃሉም ስለ ማርቆስ ጥሩነት፣ ያላቸውን ቅርርብ አውርቷታል። ሶፊያ መላኩና ማርቆስ አንዳቸው ስለሌላው በሌሉበት ስለሚያወሩት ጥሩ ነገርና አብረው ሲሆኑም ስለሚያሳዩት መከባበር አይታ የበለጠ እንድትወዳቸው አድርጓታል። እሱም ስለ ራሱ ከሞላ ጎደል ነግሯታል። ማርቆስ ሲመጣም መቂ እንደሚሄዱ አውርተዋል። አብራቸው ብትሄድ ደስ እንደሚላት ስትጠይቀው ፈቃደኛ በመሆኑ ፈንድቃለች። በተለይ ስለ መዐዛ ከነገራት በመነሣት እሷን ለማየት በጣም ነው የጓጓችው።

መላኩ ዐርብ ከሥራ ሊወጣ አካባቢ የስንክሳር ወንድም የዳንኤልን ስልክ ስብሰባ ላይ ሆኖ ካላነሣቸው ስልኮች መሃል ስላየው መልሶ ደወለለት። ስልኩን ያነሣችው ስንክሳር ስለነበረች ጆሮውን ማመን አልቻለም።

"እኔ አላምንም። ስንኪ ነኝ እንዳትይኝ ብቻ?" አለ መላኩ ተገርሞም ደንግጦም። መላኩ ስንኪ ሲላት ደስ ነው የሚላት።

"እንዲህ ነን እኛ ካስፈለገ ከተፍ ነው። እንዴት ነህ በናትህ መልአኩ መሊ?" አለች ልክ ድሮ ኮሌጅ እያሉ ስትቀልድበት በምትጠራበት ስም።

"ደኅና ነኝ። በሰላም ነው? ልመጣም ነው ምናምን አይባልም እንዴ? የምር መቼ መጣሽ?" አለ ከግርምቱ ለመውጣት እየታገለ።

"ትናንት ሌሊት ነው የገባሁት። ምን ባክህ በቃ ድብርቱ ሊገድለኝ ነው። ማሚ ዝም ብላ በሀልሚ ትመጣለች። በቃ አገሩን ታውቀው የለም ሰው ሁሉ መሮጥ ነው። ብቸኝነቱም አለ። ምናለፋህ ዲፕሬሽን ውስጥ መግባት ስጀምር ዝም ብዬ ነው ድንገት ብድግ ብዬ የመጣሁት። ወንድም ጋሼም ስነግረው ደስ ነበር ያለው። እዚህ አየሩ ራሱ ያጽናናል እኮ። ከዚያ አገር ቱራቲ የዚህ አገር ማኪያቶ ይፈውሰኛል ከድብርቱ ሁሉ" አለች ነገሩን ከነዘፈ ጋር እያይዛ ድንገተኛ በማስመሰል።

"እሺ. ለነሰሊስ ነግረሻቸዋል ወይስ እዚያም አያውቁም?" አለ ስለ ሰሎሜ ለማወቅ ፈልጎ፥

"እም ትንሽ ቀን ሲቀረኝ ነግሬያቸው ነበር። እሷም ትንሽ ቢዚ ስለነበረች እኔም ስሯሯጥ መጨረሻ በስልክ ብቻ ነው የተገናኘነው። ምን ደውላልህ አታውቅም እንዴ? ምናልባትም መምጣቴንም ትነግርሃለች ብዬ እኮ ጠርጥሬ ነበር" አለች እሷም ወሬ ለቀማ።

"እ..ም አዎን ይህቺን ሳምንት አልተገናኘንም።" አለ ነገሩን ደፈንፈን አድርጎ።

"ማርቆስስ ደኅና ነው?" አለች ጉዳይዋ ባይሆንም መላኩ እንደሚወደው ስለምታውቅ

"ማርክ ደኅና ነው ሰሞኑን ቻይና ነው ያለው። ካምስት ቀን በኋላ ነው የሚመጣው።" አለ የቢሮውን በር እየቆለፈ።

"አ ባት ኢዝ ናይስ። እኔ ምልህ ሶፊያን አገኘሃት እንዴ? እንድታገኛችሁ ነግሬናት ነበር" አለች ወደምትፈልግበት ነጥብ እየመጣች።

"አዎን ጥቂት ጊዜ ከማርክም ጋር አሁን እሱ ከሄደ በኋላም ለብቻዬ አግኝቼያት ነበር። ደኅና ልጅ ትመስላለች።" አለ ለነገሩ ትኩረትም ሳይሰጠው፤፤

"የት ነህ ታዲያ አሁን? ከሥራ አልወጣህም እንዴ? ለምን ለእራት አንገናኝም?" አለች ሁሌም ሰዎች ድንገት ሲጠየቁ እምቢ የማለት አቅም እንደማይኖራቸው ስለምታውቅ የምትፈልገውን ነገር ሳይታሰብ ነው የምትጠይቀው።

" እም አሁን የማልቀርበት ቀጠሮ አለኝ ስንኪ። ባይሆን ነገ ምናምን ተደዋውለን ይሻላል" አለ መላኩ። ሰው ማግኘት ሳይሆን እነሶስና ጋ ቆይቶ በጊዜ እቤት ገብቶ እስከ ነገ ምሳ ሰዓት እቤት ቆይቶ ከሰዓት ላይም ሶፊያን ሊያገኝ ቀጠሮ አለው። ከቻለ ወደ ማታ ነው ስንክሳርን ሊያገኛት ያሰበው። በማያውቀው ምክንያት ስንክሳርን ማግኘት አላሰኘውም። ምናልባትም የሰሎሜን ነገር ስለምታነሣበትና ሌላ ነገርም ነግራው አንጀቱን እንዳታበግነው ፈርቶ ሳይሆን አይቀርም።

በማግስቱ ከሰዓት ላይ ስልኩን ሲከፍተው የተወሰኑ የጽሑፍ መልእክቶችን አገኘ። አንዱ ከስንክሳር ሲሆን ከሰዓት በኋላ ላይ ከሶፊያ ጋር አብረው በተቀጣጠሩበት ቦታ እንደምትመጣ የሚገልጽ ነው። ትንሽ በስጨት ቢያደርገውም ብዙም አላስጨነቀውም። ሰዎች እሱ ባወጣው ፕሮግራም ውስጥ ያለሱ ፈቃድ ሲገቡበት በጣም ነው የሚበሳጨው። እሱ ቀጠሮው ቦታ ሲደርስ ሶፊያና ስንክሳር ያወሩ ነበር። ወሬ የማያልቅባት ስንክሳር አፏችውን ሳታዘጋቸው ሰዓቱ ሞልጥ ብሎ ሄደ። ከዚያም እራት አብረው በልተው ጠዋት በእንግሊዝኛ አገልግሎት የሚሰጥበት አይ. ኢ. ሲ የሚባለው ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን አብረው ለመሄድ ተስማሙና

መጀመሪያ ሶፊያን አድርሰው፣ ስንክሳርን እቤቷ ጥሎ ወደ ቤቱ ገባ። ደክሞት ስለነበር ወዲያው ነበር እንቅልፍ የወሰደው። ማርቆስም ሲደውል ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ላይ ስለነበር ስልኩ አመለጠው። ማርቆስና ግራ በየቀኑ ነው የሚደዋወሉት ቻይና ከሄደ ጀምሮ። ምንተስኖት አሁንም እዚሁ ስለሆነ ምንም አዲስ ነገር አልተፈጠረም።

በማግስቱ ከቤተ ክርስቲያን መልስ ስንክሳር ምሳ ጋብዛቸው ከበሉ በኋላ ሶፊያ ሌላ ቀጠሮ ስለነበራት እሷን ቀጠሮ ቦታዋ አድርሰዋት እነሱ ሂልተን ተቀምጠው ለማውራት ወደዚያው አመሩ። ስንክሳር አመቺ ጊዜን ስትጠብቅለት የነበረውን ነገር ለማፈንዳት ልቧ ከጅሏል።

"አንቺ ግን ይሄ መንገድ በቃ የውሃ መንገድ ሆነልሽ ማለት ነው? እኔ ጉዞውን ራሱ ሳስበው ያመኛል" አለ መላኩ መመላለሷ ስለበዛበት።

"አዬ መሌ በኔ ቦታ ብትሆን ይገባህ ነበር። እዚህ እንዳልቀር እዚያ ብዙ የሚበላሽ ነገር አለ። እዚያ ስሆን ደግሞ በቃ ያመኛል። እዚህ አየሩ ራሱ ያጽናናል እኮ። እንጃ መሄድ ባይኖርብኝ እዚህ ብኖርም ደስ ይለኛል። ግን ደግሞ ሲስተሙ ሰዉ እዚህ ነርቭህ ላይ ነው የሚወጣው። ምንም በቃ ርግጠኛ መሆን አትችልም። ንጽሕናው በዚያ ላይ ደግሞ የሰዉ ማነር አሜሪካ ይግደለኝ።" አለች እየተንገፈገፈች፡፡

"መምረጥ ግድ ነው። ሁለት ዛፍ ላይ መውጣት ከፈለግሽ ወይ ዛፎቹን ቆርጠሽ መሰላል መሥራት ነው ወይ ደግሞ አንቺ መሰንጠቅሽ ነው" አለ በሹፈት ደምፅ።

"እኔ ምልህ ሰሊ አልደወለችም ሰሞኑን ምንም? ምንም አዲስ ነገር አልነገረችህም እንዴ?" አለች አንገቷን ወደ እርሱ ዘንበል አርጋ።

"እ እ.. ከአምስት ስድስት ቀን በፊት አውርተን ነበር። በቃ ምን አለችኝ?... ያው የሶለንን ሕይወትና ሥራ በመጽሐፍ ለመጻፍ መረጃ ምናምን እየሰበሰበች እንደሆነ ነው የነገረችኝ ... ሌላ ምንም አላውቅም ... እናንተ ከዚያው የመጣችሁት ንገሩና" አለ እንደ መቀለድም ብሎ፡፡

"አይ ይገርማል። እንግዲህ ያንተን ስሜት ለመጠበቅና ነገሩን ቀስ ብላ ለመግለጽ አስባ ሊሆን ይችላል። ለቤተ ሰቦቿም ለመንገር ያሰበች አልመሰለኝም። ግን ክብሮም በቃ የሚያደርገውን ነው ያሳጣው በጣም ደስ ብሎታል። እሷም ነገሩን አሁን ብዙ እንዳይወጣ እንደፈለገች ነው የነገረችኝ። ላንተ እት ሊስት ፍንጭ ትሰጥሃለች የሚል ግምት ነበረኝ። ነገር ግን ከከፋት የተነጣ አይመስለኝም።" ብላ ላፕቶፗን አውጥታ ኢንተርኔት ለማገናኘት እየሞከረች ዝም አለች።

"ምንድነው የምታወሪው? እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለኝም። ስለዚህ ክብሮም ምናምን ስለምትይውም ልጅ የነገረችኝ ነገር የለም።..." አለ ስሜቱ እየተቀያየረ።

"ያው ስለምታከብርህና አንተን ለመጉዳትም ስለማትፈልግ ሊሆን ይችላል ግን የዛሬ ሁለት ሳምንት ምናምን ገደማ ከክብሮም ጋር የልደቷ ቀን ቀለበት አድርገዋል መሰለኝ" አለች አሁንም በጨረፍታ ፊቱን እያየች።

"ምን? ... ሊሆን አይችልም! ሰሎሜ እንደዚህ ታደርጋለች ብዬ አላምንም። ወሬ ነው...ይ..." ብሎ ከፉ ሳይጨርስ ክብሮም በላከላት ኢሜይል ላይ ያሉትን ፎቶዎች ልታሳየው ጀመረች። መጀመሪያ አብረው ጀልባ ላይ፣ ቀጥሎም የልደት ኬክ ሲቆረስ ከዚያም ተንበርክኮ ሲጠይቃትና ቀለበቱን ሲያደርግላት የተነሡትን ሁሉ አይቶ ሰውነቱ ሳያስበው መንቀጥቀጥ ጀመረ። በመጨረሻም ሲስማት የሚያሳየውን ፎቶ ሲመለከት ተነሥቶ እጁን ፊቱ ላይ አድርጎ ተነስቶ ሄደ።

ምናልባት በሕይወቱ ሙሉ እንደዚህ ዐይነት ንዴትና መከዳት ደርሶበት፣ ሰው የተሜወተበትም ጊዜ ያለ መስሎት አያውቅም። ምን እንደሚያስብም እርግጠኛ አልነበረም። ስንክሳር ተከትላው እየሮጠች "መሌ ይቅርታ እኔ እኮ አንተን ለመረበሽ አይደለም፡፡ ወይኔ እጄን በቆረጠው ዛሬ! በቃ እኔም ፌይር ስላልመሰለኝና አይ ዶኖ ጠርጥረህም ከሆን ብዬ ነው... ይቅርታ ምናልባት ይህን ሁሉ ላንተ ማሳየት አልነበረብኝም። እመነኝ፣ እሷ ግን ላንተ በጣም ነው የምታስበው..." እያለች ግራ የገባት ለመምሰል ስትሞክር፣ "ስሚ ስንክሳር.. ለምንም ይሁን ለምን ይህንን ፎቶ ያሳየሽኝ I really don't care! አንቺም ያው ነሽ እሷም ያው ነች...ሁለታችሁም... ሁላችሁም... ለውጥ የለውም። አሁን ብቻዬን ነው መሆን የምፈልገው። ወደ ቤትሽ በታክሲ መሄድ ትችያለሽ። ፕሊስ አሁን ሌላ ንግግር አልፈልግም። አንቺም እሷም ታስቡልኛላችሁ ... በጣም ነው.የምታስቡልኝ ... ወይ ማሰብ! አንድ ርግጠኛ ነገር ሁላችሁም ያው ናችሁ። በቃ ከፉ አታናግሪኝ አሁን።" ብሎ፡ እጁን እያወናጨፈ ወደ አትክልት ስፍራው ለብቻው ወደ ጓሮው ወጣ። እንደዚህ ሲሆን አይታው ስለማታውቅ እሷም ደንግጣ ተርበተበተች። ምናልባት መጀመሪያ ወሬውን ነግራው ከጥቂት ቀን በኋላ ፎቶውን ብታሳየው ይሻል እንደነበርም አሰበች። በርዶለት እስኪመጣ ሒሳቡን ከፍላ ቁጭ ብላ ጠበቀችው። ከአንድ ሰዓት በኋላ ፈጠን ፈጠን እያለ ወደ መኪናው ሲሄድ እየተከተለች፣ "መሌ መሌ ጠብቀኝ እንጂ" አለች፡፡

"የቀረሽ ነገር አለ? ተኝተው የሚያሳይ ወይም የሰርግ ፎቶ አለሽ?... ፕሊስ አሁን ላናግርሽ አልችልም እኮ ነው የምልሽ... በፈጣሪ ... ብቻዬን ነው መሆን የምፈልገው..." ብሎ ወደ መኪናው ሄደ። በምን ዐይነት ፍጥነት እቤት እንደደረሰም ሳያውቅ ቤቱ ገብቶ ለመተኛት ሞከረ። ሊልሆነም፣ ትኩስ ትኩስ እየተነፈሰ

ተንገራደደ። እሱ ጋ ያለውን የሰሎሜን ፎቶ ሁሉ አውጥቶ ማቃጠል አሰኘው። ማርቆስም፣ ሰሎሜም፣ ስንክሳርም፣ ሶፊያም መፀሃም ደውለው ነበር እንዱንም አላነሣውም፣ እንዲያውም ስልኩን ዘጋው። ሌሊቱን ሙሉ ሲገላበጥ አድሮ ጠዋት ላይ አለቃው ጋ ደውሎ ትንሽ ችግር ስላጋጠመው ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ፈቃድ ጠይቆ ከሥራ ቀረ። ሰውነቱ ሁሉ በጣም ደክሞና አእምሮውም ፈዞ ስለነበር ረፋዱ ላይ እንቅልፍ ወሰደው። ወደ ከሰዓት በኋላ ሲነሣ ቀዝቃዛ ሻወር ወስዶ ከከተማ ለመውጣትና ብቻውን ለመሆን ወሰነ።፣ለወትሮው ገና ሲነካው የሚያዘልለው ቀዝቃዛ ውሃ ምን እንደሆነም ሳያውቀው ታጥቦ የወጣው። ከዚያም የተወሰነ ልብስ ይዞ ወደ ወሊሶ መሥመር ነድቶ ነጋሽ ሎጅ ለሁለት ቀን አልጋ ያዘ። ማን እንደደወለ ማወቁ ስለማይከፋ ብሎ ስልኩን ከፍቶ ድምፁን አጠፋው።

ሁሉንም ነገር በጽናት በጥልቀት ለማሰብ ሞከረ።፣የስሜቱ መጎዳት የማሰብ ችሎታውንም በእጅጉ ቀንሶት ነበር። በሁለተኛው ቀን ቡና ደጋግሞ እየጠጣ አንድ ሐሳብ መጣለት። "በቃ ሰሎሜ የምትባል ሰው የለችም። ከማንም ጋር ስለሷ አላወራም፣ ማንም ምንም እንዲያወራልኝ አልፈቅድም። አለቀ የሚከፈለው ዋጋ ይከፈላል!" አለ በውስጡ። ከዚያም ከውስጡ አንዳች ነገር ቀለል ያለው መሰለው። የሰማውን ነገር ውስጡ ለመጠራጠር ሲሞክርበት ከት ብሎ ሳቀና "እሂ ...ሂ ...ሂ! መሌ ፎቶ ከማየት በላይ ምን መረጃ ያስፈልግሃል? አየህ እኮ ቀለበቱን ኬኩን መሳሳሙን!፣ሌላ ምን ትፈልጋለህ ታዲያ?" አለ ጮክ ብሎ ለራሱ! ከዚያም ብዙ አሳብ አውጥቶ አውርዶ ውሳኔን አጽንቶ ወደ አዲሳባ ተመለሰ።

አዲሳባ እንደገባ መጀመሪያ ስንክሳር ጋ ነበር የደወለው። ሊያገኛት እንደሚፈልግ ነግሮአት ሲገናኙ እያለቀሰች ነበር የሳመችው።

"ይቅርታ መሌ እኔ እኮ ያን ያህል ይጎዳሃል ብዬ አልነበረም። በጣም ይቅርታ ሰሎሜም እኮ ደውላ ነበር። ስልኬን አያነሣም አለችኝ።" አለች ይሄ ንዴቱን ያበርድለት ይመስል።

"አንድ ነገር ስሚኝ። በቀደም ስላሳየሁት የማይገባ ባሕርይ ይቅርታ፣ ከራሴ ውጪ ነበርኩኝ። ከዚህ በኋላ ከኔ ጋር የሚኖርሽን ግንኙነት የሚወስነው አንድ ነገር ነው። ሁሉቱ አልነግርሽም። ይህንን ሕግ ያፈረስሽ ቀን አለቀ የኔና ያንቺ ነገር።" ሲል፣ "ምንድነው?" አለች አላስችል ብሎአት፡፡

"ስለ ሰሎሜ እኔ ፊት ማውራት አይፈቀድም። ለእኔም ሆነ እኔ ባለሁበት ስለሷ ብታወሪ አለቀ! ምርጫው የራስሽ ነው።" አለ፡፡

በጣም በቁጣ ሲያወራ የምሩን እንደሆነ ስላወቀች ዝም አለች። ነገሩን ለመቀየር ብላ፣ "ሶፊያን ለራት ቀጥሬአታለሁ አብረኸን ብትሆን ደስ ይለኛል። ያልከውን ለማድረግ የቻልኩትን ሁሉ አደርጋለሁ። ግን እኮ.." ስትል ካፏ ለቀም አድርጎ፣

"ግን የለም አለቀ በቃ! ያለቀ ነገር ነው።" ብሎ ራት አብሮአቸው ለመሆን ፈቃደኝነቱን ገልጾ ማታ ላይ የተቀጣጠሩበት ፒዛ ቤት እንደሚመጣ ነግሯት ወደ ቤት ሄደ።

እቤት እንደገባ ነበር ሰሞኑን ሁሉ ደጋግሞ ይደውል የነበረው ማርቆስ እንደገና የደወለው። ስልኩን አንሥቶ ደኅንነቱንና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስልኩን እንዳላነሣ ነገረው። ምክንያቱን ሲመጣ ብቻ እንደሚነግረውና ከሦስት ቀን በኋላ ሲመጣም እንደሚቀበለው ተነጋገሩ። የመላኩ ድምፁም አነጋገሩም ስለተቀየረበት ማርቆስ መጨነቁ አልቀረም። የስንክሳርንም መምጣት ስለነገረው የሆነ ወሬ ይዛ መጥታ ይሆናል ብሎ ጠርጥሮአል።

ማርቆስ ቻይና እንደሆነ ያወቀችው ሰሎሜም ስለ መላኩ መጥፋትና አግኝታው እንደሆነ ስንክሳርን ስትጠይቃት፣ አንድ ሁለቴ እንደ ተገናኙ፣ ብዙ ጊዜ ግን ከሶፊያ ጋ ስለሚያሳልፉ የሷንም ስልክ እንደማያነሣ ነገረቻት ቀለል አድርጋ። ማታ ሦስቱም ለእራት እንደሚገናኙ ነገረቻት። ብዙ ስለ ሶፊያ አድንቆ እንደነገራትና አብረውም ደስተኛ እንደሚመስሉ አጫወተቻት። እንዲያውም እሷ የሶለን ገርል ፍሬንድ የነበረች ባትሆን ሰሎሜና ከብሮም፣ መላኩና ሶፊያ ቢጋቡ ሁሉም ደስተኛ እንደሚሆኑ እየሣቀች ስትነግራት የሰሎሜ አንጀት ማረሩ አልቀረም። በመጨረሻ ሰሎሜም፣ "ከቻልሽ ስልኬን እንዲመልስልኝ ንገሪው ለሆነ ጉዳይ በጣም እንደምፈልገው አደራ። እኔም ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ መምጣቴ አይቀርም። ያኔ እንገናኛለን ታንክ ዩ የኔ ቆንጆ አንቺ ባትኖሪኝ ኖሮ ምን ይውጠኝ ነበር?" ብላ ተሰነባብተው ስልኩን ዘጉት።

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት አልመደወሉንም ስልኳንም አለመመለሱ ስላናደዳት አጠር ያለ ኢሜይል እንዲህ ብላ ጻፈችለት፦ *"ሄይ ምንድነው ነገሩ? እኔኮ በጣም ልነግርህ የምፈልገው ጉዳይ ስላለኝና አሁንኑ መነጋገር ስላለብን ነው? እባክህ ስልኩን አንሣው ወይም ደውል። ሰሎሜ" ይላል።*

ሰሎሜ በምትሠራው ጽሑፍ አንጻር የሱን ምክርና እገዛ ፈልጋ ነበር ደጋግማ የምትደውልለት። በተጨማሪም ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሷ በፊት ለጽሑፉ አስፈላጊ የሆነ የሚቀር ነገር ካለ ከመነጋቷ በፊት እንዲነግራት ልትጠይቀው ነበር።

መላኩ ኢሜይሉን ሲያይ ጭራሽ ንዴቱ ጦፈ። ስንክሳር የነገረችውን በስልክ ልታስረዳው ነው የመሰለው። እሱም ባጭሩ፣ "ሄይ ምንም ጠቃሚ ነገር አይታየኝም። በጣም ሥራ ስለሚበዛብኝና ለወሬ ጊዜ ስለሌለኝ ባታስቸግሪኝ ደስ ይለኛል" የሚል መልስ ጻፈላት። ነገሩ ሰሎሜን ነዘራት። ስንክሳር ጋ ደውላ ነገሩን ስትነግራት እሷም የመላኩ ባሕርይ ስለተለዋወጠባት ግራ እንደገባት ነገረቻት።

ሰሎሜ በራዕ ንዴትና ብስጭት ውስጥ ገብታ ግራ ግብት አላት። ሶፊያንም በጣም ሳትጠላት አልቀረችም። የሷም ቂጣና ንዴት እየየለ መምጣቱ አልቀረም። ከነዘኑ ጋር ስንከሳር የምትነግራት ተደማምሮ እሷም መላኩን ማየትም ማግኘትም አስጠላት። ግን ደግሞ ኢትዮጵያ ስትሄድ ምንድነው የምታደርገው? ያሰበችው ሁሉ የተናደባት ስለመሰላት እንደገና ግራ መጋባት ውስጥ ገባች።

ማርቆስ ከመጣ በኋላ መላኩ ልክ እንዳልሆነ ገብቶታል። ከሶፊያም ጋር አውርቶ ያገኘው ፍንጭ አልነበረም። ሰሎሜ ደግሞ ኢሜይሉንም ስልኩንም አልመለሰችለትም። ከመላኩ ጋር ስለ ሰሎሜ ለማውራት ቢሞክር መላኩ አሻፈረኝ አለ። ጭራሽ ስለሷ ማውራት እንደማይፈልግና ማርቆስ ስለሷ ማውራቱን የሚቀጥል ከሆነ ጓደኝነታቸውን እንደሚጎዳና ላያገኘውም እንደሚችል ቁርጥ አድርጎ ነገረው። መላኩ ያለውን ከመፈጸም እንደማይመለስ ያወቀው ማርቆስም ሐሳቡን ለጊዜው ተወት አደረገው። ይሁን እንጂ አሁንም ሰሎሜን አግኝቶ ማናገር ስላልቻለ ነገሩ ሊገባው አልቻለም። መላኩ እነሶስናን ማየቱን እንደበፊቱ በየቀኑም ባይሆን አልተወም። የሰሎሜ መምጫም አሥራ አምስት ቀን ስለቀረው ሽር ጉድ ማለት ጀምረዋል። መላኩም የምትመጣበትን ቀን ስላወቀ ያንን ሳምንት እንዳለ አባቱን ፍሊጋ ወደ አፋር የሚሄድበት ጊዜ አድርጎ መኪና ኪራይንና ከመሥሪያ ቤቱ ፈቃዱን ሁሉ አስተካክሎአል። ዐይኗንም ማየት አልፈለገም። ማርቆስም መላኩን እንዴት እንደሚረዳው ገብቶታል።

የሰው አእምሮ በውሸትና በተጣመመ መረጃ ላይ እንደሚበላሽ በምንም አይበላሽም። በተለይም ውሸትን ሥራዬ ብለው በራስ ወዳድነት ስሜት የሚረጩ ሰዎች በሌሎች ልብና አእምሮ ውስጥ እሾህና አሜኬላን ይዘራሉ። ስንት ጥሩ ሰዎች በክፉና በስግብግብ ውሸተኞች ኑሯቸው ፈርሷል። ትዳራቸው ተበትኗል! ስንት ሥልጣኔዎችንና አገሮችን ከጥቅም ውጪ አድርገዋል። ኢየሌ ጨቅላዎች በውሸት በተመረዘ ንግግር እንጭጭ አእምሮአቸው ከንቱ ሆኖ ቀርቷል። ዓለምን በአንደኛነት ያጠፋው ክፉ ሰዎች የዘሩት ውሸት ነው። የሰው ውድቀት የጀመረውም በውሸት ነው። እውነትን በትዕግሥትና በሰከነ ልቦና እንደ መልካም ዘር ካልፈለግናትና ካልተንከባከብናት ውሸት እንደ አረም ከክፉ ሰዎች የልብ ዕርሻ ላይ እየተዛመተ መልካም ልቦችን ማጥፋቱና መውረሱ አይቀርም። 'እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል' የሚለው የትልቁ መጽሐፍ ቃል እንዴት ያለ እውነት ነው? በዓለም ላይ ከሁሉ አስከፊው እስር ቤት የሰው አእምሮ ባመነጨው ውሸት ሲጠፈርና በዚያ ቀንበር ውስጥ ሲኖር ነው። እውነተኛ ነጻነት የኅሊና ነጻነት ነው። የኅሊና ነጻነት ደግሞ እውነትን በማወቅና በመኖር ነጻ ከወጣ አእምሮ ብቻ የሚገኝ ጸጋ ነው።

የብዙ አእምሮዎች መቆለፍና መዛግ መንሥኤው ባንድም በሌላም መንገድ ወደ ውስጣቸው የገባው ውሸትና ነጻ የሚያወጣቸውን እውነት

አለማወቃቸው የፈጠረው ገደል ነው። ከእውነት በፊትም ሆነ በላይ ለአእምሮ ጤንነትና ነጻነት ምን መድኀኒት ይገኛል? እውነትን ማወቅ ነጻ ቢያወጣም፣ እውነት ዋጋዋ እጅግ ውድ የሆነ መድኀኒት ናት።

መተሳለፍ

ምንም እንኳ ውስጡ ያለው ቁስል አሁንም ትኩስ ቢሆንም፣ መላኩ ሥራውን መሥራትና ማኅበራዊ ሕይወቱን በከፊል ማስተካከል ችሎአል። ውስጡን እያብሰለሰለ ያስቸገረውን ስሜት ለማርገብ የተሻለ መንገድ ነው ብሎ ያሰበው ዘመዶቹ ላይ ማተኮር ነው። ለረጅም ጊዜ ነገ ነገ እያለ ጊዜ ሲጠብቅለት የነበረውን አባቱን የመፈለጉንም ጉዳይ አሁን ለማድረግ ወስኗል። ከውስጡ ሊያወጣው ያልቻለውን የሰሎሜን ጉዳይ ትንሽ እንደሚያስረሳው ተስፋ ሳያደርግ አልቀረም። ጠንካራ ለመሆን ቢሞክርም ለነገሮች ያለው ቀና አተያይ ሳይደበዝዝበት አልቀረም። ስለ ሰው ያለውን እምነቱን ሁሉ ነው ያዛባበት።

ብዙ ጊዜ መሥሪያ ቤታቸው የሥልጠና ዕድል ሲመጣ ለመሄድ ፈቃደኛ ስላልሆነ፣ አብረውት የሚሠሩት ሁሉ ይገርማቸዋል። እዚሁ በመኖር ከሚገኘው የተሻለ ሥልጠና የትም አላገኝም እያለ ይቀልዳል። ልዩነቱ አበሉ ብቻ ነው ብሎም አብዛኛው ሰው ሥልጠና የሚሄድበትን ዋና ምክንያትም በቀልድ መልክ ጣል ሳያደርግ አያልፍም። ባለፈው ሰሞን አለቃው እሱ ቢሄድ እንደሚመርጥ የነገረው የሁለት ወር ሥልጠና ነበር። መላኩ እያመነታ ነበር፤ ምክንያቱም እሱ ሲሄድ የሰሎሜ መምጫ ሊሆን ስለሚችል መሄዱን ፈጽሞ አልፈለገውም። ሥልጠናው በቀላሉ ሊገኝ የማይችል ሲሆን ይዘቱም መላኩ ሁል ጊዜ ብዙ መሥራት በሚፈልግበት ጉዳይ ላይ ነው። ቦታውም ሉዊቭል ኬንታኪይ የሚባል ከተማ አሜሪካ ውስጥ ነው። መጀመሪያ ላይ ፎዚያን እንዲልኳት ለአለቃው ሊነግረው አስቦ ነበር። አሁን ግን ሰሎሜ ስትመጣ ከአካባቢው መሄዱን እንደ በረከት ነው ያየው። ስለዚህም ለሥልጠናው ለመሄድ መፈለጉን ለአለቃው ሊነግረው አስቧል። ነገሩን ለማርቆስ በመንገርም ሆነ ባለመንገር ላይ እያመነታ ነው። ቢነግረው ማርቆስ እንደማይስማማ ያውቃል፤ ባይነግረው ደግሞ በጣም ያዝንበታል።

ማርቆስ ለስንክሳር ያለውን ስሜት ስለሚያውቅ ወደ መቂ ሊያደርጉት ባለው ጉዞ ላይ አብራቸው ለመሄድ ብትጠይቀውም አልፈቀደላትም። በየመሃሉ የምትሰጣቸው አስተያየቶችና ብዙም ማረፍ የማይችለው አፏ እሱንም ቢሆን ያደክመዋል። ማርቆስና ሶፊያ የሚያወሩት ደስ ይለዋል፤ ዝም ማለትም ስለሚችሉ

ዘና ያደርገዋል። በተለይ ሶፊያ ተጫዋችና ቁምነገረኛ የሆነች፣ የሰውን ስሜት በቀላሉ የምትረዳ ከመሆኗም በላይ፣ የአርት ተሰጥኦዋም ሊሆን ይችላል ትንንሽ ነገሮችንም የማድነቅና ሰውንም የመረዳት ችሎታ አላት። ከማርቆስ ጋር መቀራረባቸውም መላኩን ደስ ብሎታል። ዐርብ ቀን በጊዜ ከሥራ ወጥቶ መኪናውን ማርቆስ ቤት ካቆመ በኋላ ከዱባይ የገዛቸውን ልብሶችና አንዳንድ ስጦታዎች ወደ ማርቆስ መኪና አሻገሩ።

ከዛም ሶስና በጣም ስለናፈቀችው ትናንትም ደውላ ስላለቀሰችበት ትምህርት ቤቷ በር ላይ ሄደው ጠበቋት። ደስታዋ ወሰን አልነበረውም። መላኩን አቅፋ አልለቅም ብላ ስታለቅስበት ጊዜ የሱም ልብ ውሃ ሆነ። ለሶስና መላኩና ሰሎሜ አንድ ናቸው። በልቧም ሁለቱን እናትና አባቷ አድርጋ ሳትቆጥራቸው አትቀርም። ስለተፈጠረው ውዥንብር ምንም የማያውቀው ንጹሕ ልቧ እንዳይመረዝና እንዳይሰበር ፈራ። ብዙ አባብሎአትና ከመቂ ሲመለስ ሽርሽር እንደሚወስዳት ቃል ገብቶ ነው የለቀቀችው። 'ስለ ሰሎሜ ማውራት አይፈቀድም' የሚለው የመላኩ ሕግ ሶስና ጋ ሊሠራ አይችልም። መላኩም ማርቆስ እስኪገርመው ድረስ ነበር ከሶስና ጋር ስለ ሰሎሜ መምጣትና ስትመጣ ስለሚያደርጉት ነገር ስታወራው እየሣቀ ያወራት። ሁሉም እንደሕፃን የዋህና ንጹሕ ቢሆን ይህች ዓለም ምንኛ ውብ በሆነች ነበር። ሶስናን እቤት አድርሰው ሲወጡ፣ "አጅሬው እና እኛም ፀጩ መሆን አለብን ስለ እሚቴ እንደፈለገን ለማውራት ወይስ ምንድነው ምስጢሩ?" አለ ትከሻውን መታ እያደረገና መኪናውን እያበረ፡፡

"ማርከዬ ምን ላድርግ? እዩት ንጽሕናዋን ፍቅሯን። ልቤን ነው እኮ የሸንቆጠረችው። አይ ዶኖ ... ምን ማድረግ እንደሚቻል... እሱ ይርዳኝ... ምንም ማድረግ አይቻልም... ሕይወት ሚጥሚጣ የበዛባት ብጫቂ እንጀራ ናት አንዳንዴ ..." አለ መስኮቱን እየከፈተ፡፡

"ይቺ ደግሞ አዲስ ተረትና ምሳሌያዊ ፍልስፍና ናት? ባልጠፋ እንጀራ ወይ እንጀራውን መጨመር ነው አለበለዚያም ሚጥሚጣውን ማሳነስ... ግን እኔ ምልህ ዛሬስ ትንሽ ማውራት እንችላለን... ማለቴ እንደሶሲ ... በናትህ መሌ.." ብሎ ውስጡ የተከማቸውን ጥያቄ ለማፈንዳት ሲያቆበቁብ..

"ማርክ ... ይገባኛል ምን ያህል እንደምትጨነቅና እንደምታስብልኝ። ግን በቃ አሁንም ጊዜ ስጠኝ። ለጊዜው አሁን ደኅና ነኝ። ለማውራት ግን ዝግጁ አይደለሁም። ያመኛል። ደግሞ ምንም የሚለወጥ ነገር የለም። ራስ ምታት ብቻ ነው ትርፉ። ለወሬ የሚመች ነገር አለ እኮ..." አለ ስሜቱ እየተለዋወጠና ሳያስበው እጁን እያወናጨፈ።

"መሌ እኔ እኮ ስለ ምን እንደምታወራ አልገባኝም። ልክ እኔም አንተም ስለምናውቀው ነገር የምታወራ ነው የምትመስለው። ምን የሆንከው ነገር አለ?

ማለቴ አንተና ሰሎሜ ሰላም አይደላችሁም? ያለችህ ነገር አለ? ዝም ብለህ እኮ ነው ሁሉንም ነገር የጠረቃቀምከው።" አለ ግራ ግብት ብሎት፡፡

"ማርክ አንደኛ ነገር ነገሩን ማውራት ፈጽሞ አልፈልግም። ሁለተኛ ነገር ምንም ሊደረግ የሚችል ነገር የለም። በተጨማሪም ምንም እንዲደረግ አልፈልግም ከሁን በኋላ።" አለ አሁንም ነገሩን እየዘጋጋበት።

"ስማ እንጂ የኔ እኮ ጥያቄ ስለምኑ ነው የምታወራው? ልትነግረኝ ትችላለህ ምን እንደተፈጠረ? ተነጋግራችሁ ነው ወይስ ምንድነው? እኔ እኮ ፈጽሞ ግራ ነው ያጋባኸኝ።" አለ አሁንም አንዴ መላኩን፣ አንዴ ከፊቱ ያለውን በፍጥነት መሥመሩን እየቀያየረ ሰዉን ሁሉ ለመቅደም የሚሞክረውን መኪና በጥንቃቄ እያየ።

"የውልህ ማርክ ለምን ቀናችንን እናበላሸዋለን ምንም ለውጥ ለማያመጣ ነገር። እንኳን ሳወራው ሳስበውም ነው ጨጓራዬ የሚላጠው። ይልቁን እሱን እንተወውና የሆነ ነገር ልንገርህ። ግን እንዳይደብርህ ወይም ከዚህ ጋር አታያይዘው።" አለ ርእሱንም ለመቀየር ቢችል ተስፋ እያደረገ፡፡

"ገብቶኛል ሐሳቡን ለመቀየር እንደሆነ። እሺ ደግሞ ምን ተገኘ?"

"ትዝ ይልሃል ባለፈው አንድ ሥልጠና መሥሪያ ቤት መጥቶ አለቃዬ እኔ እንድሄድ እንደሚፈልግ ነግሬህ ነበር። ሥልጠናውን ብፈልገውም ለሁለት ወር አሜሪካ መሄዱን ብዙም አልፈለግሁትም ነበር። አሁን ግን ሥልጠናው ከሚያመልጠኝ ልወስደው እያሰብኩ ነው። ደግሞም ትንሽ ዕረፍትም ይሆንልኛል። ከሁሉም ነገር ራቅ ብሎ ማሰብ ሳያስፈልገኝ አይቀርም።" አለ የማርቆስን መልስ ለመስማት እየጓጓ።

" ምን...? አንተ ልጅ አብደሃል እንዴ? አይ ኖው ሥልጠናውን ትፈልገው እንደነበር፣ ግን አሁን ሳስበው ለሥልጠናው ብለህ ሳይሆን ሽሽት ነው የሚመስለው። ስማ አንተ እኮ ብትሸሽ ነገሩን ይዘኸው ነው የምትሄደው። ቆይ ለምን አታስረዳኝም ይሄንን ሁሉ የዕቅድ ለውጥ እንድታረግ የገፋፋህ ምንድነው?.. አባትህን ፍሊጋ እሄዳለሁ ያልከውንስ ተውከው ማለት ነው? ደግሞስ ሰሊ በሚቀጥለው ሳምንት አይደል እንዴ የምትመጣው? ለመሆኑ ከሄድክ መቼ ነው የምትሄደው?" ብሎ ግራ በገባው ፊት የጥያቄ ናዳውን አወረደው።

"አይ ከሆነም ከሁለት ሦስት ሳምንት በኋላ ነው የምሄደው። ከዚያ በፊት አፍር መሄዴ አይቀርም። አክስቴዋሊ በሚቀጥለው ሳምንት ነው ወደ አፍር ለመሄድ ያሰብኩት።" ብሎ የሰሎሜን የመምጣት ጉዳይ ዐውቆ ዘለለው።

"እኬይ እኬይ ... ግን ቆይ በሚቀጥለው ሳምንት እሷ ስትመጣ ...

አታገኛትም ማለት ነው?...ይቺን ብቻ መልስልኝ" አለ አሁንም ሲፈራ ሲቸር...፡፡

"ማርክ እንዳልኩህ አፍር መሄዴ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ነው። ከመሄዴ በፊት አፍር መሄድ ካለብኝ፣ ያለኝ የተሻለ ጊዜ ያ ብቻ ነው። እንደ ጨረስኩ እመጣለሁ። ሌላው ነገር ላይ ብዙም መጨነቅ አልፈልግም።" አለ ፊቱን በእጁ እያሻሸ፡፡

"ምን ... እንዴ? አንተ ልጅ በጤናህ ነው?... እሺ የሆንከውን ነገር ልትነግረኝ ፈቃደኛ አይደለህም ማለት ነው? እሺ ደግሞ ከማን ጋር ነው አፍር የምትሄደው? ማለቴ ሄደህስ ማንን ነው የምታገኘው?... ዝም ተብሎ ይኬዳል እንዴ?" አለ አሁንም ነገሩ ግራ ገብቶት።

"ማርክ የምችለውን ያህል ሪሰርች ለማድረግ ሞክሬያለሁ። አንድ ጓደኛዬ እዚያ ረጅም ጊዜ የሠራ አንድ ሰው በስልክ አስተዋውቆኛል። ደግሞ መቂስ ያው ዝም ብዬ ሄጄ አይደል የናቴን ዘመዶች ያገኘሁት። ከሆነ ይሆናል፣ ካልሆነም አለቀ በቃ! ያባቴን አገር አይቼ እመለሳለሁ ወይም ለሌላ ጉዞ የሚያስፈልገኝን መረጃ ይዤ እመጣለሁ።" አለ ትክሻውን በግዴለሽነት እየሰበቀ፣ ልቡ ግን እርገጠኛ ባልሆነ ስሜት እየተሰበቀ እንደሆነ እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው።

" መቂና አፍር ይለያያል መሰለኝ። በርግጥ ልክ ነህ አለ አይደል የሆነ ቦታ መጀመር አለብህ። እኔ አብረን ብንሄድ ደስ ይለኝ ነበር። ብቻህን መሄዱን ብዙም አልወደድኩትም። መኪና ምንድነው ያሰብከው?" አለ አሁንም ፊቱ ላይ መጨነቅ እየተነበበበት። መላኩም ማርቆስን ሳያማክር ማድረጉ ትንሽ እየጸጸተው፡፡

"በሹፌር ተከራይቼ ነው ለመሄድ ያሰብኩት። ለመንዳት አላሰብኩም። ተለቅ ያለ ደኅና መኪና ኤሲ ያለው ሳያስፈልገኝ አይቀርም።" አለ፡፡

"ለምን የኔን አዲሱን ላንድ ክሩዘር አትወስድም? ምንም መጨነቅ አይኖርብህም፣ የቆየኸውን ያህል መቆየት ትችላለህ። ሐሳብህን ከቀየርክ እኔም ሹፌር ልሆንህ እችላለሁ። ብቻህንም መሆኑ የሚሻል ከመሰለህ፣ ያጎቴ ሹፌር አሉ ያንን መሥመር በደንብ ያውቁታል እሳቸውን ላመቻችልህ እችላለሁ" ብሎ መልሱን መጠበቅ ጀመረ። መኪና ተከራይቼያለሁ ማለቱ የማርቆስን ስሜት ምን ያህል ሊጎዳው እንደሚችልና አብረው ቢሄዱም የሰሎሜን ጉዳይ ማንሣቱ የማይቀር ስለመሰለው፡፡

"እ ምም ... ጥሩ ነው። ማርክዬ ብቻዬን መሆኑን በጣም ነው የፈለግሁት። ብዙ ማሰብና መወሰን ያለብኝ ጉዳይ አለ። አብረን መሆናችን በጣም የተሻለ እንደሚሆን አውቃለሁ። ግን አንተም ብዙ ሥራ አለብህ፣ እዚህ ብትሆን ደግሞ የተሻለ ሊሆን ይችላል ለሁሉም። ግዴለህም ብቻዬን ልሂድ፣ እም ም... ሾፌሩን ማግኘት ከተቻለ አሪፍ ነው።" አለ ሊከራይ የተስማማበትን መኪና መተዉ የተሻለ

እንደሆነ በማሰብ።

“አይ ለኔ ምንም ችግር የለውም። ግን አንተ የሚመችህን አድርግ። ሐሳብህን ከለወጥከም አንዳንድ ነገሮችን እንዳስተካክል ንገረኝ። ታዲያ መቼ ነው መሄድ ያሰብከው?” አለ አሁንም የመላኩ ነገር እያሳሰበው ያሰበውንም ማስለወጥ እንደማይቻል ስለሚያውቅ፡፡

“ማክሰኞ የፊታችን። በሳምንት ጊዜ ውስጥ ነው ለመመለስ ያሰብኩት።” አለ ፊቱን ቅጭም እንዳደረገ፡፡

“ግን .. እርብ እኮ ነው ሰሎሜ የምትገባው... አታውቅም ወይስ? አስበው ወንድሟን እኮ ነው ያጣችው። እኔ ግን አይታየኝም ይሄ ሁሉ ድራማ ከየት የመጣ እንደሆነ። እኔና አንተ ከዚህ ያለፍን ይመስለኝ ነበር። እና ምንም ልትነግረኝ ፈቃደኛ አይደለህም?” ብሎ ማዘኑን በሚያሳውቅ ድምፅ ለመጨረሻ ጊዜ ጠየቀው፡፡

“ማርኮ... ተነጋግረን እኮ። ገብቶኛል ለማለት የፈለግኸው። በቃ ይሄ የኔ የግል ውሳኔ ነው። ትንሽ ነገሮች ሲረጋጉና የኔም ጭንቅላት ሲጠራልኝ ሁሉንም እናወራለን። ፕሊስ ይሄንን እንተወው አሁን። የውልህ ካወራሁህ ወደማልፈልገው ነገር ውስጥ ታስገባኛለህ። ፕሊስ ጊዜ ስጠኝ። ልነግርህ ስለማልፈልግ ሳይሆን ስለማልችል ነው። በቃ ዝግጁ ስሆን ራሴ እነግርሃለሁ። ሶፊያም ያቻትና በሩ ላይ እየጠበቀችን ነው መሰል ሳናረፍድባት አልቀረንም።” አለ ርእሱን ለመሸሸ እየሞከረና መድረሻቸው ደስ እያለው።

“እሺ ይሁን። ... የሚገርም ነው ... እኔ ግን ምንም አልተዋጠልኝም... ለማንኛውም አሁን እንተወው... እ... አንድ ዐሥራ አምስት ደቂቃ ሳናረፍድባት አልቀረንም...” ብሎ መኪናውን እሷ አጠገብ አቁመው ወረዱ። የሷን ሻንጣ ከኋላ እየከተቱና ሰላም እየተባባሉ ምንም እንዳልሆነ ሁሉ መሣሣቅ ጀመሩ። መላኩ እሷን ከፊት አስገብቶ ከኋላ ለመቀመጥ ሲሞክር ሶፊያም እሱን ከፊት ካልተቀመጥክ ብላ በትግል ነው እሺ ያለችው። ግሪክነቷም ይሁን ከበሻ ጋር መኖሯ ብዙ ነገሯ እንዳበሻም ያደርጋታል።

ሰዓቱ ወደ ዐሥር ሰዓት ግድም ስለነበር በደብረ ዘይት መሥመር መውጣቱን ብዙም ስላልወደዱት፣ በዚያውም አገር ለማየት ብለው በቡታጅራ መሥመር በዝዋይ አድርገው ነው ለመሄድ ያሰቡት። ሁሌም በመልክአ ምድር የምትመሰጠው ሶፊያ በጉራጌ አገር ገጠሩን አቆራርጠው ሲያልፉ ነፍስም አልቀረላት። አንድ አንድ ቦታ እያቆሙ ፎቶ ሲነሡና ስታነሣ ነበር። በተለይ ፀሓይ ልትጠልቅ ስትል የነበሩበት ቦታ ደስ የሚል ነበር። ከብቶቹን እየነዱ ወደ ቤታቸው ሲያስገቡ አዳፋ ልብስ የለበሱ ልበ ንጹሓን ሕፃናትን ስታይ የራሷ ልጅነት ትዝ

ብሏት ሳታስበው እንባዋ ኩልል ብሎ ፈሰሰ። አንዳንዶቹ ሕፃናት እየተከተሏቸው እጃቸውን ሲያውለበልቡላቸው ፊታቸው ላይ ያለውን የዋህነትና የልጅነት የተስፋ ጨረር እያየች በዚህ ንጹሕነታቸው ቢቆዩ ዓለም እንዴት ውብ ትሆን ነበር ብላ አሰበች።

ትንሽ እንደሄዱ ደግሞ ሁለት የሚጣሉ ትልልቅ ሴቶችን አይተው መኪናውን ቆም አደረጉ። መሰዳደባቸው ወደ ድብድብ ሲቀየር፣ መኪናውን አቁመው ሊያገላግሉዋቸው ሞከሩ። ፀጉራቸውን ሲናጩ ሻሻቸው መሬት ወድቆ እነመላኩ በማይገባቸው ቋንቋ ድምፃቸውን አውጥተው ይመላለሱ ነበር። ምልልሳቸው ስድብ ይባላል። ስድብ ደግሞ የማይታይ መርዘኛ ዱላ ነው። አጥንትን ሳይሆን ልብን የሚሰብር። በሃኪም ሳይሆን በእውነተኛ ይቅርታ ብቻ የሚፈወስ። ቃል የሰበረውን ቤት ይቁጠረው ከማለት ልቡ ይቁጠረው ማለቱ ይቀላል።

በኋላም ከአካባቢው ለመጡ ሌሎች ትላልቅ ሰዎች ጉዳዩን አስረክበው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ትንሽ ጉራጊኛ የሚችለው ማርቆስ ነገሩን ጠይቆ እንደተረዳው፣ ሴቶቹ የተጣሉት ያንደኛዋ ልጅ የሌላዋን ያለአግባብ ደብድቦታል በሚለው ምክንያት በተነሣ አታካሮ ነበር። ልጆቹ ቢጣሉም በማግስቱ አብረው ይጫወታሉ፣ አብረው አቧራ ይበትናሉ፣ ውሃ ይራጫሉ። ትልልቆቹ ግን ምናልባት ዕድሜ ልካቸውንም ተኳርፈውና ተጣልተው ይቀሩ ይሆናል። የልጅ ጥልና የልጅ ይቅርታ እንዴት ውብ ነው። አስታራቂና ፍርድ ቤት የማያስፈልገው። እንዴት ይሆን ስናድግ ወደ ቂምና ይቅር አለማለት ደረጃ የምንዘቅጠው፣ ዳኛና ፍርድ ቤት፣ እስር ቤትና ፖሊስ እስኪያስፈልገን እንዲህ የምንከፋው? አዋቂ ከመሆን ልጅ መሆን ማወቅ ሳይሆን አይቀርም።

ከዚህ በኋላ ግን ፀሓይዋም የቀኑ ጉድ የሰለቻት ይመስል የመጨረሻዋን ስንብት አድርጋ እስከ ነገ ወደሌላው ዓለም አዘነበለች። እዚያም ላሉ ሰዎች ታስፈልጋቸዋለችና። ቢዋደዱም ቢጣሉም፣ ቢጫወቱም ቢቆዝሙም፣ ቢሠሩም ቢሰንፉም እሷ እንደሆነ ሙቀቷንና ብርሃንዋን በአዳም ዘሮችና በሄዋን ልጆች ላይ መልቀቋን አታቆምም። ገና የጉዞአቸውን ሩብ እንኳን ሳይጨርሱ ያዩትና የተጫወቱት ነገር ቃል ከሚገልጸው በላይ ብልጹግ ነበር። የሶፊያ እንባ ልውጣ ልውጣ ማለቱ ይህንን ምንም ዐይነት ሽራና መድረክ የማይችለውን ሕያው የሆነ ያምላክ ኪነ ጥበብ በነጻ ውስጡ ገብታ ማየቷ ብቻ ሳይሆን፣ ሶለን ቢኖርና አብረው ቢሆኑ ምን ሊመስል እንደሚችል ማሰብ ማቆምም ስላልቻለች ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ መላኩ ዐይነት ጥሩና አስደናቂ ጭንቅላት ካለውና እንደ ማርቆስ ዐይነት ደግና እውነተኛ ሰው ጋር ባጭር ጊዜ ጓደኛ ሆና ራሷን ማግኘቷን እንደ ትልቅ በረከት ነው የቆጠረችው። ሶለን ሞቶ ሳይሆን ሁለት ሆኖ ወደ ሕይወቷ እንደገና የመጣ በሚመስል [illegible] ሐሳቧና ስሜት ስትዋጥ ከገባችበት የሐሳብ

ባሕር ውስጥ ባንነች። ነገር ግን አዲስ የተሰፋ ፍንጣቂ ውስጧን የያዘውን የነዘን ጨለማ ስርስሮ እየገባ ነበር።

አብዛኞቹ የማርቆስ እናት ዘመዶች የቡታጅራ ሰዎች ናቸው። ብዙ ዘመዶቹ ነጋዴዎች ሆነው የተሳካ ኑሮ እዚሁ ቡታጅራ ነው የሚኖሩት። ካሰቡት በላይ ስለመሸባቸው እዚሁ ብናድር ብሎ ማርቆስ ሐሳብ ሲያቀርብ፥ "አጅሬው በዚህ በኩል ያመጣኸኝ እናትህ አገር ልታሳድረኝ ነው እንዴ ለካ?" አለ መላኩ እየቀለደ።

"ኦ ይገርማል እዚህ ነው የናትህ የትውልድ አገር?" አለች ሶፊያም በጣም ደስታና ግርምት እየታየባት።

"አዎን የዚህ አገር ሰው ናት እናቴ። እም ...ላንጋኖ ገብቶ ለማደር ይመሻል፣ ይደክመናልም። እና መዐዚም ያው ነገ ጠዋት ስለሆነ የሚጠብቁን ምን ይመስላችኋል? እዚህ ጥሩ ሆቴሎች አሉ፣ ከፈለጋችሁም አያቴ ቤት ማደር እንችላለን። የጉራጌ ክትፎ በግሩም ቆሎ ሁሌም ዝግጁ ነው።" አለ ውሳኔውን ለነሱ በመተው፡፡

"እንደሱ በጉቦ ያዘን እንጂ። አይ የቀልዴን ነው። አሪፍ ነው። ሶፊ ምን ይመስልሻል? ሆቴል ይዘን ባይሆን ነገ ጠዋት ሰላም ብለናቸው ማለፉ አይሻልም? ለነሱም የድንገት እንግዳ ከምንሆን ለኛም ትንሽ ብናርፍ ጥሩ መሰለኝ" አለ መላኩ ከኋላው ወንበር መሃል ላይ ተቀምጦና አንገቱን በመካከላቸው አሾልኮ በተራ በተራ እያያቸው።

"አዎን ጥሩ ሐሳብ ይመስለኛል። እናንተ የምትሉት ሁሉ ይስማማኛል።" አለች ሶፊያም። ከሽሮ ቀጥሎ በጣም የምትወደው ምግብ ክትፎ ሲሆን ጥሬ ክትፎ በተጠበሰ ቆሎ ደግሞ እምቢ ማለት አትችልም። ለብዙ ጊዜ እምቢ ትል የነበረውንም ቁርጥ ሶለን በብዙ ውትወታ አስለምዷት አንድ ቁጥር ቆራጭ ሆናለች። የክትፎ ምንጭ ወደ ሆነው አገር ነው የመጣነው ሲሏት በደስታ ተምነሸነሸች። የቆሎንም አሠራር ለማየት ጓጉታለች። ራታቸውን በልተው ከተማው ውስጥ ትንሽ ወዲያ ወዲህ ብለው እግራቸውን አፍታቱ። ከዛም ቁጭ ብለው ብዙ ነገሮችን ሲያወሩ አመሹ። ሶፊያ በሄደችበት ሁሉ ያበሾች ቁንጅና ያስገርማታል። ኢትዮጵያን የሞዴሎች አገር ነው የምትላት። አንድ የጀመረችው ግድግዳ የሚሞላ ትልቅ ሥዕል አለ፣ የተለያየ ዐይነት ውበት ያላቸው የኢትዮጵያ ሴቶችና ሕፃናት ሥዕል ሲሆን የያዘው ርእስም የሞዴሎች ምድር (The Land of Models) ነው የሚለው። ምናልባትም ከዓመት በላይ ይወስድባት ይሆናል።

ጠዋት ተነሥተው ወደ ማርቆስ አያት ቤት ሄደው መለስተኛ ድግስ የሚመስል ቁርስ ተዘጋጅቶላቸው ስለነበር አረፋፍደው ነበር መውጣት የቻሉት። የማርቆስ አያቶች ማርቆስ የመጨረሻ ልጅ ቢሆንም፣ የቤተ ሰቡ መካሪና ቁምነገረኛ

ስለሆነ በጣም ነው የሚወዱት። በተለይ ሴት አያቱ አዲሳባ ሲመጡ ማርቆስ ጋ ነው ማረፍ የሚወዱት። ልጅ ሆኖም ብዙ ጊዜ ክረምቱን የሚያሳልፈው ቡታጅራ ነበር። እንደ አብዛኛው ጉራጌ ከዝቅተኛ ኑሮ ተነሥተው ነው አሁን ያሉበት ደረጃ የደረሱት። አሁን በቡታጅራ አካባቢ አሉ ከሚባሉ ትልልቅ ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው። ለልጆቻቸውም ያወረሱት ትልቁ ነገር ሀብት አይደለም። ያወረሱዋቸው ነገር ሀብት የሚያገኙበትን የእችላለሁን አስተሳሰብና ሥራን ሁሉ የማክበርን የስኬት ቁልፍ ነው። ልጆቻቸውም ሆኑ የልጅ ልጆቻቸው የገንዘብን ጥቅምና ዋጋ በሕፃንነታቸው ነው እንዲረዱ የሚያደረጉት።

የልጅነት ትምህርት ጥቅሙ አንድም ለመማር ያለው ቅለት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ አንዴ ከተማሩት የማይጠፋ የሕይወት ዘመን ማኅተም መሆኑም ነው። ለዚህ ነው 'ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከርሱ ፈቀቅ አይልም፣' የሚለው የጠቢቡ ቃል እውነትነቱ ዘላለማዊ የሆነው። ለምሳሌ ቋንቋ በልጅነት ስንማረው አይከብድም፣ የምላስ እጥፋት (accent) እንኳን አይኖረንም። ካደግን በኋላ ግን መማሩም መከራ ነው፣ የምላስ እጥፋቱም ጠፍቶም አይጠፋም። የጉራጌ ልጆችም በልጅነታቸው የሚማሩት የገንዘብና የንግድ መርህ ቢዝነስን እንደ ልጅነት ቋንቋቸው እንዲያቀላጥፉት ሳይጠቅማቸው አልቀረም። የሊስትሮ ስራ ደግሞ ባሬ አንቱ የተባሉ ብዙ የጉራጌ ሃብታሞች የገንዘብን ቋንቋ አፍ የፈቱበትና አቀላጥፈው መናገር የቻሉበት የመጀመሪያው ድንቅ የቢዝነስና ፋይናንስ ትምህርት ቤታቸው ነው።

ሌላው ሰው በጉራጌ ገንዘብ መውደድ ቢያሾፍም ቢቀልድም ጉራጌ ግን የተማቶ መሥራትና የስኬት ተምሳሌት የሆነ ያገራችን ዕንቁ ሕዝብ መሆኑን ማንም አይክድም። የነማርቆስ ቤተሰብ ሥራንና ስኬትን ብቻ ሳይሆን፣ መስጠትንም ከልጅነታቸው ስለሚማሩ ከሥራ እንጂ ከገንዘብ ጋር የተጣበቀ ልብ የላቸውም። የማርቆስ ወንድሞች የሚጠቀሙት አቋራጭና የተጭበረበረ መንገድ አያታቸው ፈጽሞ የሚጸየፉት ሲሆን፣ ነገሩን ቢያውቁት ርግማናቸውን እንደሚናገሩባቸው ጥርጥርም የለውም። ሁሌም የማርቆስ ወንድ አያት የሚሉት 'አቋራጭ ሥራውንም ሠሪውንም ቆርጦ የሚጥል ገደላማ መንገድ ነው። አቋራጭ የቆረጠውን አምላክም አይቀጥለው።' ነው። እውነትም ስንቱ ባቋራጭ ሲያቋርጥ ካሰበው ህልም ተቆራርጦ ቀርቷል።

መቂ ሲገቡ ስድስት ሰዓት አካባቢ ነበር። መጀመሪያ ሲመጣ ያጋጠመውን ነገር እየነገራቸው ስለነበር፣ ማርቆስም ሶፊያም በቀለ ሞላ ለመቆምና ካሉ ወይዘሮ ብሬቱን ለማግኘት ቋምጠዋል። በቀለ ሞላ ሲቆሙ ሊያስተናግዳቸው የመጣው ዕድሜው አርባ አካባቢ የሆነ ወንድ አስተናጋጅ ነበር። ከማዘዛቸው በፊት መላኩ ተጣድፎ፣ "ትየ ብሬቱ አልገቡም እንዴ ዛሬ?" ብሎ ሲጠይቅ፣ "አሁን እዚህ ነበሩ ወደ ውስጥ ገብተው ይሆናል፡፡እጠራላችኋለሁ እልክዜያ ምን ልዘዝላችሁ?" አለ አሁንም

እውነተኛ ፈገግታውን እየቸራቸው። ሶፊያ ኢትዮጵያን ከምትወድበት አንዱ ምክንያት የሰው ብሩህና ንጹሕ ፈገግታ ነው። ሁሉም ማኪያቶ አዘዙ። ብዙም ሳይቆይ ወይዘሮ ብሪቱ ብቅ ሲሉ መላኩን አይተው ልጃቸውን ያገኙ ያህል፤ "ውይ ውይ የኔ አንበሳ የኔ መላክ እንደምነህ" ብለው አንቅ አርገው ሳሙትና ማርቆስንና ሶፊያንም አስተዋወቃቸው። ሶፊያን፣ "የኔ ቀውላላ እንዴት ታምሪያለሽ፣ ካይን ይሰውርሽ ማን አልሽኝ ስምሽን?" አሉ አበሻ ነው የመሰለቻቸው። መላኩ ቀበል አድርጎ፣ "ትየ ብሪቱ እሷ አሜሪካዊት ስለ ሆነች አማርኛ ብዙም አትችል። ስሟ ሶፊያ ይባላል። የኛ ጓደኛ ናት።" አለ መላኩ ለሶፊያ ያሉትን ደግሞ ማርቆስ እየተረጐመላት። ሶፊያም ነገሩ ቢገባትም ወይዘሮ ብሪቱ ሲያወሩ ፈጣን ስለሆኑ ትንሽ ቸግሮአት ነበር ለመከታተል። በወይዘሮ ብሪቱ ደግ አስተያየትና እናታዊ ፊት ሳትመሰጥ አልቀረችም። እሷን ተንጠራርተውም ቢሆን ዕቅፍ አድርገው።

"ሃው አር ዩ? ዌል ካም ማይ ገርል።" አሉ ያለቻቸውን እንግሊዝኛ አሰባስበው በማዝመት። እሷም ያላትን አማርኛ እንደ ምንም አስተባብራ፡፡

"እ.ማማ በታም አመሰግናለ። ትሩ ሲትዮ ናቹ። አንገት ላይ ያለ ታቱ በታም ደስ ይላል" አለች። እጇን እንደያዙ ሣቃቸውን ለቀቁትና፡፡

"አይ የኔ ልጅ የኔ አፍ ቁርጥ ይበልልሽ፣ አፏ ሲኮላተፍ ሲያምር። ውይ ካይን ይሰውርሽ። አንገት ላይ ያለችው ንቅሳቴን ነው?" አሉ ወደ መላኩ ዞረው። ሁሉም እየሣቁ አዎን ብለው የበለጠውን አንገታቸውን ገልጠው አሳዩዋት። አሁን ያሉትን ግን መተርጐሙ ከባድ ስለነበር ሙሉ በሙሉ የተረጐመላት አልነበረም። 'አፌ ቁርጥ ይበልልሽ' እና 'ካይን ይሰውርሽ' በእንግሊዝኛ እውነትም ለመተርጐም ሳይከብድ አይቀርም። ከዚያም አብረው ፎቶ ተነሡ። ከመኪና ውስጥ መላኩ ያመጣላቸውን ቆንጆ ብርድልብስና ሌሎች ልብሶች ሲሰጣቸው ደስታቸው ልክ አልነበረውም። አቅፈው ስመው ስመው ሊጨርሱት ነበር።

"ድሮም ቢሆን የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል። እሷ እመቤቱ ታስብልህ እንዲህ የሞቀ ትዳር የምታስብ ልዕልት የሆነችዋን ይስጥህ።" አሉ ሲመርቁት። አፋቸውን እንደምንም ይዘውት እንጂ ሶፊያን ይስጥህ ቢሉም ደስታውን አይችሉትም ነበር። ከዚያም ማታ ለእራት ወይዘሮ አሰለፈች እንደጠሯቸውና እንደሚመጡም ነግረዋቸው፣ እነመላኩም ለጊዜው ተሰናብተዋቸው ወደ አክስቱ ቤት አቀኑ። የኔንም ቤት ታያላችሁ ብለዋቸው ተስማምተዋል። ፊታቸው የመንገድ ባውዛ መስሎ እያበራ ነው የሸኙዋቸው። ሶፊያም ወይዘሮ ብሪቱን ከልቧ ነው ያፈቀረቻቸው። ልትሥላቸውም ቋምጣለች።

ገና ሰፈር ገብተው ቤቱ ጋ ሲደርሱ ነው ልጆቹ በሰማይ ላይ እንደተዘሩ ከዋክብት ከበዋቸው የጨረቃነት ስሜት የፈጠሩባቸው። በተንጣለለው ጠቆር ያለ

አስፋልት ምድር ላይ። ካሳሁን ከየት መጣ ሳይባል መላኩ ላይ፣ ቀጥሎም ማርቆስ ላይ ተጠምጥሞ የማያልቅ ወሬውን ጀመረ። ሌሎቹም ልጆች ልክ በሌለው ደስታ ነው የተቀበሉዋቸው። መኪናውን እየዞሩ መንጫጫታቸውን ቀጠሉ። ግቢውን ቀይረውታል። አጥሩ በደንብ ታጥሮአል፣ ትልቁ ቤትም ታድሶ ሌላ ቤት ነው የሚመስለው። የበረንዳውም ሊሾ ተስተካክሎ ያምራል። ውስጡ ያለው ዕቃ ተቀይሮ፣ ግድግዳው ቀለም ተቀብቶ የተሰቀሉት ፎቶዎች ፍሬማቸው ተለውጦ በቃ ሌላ ቤት ይመስላል።

በአጥሩ ዙርያ ችግኝ ለመትከያ ይመስላል ጉድጓዶች ተቆፍረዋል። ያሉትም አትክልቶች ዙሪያቸው ተኮትኩቶ ወደ አረንጓዴነት እየተቀየሩ ነው። ከጓሮ የተጀመረ ሰርቪስ ቤትም ይታያል። ሁሉም ልጆች አዋቂዎቹም ጽድት ብለው ደኅና ልብስ ነው የለበሱት። ከጥቂት ወራት በፊት ሲመጣ የነበረው ቤተሰብም አይመስልም። ከሁሉ በላይ ግን በሁሉም ላይ የሚታየው በራስ የመተማመንና የተስፋ ኃይል በቀላሉ ይጋባል። አክስቱን፣ ያክስቱን ልጆች ሁሉ ሰላም እያለ እነማርቆስን አስተዋወቃቸው።፡እንደሁሌውም ሶፊያ አበሻ እየመሰለቻቸው ባማርኛ ነው የሚያወሩዋት። እንግሊዝኛ ተናጋሪ መሆኗንና ትንሽ አማርኛ ብቻ መቻሏን ሲያውቁ ሰበሰበ ይላሉ። ያላትን ሞቅ ያለ ሰብእናና የደስደስ አይተው ግን ርቀውም አይርቋት።

መዐዛ መላኩንም ማርቆስንም ተጠምጥማ ሰላም ብላ ሶፊያን ተዋውቃ፣ እሷንም እቅፍ አድርጋ ነው ሰላም ያለቻት። ሶፊያ የቤቱ ዕቡጥ ሙቀትና ፍቅር አይታ የፍቅር ጥምቀት እንደወሰደች ተሰማት። መላኩ ከጥቂት ወራት በፊት ያገኛቸው ዘመዶቹ አይመስሉም። እቤት ሲገቡ ቡና ፈልቶ ስለነበር ወዲያው ምሳ ቀርቦ ጨዋታው ደራ። ምሳ ላይ ቤተ ሰቡ ብቻ ሲሆን ያለው ለእራት ግን አንዳንድ ሰዎችን ጠርተው ነበር። የበሉት ምሳ ግሩም ነበር። ከምሳና ከቡና በኋላ መዐዛ ግቢውን እያዞረች የጀመሯቸውን ለውጦች ሁሉ አሳየቻቸው። ሰርቪስ ቤቱ ሦስት ትልልቅ ክፍል ያለው ሲሆን፣ አንድ ለጀመሩት ሥራ ማከናወኛ የሚሆን ማብሰያና ማዘጋጃ ክፍል፣ ሁለተኛው የልጆች የጥናት ክፍል ሦስተኛው ደግሞ ሲያልቅ ለሁለት ተከፍሎ የልጆቹ መኝታ ክፍል እንዲሆን ማሰቧን ነገረቻቸው።

ከሰዓት በኋላም ወጥተው የጀመረችውን የፍራፍሬ ቤትና ካፌ አሳየቻቸው። በሰው እጅ ነው። ወደፊት ጁስ ቤትና የተሻለ ምግብ ቤት ሊያደርገው እንደምታስብና ሌሎቹንም ቢዝነሶችን ለመክፈት እንደሚያስበ ነገረቻቸው። ባካባቢው ላሉ ሥጋ ቤቶችና ምግብ ቤቶችም እንጀራ ማቅረቡ እያደገ እንዳለና እስከ አምስት ምጣዶችን ገዝታ ሥራውን ለማስፋት፣ ዳቦም ለማቅረብ እንዳሰበች ነገረቻቸው። በአበባ እርሻዎችም ላይ ካፌዎችን ለመክፈት ስምምነቱን ጨርሳ ዕቅዱን ለማስፈጸም በቅርብ ፕሮጀክቱን እየሠራች እንደሆነና ባንክም ለብድር ተስፋ እንደሰጡዋት ገለጸችላቸው። መላኩ መዐዛ ከሚያስበው በላይ

ቀድማው እንደሄደች ገባው። በምትችላት ትንሽ እንግሊዝኛም ቢሆን ሶፊያን ሳትፈራ አዋራቻት። ይሄ የብዙ አበሻ ችግር ሲሆን መዐዛ ግን ቋንቋን መግባቢያ ብቻ እንደሆነ በማሰብ በማውራትም ስለሚያድግ ማውራቱ አያስጨንቀኝም አለቻቸው። በራሷ መተማመን ስለምትችል በፍጥነት ማደጓ እንደማይቀር ያስታውቃል።

ወደ ማታ ላይ ወደ ቤት ሲመለሱ መላኩ ከዱባይ፣ ማርቆስ ደግሞ ከቻይና ያመጣላቸውን ስጦታ ሲቀበሉ የተፈጠረውን ደስታ እዚያ በመኖር ብቻ ነው ማወቅ የሚቻለው። እክስቱ የህይወታቸው ሕይወት እንደገና የታደሰ ይመስሉ ነበር። ዘለቃና ሠናይት እምብዛም ስለማያወሩ መላኩ ከሁለቱም ጋር ጠጋ ብሎ እየተቀመጠ ነበር ያጫወታቸው። እነሱም ደስተኞች ነበሩ። ከአርባምንጭ በሌሊት የተነሣው የካሳሁን አባት፣ የመዐዛ ወንድምም ከሰዓት ላይ የጫነውን ፍራፍሬ ይዞ ደረሰ። ጊዜ እየመሸ ስለነበር መላኩ መዐዛን ወደ ውጪ ጠርቶ፣ "መዐዚ እኛም ሦስት ስለ ሆንን ማደሪያ ሊያንስ ስለሚችል በቀለ ሞላ ብንይዝ አይሻልም?" አለ እሺ እንደማትለው ቢያውቅም፡፡

"ኧረ መሊ ... አንድ ቀን ናት እዚሁ ነው የምታድሩት። ለሶፊያ አንድ መኝታ ቤት አለ የተዘጋጀ። አንተና ማርክ እማዬ መኝታ ቤት በቃ ሌላው እንደሚሆን ይሆናል። እማዬም ታዝናለች። ደግሞ ዋናው እኮ አንድ ቤት ማደሩ ላይ ነው በረከቱ ... በሚቀጥለው ስትመጡ አንዳንድ መኝታ ቤት ነው" ብላ በማቋ አሰፋችው የቤቱን ጥበት፡፡

"እኛማ ደስ ነው የሚለን። ርግጠኛ ነኝ ሶፊያም ደስ ነው የሚላት።" አለ ትከሻውን በደስታ እየሰበቀ።

"አይዞህ የረገበ አልጋና የለሊት ተፋላሚዎች ሁሉ ጠፍተዋል..." ብላ አሁንም የትኋኖቹና የሽቦው አልጋ ጉዳይ እንዳያስጨንቀው በማቅ አጅባ ነገረችው። እሱም ማቂን መቆጣጠር እያቃተው፡፡

"አንቺ ልጂ ጉደኛ ነሽ። በናትሽ እነዚያ ጫጩቶችስ ስንቱ አደጉ?" አለ ድመቷ የመነተፈቻት ጫጩት ትዝ እያለችው፡፡

"እም ... ከዚያ በኋላ እምስቱን እኗ በላቻቸው፣ የሆኑ በሽታም ገብቶ ነበር መሰለኝ። ብቻ ሦስት ናቸው የተረፉት" አለች ፈገግ ብላ። ጫጩቱ ብቻ ሳይሆን ልጆችም እኮ በዚህም በዚያም እንዲሁ ነው ረግፈው የሚያልቁት የሚለውን ሐሳብ እያውጠነጠነ ተያይዘው ወደ ውስጥ ገቡ። ማታውም በጣም ጥሩ ነበር። ሶፊያም ለብቻዋ ሳይሆን በመዐዛና በዘለቃ ልጆች ተከባ ነው አልጋውን ሞልተው አብረዋት ያደሩት። በሷ አማርኛና በነሱ እንግሊዝኛ ሲግግቱ ነው ግማሹን ሌሊት የጨረሱት። በሕይወቷ እንደዚህ የተደሰተችባቸው ቀኖች ጥቂት ናቸው። ጥዋትም

ወይዘሮ ብሪቱ ቤት ቁርስ በልተው፣ ቡና ጠጥተው፣ ሶፊያም የፈለገችውን ያህል ፎቶ እንሥታቸው ተለያዩ።

በመጨረሻም ምሳ በልተው ወደ ስምንት ሰዓት ላይ ወደ አዲሳባ ጉዞ ጀመሩ። የደብረ ዘይት መንገድ በተለይ እሑድ ከሰዓት ከሞጆ እስከ አቃቂ አሰልቺ ነው። አደጋም ይበዛዋል። ስንክሳር ደጋግማ ብትደውልም መላኩ ስልኩን ለማንሣት አልፈለገም። ይህም ሳያናድዳት አልቀረም። ሰሎሜ ቅዳሜ ማታ ደውላላት ስለነበር መላኩ ሶፊያን ከቤተ ሰቦቹ ጋር ሊያስተዋውቃት፣ ማርቆስንም ይዞ መቂ እንዳሉ ነግራት ነበር።

*　　　　*　　　　*

ሰሎሜ ስትደውልላት ውስጧ በንዴት የበገነው ስንክሳር ነገሩን ከሆነው በላይ አጋናና የራሷን ፈጠራ ጨማምራ ነበር የነገረቻት።

"እኔ እኮ የማውቀውም መላኩ አልመሰለኝም። ሶፊያም ከሱ ጋ ስትሆን የማላውቃት ትሆንብኛለች። ለማንኛውም ያንችንም መምጣት ስነግረው እምብዛም ግድ አልሰጠውም መሰለኝ።" አለች ስንክሳር ንዴቷንም ለመወጣት፣ ሐሳቧንም ለማሳካት።

"በናትሽ ስንኪ ስለ መላኩና ስለ ሶፊያ አለማውራት እንችላለን። ልቤ ይበጠበጣል። እኔ አሁን ሌላ ብዙ ነገር አለ የሚያሳስበኝ። ከዚህ ደውዬ አለቃዬንም አናግሬያት መቀሌ አዲስ ፕሮጀክት እየከፈቱ ስለሆነ ለሦስት ወር እንድሠራላቸው ተስማምተናል። አዲሳባ ሆኜ ስለነሱ በማሰብ መበጥበጥ አልፈልግም። ከሦስት ወር በኋላ ደግሞ እግዜር ያውቃል። ማሰብም ነው የሚያስጠላኝ። እሮብ እንደምመጣ ያውቃሉ እንዴ?" አለች በሚንገፈገፍ ድምፅ "የሶፊን አላቅም መላኩ ግን ሳያውቅ ይቀራል ብለሽ ነው? እሱ ካወቀ ደግሞ እሷም ታውቃለች። ግን ርግጠኛ አይደለሁም። እነማሚ እንዴት ናቸው? መቼም መምጣትሽ ሳይደብራቸው አይቀርም።" አለች እሷም ስለነመላኩ ማውራት የሰለቻት በሚመስል ድምፅ፡፡

"ደኅና ናቸው፣ ምን ይሆናሉ ብለሽ ነው። በጣም ነው በተለይ ባቢ የደበረው። ግን ደግሞ የምመጣበትን ምክንያት ስላመኑበት ምንም ማድረግ አይቻልም።" አለች ሰሎሜ፡፡

"እኔ ምልሽ ከብሮምንስ አናገርሽው ወይስ በዚያው ጠፍቶ ቀረ? ደውሎ ያውቃል? እነማሚስ ምንም አላሉም እንዴ?" አለች ርእሱን እየቀየረች፡፡

"እኔንጃ ባክሽ ምናቃለሁ ብለሽ ነው? አንድ ሁለቴ አውርተን ነበር መሰለኝ። እቤት ግን እንደ ድሮው ስለማይመጣ እነማሚም ያው ነገሩን ለማርገብ

ሞክረው ነበር፣ እኔ ግን ዝርዝር ውስጥ ለመግባት አልፈለግሁም። ያው ጊዜውን ጠብቆ ይፈታል ሁሉም። አሁን ጠቃሚ ነገሮች ላይ ነው ማተኮር የምፈልገው" አለች ስልችትና ዝግ ባለ ድምፅ። ከዚያም የስልኩ ካርድ ስላለቀ ተዘጋ። ስለሚያም መልሳ አልደወለችም።

እንመላኩ ደስ የሚል ጊዜ አሳልፈው ነበር አዲሳባ የገቡት። መቂ ያሳለፉት ጊዜ ውስጡ የተሸከመውን የስሜት ሕምም ሁሉ እንደ ጥሩ ማስታገሻ ጸጥ አርጎለት ነበር። አዲሳባ ሲገባ ግን በሽታው ያገረሽበታል። የመዐዛና የቤተ ሰቡ ለውጥ ማርቆስንም አስገርሞታል። ማርቆስና ሶፊያ ልጆቹን ይዘው ከከተማ ውጭ ለሽርሽር ሲሄዱ፣ መላኩና መዐዛም እዚያችው ባለቀሰችባት የበቀለ ሞላ ወንበር ላይ የመዐዛን ትልልቅ ህልሞች እየማቁ እያወሩ ነበር የጠበቁዋቸው። ቆይቶም ከመዐዛ ተሰናብተው ጉዞአቸውን ጀመሩ። አዲሳባ ደርሰው ሶፊያን ቤቷ ካደረሷት በኋላ ወደ ቤት ሲሄዱ ማርቆስ ለንመዐዛ ያሰበውን ለመላኩ አጫወተው፡፡

"እኔ ከአእምሮዬ በላይ ነው የሆነብኝ የንመዐዚ ለውጥ። አንተ እንኳን ከነገርከኝ ተነሥቼ ምን ያህል ለውጥ እንዳለ ደግሞም ወዴት እንደሚሄዱ ይታየኛል። ይሄ በጣም ክሪቲካል ጊዜ ነው። በባንክ ብድር ውስጥ ከምትገባ እኔ ጋ በቂ ገንዘብ አለ የተወሰነ ብር ላበድራት እችላለሁ። ደግሞ ያክስቴ ልጅ ባለፈው ወር ወደ ውጪ ስትሄድ የዘጋችው የጁስ ቤት ዕቃ ተዘግቶበት ነው ያለው። እንዲያውም ሁሉንም እኔ እገዛውና መቂ ወስደን እሷ ትሰራበታለች። ከገንዘቡም እሱ ይሻላል። ምናልባትም መቂ ካሉት የተሻለ ካፌ መክፈት ትችላለች። ርግጠኛ ነኝ ከዚ የተሻለ ዕቃውን የሚጠቀምበት አይገኝም።" አለ መዐዛ በፍጥነት ከፍተኛ ደረጃ እንደምትደርስ ከልቡ በማመን። መዐዛም ምንም ነገር ለማድረግ ስታስብ ማርቆስን ማማከር ልማዷ ሆኖአል። መላኩን በተለይ ከቢዝነስ አኳያ ማስጨነቅ አትወድም። ምንም ስትለው እሱ ወጪውን ካልረዳሁሽ እያለ ስለሚያስቸግራት። እሷ ደግሞ ከገንዘብ ይልቅ የሐሳብ ምክር ነው የምትፈልገው። ከመላኩ ይልቅ ደግሞ ማርቆስ ልምዱም ስላለው የሚሰጣት ምክር በጣም እየጠቀማት ነው። ማርቆስን በመላኩ ዐይን ስለምታየውና እሱም ተሳክቶላት ማየት ስለሚፈልግ ጥሩ ተግባብተዋል።

መላኩ ሐሳቡ ጥሩ እንደሆነና ግን ለሱ በጣም ትልቅ ወጪ እንደሚሆንበት በማሰብ ሲነግረው፣ "ትቀልዳለህ እንዴ መሌ? እሷ እኮ ወጣች ማለት ይዛ የምትወጣውን ሰው ብዛት አስበው። እኔ የሚታየኝ ወደፊት በጣም ብዙ መቶ ሰዎች ቀጥራ ማሠራት እንደምትችል ነው። ደግሞ ይሄ ብቻ ሳይሆን በጣም ብዙ ሺህ የሷና የነሱ ቤት ሰብ ዐይነት ቤተሰቦችንም ከድህነት የመውጫውን መንገድ ለማሳያ እሷ እኮ ሰርቶ ማሳያ ናት። እኔ ገንዘቤን እንኳን ያንተ እኅት ሆና ይቅርና እንደሷ ዐይነት ማንም ላይ ባወጣ አይቆጨኝም። ለእኔ እኮ የዚህ ስኬት ተሳታፊ መሆኔ ራሱ ትልቅ ክብር ነው" አለ አሁንም ስሜቱ እንደጋለ።

"ሙሉ በሙሉ ነው የምስማማው ሮክፌለር ማርክ" አለ ፈገግ ብሎ በሹፌት መልክ።

"ፈላስፋው በቃ እርሶም የደከሙ ይመስላሉ። ለነገሩ እርሶ ጭንቅላቶትን ወጥሮ የያዞት አባዜ እስኪለቅዎ ምንም ማድረግ አይቻልም። እኔ ምለው የምር ከነገ ወዲያ ወደ አፋር ለመሄድ ወስነሃል ማለት ነው?" አለው አሁንም እንዳላመነ ያህል።

"አዎን ማርክ ... አሁን እንኳ ወጣ ስላልን ልቤ ቀለል ብሎታል። ሂጄ እስኪ እኔም የተፈጠርኩባትንና የሰው ዘር ሁሉ ምንጭ የሆነችውን የሉሲንና የአቶ ሃሰንን ሃገር ልበርብር። ማን ያውቃል ወይ አቶ ሃሰንን ወይ ራሴን አግኝቼ እመጣለሁ።" አለ ዘና ብሎ፡፡

"መጥፋትህንም ማመንህ አንድ ነገር ነው? ... ይሁና እንግዲህ። በቃ እኔም መኪናውንና ሾፌሩን አዘጋጅልህና ነገ እዚሁ አድረህ በፈለግኸው ሰዓት መነሣት ትችላለህ። ዛሬ እኔም ብራዘር ጋ ነው ለማደር ያሰብኩት ሚስቱ ትንሽ አሚታል መሰል። ደክሞሃል እንጂ አንተም ብትመጣ ጥሩ ነበር" አለው።

"ኡ ... አይደል ደግሞ እስኪ ለመዘጋጀትም ለማንኛውም እቤት መሄድ ሳይኖርብኝ አይቀርም። ከቻልኩም እነሶሲን አይቼ ብሄድ ደስ ይለኛል" አለ። ከዚያም መኪናውን ይዞ መጀመሪያ እነሶስና ጋ ደረስ ሊል ቢሄድ ቤቱ ተዘግቶ አገኘው። ስለሚ አክስት ጋ ሄደው ይሆናል ብሎ ብዙም ሳይጨነቅ ወደ ቤቱ ሄደ። መጨረሻም ቤቱ ገብቶ ሻወር ወስዶ ፒጃማውን ቀያይሮ ሰንከሳር ጋ ሲደውል ስልኩን አላነሣችም። በጣም ደክሞት ስለነበር ወዲያው ነው እንቅልፍ የወሰደው። ጥዋት ቢሮ እንደገባ አለቃውን ከሁለት ሳምንት በኋላ አሜሪካ የሚጀምረውን ሥልጠና ለመካፈል እንደወሰነ ነገረው። አለቃው በመገረምም በመደሰትም ሃሳቡን ተቀበለው። መላኩ የሚያገኘውን ሥልጠናም ይሁን ዕድል ካመነበት ብቻ እንደሚጠቀም ያውቃል። ብዙ ጊዜ የሥልጠናና የስብሰባ ዕድሎችን ጠቃሚ ካልመሰሉት ያሳልፋቸዋል። የጉዞና የምዝገባ ሂደቱን ወዲያው እንዲጀምርም አብሮ ነገረው። አፋር የሚሄድበትንም ምክንያት ስለነገረው መልካም ዕድል ተመኝቶለት በጊዜ የወጣው። ለአለቃው ወይም ለፎዚያ ካልሆነ ከሌሎች የመሥሪያ ቤት ባልደረቦቹ ከማንም ጋር ብዙ የግል ምስጥሩን አያወራም። ፎዚያ ደግሞ የድሬዳዋውን ፕሮጀክት ለማገዝ ሰሞኑን እዚያው ናት።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ላይ የአፋር ጉዞውን ጀመረ። ሾፌሩ በዕድሜ ጠና ያሉ ሲሆኑ መላኩን ሲያናግሩት እየተሽቆጠቆጡ ነው። ብዙ ጊዜ ከኤምባሲ ኀላፊዎችና ከቱሪስቶች ጋር ሠርተዋል፣ በአፋር መሥመርም የተወሰነ ጊዜ ሄደው ያውቃሉ። ለቁርስ እንደለመደው ደብረ ዘይት ፒራሚድ ሆቴል ቆሙ። እኔ በልቻለሁ ብለው ቁርስ አልበላም ስላሉት፣ ግዴለም ቡና ይጠጡ ብሎ አብረው

ከተቀመጡ በኋላ፡ የጉዞውን ደንብ ግልጽ ማድረግ እንዳለበት ዐሰበ። እሳቸውም እንዳይሳቀቁ እሱም እንዳይጨነቅ።

"አቶ ደምለው አሁን እርሰዎ ሽርሽር ላይ እንዳሉ ያስቡ። ዘና ይበሉ። ለርሰዎ ዕረፍት እንዲሆን ነው የምፈልገው። ማንኛውንም ወጪ የምሸፍነው እኔ ነኝ። እም ም... ምግብም አብረን ብንበላ ደስ ይለኛል። ግን የራሶትን ጊዜ ከፈለጉና አረፍ ማለት ሲያሰኞት ነጻነት ይሰማዎት። ብዙ ባይከብዶት ደስ ይለኛል።" አለ ትንሽ ፈገግ ብሎ፡፡

ውስጣቸው ደስ እያለው "እሺ. ኧረ ልጄ ... አመሰግናለሁ። አመሰግናለሁ አሉ።" አሁንም ከመቀመጫቸው ብድግ እያሉ። ልማድ እኮ መቼም አይለቅም።

ምሳ አዋሽ ለመብላት ስላሰቡ ብዙም ጭንቅንቅ ያልበዛበትን መንገድ ላስ አድርገው ወደ ቀኑ ስድስት ሰዓት ተኩል አዋሽ ፓርክ መግቢያ ደረሱ። ወደ መግቢያው ከመዞራቸው በፊት ምሳ ከተማ ይሻላል ወይስ ሎጁ ውስጥ ብንበላ የሚለውን ለመወሰን ትንሽ ቆም ብለው ተነጋገሩ። ሎጁን በዛውም አይተውት ለማደርም የሚሻል ከሆነ እዚያው ለማደር ካልሆነም አዋሽ ሰባት ለማደር ወስነው ወደ ውስጥ ለመግባት ተስማሙ። ፓርኩ መግቢያ ላይ አንድ የአካባቢው ተወላጅ የሆነ ጥቂት አማርኛ የሚችል ሬንጀር የለበሰ ጠብመንጃ የታጠቀ የፓርክ ጠባቂ ብቻ ነበር ያገኙት። የሎጁን አቅጣጫ ከጠየቁት በኋላ ቲኬት ለመቁረጥ እንዲጠብቁ ነግሮአቸው ሰው ሊጠራላቸው ሄደ።

"ፓርኩን ለመጐብኘት ከፈለግህ ጥበቃዎቹን ይዘን መሄድ ይኖርብናል። ምክንያቱም እንደ አስጐብኚም ሆነው የሚሠሩት እነሱ ናቸው አካባቢውንም በደንብ ነው የሚያውቁት" አሉ አቶ ደምለው መኪናውን ከማስነሣታቸው በፊት።

"እ...ም እስኪ ገብተን እንየውና ምሳችንን እዛው በልተን እንወስናለን። አሁን በዚህ በጠራራ ፀሐይ ምንም ሊታይ የሚችል ነገር ያለ አይመስልም። እራዊቱም ቢሆን አሁን ውጪ ላይኖሩ ይችላሉ።" አለ መላኩ መጀመሪያ ሎጁን ለማየት ጓጉቶ።

ፀሐዩ ከርር ያለ ነው። እጅግም ነፋስ አለመኖሩ ደግሞ ሙቀቱን አብሶታል። አንድ ዐሥር ኪሎ ሜትር አካባቢ ወደ ውስጥ በጫካው መሃል ነድተው አዋሽ ፓርክ ሎጅ ደረሱ። መንገዱ ጥርጊያ ቢሆንም ለመንዳት ያን ያህል አያስቸግርም። ጊዜው ከሰአት በኋላ ስለሆነም ሊሆን ይችላል ምንም ዐይነት የዱር እንስሳት ሳይዩ ነበር ሎጁ ጋ የደረሱት።

መላኩ ግመሎችና ሌሎች የቤት እንስሳት ፓርኩ ዉስጥ ተመስገው ሲያይ "እኔ ምለው ጫካው ውስጥ የዱርና የቤት እንሰሳት አንድ ላይ ተደባልቀው ነው እንዴ የሚኖሩት?" አለ ነገሩ አስገርሞትም አደናግሮትም።

"አሁን አሁን ይሄው ድርቁና የግጦሽ ሳር እጦቱ እየተደራረበ ሲመጣ እንሰሶቹን እዚሁ ይለቋቸዋል። በዛ ላይ በከረዩዎቹና በአፋሮቹም መካከል የይገባኛል ጥያቄም አለ አሉ። ግን በቃ እንደምታየው የቤት እንስሳቱ እዚህ ሲለቀቁ አራዊቱ ይሸሻሉ። ይህም አገር አቋርጦ የሚመጣውን ቱሪስት እንዴት መሰለህ የሚያበሳጭ።" አሉ የሚያውቁት ርእስ በመሆኑ ገለጻቸውን በድፍረት በመስጠት።

"አልፈርድባቸውም። እኔም ብሆን አንበሳ ለማየት መጥቼ ፍየል፣ ከርከሮም እያለሁ ብዬ የከሳ ላም ባይ በጣም ነው የምናደደው። በዛ ላይ ለጫካውም ቢሆን ጥሩ አይመስለኝም።" አለ በግራና በቀኝ ያሉትን ከብቶች እያየ።

"ምን እሱ ብቻ የባስ የሚያበሳጭ ስንት ነገር አለ መሰለህ።" አሉ ከግቢው ስለደረሱ መኪናውን ወደ ጥላ አካባቢ እያቆሙ።

መላኩም ከመኪናው ወርዶ ኮፍያውን እያደረገ 'ምን?' በሚል አይን ሲያዩቸው.

"ያው ሁሊም ግጭት አይጠፋም። ታዲያ አንዳንዴ ባንዱ ንዴት አንዱ ጫካውን በእሳት ያጋየዋል። ይህም የአራዊቶቹን መኖርያ እያመናመነው ነው።" አሉና ተከታትለው እያወሩ ወደ ሎጁ አቀኑ።

የሎጁ አቀማመጥ በአዋሽ ፏፏቴ አፋፍ ላይ በመሆኑ የፏፏቴው ድምፅና ያካባቢው እንጻራዊ ልምላሜ ሸው ከሚለው ለሰስ ያለ ነፋስ ጋር ደስ የሚል ስሜት ይፈጥራል። የሎጁ አሠራር ባህላዊ ውበትን የተላበሰ ነው። በዋናው ምግብ ቤት ውስጥ እንደ ደርብ ወደ ላይ ተወጥቶ ፏፏቴውን በቀላሉ የሚያሳይና ያካባቢውን ሙቀት ቀነስ የሚያደርግ ከፍት የሆነ ክፍል አለው። ጥቂት ወጣት ቱሪስቶች እየተማማቁ ሲዝናኑ ተመለከተ። በሙቀቱም ምክንያት ጥቂቶቹ ከወገብ በላይ ልብሳቸውን አውልቀውታል። መላኩና ሾፌሩም ከወደ ጥግ ተቀምጠው ምሳቸውን በሉ። ወቅቱ የዝናብ ስላልሆነ ፏፏቴው ደከም ያለ ሲሆን ብዙም መደፍረስ አይታይበትም። ከምሳ በኋላ ወደታች ወርደው ማደሪያ ክፍሎቹን አዩ። አቶ ደምለው ብዙም የተመሰጡ አይመስሉም፣ በተለይ ዋጋውን ሲሰሙ በድንጋጤ ወደ መላኩ ጠጋ ብለው፣ "ኧረ ምነው ልጄ እዚህ በረሐ ውስጥ ለማደር ይህን ያህል ብር መክስክስ። ፈረንጆቹስ ያው እንዴ አብደዋል። አዋሽ ሰባት ስንት ጥሩ ሆቴል አለ መሰለህ፣ አሁን ይሄ ምኑ ነው እንዲህ ያስወደደው?" አሉ ለአንድ ቀን አዳር የሚከፈለው ገንዘብ አልዋጥልህ ብሏቸው።

"አይደል ... እስኪ ሌሎቹንም ክፍል እንያቸውና እንወስናለን።" ብሎአቸው ወደ አስተናጋጁ ቀረብ ብሎ "ቅናሽ የለውም እንዴ?" ብሎ ጠየቀው።

"ያው ዐሥር ፐርሰንት ቅናሽ አደርግላችኋለሁ። አሁን ጥላው በረድ ሲል በጣም ነው አካባቢው የሚያምረው።" አለ አስተናጋጁ ሊያግባባው እየሞከረ።

"እስኪ ሌሎቹንም ክፍሎች አሳየኝና እንወስናለን።" አለ መላኩ ከክፍሉ

እየወጡ፡፡

ወደ ታች ወርደው ከአፋፉ ላይ ካሉ ትንንሽ ጎጆዎች ባንዱ ውስጥ ተቀምጠው፣ ቡናና ድንች ጥብስ አዘው ፏፏቴውን ማየት ጀመሩ፡ አቶ ደምለውም ራቅ ብለው ሲጋራቸውን ማክሰል ጀምረዋል። ከሰሉ እየበነነ የሚጠፋ ዐመድ ሆነ እንጂ። መላኩም ዞር ዞር እያለ ፎቶዎችን ማንሣትና ከፍ ያለ ቦታ ቆሞ ዙሪያ ገባውን መቃኘቱን ቀጠለ። በመጨረሻም ያለውን አማራጭ ተነጋገሩና ከተማ ሄደው ማደር ወሰኑ።

የጉዞ ዋና ውበቱ የቦታው ማማርና ማፍዘዝ ብቻ ሳይሆን አብሮ ያለውም ሰው ነው። አቶ ደምለው ሥራቸው ብቻ ሆኖ እንጂ ተፈጥሮን ዘና ብሎ ለማድነቅ ሎተሪ ቢወጣላቸውም፣ አዋሽ ይመጣሉ ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው። አሁንም ቶሎ ሂዶ ከተማ ቀዝቀዝ ያለ ቦታ አረፍ ማለት ነው ያማራቸው። ትንሽ አረፍ ብለው አስተናጋጆቹን አመስግኖና ሒሳቡን ከፍሎ ቦታውን ለቀው ወጡ። አዋሽ ሰባት ከዚያ ብዙ አይርቅም፣ አዋሽ አርባ ከማደር የተሻለ ነው ስለተባሉ ከተማዋን ዞር ዞር ብለው ካዩ በኋላ አልጋ ያዙ። መላኩ ትንሽ ለማረፍ ከቻለም የጀመረውን መጽሐፍ ለማንበብ አስቦ ወደ ክፍሉ ገባ። በረድ ሲል ወደ አዋሽ አርባ ሄደው አካባቢውን ዞር ዞር እያሉ ለማየት አስቧል።

ክፍሉ ውስጥ እንደገባ ለሰስ ባለው ውሃ ሻወር ወስዶ ቀለል ያለ ቁምጣና ቲሸርት በመልበስ አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ማሰብ ጀመረ። አባቱ ሃሰን ከመሆኑ በቀር ሌላ ምንም መረጃ ሳይዝ ፍለጋ ወደ ማያውቀው አገር መሄዱ ወፈፌነት መስሎ ተሰማው። ባንድ በኩል ደግሞ አባቱን አገኘም አላገኘም የተወለደበትን ከተማና የወገኖቹን የአፋር ሕዝቦችን አኗኗር ማየቱም በራሱ አንድ ትልቅ ነገር እንደሆነ ነው ያሰበው። ስንቱ ምናልባት ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የሰው ልጅ የመጀመሪያ መገኛ ይሆናሉ ብሎ የሚገምታቸውን 'የቅድመሰውና ድኅረዝንጀሮ' ዐፅም ፍለጋ አሀጉር አቋርጦ መጥቶ ከርሠ ምድር ይቆፍር የለ። ሰው ከየት መጣሁ? ወላጁ ማነው? ምንጩስ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚፈጠርበትን እንቆቅልሽ ለመመለስ ለምንድነው እንዲህ የሚማስነው? የሉሲን ቅሪተ ዐፅም እዚሁ አፋር ከብዙ ፍለጋ በኋላ ያገኟት ፈረንጆች ነበሩ፣ እድሜዋንም ከሦስት ሚሊዮን ዓመት በላይ ይሆናል ብለው ገምተዋል። ኋላ ደግሞ አርዲ የተባለው ቅሪተ ዐፅም ተገኘ፣ ከ18 ዓመታት በኋላ እዚያው አፋር። እሱን ደግሞ ዕድሜው አራት ሚሊዮን ዓመት አካባቢ ሆኖታል አሉ። በየአህጉሩና በየአገሩ የሰውን ዘር ምንጭ ለማግኘት ያለው ውጣ ውረድና ድካም ይህ ነው አይባልም።

መላኩም ምንጩንና የተፈጠረበትን ቦታ ፍለጋ መሄዱ ሰዋዊ ተፈጥሮው የፈጠረበት ግፊት ሳይሆን አይቀርም። የሚቆፍረው መሬት አይኑረው እንጂ አቶ ሃሰንን ማግኘት የከርሠ ምድር በላይ በሕያዋን መካከል የሚደረግ ቅሪተ ወላጅ አሠሣ ነው የያዘው። ከሰላሳ ዓመት በፊት የነበረችው አሳይታ ከተማም በጣም

ልትቀየር እንደምትችል ምንም ጥርጥር የለውም። አሁን ፎቶው ላይ ያለውን ወጣት ሳይሆን ምናልባትም እስከ ስልሳ ዓመት ሊሆነው የሚችለውን አባቱን ፍለጋ ነው የሚሄደው። ስመኝን ያስጠጓት ሴትም እስካሁን በሕይወት ይኖራሉ ብሎ ማሰቡ የማይመስል ነገር ነው፣ ቡና ቤታቸውንም ሆነ ስማቸውን አያውቀውም። የያዘው ፎቶም ምንም ያህል የሚረዳ አልመሰለውም። ሙሉ ስሙን እንኳ የማያውቀውን ሰው እንዴት ብሎ ነው የሚያጠያይቀው። ያለ ጥርጥር ብዙ ሃሰኖች ይኖራሉ።ደግሞ አፋሮች የሦስት አገር ሰዎች ናቸው፣ ጉዞም ይወዳሉ። ሃሰን አሁን አሳይታ ይኖር ይሆን? በሕይወት ያለን ሰው ቆፍሮ ማግኘት ቅሪተ ዐፅምን ከከርሠ ምድር ቆፍሮ ከማግኘት ሊከብድም እንደሚችል አሰበ። አንድም አንድ ቦታ አይቀመጥም፣ ሁለትም ለውጦቹ ዝግመታዊ ሳይሆን ቅጽበታዊም ስለሚሆኑ። በዚህ ሐሳብ ውስጥ እያለ ነው እንግዲህ ስልኩ ሲጮኽ ከገባበት ሐሳብ ያወጣው። ስንክሳር ነበረች። ላያነሣው አስቦ አነሣው፡፡

"ሂይ መሌ ይቅርታ ማታ ስልኩን ማንሣት ስላልቻልኩኝ። ከሰዎች ጋር ስለነበርኩ ነው። ደግሜ ሞክሬ ነበረ። እንዴት ነበር ጉዞ? አዲሳባ ገባችሁ በሰላም?" አለች ረጋ ባለ ድምፅ፡፡

"አይደል ... እኔም እኮ ሞክርኩና በቃ በጣም ደክሞኝ ስለነበር ዛሬም ጉዞ ስለነበረኝ ዝም ብዬ ተኛሁ። እንዴት ነሽ አንቺ?" አለ ጉዞውን ቀለል አድርጎ።

"ኧረ ... ደግሞ የት ነው ዛሬ የምትሄደው? ሥራ የለም እንዴ? ... ወይስ የሥራ ፊልድ ነው? ምንም ሳይናገሩ መጥፋት ተጀመረ እንዴ? " አለች የምርም በመገረም ዐይነት።

"አይ ሥራ እንኳ አይደለም። ባለፈው እኮ ትንሽ ልነግርሽ ሞክሬ ነበር። አባቴ ያው አፋር አሳይታ አካባቢ አይደል የነበረው ቢያንስ እኔ ስረገዝ። እስኪ የሚሆነውን ልይ፣ በዚያውም አገሬንም ማየቱ አይከፋም ብዬ ነው። ሳምንቱን ሙሉ ፈቃድ ወስጄ ነው ዛሬ የተነሣሁት።" አለ ሳይነግራት መሄዱ መብቱ መሆኑን እንድታውቀውም የፈለገ በሚመስል ድምፅ፡፡

" እኔ አላምንም። ታዲያ ምናለበት ብትናገር፣ አብረን እንሂድ እንዳንል ነው? ርግጠኛ ነኝ ማርቆስና ሶፊያ ያውቃሉ አይደል?" አለች። አንዳንዴ የምትጠይቀው ጥያቄ ምን ዐይነት ግምት ውስጥ እንደሚከታት ልብ አትልም።

"ምን ለውጥ ያመጣል? ማለቴ እነሱ ማወቅ አለማወቃቸው? ይሄ የኔ ሕይወት ነው፣ መንገሩ ያን ያህል አስፈላጊ ስላልመሰለኝ ነው።" አለ ጥያቄዋን አውቆ ሳይመልስ። ለምን እንደዚህ ውስጡ ቆጣ ቆጣ እንደሚልበትና ዝርዝር ነገሩን ከስንክሳር ጋር ማውራት እንዳልፈለገ ለራሱም አልገባውም። እሷም የጀመረችው አካሄድ ብዙም እንደማያዋጣት ያወቀች ይመስል

" አይ መልካም ዕድል፣ በናትህ ቀላል አይደለም እኮ። ደግሞ ተጠንቅቃቸሁ ንዱ። ራስህ ነህ የምትነዳው ወይስ አገር የሚያውቅ ሰው አብሮህ አለ? ደግሞ ሊፍት ምናምን አትስጥ የማታውቀው አገር እንዳይተናኮሏችሁ።" አለች መጨነቋን ድምፅዋ እያሳበቀ።

"እ...ምም በሹፌር ነው የምሄደው። እኔም አፋሬ ስለሆንኩ አገሬ ነው። አትጨነቂ ያን ያህል መንገደኛ አንተናኮልም" አለ ትንሽ ሣቅ እያለ።

"አይደል? እኔ የምልህ ግን ሰሎሜ ነገ ማታ እንደምትገባ አላወቅህም እንዴ?" አለች ሳታስበው ነገሩ ብልጭ ሲልላት።

"እምም ... እ ነገ ነው የምትገባው? ጥሩ ነው። ያው እኔ ግን ከሳምንት በኋላ ነው አዲሰባ የምመለሰው።" አለ ነገሩን ሳያካብድ ስለ አንድ በሩቅ ስለሚያውቀው ሰው እንደሚያወራ ያህል። ስለ ሰሎሜ ማውራቷ እንደ በፊቱ ምንም ስላላስቆጣው ገርሟት ትንሽ ድፍረት አግኝታ፤ "መሊ ቢያንስ ግን እየህ ወንድሟን ነው እኮ ያጣችው፤ ደግሞ ምንም ቢሆን ቤተ ሰብም አለ፣ እንደዚህ ጥፍት ስትል ጥሩ አልመሰለኝም። እኔንጃ አንተ ታውቃለህ። ቢያንስ ፊትህን አስመትተህ የፈለግሽውን ማድረግ ትችላለህ።" አለች አሁንም የሚለውን ባለማወቅ።

" በናትሽ ስንኪ ነግሬሽ ነበር እኔ ስለዚህ ጉዳይ ማውራት አልፈ-ል-ግ-ም... እኔ ለቤተሰብ ፊት ለማስመታት ምናምን ብዬ ኑሮዬን አላመሳቅልም። አንድ መላኩ ነኝ። አሁን ሌላ የምናወራው ነገር አለ?" አለ የድምፁ አወራረድ እየተቀየረ።

"አይ ይቅርታ ... ላበሳጭህ ብዬ አይደለም ስለጨነቀኝ ነው ነገሩ። መቼ ትመለሳለህ ታዲያ?" አለች ነገሩን ለማብረድ እየሞከረች፡፡

" እኔ እንጃ ... ያው እንደቀናኝ ነው፣ ወይም እንዳልቀናኝ ልበል መሰለኝ። ሳምንት ምናምን። ስመጣ እደውልልሻለሁ። እዚያ የስልኩም ሲግናል ያን ያህል ላይሆን ይችላል" አለ አልጋው ላይ እያለ በመቁነጥነጥ ስሜት። "እኔም እጸልይልሃለሁ። አይዞን ጉድ ላክ። ይቅርታ ግን አንድ ጥያቄ ብቻ፣ ስላንተ ከጠየቀችኝ የት እንዳለህ መንገሩ ችግር አለው?" አለች የሰሎሜን ስም መጥራት የመላኩን ቁጣ የሚቀሰቅስ ይመስል፡፡

"ስንኪ ነገርኩሽ እኮ አንቺ ስለ እኔ የምታውቂውን ሁሉ ልትነግሪያት ትችያለሽ። እኔ አያገባኝም። እም ... ም ... እኔ የምኖረው ኑሮ እኮ ድብቅም አይደለም። ሁሉም ነገር በቀን የሚደረግ ነው... ግልጽ ነው?" አለ አሁንም ባልተረጋጋ ድምፅ፡፡

"እሺ እሺ ያው ለማረጋገጥ ብዬ ነው" አለች። ቀጥሎም ትንሽ ነገሮችን አውርተው ስልኩን ዘጉት። ማርቆስ ጋ ደውሎ አወሩና ለመተኛት ቢሞክርም፣

እንቅልፍ ሊወስደው ስላልቻለ ተነሥቶ መስኮቱ አካባቢ ቆሞ አላፊ አግዳሚውን ማየት ጀመረ። በዋናው መንገድ በኩል ሆኖ የከሰዓት በኋላ ጥላ ያለው ክፍል ስለነበር እይታው ደስ ይላል። አልፎ አልፎ ባህላዊ ልብስ የለበሱና ጊሊያቸውን የታጠቁ ወጣት ያካባቢው ተወላጆችም ስድስትና ሰባት ሆነው ሲያልፉ ይታያል። ብዙው ሰው ግን ከተሜ ነው። ከባሻገር ደግሞ ከተማዪቱን ያቀፈው ተራራ አንዳች ግርማ ተጐናጽፎ ተኮፍሶአል። እንዴ አሳይታ፣ እንዴ አዲስ አበባ በሐሳቡ ሲገሞገሞ ቆይቶ አሁንም የማያርፈውን ስልክ ከሐሳቡ አወጣው። ሣራ ነበር የደወለችው። ምንተስኖት ከጥቂት ቀናት በፊት ወደ አሜሪካ እንደተመለሰና እየጠጣና የሆነ ያልሆነ ነገር እያለ እንደሚረብሽ ነገረችው።

"የፍቺ ሂደቱን ጀምሬዋለሁ። በዚህ ከቀጠለ ፖሊስም መጥራት ሳይኖርብኝ አይቀርም። በቃ ልጆቹንም መከራቸውን እያሳያቸው ነው። የሚሠራውን ነው ያሳጣው። ገንዘቡንም እያወጣ እየበተነ ስላስቸገረኝ ሌላ የራሴን አካውንት መክፈቴም ጭንቅላቱ ላይ ወጥቶበታል።" አለች ድምፅዋ ቁጣዋን ሳይደብቅላት፡፡

"እኔ ምልሽ ሣሪ ምንድነው አሁን እሱ የሚፈልገው? ማለቴ ትዳሩን ይፈልጋል ወይስ ምን አድርጊ ነው የሚልሽ?" አለ ግራ የገባው መላኩም።

"እኔንጃ መሊ። የውልህ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ ውርደት ነው የሚመስለው። ሁሉ ሰው የሱ አሽከር ነው የሚመስለው። ከተጋባን ጀምሮ ይቅርታ የምትል ቃል ከፉ የወጣችበትን ጊዜ አላስታውስም። እንዲያውም ባለፈው ካንተ ጋር ሲያወራ ይቅርታ ሲጠይቅህ ገርሞኝ ነበር። አሁን በቃ ሁሉንም ሰልችቶኛል።" አለች፡፡

"ምን ብሎ ነው የሚዝተው? ማለቴ አንቺ ላይ ነው ወይስ?" አለ መላኩ፡፡

"በቃ ምን መላ አለው መሰለህ። ያው ቀናተኛነቱኮ እያደርስ ነው። ልክ እንደ ጨዋ በቃ ደርሶ የት ገባሽ የት ወጣሽ ነው። እሱ ብቻ ሳይሆን ፍቺውን የምቀጥል ከሆነ ሕይወቴን ሙሉ የሚጸጽተኝን ነገር እንደሚያደርግ ነው የሚቀባጥረው። አንዳንዴ የሦስት አመት ሕፃን ነው የሚመስልህ። በምን ቀን ከሱ ጋር እንደተገዳኘሁ ነው ዕድሌን የምረግመው።" ብላ ማልቀስ ስትጀምር መላኩም ተነሥቶ ቁጭ አለና እሷን ማጽናናቱ ብዙ ደቂቃ ወሰደበት። የቻለውን ያህል አበረታቶአትና አጽናንቶአት ስልኩን ዘጉት።

ጥላው በረድ ሲል ጀምበር ከመጥለቋ በፊት አዋሽ አርባን ዞር ዞር ብለው ለማየት፣ የተሻለ ምግብ ቤት ካለም ራት እዚያ ለመብላት ሄዱ። ከፍተኛው ቦታ ብዙም እልፍ ሳይሉ ወደዚያው የሚሄድ አንድ ያካባቢው ተወላጅ የሚመስል ሰው ሊፍት ጠይቆአቸው ጫኑት። ሰውዬው ፀጉሩ ሉጫ ቢሆንም ጭብርር ብሎአል። ጉንጩ በጫት ተወጥሯል። በእጁም አንድ የተጀመረ ትንሽ ጥቅል ይዟል። ዐይኖቹ ቀልተው ደፍርሰዋል። እጁን እያወናጨፈ ሲያወራላቸው የተቆጣ ያስመስለዋል።

በየመሃሉ ደግሞ ሲሥቅና ፈገግ ሲል ሌላ ሰው ይመስላል። አጠገቡ ከተቀመጡት እሽግ ውሃዎች መውሰድ እንደሚችል ጠየቀና አንድ ላስቲክ ውሃ ወስዶ እዚያው መጐንጨት ጀመረው። በስተ ግራ ያለው ትልቅ ሕንጻ የሜካናይዝድ ጦር ማሠልጠኛ መሆኑን ነገራቸው።

ከተማዪቱ ውስጥ ትንንሽ ቡና ቤቶች፣ በር ላይ የተኰለኰሉ ሴቶች፣ ከጅቡቲ ዕቃ ጭነው የመጡና ወደዚያውም የሚመለሱ ከባድ መኪኖች ናቸው በብዛት የሚታዩት። እገሌት ቡና ቤት ወይም ምግብ ቤት ሻወር አለ ይላሉ ብዙ ቤቶች ላይ ያሉ ማስታወቂያዎች። አለበለዚያም እገሌ ጋራጅ የሚሉ ሰፋፊ ግቢዎች ናቸው ቀልብ የሚስቡት። ባዋሽ ሰባትና ባዋሽ አርባ መካከልም ባለው እሸሃማ ጫካ ውስጥና በመካከል ከብቶቻቸውን የሚነዱ ሕፃናትና ሴቶች በብዛት ይታያሉ። እዚህ አካባቢ ሰው ለመዝናናትና ለማረፍ ምን ማድረግ ይችላል? የሚል ጥያቄ ሲያስብ ምንም አልመጣለትም። ከዚያም ዞር ብሎ የተሳፈረውን ሰውዬ ጥያቄውን ሊጠይቀው ሲል፣ ሰውዬው በመቃም እየተዝናና መሆኑን ዐወቀና ለራሱ ፈገግ አለ። በዚህ መሃል ሰውዬው መውረድ እንደሚፈልግ ተናግሮ አመስግኖአቸው ሄደ። እነመላኩም በከተማዪቱ ጫፍ ላይ ደርሰው ወደ አዋሽ ሰባታቸው ተመለሱ።

በርግጥም ካለመሥራት እኩል በትክክል አለመዝናናትና አለማረፍም የሰውን ጭንቅላት ምን ያህል እንደሚጐዳ ብዙ ሰው ልብ የሚል አይመስልም። ጫት በመቃም ወይም ዘወትር በመጠጣት ለመዝናናት መሞከር ለአእምሮ ጤና ሳይሆን ጤናን የሚፈጥር ሱስ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ለምሳሌ ጫት የሰውን አእምሮ አሠራር ሊያውኩና ሱስንም ሊፈጥሩ የሚችሉ ኬሚካሎችን የያዘ ቅጠል ነው። ካቲኖን እና ካቲኖል የሚባሉ ንጥረ ነገሮች የሰውን ስሜትና መነሣሣት ከፍ በማድረግ ምርቃናን በመፍጠር በሱስ ከጠመዱ በኋላ ቃሚውን ጫቱን ካላገኘ መንቀሳቀስ የማይችል ጥገኛ ማሽን ያደርገዋል። በሃራራና ምርቃና መካከልም እየዋዠቀ ቆይቶ በፍጻሜው ውድ የሆነ አእምሮው ከጥቅም ውጪ ወደ መሆን ሲመጣ የጀዝባነትን ጎራ ይቀላቀላል። ከዚህም በተጨማሪ በጫት የተፈጠረውን ምርቃና ለማገዝ ማጨስ የተለመደ ሲሆን ያንን የናረ ስሜት ለማርገብ ደግሞ መጠጥ የግድ ይላል። ሌሎች መጠጥ የማያዘወትሩ ሰዎች ደግሞ እንደሃሺሽና የእንቅልፍ ኪኒን ዐይነት መድኀኒቶች ሱስ ሳያስቡት ከጫቱ ጋር በተጣማጅ ይጠናወታቸዋል። ይሄ እንግዲህ በጥርስ፣ በጨጓራና በኪስ ላይ የሚፈጥረው በሽታ ሳይቆጠር መሆኑ ነው። ሰዎች በሚቅሙበት ጊዜም የጊዜ ባቡር አፈጣጠኑ ስለሚቀየር በብዛት የሚቅሙ ሰዎች በዕድሜያቸው ላይ ቁማር መጫወታቸው አይቀርም። እንኳን በጫት ታግዞ እንዲሁም ባህላችን የጊዜ ፀር ነው።

ባንድ ወቅት በጥቂት የሃገሪቱ ክፍሎች ብቻ ከሃይማኖታዊና ባህላዊ ወግ ጋር ተመጥኖ ለግልጋሎት ይውል የነበረው ጫት ዛሬ ከጥቂት ያገሪቱ ክፍሎች በቀር እስከ ዳር አካሉ ማየቱ አሳዛኝም አስፈሪም ነው። ከናዝሬት አስካዲስባ ባለውም አስፋልት ዙሪያ ዘመናዊ ቃሚዎች መኪናቸውን ደርድረው 'እየበዙ

ሲዝናኑ ማየት' ችግሩ ገና ፋሽን እንጂ ፍርሀት እንዳልፈጠረ ያሳያል። ከባለሥልጣን እስከ ነጋዴ፣ ከምሁር እስከ ሥራአጥ፣ ወንድና ሴት ሳይባል በጫት አባዜ ተይዘው አለመቃም የሚያሳፍርበትና እንደ ሞኝ የሚያስቆጥርበት ጊዜ ላይ መድረሳችን ነበር ማሳፈር ያለበት። ቡናን የሚቀናቀን የውጭ ምንዛሪ አምጪ ተክል መሆኑም ከኮሎምቢያ ኮኬንና ከአፍጋኒስታን ሄሮይን የኛንስ ጫት ሕጋዊ ከመሆኑ በቀር ምን ይለየዋል።

ቴክኖሎጂው ቢኖረን ኖሮ ጫትም ወግ ደርሶት በክንድ የሚወጋና ባፍንጫ የሚሳብ የተጣራ ካቲኖን ሳይሆን አይቀርም ነበር። በምግብ ራሱን ያልቻለ ሕዝብ ፀረ አእምሮ የሆነ ተክል በየአገሩ እንደ ቁምነገር ሲልክ አእምሮ ቢስነት እንጂ እድገት ሊሆን አይችልም። በየከተማው እንደ አሸን የፈሉት የጫት ቤቶች የትውልዱን አእምሮ ለመግደል እንደተቋቋሙ መርዝ ቤቶች እንጂ የአገርንም ሆነ የሰውን ሕይወት በምንም መንገድ ሊረዱ እንደሚችሉ ቢዝነሶች ሊታዩ አይገባም። ጫት መቃም ከአእምሮ ሕመም ጋር በከፍተኛ ደረጃ መያያዙም በሰው አንጎል ውስጥ ገብቶ ከሚፈጥረው የኬሚካል መዛባት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። የተወሰኑ ሰዎች እየቃሙ አእምሮአቸው በሽተኛ አልሆነም ማለት በሚያዳልጥ መሬት ላይ ትናንት የሄዱ ሰዎች ወድቀው ስላልተሰበሩ ዛሬ ሰውን ሁሉ አሰልፎ በጭቃው ላይ እንደማስሮጥ የሚቆጠር ነው።

እንደኛ አገር ባለ አንድም ከሱስ የማገገሚያ ሆስፒታልና ማእከል በሌለበትና የህክምናው ዋጋ ለሰለጠኑትም አገሮች ወገብ ሰባሪ ሆኖ እያለ እንደ ጫትና ሃሽሽ ዐይነት አደገኛ ዕፆች ዕድሜያቸው ባልደረሱ አዳጊ ሕፃናት ሳይቀር እንደ እንጀራ ሲበላ ማየቱም መንግሥትን ብቻ ሳይሆን የትውልድ ኀላፊነት አለብኝ የሚል ሰውን ሁሉ ተጠያቂ ያደርጋል። እንኳን እነዚህ አደገኛ ዕፆችና አልኮሆልም ቢሆን ዕድሜያቸው ለጋ በሆነና አእምሮአቸው በማደግ ላይ ባሉ ወጣቶች እንዳይወሰድ ሕጋዊና ማኅበረ ሰባዊ ከለላ ያስፈልጋል። ለዚህም በየሆቴሉ ጨቅላ ተማሪዎችን የሚያማልሉ የቀን ፓርቲዎችና የየሰፈሩ ጠላና ካቲካላ ቤቶችም ትልቅ ግፍ በትውልድ ላይ እየሠሩ መሆኑ ተገልጦ መነገር አለበት። ይሄ ሁሉ አሁን በመላኩ አፍ አይነገር እንጂ እሱው ሁሌም ከጓደኞቹ ጋር የሚሟገትበት፣ የሕዝባችንን አእምሮ የበላ የቀን ጅብ ሆኖ ያገኘው ጉዳይ ነው።

* * *

መላኩና ሾፌሩ ምሽቱ ላይ መኪናቸውን አቁመው ከተማ ውስጥ ሲዞሩ ነበር ያመሹት። አዋሽ ሰባት ደመቅ ያለች ከተማ ስትሆን ማታ ላይ ደግሞ መንገዱ ሁሉ በከባድ መኪና ተሞልቶ መጠጥ ቤቶቹም በደብዛዛ ብርሀናቸውና በደማቅ ሙዚቃቸው ተሽቀርቅረው እዚህ ግቡ ይላሉ። በበረሐ ሲንከራተት የዋለው የከባድ

መኪና ሾፌርና ረዳት ደግሞ በቀዝቃዛ ቢራ ሲደነዝዝ ያመሸና በሙት ገላ ታቅፎ ያድራል። በዚህም መልክ ነበር በሃገራችን ኤይድስ ብዙ ሰው ለመቅጠፍ ያለምንም ክፍያ ካገር አገር ብቻ ሳይሆን ከቡና ቤት ወደ ትዳር ቤትም የተዛመተው። በጉዳዩ ብዙ ጊዜ ሴትኛ አዳሪዎች ላይ ጣት ቢጠቆምም፣ ገንዘብ እየከፈሉ ቫይረሱን የሚሸምቱት ወንድኛ አዳሪዎች ግን የችግሩ ዋነኛ አጓጓዦችና አራቢዎች መሆናቸው ተወቃሽ ሊያደርጋቸው ይገባል። ወንድኛ አዳሪ የለም ለሚሉ ብቻዋን የምታድር ሴት ሴትኛ ዐዳሪ ሳይሆን ሴት ወይዘሪት ብቻ ነው የምትባለው፤ አግብታ ሴት ወይዘሮ እስክትሆን። የከፈለ ሳይሆን የተከፈለው ነው ስድቡን የሚሸከመው ካልተባለ።

የበሉት ራት እንደ ነገሩ ነበር። እጅግም ስላልራባቸው አልተጨነቁም። መላኩም አንድ ሦስት ጊዜ ጉርሶ ነበር የተወው። ከዚያ ሲወጡ ደግሞ መንገድ ላይ የሚጠበስ እሸት በቆሎ አግኝተው እሱን እየበሉ አግራቸውን እስኪደክማቸው ዞሩ። መላኩ እስካሁን ቀርቦ ያናገረው ያካባቢው ሰው ባይኖርም፣ ወዲያ ወዲህ መዞሩ ራሱ ደስታን ፈጥሮበታል።

በማግስቱ አረፋፍደው ቁርስ በልተው የመኪናውን ነዳጅ እስካፉ ሞልተው ወደ አሳይታ ጉዞአቸውን ጀመሩ። ደንና መኪና ስለያዙ ምሳ ሎጊያ ላይ በልተው ቀስ ብለው ካስር ሰዓት በፊት አሳይታ እንደሚገቡ ገምተዋል። ረፋዱ ላይ አየሩ ያንንም ያህል ስለማይሞቅ መስኮቶቹን ከፍተው ነፋሱን እየተቀበሉ ነበር የሚነዱት። መላኩ ከመኪናው የሚወጣው የቀዘቀዘ አየር አይስማማውም። በቀላሉ አፍንጫውን ያሳክከዋል። እፍንም ያደርገዋል። ስለዚህም አማራጭ ካላጣ በቀር አይጠቀምም። ከጅቡቲ የሚመጡት ከባድ መኪኖች ብዛትና ክብደት ይሆናል አስፋልቱ በግማሽ ተጉረባብጧል። ወደ አዲሳባ የሚሄደው አቅጣጫ መንገዱ ተጠረማምሶና ጉረባብጦ ይታያል። ወደ ጅቡቲ የሚወስደው መንገድ አሁንም አዲስ የተሠራ ይመስላል።

"አይገርምህም በአንድ ጊዜ ተሠርቶ ከወዲያ ያለው መንገድ እንዴት እንደተበላሸ። ካቅሙ በላይ እኮ ነው እየሠራ ያለው። ወይ ደግሞ በየጊዜው ቢያሳድሱት ምናለ? እነሱ እኮ ያንኛውን በኩል ሲሸሹ ስንት ሰው መሰለህ የሚያልቀው " አሉ አቶ ደምለው አንድ ከባድ መኪና አጥብቦባቸው ሲመጣ ወደ ዳር ወጥተው ካለፉ በኋላ።

"በጣም ነው የሚገርመው። ጭነቱ ነው እንዲህ ያጉረባበጠው ማለት ነው?" ብሎ መላኩም እጅግም ልብ ያላለውን መንገድ በማየት ተገረመ። ወዲያው ነገሮችን ማሰብ የሚወደው የመላኩ አእምሮ ነገሩን ማውጠንጠን ጀመረ። ነገሩ ወደ አገር ውስጥ የምናስገባው ወደ ውጪ ከምንልከው ምን ያህል እንደሚበልጥ የሚያሳብቅ መሰለው። በተጨማሪም ዕቃ ተሸክመው ከወደብ ወደ መሃል አገር

የሚመጡት መኪኖች ሲመለሱ ደግሞ ባዶአቸውን እየተንኳኩ ወደ ወደብ ሲሄዱ የሚባክነውን ነዳጅ፤ የሰው ጉልበትና ጊዜ ማሰቡ ዘገነነው። አገራችን የተሻለ ስታድግ ሁለቱም መንገዶች እኩል ያረጃሉ፤ ከዚያም ሌሎች ከኛ የሚፈልጉት ነገር እየበዛ ሲሄድ ደግሞ ወደ ጅቡቲ የሚወስደው መንገድ ቀድሞ ሲበላሽ ታይቶት ለራሱ ፈገግ ሲል፥

"ምን ሰዉ እኮ ስግብግብ ሆኖ ካቅሙ በላይ እየጫነ ነው እንዲህ መንገዱን ያለዕድሜ የሚያስረጀው?" አሉ አቶ ደምለውም ነገሩን ከጭነት ብዛት ጋር እያያይዘው፡፡

መላኩም የመንገዳችን ጥራት ምን ያህል እንደሆነም ሸክሙ እንደሚያጋልጥ እያሰበ ሳለ መኪኖቹ ፍጥነታቸው እየቀነሰ በኋላም ጭራሹኑ ቆመው አንድ ሃያ ደቂቃ ቆይተው ሲሄዱ ከፍተኛ ክብደትና መጠን ያላቸው ትራኮች እያለፉ በተፈጠረው የመንገድ ጥበት የተፈጠረ ችግር እንደሆን አወቁ። መንገዳችን ክብደትን ብቻ ሳይሆን ስፋትንም ለማስተናገድ ገና እንደሆነ ተረዳ። ባንድም በኩል ያለው መንገድ መበላሸቱ ከድሮው ይልቅ ብዙ ነገሮችን ማስገባት መቻላችን የመግዛትና የመጠቀም አቅማችን መጨመሩን ማሳየቱ ነው ብሎ በውስጡ ተጽናና። ባለፈው ሰሞን ያነበበው አንድ ጽሁፍ ትዝ አለው። ጽሁፉ እንደሚለው ቻይና ከአፍሪካ ጋር ባደረገችው የንግድ ልውውጥ ያስገባችው ገንዘብ ከከፈለችው ጥሪት በሰባት ስምንት ዕጥፍ እንደሚበልጥ ነው። ሸቀጡ በዋጋው ልዩነት እንጂ በብዛቱም ላይሆን ይችላል የተበላለጠው። ዋጋን የሚጨምረው ደግሞ ጥሬ ዕቃ ላይ የሚጨመረው የሰው አእምሮ ነው። ለዚህ ነው ከሃያ ጥሬ የበግ ቆዳ ይልቅ ከብጣሽ ቆዳ የተሠራች የገንዘብ መያዣ ቦርሳ በዋጋ የምትበልጠው።

ጥቂት ትንንሽ ከተሞችን እያለፉ ገዋኔ እስኪደርሱ ያየው የከሰል ብዛት እንደ ድንጋይ ከሰል ከመሬት የሚወጣ እንጂ ዛፍ ተቃጥሎ የከሰለ አይመስልም። ይሄን ሁሉ ከሰል ለማምረት የሚበቃ ጫካ አፋር ውስጥ ይኖራል ብሎ ማሰብ አልቻለም። ምክንያቱም አብዛኛው መንገዱን ተከትሎ ያለው እስካሁን ያየው አካባቢ በረሐ ስለሆነ ነው። አንዳንዱ ከተማ መንገዱ ሁሉ ጠቁሮ ከሰል መስሎአል። በገዋኔና በሌሎች ትንሽ ውሃ ባላቸው አካባቢዎች ሲያልፉ አካባቢው ሁሉ ባንዴ አረንጓዴ ይሆናል። ይህም የውሃን ኀይል ይናገራል። ርግጥም ውሃ ሕይወት ነው። ከዛ በተጨማሪ ባለፉባቸው ከተሞች ሁሉ መንገዱን ተከትለው በተሠሩት ቡና ቤቶች ደጃፍ ላይ እጅብ ብለው የተቀመጡ ወጣቶችና አካባቢውን የሞሉ ልጆችን እያየ ሕይወት ለነሱ ምን እንደምትመስል ለማወቅ ቢጓጓም ቆመው ያንን ለመመራመር ጊዜም አላገኘም። ወደ አፋር ከመሄዱ በፊት ሊያዋራቸው የሞከራቸው ስለ አፋር ያውቃሉ የተባሉ ሰዎችን ሊያገኛቸው ስላልቻለ ጥቂት የራሱን ጥናት ለማድረግ ሞክሯል። ግን ያንን ያህልም ጥልቅ የሆነ የተጻፈ ሥራ ማግኘት አልቻለም።

ከገዋኔ ሊወጡ ሲሉ ሁለት ጀሪካን የያዘ አንድ መካከለኛ ዕድሜ ላይ ያለ አፋሬ ሊፍት እንዲሰጡት በመማጸን እጁን ሲያውለበልብ "ይዘነው እንሂድ እንዴ?" አለ መላኩ፡፡

"ኧረ ልጄ ይሄኔ እኮ ከዛው አቅጣጫ ነው የመጣው። እነሱ መኪና ወደሄደበት ሁሉ መሄድ ነው የሚፈልጉት። ደግሞ ከፈለግ ስንት አገር ቂጥ ይዘኸው ሄደህ ውረድ ስትለው መልሰኝ ብሎ ያፈጥብሃል። እምቢ ካልክ ደግሞ ችግር ነው። እንዲሁ በሰላም ብንሄድ ይሻላል። አላየኸውም የትናንቱን ሰውዬ የሚወርድበት ቦታም ሆነ የሚሄድበት ምክንያት አልነበረውም እኮ።" አሉ ፍጥነታቸውን ሳይቀንሱ።

"አይ አንዳንድ ሰዎች እንደዚያ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሌሎቹ ግን እንደማንኛውም ሰው ተቸግረው ነው ሊፍት የሚለምኑት። አንድ ከአፋሮች ጋር ብዙ የኖረ ወዳጄ እንደነገረኝ አፋሮች ወዳገኙበት አቅጣጫ ያለውን እድል ተጠቅመው የሚሄዱት ሽርሽሩን ወደው ሳይሆን በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ሊጠይቋቸው የሚፈልጉ ዘመድ ወዳጆች ስላላቸው ነው። ግን በቦታ ርቀትና በተለያየ ምክንያት ይህንን ለማድረግ አይችሉም። ስለዚህ ወደምስራቅም ሆነ ወደ ምዕራብ ቢሳፈሩ ይህንን አላማቸውን መፈጸም ይችላሉ። በባህላቸው በጣም የሚቀራረቡና ለማህበራዊ ሕይወትና ዝምድና ትልቅ ቦታ የሚሰጡ ህዝቦች ናቸው። ደግሞ ሰው ዝም ብሎ አፋሮችን ከመሬት ተነሥተው እንደሚተናኰሉ ስለሚያስብ ነው እንጂ ጥሩ ያረግላቸውን የሚጎዱ አይመስለኝም። አሁን ያለፍነውን ሰውዬ እኔም እያወራሁት ብሄድ ደስ ይለኝ ነበር።" አለ ነገሩን ሙሉ በሙሉ እንዳልተስማማበት በሚገልጽ ድምፅ።

"ይገርማል ልጄ! እኛ እኮ በቃ ሲባል የምንሰማውን ነው። እዚህ ብዙ የሠሩ ሰዎች የሚሉትን ነው እንጂ እኔ እንኳን ምንም አጋጥሞኝ አያውቅም። ለነገሩ እኔም አሳዝኖኝ ነበር፡ ይሄኔ ያን ያህል ሽክም ተሸክሞ እኮ የትዬ ለሌ መንገድ ይሆናል የሚሄደው" አሉ እሳቸውም ነገሩን አለሳልሰው። እየወሩ እያለ አንድ ሰው ትላልቅ ነጫጭ ነገሮች ይዞ እጁን እያነሣ አይተው ጠጋ ሲሉት የሰጎን ዕንቁላል ነበረና የሰጎን ዕንቁላል አይቶ የማያውቀው መላኩ ሊገዛው አቆሙ። ዋጋውን ሃያ አምስት ሃያ አምስት ብር ብሎ ድርቅ ስላለ ደፍን አምሳ ብር ሰጥቶት ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ሰውዬውም በደስታ ተምነሽንሾ ከአስፋልቱ ወጥቶ ጉዞውን ቀጠለ። ምንም አማርኛ ስለማይችል ምንም ማውራት አልቻሉም ነበር። የለበሰው ባህላዊ ልብስ ጽድት ያለና ቁመናው የሚያምር ጠይም ሰው ነው። መፋቂያው ባፉ፣ ሚዶውም ፀጉሩ ላይ እንደተሰካ ሲያየው መላኩ ዐብሮት ፎቶ ለመነሣት አሰበ። ግን ቋንቋ ግድግዳ ሆኖባቸው ተላለፉ።

ሚሌ እስኪደርሱ ጥቂት ሰዎች ሊፍት ቢጠይቋቸውም የአቶ ደምለውን

ሐሳብ ላለመቃወም ብሎ ስላካባቢው ያለውም ዕውቀት ውሱን ስለሆነ ዝም ብለው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ወደ ሚሌ ከተማ ሲታጠፉ ደሴ የሚለውን ምልክት ሲያይ፣ "እንዴ በደሴም ይመጣል እንዴ? ከዚህ ደሴ ምን ያህል ይርቅ ይሆን አቶ ደምለው?" አለ ያልጠበቀው ነገር ሆኖበት፡፡

"ትንሽ የጠጠር መንገድ አለው እንጂ በባቲ አድርጎ ደሴ የሚሄድ መንገድ አለ። አንድ ሁለቴ መጥቼበታለሁ። መቶ ሰማንያ አካባቢ ነው። ያምራል ያው መንገዱ አስቸጋሪ ስለሆነ እንጂ። በዚህ መኪና ግን ምንም ችግር ያለው አይመስለኝም።" አሉ እንቁላሎቹ ላይ ጃኬታቸውን ጣል እያደረጉ። መላኩ ልብም አላላቸውም ነበር።

"እንደሱማ ከሆነ ስንመለስ ወይ ደሴ አድረን በዚያው ወዳዲሳባ እንገባለና" አለ። መንገድ ሲሄድ መደጋገም አይወድም መላኩ፣ ስለዚህ ደስ ብሎታል።

"ጥሩ ነው ከደሴም አዲሳባ ሄደህ ካላወቅህ መንገዱ ዳገት ቁልቁለት ቢበዛውም ደስ ይላል። ካራት መቶ ኪሎ ሜትር አይበልጥም።" አሉ ነገሩ እንዲያውም የተሻለ አማራጭ እንደሆነ በማሰብ።

ካንድ ሰዓት በኋላ ሎጊያ ሲገቡ ሁለቱም ርቦአቸው ስለነበር ለምሳ ቸኩለዋል። በተለይ አቶ ደምለው ቡናና ሲጋራ ጠምቶአቸዋል። የተሻለ ምግብ የት እንደሚገኝ ጠይቀው ወደዚያው ሲሄዱ ብዙ መኪኖች ቆመው ያገኙበት ሆቴል ብዙም ሳይጨነቁ ገቡ። ቤቱ ሰፊ አብዛኛው ሰው የፍየል ጥብስ የሚበላበት ቤት ነው። እነሱም እጃቸውን ታጥበው ከተቀመጡ በኋላ ልትታዘዛቸው የመጣችውን ልጅ እግር ወጣት ትንሽ አዋርተዋት ደረቅ የፍየል ጥብስ አዘዙ። ከምሳው በኋላ ሌላ ቤት ሄደው ቡና ከጠጡ በኋላ ትንሽ አረፍ ብለው ወደ አሳይታ መንገድ ጀመሩ። አዲስ በመገንባት ላይ ያለው የክልሉ ዋና ከተማ ሰመራ ከሎጊያ ብዙ አይርቅም። ከተማዋ ባዳዲስና ባላለቁ ሕንጻዎች የተሞላች ሲሆን ገና ዛፍና ሰው እምብዛም ስለሌለባት ካምፕ ካምፕ እንጂ ከተማ ከተማ አትሸትም።

ብዙ ከተሞቻችን አስፋልት ተከትለው በተጀመሩ መንደሮችና የንግድ ቤቶች ላይ ያለፕላን የተሠሩ ስለሆነ ቶሎ ከተማ ቢሆኑም ከተማ ሳይሆኑ ነው የሚያረጁት። ሰመራ ግን በቂ ውሃና መሠረተ ልማቶችን ካገኘች፣ ምናልባትም በኢትዮጵያ ውስጥ ምርጥ ከሆኑ የብረሐ ገነቶች አንዷ ሳትሆን እንደማትቀርና በተለይ የዩኒቨርሲቲው እዚህ መሆን ትልቅ ተጽዕኖ እንደሚያመጣ መላኩ አሰበ። በረሀነቱም ሆነ ያካባቢው ደረቅነት ከላስቬጋስ አይብስም። ቁማር ላስቬጋስን የዓለም የመዝናኛ ማእከል ካደረጋት፣ ሰመራም የራሷ ማንነትና በፈጠራ ችሎታቸው የተካኑ ልጆቿ ከተደበቁበት ሲወጡ፣ ማን ያውቃል የዓለም ሕዝብ የሚጐርፍባት የአፋር ከተማ ትሆን ይሆናል። መላኩ ይህንን እስቦ ሳይጠግብ ዋናውን መንገድ ትተው ወደ አሳይታ በሚታጠፈው መንገድ ገቡ።

መንገዱ ጭር ያለ ሲሆን ምንም መኪና አይታይም። ከግራና ከቀኝ ያለው ለጥ ያለው አሸዋማ በረሐ ዐይን ያደክማል እንጂ ታይቶ አያልቅም። እያለፉ እያለፉ ትንንሽ የአፋር መንደሮች ይታያሉ። መንደሮቹ ከመንገዱ ብዙም አይርቁም። ቤቶቹ በቀላሉ የሚፈርሱና የሚሠሩ ሲሆኑ እንደተለመደው ቤት ሳሎንና መኝታ ክፍሎችም ሆነ በቂ መስኮት የላቸውም። ክልጆች በቀር ትልቅ ሰውም የሚያስቆመውም አይመስልም። ኩሽናና መታጠቢያ ቤት፣ ቤተመጻሕፍትና ቢሮ እዚህ የማታሰቡ አይደሉም። ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የሚኖሩ ሰዎች ቤት ዋነኛ መለያው ፈርሶ የሚሠራ ተንቀሳቃሽ መሆኑ ነው። ውስጡ ግን እምብዛም የሚያንቀሳቅስ አይመስልም። ቤቱን መሥራትም ማፍረስም የሴቶቹ ሥራ ነው። በዚህ በረሐ እንደዚህ ዐይነት ቤት ውስጥ እንዴት እንደሚኖር ለመላኩ ሊገባው አልቻለም።

መንገዱን ግራና ቀኝ ያጠረው ተክል ከናዝሬት ከወጣ ጀምሮ ቢያየውም፣ እስከአሁንም ምን እንደሆነ አላወቀውም። ግመሎችና ፍየሎች ተንጠላጥለው ሲበሉት አይቶአል። በጣምም ትልቅ ዛፍ ባይሆንም አልፎ አልፎ መጠነኛ ግንድና ቅርንጫፎችን አውጥቶ አይቶታል። የገረመው ነገር በቃጠሎው በረሓ ውስጥም ሳይቀር እንደለመለመ ያለ ብቸኛ ተክል እሱ ብቻ መሆኑ ነው።

"ይሄ ተክል ምንድነው የሚባለው? ሌላ አካባቢ አይቼው አላውቅም።" አለ ወደ አቶ ደምለው ዞሮ፡፡

"ስሙን አላውቀውም ልጄ፣ ግን በደርግ ጊዜ ነው አሉ አንድ የእርሻ ምርምር ባለሙያ ድርቅ ይቋቋማል ብሎ አምጥቶ የዘራው። ብዙም ሳይቆይ ሁሉንም ተክል አጥፍቶ እሱ አገሩን ወረሰው። አሁን እሱን ለማጥፋት ቢሞከሩም የሚቻል አልሆነም። ስለዚህ የማጥፊያውን ዘዴ እያጠኑ ነው አሉ።" ብለው ሲያስረዱት በጣም ተገረመ። እስከ ዛሬ ስለዚህ ምንም ባለመስማቱ፣ "የሚገርም ነው። እንዴት ይሄንን ያህል ቦታ ሊሸፍን ቻለ፣ ደግሞስ ድርቁን የሚቋቋመው እሱ ብቻ እንዴት ሆነ?" ብሎ አሁንም በግራና በቀኝ ባግራሞት ማየቱን ቀጠለ።

"ግመሎቹ ፍሬውን ከበሉት በኋላ ሳይፈጭ ወጥቶ እየበቀለ ነው አሉ እንደዚያ አገሩን ሁሉ የወረሰው። እስከ ድሬዳዋ ድረስ ነው መሬቱን ሁሉ የወረሰው። የሚያሳዝነው ሌላውን ዛፍና ተክል ሁሉ ነው አሉ አድርቆ የሚያጠፋው።" አሉ አቧራ የሞላው መንገድ ሊያንሸራትታቸው ሲል ፍጥነታቸውን እየገቱ፡፡

መላኩን ግራ ያጋባው ተክል ፕሮሶፒስ የሚባል ሲሆን፣ ያካባቢው አርብቶ አደሮች የሰይጣን ዛፍ ይሉታል። ድርቅ ይቋቋማል በሚል ምክንያት በሰባዎቹ አጋማሽ ላይ ነው የተራባው። በትክክል ከየት አገር እንደመጣ ባይታወቅም ከህንድ ነው የመጣው የሚለው እምነት ያመዝናል። ውሃና ዐሐይን በመከልከል ሌሎቹን

ነዋሪ ተክሎች ሁሉ አፍኖ ይገድልና ለብቻው በመሬቱ ላይ ይነግሣል። ብዙ ዐይነት ዝርያዎች ሲኖሩት እኛ አገር ያለው ግንዱም ያን ያህል የማይወፍር፣ ዛፍም ሆኖ ዛፍ የማይሆን ሲሆን ለጥቅም ተብሎ ሳይሆን ድርቅን እንዲቋቋም ብቻ ተብሎ ይመስላል የተተከለው። በርግጥ ድርቁን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ነው የተቋቋመው። አሁን ሰዎችንና መሬቱንም ተቋቁሞ ስላስቸገረ እሱን ለማጥፋት ደግሞ ለሚደረገው ምርምር ብዙ ገንዘብ እያስወጣ ነው። ሥሩ እስከ ዐምሳ ሜትር ጥልቀት ወደ መሬት የሚገባ ሲሆን ይህም ድርቅን ለመቋቋም ይረዳዋል። ልክ እንደዚሁ አንዳንድ ባህሎች፣ አስተሳሰቦችና ልማዶችም ለጥቅም ሳይሆን ችግርን ለመወጫና ለጊዜያዊ መፍትሔነት እንደ ቀልድ ተጀምረው አገሩን ሁሉ ሲቆጣጠሩ በኋላ ማጣፊያው ያጥራል። ክፉ አስተሳሰብም ሲዘሩት እንጂ ላጥፋህ ሲሉት እንደዚሁ ተክል አሻፈረኝ ማለቱ ብቻ ሳይሆን በፍጥነት መራባቱ አይቀርም።

አሳይታ ከተማ መግቢያ ላይ ሲደርስ ለጓደኛው ወዳጅ ለአቶ ባሕሩ ደውለውለት ስብሰባ ላይ ስለነበረ ወዲያው ሊያገኛቸው አልቻለም። ወደ ማታ መገናኘት እንደሚችሉና እስከዚያ ሆቴላቸው አረፍ እንዲሉ አቅጣጫውን ጠቆማቸው። ከተማዪቱን መሃል ለመሃል የሚያቋርጠውን መንገድ ይዘው ሲገቡ መሃል ፒያሳው ላይ ደረሱ። አደባባዩ መሃል የተተከለችውን የሚሊኒየም ድልና መልካም ምኞት የተጻፈባትን ሐውልት አልፈው ሲሄዱ ከተባለው ሆቴል ደረሱ። አስፋልቱን ተከትለው ወደ ከተማው መጨረሻ ሲደርሱ አስፋልቱም አለቀ። ከዚያ በኋላ የአዋሽን ተፋሰስ ተከትሎ በተንጣለለው እርሻ አፋፍ ላይ ቆሙ። አረንጓዴነቱ በጣም ያምራል። ከዚያ ሁሉ በረሓ በኋላ ይህንን ልምላሜ ማየት ነፍስን ያስደስታል። የቴምር ዛፎችና ሌሎችም የፍራፍሬ ዛፎች ይታያሉ። ወደ ውስጥ ዘልቀው መግባት አልፈለጉም።

ተመልሰው ወደ ሆቴሉ ሄደው ከበረንዳው ላይ ባሉ ወንበሮች ላይ ተቀመጡ። አንድ ዐሥር የሚሆኑ ሰዎች ተሰባስበው እየተጫወቱ ቡና ሲጠጡ ነበር የደረሱት። ሌሎች ሁለት ወጣት ፈረንጆች ደግሞ ወጣ ገባ ይላሉ። በረንዳው ሰፋ ያለ ሲሆን ብዙ ወንበሮችና የጠፍር ድንክ አልጋዎች ዝብርቅርቅ ብለው ተደርድረዋል። አቶ ደምለው ያዘዙትን አምቦ ውሃ ይዘው ፊንጠር ብለው ተቀምጠው ሲጋራቸውን ያጨሳሉ። መላኩ ደግሞ ቡና ከሚጠጡት ሰዎች ብዙም ሳይርቅ ያዘዘውን ባለ አንድ ሊትር ተኩል ውሃ እየጠጣ ሳያስበው ከሰዎቹ ጋር ማውራት ጀምሮአል። ሴቶቹና ወንዶቹ ደግሞ ባል ከሚስቱ ውጪ ቢሄድ ምንም አይደለም፣ ሚስት ግን ያን ማድረጓ ትልቅ ነውር ነው መባሉ ልክ ነው አይደለም እያሉ ይሟገታሉ። ከሁለት ስሕተቶች የቱ ነው ትክክለኛው ብሎ ሙግት ለመላኩ ባይገባውም፣ ክርክራቸው ግን ባህላችን ልክ ብሎ የተቀበለውን ነገር እየሞገተ ያለ ስለነበር ደስ ብሎት ነው ጣልቃ ሳይገባ የሰማው።

በኋላም ከቡና ጠጪዎቹ አንዱ፣ የቤቱ ባለቤት፣ ሌሎቹ ጎረቤቶች፣

ሠራተኞችና ጓደኞች እንደሆኑ ተረዱ። ሙቀቱ አሁንም መላኩን እየተፈታተነው ነው። ዕድሜያቸው ወደ ስድሳዎቹ አጋማሽ የሚጠጋ ሽማግሌ ከመላኩ አጠገብ መጥተው ሲቀመጡ ከሳቸው ጋር ወሬ ጀመሩ። አብዮቱ ሊፈነዳ ጥቂት አመት ሲቀረው ጀምሮ እዚሁ አሳይታ እንደኖሩ ቤተ ሰብም እንደሌላቸውና እዚሁ የሆቴሉ ጠባቂ ሆነው እንደሚሠሩ ነገሩት። መላኩ ምናልባትም ለመጣበት ጉዳይ ከማንም ይልቅ ሊረዱት እንደሚችሉ አምኖአል። ግማሽ ሰዓት አካባቢ አወሩ። የአሳይታ ገበያ በማግስቱ ማክሰኞም እንደሚውል ነገሩት። ከዚያም ምሽቱ ላይ እንደሚያገኛቸውና ነገም ከቻሉ ከተማውንና ገበያውን እንዲያሳዩዋቸው ሲጠይቃቸው በደስታ ተስማሙ። ትንሽ ቆየት ብለውም አቶ ባሕሩ አሊጋ እንደ ያዘላቸው ለባለቤቱቱ ተናገሩ። የክፍላቸውን ቁልፍ ተቀብለው መላኩ ወደውስጥ ሲገባ አቶ ደምለው ግን እዚያው ቡናው ጋ እያወሩ ቆዩ።

ሆቴሉ ከፊቱ የከተማው መንገድ፣ ጀርባው ደግሞ በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ከገደሉ አፋፍ ላይ ሆኖ ቁልቁል የአዋሽ ተፋሰስና እርሻዎች ይታያሉ። እይታው እጅግ የሚያምር ነው። በተለይ ከሆቴሉ ጣራ ላይ ማታና ጠዋት ያለው እይታ ማራኪ ውበት አለው። ሙቀቱ በጣም ሲበዛም እንግዶች ዕቃቸውን ከፍላቸው ቀልፈው ጣራ ላይ በተዘረጉት ድንክ አልጋዎች ላይ ነው የሚተኙት። ቤቱ ባጠቃላይ በጣም ደማቅ በሆኑ ሰማያዊ፣ አረንጓዴና ሌሎች ቀለማት ያሸበረቀ ነው። ክፍሎቹ ጠባብ ናቸው። አንድ ባለጉድጓድ የጋራ ሽንት ቤትና ሁለት በራቸው ከትክሻ ከፍ የማይል የሻወር ቤቶችን እንግዶች በወረፋ ይጠቀማሉ። መላኩ በእንዲህ ዐይነት ሽንት ቤት ሲጠቀም ከረጅም ጊዜ በኋላ ስለ ነበር በትክክል መቀመጥ እንኳ ፈትኖት ነበር። እንኳንም ወፍራም አላደረግኸኝ ብሎ ተመስገን አለ። የራሱን ሶፍት ወረቀት ያልያዘ ሰው ሊሰናከል አልያም መቶ ብሩን ለመጠቀም ይገደዳል። ደብዳቤ ስለቀረ አሁን ኪስ ውስጥም ደረሰኝ ከሌለው ኢሜይል እንደሆነ መጠቀም አይቻልም።

በጠባቧ መስኮት አካባቢውን ለመቃኘት ሞከረ። ትንኞችን ለመከላከል የተገጠመው ወንፊት ሽቦ ብዙም አልፈቀደለትም። ጣራ ላይ ወጥቶ ቁጭ ብሎ ብዙ እያሰበ ፀሐይዋ ስትጠልቅ ማየት በመቻሉ ደስ ብሎታል። መላኩ ፀሐይ ስትወጣና ስትጠልቅ ማየት ይወዳል። ስትወጣ ማየት ተስፋና የልብ ሙቀት ሲፈጥርበት፣ ስትገባ ማየት ደግሞ ትዝታንና ጥልቅ የሐሳብ ድባብን ይጥልበታል። ነገር ግን የዛሬውን ድባብ እጅግም አልወደደው።

ማታ ላይ ከዘበኛው ካቶ አያሌው ጋር ብዙ ነበር ያወሩት። ታሪኩን ሁሉ ነግሮአቸው ለምን እንደ መጣም ገለጸላቸው። አባቱን ሃሰንንም ሆነ መሰል ታሪክ ምንም እንደማያውቁ ነበር ነገሩት። በማግስቱ ግን ከዛሬ ሠላሳ ዓመት አካባቢ ጀምሮ የነበሩትን ቡናቤቶች ሁሉ እየዞሩ መጠየቅ እንደሚችሉ ተስፋ ሰጥተውታል። ፎቶውንም ቢያሳያቸው ብዙም አልጠቀመም። ኢሕአዴግ ሲገባ

አካባቢና ከዚያም በኋላ ብዙ ሰዎች ለቀው እንደወጡ ነው የነገሩት። አቶ አያሌው ብዙ ጊዜ ቢያገቡም መውለድ እንዳልቻሉና አግብተው የፈቷቸው ሴቶች ሁሉ ወልደው ከብደው የልጅ ልጅ እንዳዩና እሳቸውም ፈጣሪ የሰጣቸውን ዕጣ ይዘው መኖርን መምረጣቸውን አጫወቱት። ምናልባት እኩ ችግራቸው በህክምና በቀላሉ ይፈታ ይሆናል ብሎ አሰበ። ደግሞም ስንት ልጅ ወላጅ አጥቶ በየመንገዱ ተጥሎ ማሳደግም ይቻል ነበር ብሎ አሰበ። አቶ ባህሩን ቀደም ብሎ አመሻሹ ላይ ላጭር ጊዜ አግኝቶት ነበር፣ ከሱም ብዙ ርዳታ አላገኘም። ግን አንድ እዚህ አገር ብዙ የኖሩ አፋር ሰው እንደሚያውቅና እሳቸውን መጠየቅ እንደሚችል የተስፋ ጭላንጭል ሰጥቶት ነበር የተለያዩት።

በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ተነሥቶ ጣራው ላይ ተቀምጦ ፀሐይዋ ስትወጣ ተመልክቶ እዚያው ጸሎቱን አድርሶ ነበር ቀኑን የጀመረው። እጁን ለመታጠብ ወደ ኩሽና ሲሄድ ያየውን የንጽሕና ሁኔታ እጅግም አልወደደውም። እንኳን እዚህና በየከተማው ያሉ ትላልቅ ሆቴሎችም የኩሽናና የመታጠቢያ ቤት ንጽሕና ጉድለት ሁሌም ያበሳጨዋል። በረንዳና አጥር እያሳመርን ጓዳ ኩሽናችን ለምን እንደሚቆሸሽ ሁሌም ግራ ይገባዋል። አንዳንዴ ደግሞ ያስተሳሰባችንና የልቦናችን ነጸብራቅ ሳይሆን አይቀርም ይላል። ወደ ረፋዱ ላይ ተያይዘው ወደ ገበያው ሄዱ። የአሳይታ ገበያ ደስ ብሎታል፣ አስደንቆታልም። የሌለ ቅመማ ቅመም የለም። እህሉ፣ ፍራፍሬው፣ አትክልቱና ሸቀጣሸቀጡ አስገርሞታል። ግመሎችን በቅርብ ርቀት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየው እዚሁ ገበያ ውስጥ ነበር። ሲደርሱ ገበያው ደርቶ ነበር። ሰውም ያለውን ለመሸጥና ለመግዛት ይራኮታል።

በሚቀጥሉት ቀናት ብዙ ሰዎችን ለማናገር ሞከረ። አንዳንድ ያገሩም ሰዎች አባቱን ፍለጋ እንደመጣ ሲያውቁ ሊረዱት የሚችሉትን ጥረት ሁሉ አደረጉለት። ሆኖም እናቱ ትሠራበት የነበረውን ቡናቤትም ሆነ ሃሰንንም የሚያውቅ ሰው አልተገኘም። እሱም ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ሲያገኝ እሷን ለማጣራት ነገ ነገ ሲል እዚያው አራት ቀን አደረ። በመጨረሻም እሱ ራሱ ያሳይታን ከተማ ለማካለል የሚበቃ ዕውቀት ስለ ቀሰመ ብድግ ብሎ ለብቻው እየዞረ መጠየቅ ጀመረ። የፈራረሰውን የሱልጣን አሊ ሚራን ቤተ መንግሥትና ባካባቢው ያሉትን ከድንጋይ የተሠሩ ቤቶችን፣ እስር ቤቱን፣ የመጀመሪያውን መስጊድና ሌሎችንም ስፍራዎች ሁሉ እየዞረ ጎበኘ። ሽርጥ ማድረጉ ሰዎችን ሲያናግር የፈጠረውን ቀና ለውጥ ስለተረዳ እሱም ቋሚ ሽርጥ ለባሽ ሆኖአል። መልኩና አፍሮውም ሳይረዳው አልቀረም።

ማታ ላይ በጥቂት ቀን ቆይታው የቀረባቸውንና ሊረዱት የሞከሩትን ሰዎች እራት ጋብዞ ለመጫወት ተቀጣጥረው ስለነበር እነርሱ እስኪመጡ አመሻሹ ላይ በረንዳ ላይ ቁጭ ብሎ ቡና ሊጠጣ ወጣ። ሁለት ዕድሜያቸው ገፋ ያለ ያገሩ ሰዎች እየተጫወቱ አይቶ ከእነርሱ ብዙም ሳይርቅ ተቀመጠ። ካስተናጋጇ ጋር

ባማርኛ ሲያወሩ ስለሰማ አስተናጋጁ እንደሄደች ይቅርታ ጠይቆ አብሮ ጠጋ ብሎ ተቀመጠ። ትንሽ እንዳወራቻቸው እዚያው ተወልደው ያደጉ ሰዎች መሆናቸውን ተረዳ። ታሪኩን ባጭሩ ነግሮአቸው የናቱንና የሃሰንን ፎቶ ከሠላሳ ዓመት በፊት የተነሣ መሆኑን አስረድቶ አሳያቸው። አንደኛው ሰው ኢሕአድግ ሲገባ ጠቅልለው ወደ ጅቡቲ የገቡ እሱን የሚመስል ሃሰን የሚባል ሰው እንደሚያውቁ እየተጠራጠሩ ፊታቸውን ጨምደድ ፊታ እያደረጉ ነገሩት። በሚቀጥለው ወር ወደዚያ ሲሄዱ ሊያጣሩለት እንደሚችሉም ቃል ገቡለት። ያልጠበቀው ሲሳይ ስለነበረ አባቱን ያገኘ ያህል ነው ደስ ያለው። የራሱንና የማርቆስን ስልክ ሰጥቶአቸው፣ የእነሱንም ስልክ ወስዶ ትንሽ ተጨዋውተው የጋበዛቸው ሰዎች ስለ መጡ ተሰነባበቱ።

*   *   *

ሰሎሜ ብዙም ሰው እንዲቀበላት ስላልፈለገች በረራዋን ቀይራ ማክሰኞ ነበር የገባችው። ታክሲ ይዛ አክስቷ ቤት ስትገባ ሁሉም ነበር የደነገጡት። ከዚያም እነሶስናን ያክስቷ ባል እዚያው ሲያመጣቸው፣ የሶስናና የብርቄ ድንጋጤና ደስታ ልክ አልነበረውም። ሶስና ከሷ ላይ ተለጥፋ ማንም ሊያላቅቃት አልቻለም። አያቷ ወይዘሮ መገርቱም አገራቸው ሄደው ስለነበር ገና ረቡዕ ነው የሚገቡት።

የመላኩ አለመኖር ግርታን ስለፈጠረባቸው መምጣቱዋን ያውቅ እንደሆን ጠየቁዋት። ከከተማ ውጪ እንዳለና ራሷ እንደምትደውልለት ገልጻ አሁን ግን ትንሽ ጸጥታ እንደምትፈልግ ነገረቻቸው። ሰው አጋጥሞት የማያውቅ ችግር ሲያጋጥመው ነው እውነትም አቅሙና ጥንካሬው የሚለካው። የምንችለው ከምናወራው በብዙ እጥፍ ያነሰ መሆኑን ብዙ ጊዜ አናውቅም። እውነትን ማወቅና መኖር በደኅና ቀን ወይም በሌላ ሰው ጉዳይ የሚያምርና ቀላል ጉዳይ ይመስላል። ራሳችንን የሚፈትን ሆኖ በተለይ በምንወደው ሰውና ጉዳይ ላይ ሲመጣ ግን ውሸትን አብጠርጥረው እውነት ላይ የሚደርሱ ጥቂቶች ብቻ ናቸው። እነዚህ ደግሞ እጅግ የበሰሉ፣ ስሜታቸውን የገዙ የሕይወት ጀግኖች የምንላቸው ናቸው። የመላኩና የሰሎሜ የስንክሳርን በውሸት የተገነባ ወጥመድ ማምለጥ መቻላቸውም በዚሁ ላይ የተመሰረተ ነው የሚሆነው።

ሰሎሜ አዲሳባ ገብታ ከሦስት ቀን በኋላ ነበር ለስንክሳር የደወለችላት። ደክሞአት ስለነበር ማረፍ ፈልጋ መምጣቷን ለማንም አለመንገሯን አስረድታት ይቅርታ ጠየቀቻት። ለአክስቷ ቤት ስለሚቀርብ ሳር ቤት አካባቢ ያለው ካልዲስ ለቡና ተቀጣጥረው ትንሽ ካወሩ በኋላ ሰኞ ወደ መቀሌ እንደምትሄድና ሶስናና ብርቄም እሷ እስክትመጣ አክስቷ ጋ እንደሚሆኑ ነገረቻት። ቤቱን በሚቀጥለው ሳምንት ከኒውዮርክ የሚመጣው አጎቷ ትንሽ ስለሚቆይ እሱ እንዲያርፍበት ማቀዱንም አጫውታታለች። ሰሎሜ በጣም ከስታለች። ብዙም የማውራትና ሰውን ለማግኘትም ያላት ፍላጎቷ ጠፍቶአል። ሥራውንም እንዴት እንደምትሠራው፣

የሶለንንም ታሪክ ለመጻፍ መቻሉዋን ተጠራጥራለች። መጀመሪያ ያሰበችው ከመላኩ ጋር እንደሚጽፉትና ሶፊያም ብዙ አስተዋፅኦ ማድረግ እንደምትችል ነበር።

"እኔ ምልሽ መቀሌ ድረስ መሄዱ ግን ያስፈልጋል? በመራቅ ምን ይፈታል?" አለቻት ስንክሳር ቅንድቧን ከፍ ዝቅ እያደረገች እንደ ተጨነቀ ሆና፡፡

"ምንም የሚፈታ ነገር የለም። እኔ ግን ራቅ ብዬ አሁንም የራሴን ችግር ነው መፍታት የምፈልገው። ደግሞ ሥራውንም የምወደው ይመስለኛል። ትንሽ ከተረጋጋሁም ለመጻፍም ሳይረዳኝ አይቀርም ከቤተ ሰብም ራቅ ማለቴ" አለች ድክም ባለ ድምፅ። ወዲያው የስንክሳር ስልክ ተደውሎ ከቦርሳዋ ስታወጣው ሶፊያ ነበረች።

"ሶፊያ ናት ... ልታናግሪያት ትፈልጊያለሽ?፡ምክንያቱም በቃ ስትጨቀጭቀኝ ነበር። ኢሜይልም ደጋግማ አድርጋልሽ ምንም እንዳልመለስሽላት ነው የነገረችኝ።" አለች ስልኩን ሃሎ ከማለቷ በፊት። ሰሎሜም በግዴለሽነት መልክ ትከሻዋን ሰበቀች። ነገሩን እንደ እሺታ ወስዳ ትንሽ አዋርታት ሰሎሜን አሁን ገና እንዳገኘቻት ነግራት ስልኩን ሰጠቻት። ሶፊያ በስሜት ሆና ምን ያህል እንዳሳሰበቻትና በሰላም መሆኑን ጠየቀቻት። ስለ ቤተሰቦቿና ስለ ክብሮምም ስትጠይቃት ቅዝቅዝ ብላ ነበር ሁሉም ደኅና እንደሆኑ በደምሳሳው የነገረቻት።እሷም ደክሞአት ስለነበር ትንሽ ዐረፍ ብላ ልታገኛት ማሰቧን ስትነግራት ልታዋራት እንዳልፈለገች ቢገባትም ሶፊያም እንደምትረዳትና እስክታያትም እንዴት እንደቸኰለች ነግራት ከመዝጋቷ በፊት፡-

"መላኩና ማርቆስ የሚገርሙ ሰዎች ናቸው። መቂም ሄደን የመላኩን ቤተ ሰቦች ተዋወቅን። በሕይወቴ እንደዚህ ደስ ብሎኝ አያውቅም። የሚገርም ልጅ ነው። እኔ ነኝ ወይስ የሆነ ሶለንን የሚመስል ነገር አለው?" አለቻት ሳታስበው ፍልቅልቅ ብላ፡፡

"ይቅርታ ሶፊያ አሁን ትንሽ ራሴንም ስላመመኝ ብዙ ማውራት አልችልም። ሰሞኑን ስንገናኝ ብናወራስ?" አለች ስንክሳር ከነገረቻት ጋር ነገሩ እየተገጣጠመባትና የሶፊያ ዐይናውጣነት እያናደዳት።

"እሺ እሺ ይቅርታ። በቃ ደስ ስላለኝ ለፈለፍኩብሽ አይደል? በቃ ስትችዪ ዐረፍ ብለሽ ደውይልኝ ያንቺን ስልክ እጠብቃለሁ። መላኩም አባቱን ፍለጋ ምንድነው ስሙ ጠፋኝ የከተማው ስም እንደሄደ ነው በስልክ አገኘሁሽው እንዴ?" ስትላት፡- "እምም.. አዎን ሰምቼያለሁ ... ምንም አይደለም... ይቅርታ ትንሽ አሁን ራስ ምታት ስላስቸገረኝ ነው። ሶፊያ ደስ ብሎኛል ስለለመድሽ። በቃ እደውልልሻለሁ። ስንክሳር ጋ ልመልስሽ።" ብላ ስልኩን ለስንክሳር ሰጠቻት።

ስንክሳርም ሶፊያን ትንሽ አውርታ ስልኩን ዘግታ ሰሎሜን ለማጽናናት ርእሱን ለውጣ ስለ አጎቷና ልትጽፌው ስላለው መጽሐፍ ምናምን ማውራት ብትሞክርም፣ ሰሎሜን ከገባችበት ድብርት ውስጥ ልታወጣት አልቻለችም። በመጨረሻም ቤት ሄደሽ ብታርፌ ይሻላል ብላ ተለያዩ። ሐሳብ ውስጥ ገብታ ስትነዳ ሁለት ጊዜ ከሌላ መኪና ጋር ልትጋጭ ነበር። ከዚያም እቤት ገብታ ራትም ሳትበላ በጊዜ ተኛች።

መላኩ ከክር የቀጠነች ተስፋውን ይዞ አንድ ቀን ደሴ አድረው በየመሃሉ እያረፉ እሑድ ከሰዓት ላይ አዲሳባ ገቡ። ማርቆስ ደግሞ ወደ አዋሳ ሐሙስ ነበር ለሥራ የሄደው። የጁስ ቤቱን ዕቃዎችም እግረ መንገዱን ለመዐዛ አድርሶላታል። ሰፋ ያለ ቤት ተከራይታ ያሉትን ዕቃዎች አስተካክላ ስትጠብቀው ነበር። ትንሽ ሥራዋ ወጣ ወጣ ሲልና መታየት ሲጀምር እንቅፋቱም በዚያው ልክ በየሰበቡ ፊቷ እየተደነቀረ አላሠራ እያላት ነው። ከቀበሌና ከተማ መስተዳደር አካባቢ በፊታድ ሰበብ በሆነው ባልሆነው ሲያመላልሷት ከርማለች። እንጀራ ከምታቀርብላቸው ሥጋ ቤቶችና ሆቴሎችም የተወሰኑት በቅናሽ ዋጋ ሌላ ደንበኛ ስላገኙ ከሷ መረከቡን አቁመውባታል። በኋላ እንደተረዳችው እነሱ ጎረቤቶቿ የሆኑና ልትረዳቸው ያሰበቻቸው ሰዎች ናቸው ዋጋዋን ሰብረው ለማቅረብ የተስማሙት። ፈጠራ በሞተበት ማኅበረሰብ ውስጥ ኩረጃንና ሙስናን ማሸነፍ ትልቁ ፈተና እንደሆነ በቅጡም ገና አልተገለጠላትም። በዚህና ሰሞኑን ባጋጠሟት ውጣ ውረዶች ጭንቅላቷ ተበጥብጦ ነው ማርቆስ ያገኛት። ያለወትሮዋ ስሜቷ ዝቅ ብሎ ስላየት፦

"መዐዛ ሰላም አይደለም እንዴ? ምነው የደበረሽ ትመስያለሽ?" አለ ቂጭ ብሎ የቀረበለትን ለስላሳ እየተጎነጨ።

የሆነውን ሁሉ ካስረዳችው በኋላ "ምን እባክህ ገና እኮ ዕልፍ ሳትል እልፍ መከራ ነው የሚጋፈጥህ። ሥራው ሳይሆን የሰዉ ክፋትና ተንኰል እኮ ነው አቅምህን የሚበላው።" ብላ እጇን ደገፍ ብላ ዝም አለች።

"መዐዛ ይህ እኮ የሚያሳየው በትክክለኛው መንገድ ላይ እንዳለሽ ነው። ደግሞ አንቺን ጠንካራ የሚያደርግሽ ሥራው ብቻ ሳይሆን እንደዚህ ዐይነት ዕንቅፋቶችንም ማለፍ መቻልሽ ነው። ሰዉ ለሥራ አለርጂክ ስለሆነ አንቺ ስትሠሪ በርበሬ እንደታጠነ ሰው ነው የሚያቅበጠብጠው። አንዱ ሠራተኛ ይመስላል ሌላው አጋዥ፣ ሌላው ደግሞ ሕግ አስከባሪ። እውነቱ ግን ሰነፍና ምቀኛ መሆናቸው ነው። አንዱ እታች ከሚተረማመሰው፣ ግራና ቀኙን ከማያውቀው፣ ከማይሠራ ወይም ከማያሠራው ብዙኃን ራቅ እስክትዪ ድረስ መጽናት ነው። አይዞሽ ይሄ ሁሉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይረሳል። ደግሞ ይሄንን ሁሉ አትነኩሮት ከሳብሽ የምትሰሪው ነገር ምን ያህል ጥሩ መሆኑን ነው የሚያሳየው።" ብሎ ዲስኩሩን ሲጨርስ መዐዛ ቀበል አድርጋ፡

"ልቤማ እኮ ይገባዋል ግን በቃ ያናድድሃል። ደግሞ ስንቱን ታግለህ

ትችለዋለህ? ደግሞ ጨርሼም ተስፋ እንዳልቆርጥ የሚያደርገኝ በሌላ በኩል አምላኬ አለ አጠገቤ፣ አንዱ በር ሲዘጋ ሌላውን እመቤቴ ትከፍተዋለች። የሚገርምህ ይህ ሲያስከፉኝና ሲያሳርረኝ በማግስቱ ሦስት የአበባ እርሻዎች ናቸው ካፌ እንድከፍት ፈቃድ የሰጡኝ። ስለዚህ እያንዳንዱ ፈተና የሌላ ድል መምጫ እንደሆነ ነው እየገባኝ የመጣው።" አለችና ዘለቃ ከጓዳ ምሳ በትሪ ይዛ ስትመጣ አይታ ጠረጴዛውን ማቀራረብ ስትጀምር

"አዪ መዐዛ በጣም ነው የምቸኩለው። መሄድ አለብኝ። ደግሞ በቅርብ ነው የበላነው። አሁን እዚያው ሄደን ቶሎ ዕቃውን ይግጠሙልሽ፣ ሰዎቹም ይቸኩላሉ ወደ አዲሳባ ለመመለስ። እኔም ወደ አዋሳ ቶሎ መድረስ አለብኝ።" ብሎ ብትል ብትሠራው አሻፈረኝ አለ። በተከራየችው አዲስ ቤት ውስጥ ዕቃዎቹን ሁሉ አስገቡላት፣ ማሽኖቹንም ቦታ ቦታ አስይዘው ገጣጠሙላት። ሰዎቹን ወደ አዲሳባ ከሸኘ በኋላ እሱም እነመዐዛን ተሰናብቶ ወደ አዋሳ ጉዞውን ቀጠለ። መዐዛም ሆነች ቤተ ሰቡ ማርቆስን መሸከም እስኪያቅተው ነው ምስጋናቸውን ያዘነቡበት። ሰሞኑን ባጋጠማት ተግዳሮት ልቧ ወድቆ የነበረችው መዐዛም እንደገና ተስፋዋ አንሰራርቶ ጉልበት ተሞላች። ማርቆስ ወደ አዲሳባ የሚመለሰው ገና ማክሰኞ ነው። ከሰሎሜ ጋር የነበራትን ግራ የሚያጋባ ዐጭር የስልክ ንግግር ሶፊያ ከነገረችው በኋላ ሰሎሜ ጋ ደጋግሞ ቢደውልም፣ ስላላነሣችለት የሚያደርገው ግራ ገብቶታል። ስንክሳር ጋ መደወል ደግሞ አልፈለገም፣ ስለዚህ ረጋ ብሎ አክስቷን ለማናገር አሰበ።

መላኩ ሰኞ ሥራ ሲገባ ብዙ ነገር ተቀልሎ ነበር የጠበቀው። ሶፊያንም ስንክሳርንም በስልክ አግኝቶአቸው ሥራው በጣም ስለተቆለለበት ከረቡዕ በፊት ሊያገኛቸው እንደማይችል ነግሯቸዋል። በማግስቱ ደግሞ ድሬዳዋ ያለው ፕሮጀክት ላይ ማናጀሩ ለቆ ችግር ስለተፈጠረ ለአምስት ቀን ወደዛው በመሄዱ ከማርቆስ ጋርም ተላለፉ። በዚህ መሃል ሰሎሜም መቀሌ ሄዳ አዲሱን ሥራ ጀምራለች። መቀሌ ስትሄድ ከልጅነቷ ጀምሮ አግኝታቸው የማታውቃቸውን የናቷን አባትና ዘመዶቿን ብዙም ሳትቆይ ነበር ያገኘቻቸው። እነሱም ሆቴል አታርፊም ብለው ሳምንቱን ሙሉ ከቤት ቤት እያዞሩ ሲጋብዟት ከረሙ። አዲስ አበባ ደግሞ አክስቷና አያቷ የሰሎሜ ባሕርይ እንደዚህ መለዋወጥ ከሶለን ሞት ጋር የተያያዘ ቢመስላቸውም፣ የመላኩ መጥፋት ግን ከንክኖአቸዋል። እነሱም ደጋግመው ቢደውሉለትም ስልካቸውን ስላልመለሰ ግራ ገብቶአቸዋል።

መላኩ ከድሬዳዋ ሲመለስ ማርቆስ ደፍሮ ሊያናግረው ቢሞክርም፣ እንደ በፊቱ ቂጣ ቂጣ ሳይለው አሁንም አንድ ሁለት ሳምንት እንዲሰጠውና ከዚያ በኋላ ሊነጋገሩበት እንደሚችሉ ነበር የነገረው። በሌላ በኩል ወደ አሜሪካ በቅርብ ሲሄድ ትንሽ ከሁሉም ነገር ዕረፍት አግኝቶ ሕይወቱን ለማስተካከል እንደሚረዳው አስቦአል። ማርቆስ በሱና በሰሎሜ መካከል ገብቶ ለማስታረቅ መሞከሩ ምንም ፋይዳ እንደሌለውና ሊቋቋመው የማይችለውን ቁስል እንዳይፈጥርበትም

ፈርቷል። እሱ የመረጠው መንገድ ነገሩ ለጊዜው እንደዚሁ እንደተዘጋ እንዲቀር ነው። ማርቆስ ጉዳዩን ከሰሎሜ እክስት ጋርም ተወያይቶበታል። እሷም እሱም ለማውራት ፈቃደኛ አለመሆን ብቻ ሳይሆን አሻፈረኝ ስላሉ ትንሽ አይተዋቸው ነገሩ በዚህ ከቀጠለ፣ ሌላ መንገድ ሊፈልጉ ነው የተስማሙት።

ክብሮም በበኩሉ እየደወለ ያለውን ሁኔታ ከስንክሳር ጋር መመካከሩንና ማውራታቸውን ቀጥለዋል። ያለውን ሁኔታም ስታስረዳው

"ሰሎሜ መቀሌ ገብታለች። መላኩንም ሆነ ሶፊያን ማየትም፣ ስለነሱ መስማትም አስጠልቷታል። ሶፊያ እኮ ሳላስበው ጥሩ መጠቀሚያ ነው የሆነችን። ግን አሁን ትልቁ ቁልፍ በሁለቱ መካከል ያለው ገደል በሆነ መንገድ ሳይደፈን እሷ ይሄ አገር አስጠልቷት እንድትመጣ ማድረግ ነው።፡አሁን መቀሌ መሆኗ ትንሽ ጊዜ ይገዛልናል። መሌም ፎቶውን ካየ በኋላ እንደ ዕብድ ነው ያደረገው። አሁን ሰሎሜ ለሚለው ስም ሁሉ ነው አለርጂክ የሆነው።" ብላ በረጅሙ ሥቃ " አንተ አሁኑን ማሰብ ያለብህ እንዴት እዚህ መጥተህ ምን ያህል እንዳዘንህ ነግረሃት ይቅርታ በመጠየቅ የሷን ልብ ለማለሳለስ ነው። ድሮውንም ስለምትወድህ በዚያው ቀስ እያልክ በዚህ ከባድ ጊዜ አብረሃት ከሆንክ ምንም ጥያቄ የለውም በጥቂት ጊዜ የራስህ ታደርጋታለህ። ይህም ትንሽ እንጥፍጣፊ ተስፋ እንኳ ቢኖር ሙሉ በሙሉ ነው ከሁለቱም ልብ ውስጥ የሚገድለው። በተለይ መላኩ አንተ እሷን ልትጠይቅ እዚህ እንደመጣህ ሲያውቅ።" አለች ድል ድል በሚሸት ድምፅ።

"አሳቡ ጥሩ ነበር ግን እኮ እኔ ምንም ፈቃድ የለኝም። በሆነ መንገድ ትንሽ ጊዜ አግኝቼ ብመጣ እንኳን ምን ተስፋ አለው ብለሽ ነው። እዚህ ራሱ አላናግር ብላኝ በስንት መከራ ነው ስትሄድ እንኳ ያዋራችኝ" አለ ክብሮም ነገሩ እየከበደው፡፡

"ክብርሽ በቃ እኮ አለቀ። አሁን አየህ እሷ እዚህ ድረስ መጥተህ ይቅርታ ስትጠይቃት በየዋህነት እንዳደረግኸው ደግሞም ምን ያህል ለሷ ጥንቃቄ እንደምታደርግ ነው የሚያሳያት። ሴት ልጅ ደግሞ ጥንቃቄ በሚያደርግና ትሑት በሆነ ሰው መረታቷ የማይቀር ነው። እኔ ይሄን ሁሉ ለመላኩ ብዬ የማደርገው ለምን ብዬ ይመስልሃል። ቁንጅናው ወይም ሀብቱ እኮ አይደለም። ደግሞ ድንገተኛ የቤተሰብ ጉዳይ አጋጥሞኝ አፍሪካ ልሄድ ነው ብትላቸው እምቢ አይሉህም። ነገሩ ድንገትኛ የቤተ ሰብ ጉዳይ እንደሆነ አትርሳው! " ብላ ቆፍጠን ባለ ድምጽ ስትነግረው ነገሩ አሳማኝ ሆኖ ታየው፡፡

"እሺ. እስኪ ሁሉንም ነገ አይቼ እደውልልሻለሁ" ብሎ ትንሽ አውርተው ስልኩን ዘጉት። ከዚያም ሥራ ቦታ የቤተ ሰብ ጉዳይ ገጥሞኝ አፍሪካ ልሄድ ነው ብሎ የቤተሰብ ፈቃድ ተሰጠው። ለሕያውም እንዴት እንደሚነግረው ግራ ስለገባው

ሳይነግረው ነው ብድግ ብሎ የሄደው። አዲስ አበባ ከገባ በኋላ ነው ከከተማ ውጪ መሆኑንና ከሳምንት በኋላ እንደሚመለስ ብቻ ኢሜይል ያደረገለት። ሕያውም ከሰሎሜ ጋር ያላቸው ጓደኝነት ክብሮምን እያመሳቀለው እንዳለ ቢያውቅም፣ ምን ብሎ እንደሚረዳው ስላላወቀ ዝምታን ነው የመረጠው። እንኳን ጓደኛው ወዶ እንኳ ደግሞ ለሱ ግድ እንደሌላት ካወቀ ምን ማድረግ ይችላል?

መላኩ ለአሜሪካው ሥልጠና ለመሄድ ዝግጅት እያደረገ እያለ ከዚያው ያልተጠበቀ ዜና በስልክ መጣ። ስልኩን የደወሉት የማራ እናት ነበሩ። ጊዜው ከሌሊቱ ስምንት አካባቢ ስለነበር ከእንቅልፉ ደንግጦ ነው የተነሣው። በዚህ ሰዓት ደውለውለት ስለማያውቁ የድምፃቸውም ሁኔታ የሆነ መጥፎ ነገር መኖሩን ይናገር ነበር። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፡-

"ምንድነው እቴትዬ ሰላም አይደለም እንዴ? ደኅና ናችሁ?" አለ መላኩ እየተደነባበረ። እሱም እንደነማራ እቴትዬ ነው የሚላቸው።

"አዬ መላክዬ ምን ሰላም አለ ባክህ። ጉድ ሆኜልሃለሁ ልጄ" ብለው ልቅሶአቸውን ሲለቁት ጭራሽ ተረብሾ፣ "ምንድነው? ምን ሆናችሁ?" አለ ድንጋጤው የእንቅልፍ ድምፁን እያጠፋው፡፡

"ማራ ማራ .." ብለው አሁንም ሲያለቅሱ የባሰውን የሚይዝ የሚለቀውን አጥቶ፣ "እ እ .. ማራ ምን ሆነች ምን ሆነች .." አለ ደንግጦ ወደ ሳሎኑ በደመነፍሱ እየሄደ፡፡

"የ መከረኛ ባሏ ... እሷንም ልጆቹንም... ኧረ እንዴት ነው የሚወራው... አምላኬ..." እንጃ እያሉ ልቅሶአቸውን ሲቀጥሉ፣ "እቴትዬ ባክሽን እስኪ ተረጋግተሽ ንገሪኝ... ምን ሆኑ ምን አደረጋቸው?" አለ ብዙ ክፉ ነገር አእምሮውን እየሞላው፡፡

"ባለፈው ሰሞን ትንሽ ተጋጭተው ስለነበር እሷን መትቶአት ትልቁ ልጁ 911 ደውሎ ፖሊስ ጠርቶ እነሱም ወስደው አሰሩት። በማዕቀብና በማስጠንቀቂያ ካሥር ቀን በኋላ ለቀቁት፣ አጠገባቸው እንዳትደርስ ብለው። ትናንት ይሄው ጠዋት ላይ ማንም ሳያስበው ቤት ሄዶ አንድ አንድ ሲሉ ጭቅጭቅ ተፈጥሮ እንዴት እንደሆነ አይታወቅም ትልቁንና ትንሹን ልጅ ገድሎአቸው፣ እሷንም ባምስት ጥይት አርከፍክፎባት በመጨረሻም ራሱንም ገድሎ ቤቱ ሁሉ ሬሳ በሬሳ ሆኖ ተገኘ። ምንስ ተብሎ ይወራል ..." አሉ አሁንም ነገሩን እንዴት እንደሚናገሩት ግራ የገባቸው የማራ እናት "እኔ አላምንም.. አምላኬ...!" ብሎ እሱም ሮሮ ማልቀስ ጀመረ። እንደምንም ራሱን ተቆጣጥሮ "ማራስ እንዴት ናት ተርፋለች?" አለ

የደመነፍሱን፡፡

“እሷ አሁን ሆስፒታል አይሲዩ ናት። ሁለቱ ልጆች ያው ወዲያው ነው የሞቱት። ትንሿ ሚጢዬም ያን ሁሉ ነገር ሳታይ አልቀረችም እስካሁንም በድን እንደሆነች ነው። እሷም ሆስፒታል ናት። እንጃልኝ ዘንድሮ እንዴት እንደምሆነው ልጄ...” እያሉ ሲያለቅሱ እሱም አብሮአቸው ማልቀስ ብቻ ነበር የቻለው። የተወሰነ አውርተው የቻለውን ያህል አረጋግቶአቸው ከሳቸው ጋ ስልኩን እንደዘጋ አሁንም እያለቀሰ ማርቆስ ጋ ደውሎ ባስቸኳይ እንዲመጣ ነገረው። ወዲያ ወዲህ እያለ የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቶ ሲንጐራደድ ማርቆስ በሩን አንኳኳ።

ቅንብር

ስንክሳር የክብሮምን ጉዞ በማቀናጀት ተጠምዳለች። አብራው መቀሌ ለመሄድም አስባለች። ሰሎሜ መቀሌ እንደምትቆይ አረጋግጣለች። በሚቀጥለው ሳምንት ላይ መጥታ እንደምትጐበኛትና አገሩንም ለማየት እንደምትፈልግ ስትነግራት እያቅማማች ነው ሰሎሜ እሺ ያለቻት። የክብሮምን መምጣት ቢያንስ አሁን ልትነግራት አልፈለገችም። ምንም ሳታውቅ ድንገት እሱን ይዛ መቀሌ መሄድ እንደሌለባትም አውቃለች። ስለዚህ ምን ማድረግ እንዳለባት እያሰበች ነው። ስለዚህ ዋና ግቧ ሰሎሜን ቢቻል አሳምኖ ከክብሮም ጋር እንዲሆኑ ማድረግና ወደ አሜሪካ መመለሷን ማፋጠን ሲሆን፤ ካልተቻለ ግን እዚህ መኖሩን ጠልታው ወደ አሜሪካ እንድትሄድ ነገሮችን ማመቻቸት ነው።

ስንክሳር እስካሁን ቅንብሯና እቅዷ ሁሉ ባሰበችው መንገድ እየሄደላት ይመስላል። ግን ያሰበችው ሁሉ ቢሆንና ከመላኩ ጋር መሆን ብትችል፤ ከሰሎሜ ጋር ያላትን ግንኙነት እንዴት ልታደርገው ነው? ሁሉንም ነገር ቀድሞ የማሰብ ዝንባሌ ያለው የስንክሳር ጭንቅላት ይህንንም ማውጠንጠኑ አልቀረም። ተበዳይ ሆና ከሰሎሜና ከክብሮም ጋር እንዴት እንደምትኰራረፍ ዐቅዳለች። ከመላኩ ጋር ያላቸውን ጓደኝነትም እንደተጐዳ ሆና በመቅረብ ቅርርባቸውን አጠናክራ ግቧን ማሳካት ነው። ማርቆስንና መላኩን ማራራቅም የግድ ሳያስፈልግ እንደማይቀር ከወዲሁ ተገንዝባለች። እንዴ ሰሎሜ ከሄደች በኋላ ያ የሚቀጥለው ሥራዋ ስለሆነ ለርሱም ነገር እየጐነጐነችለት ነው። ሶፊያ ለዚህ ሳትጠቅማት እንደማትቀር ጠርጥራለች። ነገር ግን ማርቆስን ከመጀመሪያውም በማይገባት ሁኔታ ስለምትፈራው ይሄኛው ሥራ ሳይከብድባት እንደማይቀር ልቧ አውቆታል።

የሁለቱ የሣራ ልጆች አሟሟት የካንሳስ ከተማን ሕዝብ ሁሉ ያስደነገጠ ክሥተት ሆኖአል። ደጋግሞ በጥይት ስለመታት ብዙ ደም ፈስሷት ቶሎ ራሷን መሳቷ ከሞት ያተረፋት ሣራ አሁንም ሆስፒታል ውስጥ ለሕይወቷ እየታገለች ነው። በዚህም ምክንያት በልጆቿ ቀብር ሥነ ስርዐት ላይ መገኘት አልቻለችም። መካከለኛ ልጇም በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ሆስፒታል ተኝታ አንድም ቃል አይወጣትም። ትንሽ እንቅልፍ ሲወስዳት ደንብራ ትነሣለች። ደጋግማም አልጋዋ

ላይ ሽንቷን ትስታለች። አያቷ ወይዘሮ የትናየት እንዲለዩአት አትፈልግም። ከዚህም የተነሣ ቤተ ሰቡ ሁሉ በከፍተኛ ኀዘንና ንዴት ውስጥ ነው የሚገኘው።

አብረዋት የሚሠሩት ሃኪሞችና ነርሶችም ድንጋጤው እስካሁን አልለቀቃቸውም። እንዲህ ዐይነቱ ጭካኔ የተሞላው ግድያ የሚፈጸመው አልፎ አልፎ ነው። በነገሩ አበሻው ማኅበረሰብ በከፍተኛ እፍረትና ድንጋጤ ውስጥ ገብቶ አንገቱን ደፍቶአል። ብዙ ጋዜጠኞች ፍርድ ቤቱ ምንተስኖትን መልቀቅ እንዳልነበረበትና ሚስቱ መክሰስ ብትፈልግም ባትፈልግም፣ ጤነኛነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ቢታሰር ኖሮ፣ ይሄ ሁሉ ባልደረሰ ብለው ወሬው ላይ ቤንዚን እየጨመሩ አጧጡፈውታል። የምንተስኖት ወላጆች ወሬውን ሲሰሙ የሚገቡበት ነው ያጡት። ከመሄዱ በፊት ያሰማ የነበረውን ዛቻ ነው የፈጸመው። ያኔ አባቱ ነገሩ የንዴት ቀረርቶ እንጂ የምር አልመሰላቸውም። እናቱ ግን አሁንም እናት ናቸውና ደግሞም ማራን ከድሮም ስለማይወዷት ጥፋቱ የልጃቸው ሳይሆን፣ የሷ መሆኑን ነው ማመንም ማሳመንም የሚፈልጉት። እሷ እንደዚያ ባታናድደው ኖሮ የሳቸው ልጅ የዋህና ሆደ ቡቡ እንጂ ነፍሰ ገዳይ እንዳልሆነ ሽንጣቸውን ገትረው ይሟገታሉ። ሬሳው ተልኮ አዲሳባ መቀበሩ የሚያመጣውን ማኅበራዊ መዘዝ በማየት እዚያው በመቀበሩ ተስማምተው ነው የተቀመጡት።

መላኩ ነገሩን የሰማው ዐርብ ሌሊት ለቅዳሜ አጥቢያ ሲሆን ለቪዛ ኤምባሲ የሚገባው ገና ሰኞ ነው። ሥልጠናው የሚጀምረው ከሳምንት በኋላ ቢሆንም፣ ቪዛውን ካገኘ ሰኞውኑ ማታ ለመሄድ ነው ያሰበው። ከማርቆስ ጋር ሆነው በድጋሚ ወይዘሮ የትናየት ጋ ደውለው ነገሩን እንደገና በደንብ ጠየቋቸው። ሁሉ ነገር ደህና ቢሆን እንኳ ቢያንስ ሁለት ሳምንት ያህል ማራ ሆስፒታል መቆየት እንደሚኖርባት ነው ሐኪሞቹ የነገሩዋቸው። መላኩ ቪዛውን ከሰጡት ሰኞ ማታ ለመሄድ እንዳቀደና ቲኬቱን በካንሳስ በኩል እንደሚያደርገው ነግሮአቸው የማራ እናት ሊቀበሉት ዐቅደዋል።

የሆነው ነገር እንዲህ ነው። ምንተስኖት ታስሮ ከተፈታ በኋላ በንዴትና በጸጸት ሲበሳጭ ነበር። ሐሙስ ማታ ሲጠጣ አምሽቶ ሌሊት ላይ ነበር ወደ ቤት የገባው። ጠዋት ላይ ሲነሣ ብስጭቱ ጨምሮ ነበር። ደጋግሞ ቢደውልም ማራ ስልኩን ስላላነሣችለት በንዴት ጦፎ ነበር ወደ ቤት የሄደው። ማራ ደግሞ ልጆቹን ትምህርት ቤት አድርሳ ሥራ ለመግባት በጥድፊያ ላይ ነበረች። ትንሹን ልጅ እያበላችና ከትልቁ ልጅ ጋር እያወራች ነበር በሩን በርግዶ የገባው። አንድ አንድ እያለ የጀመሩት ንትርክ ግሎ እሱም ደረጃውን ወጥቶ ወደ መኝታ ቤት አመራ። ከቤት የማይወጣ ከሆነ ፖሊስ እንደምትጠራ ስትነግረው ተመልሶ ክንዷን አፈፍ አድርጎ እየታገለችው ይዟት ወደ ላይ ወጣ።

ቁምሣጥኑ ውስጥ ያስቀመጠውን ሽጉጡን ማራን ለማስፈራራት አውጥቶ ከሷ ጋር እየተፏፏኹ ወደ ታች ሲወርዱ፣ ትልቁ ልጅ ስልኩን ፖሊስ ጋ ደውሎ

እያለቀሰ ሲናገር አይቶት በደም ፍላት የተኰሰው ጥይት እዛው ስልኩን እንደያዘ ዘረረው። ማራም እየጮኸች እጁን ነክሳ ሽጉጡን አስጥላው ወደ ልጇ ስትሮጥ የወደቀውን ሽጉጥ አንስቶ እሷንም ደጋግሞ በጥይት መታት። ዞር ሲል ትንሹ ልጅ ደግሞ ይጮኻል። አሁንም የሚያደርገውን የማያውቀው በደም የሰከረው ምንተስኖት 'አንተስ ብትሆን እሷ ከሞተች ማን ሊያሳድግህ ነው? የፈረንጅ መጫወቻ ከምትሆን እነሱኑ ብትቀላቀል ይሻልሃል' ብሎ እሱንም ባንድ ጥይት ጨረሰው። በመጨረሻም የራሱን ጭንቅላት በያዘው ሽጉጥ በታትኖ ብዙም ሳይቆይ ፖሊሶቹ ደረሱ። ይህንን ሁሉ ነገር ከበር ሥር ተደብቃ ስታይ የነበረችው መካከለኛዋ የማራ ልጅ ግን እስከ አሁንም አንድ ቃል እንኳ አልወጣትም።

*   *   *

ስንክሳር ሰሞኑን ከውጪ የመጡ ጓደኞቿ ስላልለቀቋት ከመላኩ ጋር ብዙም አልተገናኙም። የሚደዋወሉትም ላጭር ደቂቃዎች ስለነበረ ናፍቋታል። መላኩ ደግሞ ሰኞ ኢምባሲ ገብቶ ቪዛ እስኪያገኝና መሄዱ እርግጠኛ እስከሚሆን ድረስ ለስንክሳር መንገር አልፈለገም። ማርቆስን ለሶፊያ እስከ ሰኞ እንዳይነግራት ያስጠነቀቀው ለዚሁ ብሎ ነው። ሰኞ ጠዋት ላይ ከአጭር ኢንተርቪው በኋላ ነበር ያለ ብዙ ችግር ቪዛው የተሰጠው። ስለዚህም የቀረችው ከሰዓት በኋላ አጭር ጊዜ ስለነበረች ትንፋሽም አላገኘም። ስንክሳር የመላኩን የዚያን ለታውኑ ማታ መሄድ ስትሰማ በድንጋጤ ክው አለች። ገና ከናዝሬት እየመጡ ስለነበር ባለበት ቦታ ሄዳ ልታገኘው ተለማምጣው ተቀጣጠሩ። ነገሩን ለሰሎሜ እንዴት አድርጋ መንገር እንዳለባት ለማወቅ ዕቅዶቿን ሁሉ እንደገና ማየት እንዳለባት አሰበች። ነገሩ ፈጽሞ ያልጠበቀችው ስለሆነ ግራ ገብቷታል። መላኩም አንዳንድ ነገሮችን ሳይነግራት ሲያደርግ የመጀመሪያው ስላልሆነ ትንሽ ነገሩ ሳይረብሻት አልቀረም። ቢሆንም አሁን ትኩረቷን ሁሉ እሱን በሰላም መሸኘቱ ላይ ማድረግ እንዳለባት ወሰነች።

መላኩ ከመሄዱ በፊት ማርቆስ ስለ ሰሎሜ ደጋግሞ ሊያናግረው ቢሞክርም አልሆነለትም። አሁን ማንም ምንም ማድረግ እንደማይችልና ሁሉንም ነገር ጊዜ ቢፈታው እንደሚመርጥ ነው የነገረው። በዚህ ጊዜ የሱ ትልቅ ጉዳይ ማራ እንደሆነች ነግሮት ጉዳዩን እንደተንጠለጠለ ተወው። ምናልባት ቢሰማኝ ብሎ እሱ ራሱ የሚያውቀውን በተንኰል ያጣትን የጓደኛውን የማርታን ታሪክ አስታውሶት፣ በሠራው ስሕተት ሕይወቱ ምን ያህል ተመሳቅሎ እስከ ዛሬ ድረስ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያደርግበት አስታወሰው። መላኩም የሱ ሁኔታ ከማርቆስ በጣም የተለየ እንደሆነና አንድ ቀን ታሪኩን ሲሰማውም እንደሚረዳው ሊያስረዳው ሞከረ። አሁን ግን መነጋገሩ በማይፈልገው የስሜት ረመጥ ውስጥ እንደሚጨምረውና ለዚያ የሚበቃ አቅም እንደሌለው ነገረው። እንደዚህ እየተባባሉ

ለጉዞው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሲገዙ ቆዩ።

በሌላ በኩል ሰሎሜ መቀሌን ለመልመድም ለመውደድም እየጣረች ነው። አሜሪካ ከርሞ ለመጣ ሰው እንኳን መቀሌ አዲሳባም ግራ ነው። የፈለጉትን በፈለጉበት ጊዜና መጠን ማግኘት አይታሰብም። ጸጥታና ሰላሙን ግን ወዳዋለች። አሁንም በሀልሟ እንደምትኖር፣ በእንቅልፍ ልቧም እንደምትራመድ ቢሰማትም፣ ቀስ እያለች ግን ሁሉንም ነገር እየለመደች ነው። አያቷ አቶ አጽበሃ ዕድሜያቸው ከሰባው አጋማሽ የዘለለ ቢሆንም፣ አሁንም አእምሮአቸው ብሩህ፣ ሰውነታቸው ሸንቅጥ ያለ ነው። አንዳንዴ የልጃቸውን ታክሲ ይይዙና ከተማውን እየዞሩ የድሮውንና ያሁኑን መቀሌ እያነጻጸሩ ሲያስጎበኟት ደስ ይላታል፤ እሳቸውም ትልቅ ኩራት ይሰማቸዋል።

የአቶ አጽበሃ ትንሹ ልጃቸው ተግባቢና ሰው ወዳድ ነው። ለሰሎሜ የሚያስፈልጋትን ሁሉ የሚያደርግላት እሱ ነው። ትንሹ አጎቴ ነው የምትለው ስትቀልድበት። ሰሎሜ በመጣች በሦስተኛው ቀን ነበር ከተማውን አዙሮ ያሳያት። ብዙም ሳይቆይ ነበር 'ዛሬ አንድ የምወዳትን ቁርስ ቤት አሳይሻለሁ' ብሎ በጣም በጠዋቱ ሞቅ ብሎ ወደ ደራው የንግድ ሰፈር አምጥቶ ሰው ከታጨቀባት ጠባብ ቤት ይዞአት የገባው። አስተናጋጆቹ ሁሉ በስሙ ነው የሚያውቁት። በጣም ጨኸት ቢኖርም ሁሉም ሰው ደስተኛ ይመስላል። ቤቷ ውስጥ ያሉትን ተስተናጋጆች ቀርቶ አስተናጋጆቹንም መቻሏ ይገርማል። መቀመጫ ቦታ ስለሌለ አስተናጋጆቹ እየሣቁና እየጮኹ ሰውን ጠጋ ጠጋ እያደረጉ ነው ዐዲስ የመጣውን የሚያስቀምጡት። ምግቡን ጨርሶ የደራ ወሬ የያዘውንም 'የበላን ወደ ሥራ ከፊት ከፊት' እያሉ እየቀለዱም እያሣቁም ሊበላ ለሚመጣው ቦታ ያስለቅቃሉ። ሰዉ የሚለውን በተሰባበረ አማርኛው ትርጉሙን የሚነግራት ያው ትንሹ አጎቷ ነው። ቁርስ ምን ምን እንዳለ ሲጠይቁ..

"ናሺፍ ... ስፐሺያል ስልስ ... ፉል ... ማኅበራዊ ..." እያለ ዘረዘረው... ሰሎሜ መያዝ አቅቷት ስትሥቅ ያየው ልዑል ... በትግርኛ የሆነ የሆነ ነገር ብሎት ተሣሥቀው፣ አስተናጋጁ ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ ኩሽና ቸኰለ።

ጣራና ግድግዳውን፣ ከዚያም ሰዉን በማየት የተደነቀችውን ሰሎሜን፣ "አንቺ ስሚ ብዬው ነው እንጂ ... ሳይነግርም እኔም ላዝ እችላለሁ... ምንም ችግር የለም በቃ እዚህ ከመጣሽ ማቆም የለም... ነገም አምጣኝ ነው የሚያስብልሽ። ችግር የለም እንመጣለን።" አለ እሱም እየሣቀ ትንሽ በተሸራረፈ አማርኛው።

እሷም ሣቅ ብላ "በጣም ነው ደስ የሚለው፤ የሰዉ ፍጥነት፣ ቤቱም የምግቡም ሽታ ቢሆን ... ግን ለምንድነው እዚያ ጋ የቀረበለትን ዳቦ የሚፈረፍረው?" ብላ ሳትጨርስ ሁለት ዳቦዎች የያዘ ጐድጓዳ የብረት ሳሕን ጠረጴዛቸው ላይ አሽከርክሮ ሄደ አስተናጋጁ፡፡

ልዑልም እየሣቀ "ስፐሺአል ስልስና ማኅበራዊ አዘናል በጣም አሪፍ ምግብ ነው፣ ራስሽ ነሽ ዳቦውን የምትፈረፍሪው .. ምክንያቱም የራስሽ እጅ ይሻላል። ነይ ታጥበን እንምጣ እጃችንን" ብሎ ይዟት ወደ ጓሮ ሄዱ። እጃቸውን ታጥበው ሲመለሱ አንደኛው ምግብ ደርሶ ጠረጴዛቸው ላይ አድርጎላቸው ሄዷል። እሱ እያሳያት ዳቦውን ፈርፍረው በሳሕኑ ውስጥ ሞላት። ማኅበራዊውን በትንንሽ ሳሕን ፊታቸው ከቀረበላቸው እርጎ ጋር በዳቦ እየበሉ ሳለ፣ ሌላው ምግብም ደርሶ ኖሮ ሳህን ውስጥ ያለውን ዳቦ ጨምሮ በማንኪያ እየማሰለ፣ በእጁም እያወዛወዘ ደባልቆ ፊታቸው ሲያስቀምጠው ምግብ ብሎ ዝም ሆነ። ቤቱ መቀመጫዎቹም ደማቅ፣ ግድግዳውም ደማቅ፣ ሰዎቹም ደማቅ፣ ምግቡም እጅ የሚያስቆረጥም ነበር። ይሄው ከዚያ ወዲህ ሰሎሜ በሳምንት አንዴ ወይ ሁለቴ ቁርስ መብላት ጀምራ አስተናጋጆቹም ዐውቀዋታል። ዘመናዊ ቁርስ ቤት ይባላል ቤቱ።

ሥራዋ ከሞላ ጐደል እየተያያዘ ነው። የአያቷና የነሶስና ናፍቆት አላስቀምጥ ስላላት አዲሳባ ለመሄድ አስባለች። ወይዘሮ መገርቱ ጊምቢ በሚኖሩ የእኅቶቻቸው ልጆች መካከል ችግር ተፈጥሮ እሱን ለመዳኘት እንደሄዱ አልተመለሱም። በስልክም እንደፈለጉ ስለማይገናኙ የአያቷ ነገር ሰሎሜን ዕረፍት ነሥቷታል። በተለይ ባለፈው ታመው ከተነሡ በኋላ ብዙም ጤና የላቸውም። መጀመሪያ በነበራት ዕቅድ መሠረት ጊምቢ ሄዳ ቆይታ ነበር መጽሐፉንም ለመጀመር ያሰበችው። እማማ መገርቱ ከመላኩ ጋር እንደሚቀራረቡ ስላወቀችና በጉዳዩ ጣልቃ ልግባ ማለታቸው ስለማይቀርም ነው መቀሌን የመረጠችው። ሥራዋን እዚህ መሥራት እንደምትችል ስታውቅ መቀሌ መምጣቷን የበለጠ የተሻለ አድርጎ አሳያት። አያቷን አቶ አጽበሃንና ዘመዶቿንም ለማወቅ መቻሏን ሌላ ምክንያት አድርጋ ብታስብም፣ ዋናው ምክንያት ግን ከመላኩና ከሶፊያ መራቅ ነበር።

መላኩ ወደ አሜሪካ ከመሄዱ በፊት ስንክሳርን ሊያገኛት የቻለው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነበር። እሱንም በስንት ውጥረት። እሷም ምናልባት ከጥቂት ሳምንታት በኋላ መመለሷ እንደማይቀር ነገረችው። ሥልጠናው ሉውቪል ከተማ ኬንተኪይ ግዛት ውስጥ መሆኑን ሲነግራት እሷ ከምትኖርበት ከተማ ቅርብ በመሆኑ በልቧ ጮቤ ነው የረገጠችው።

በመሃል ከቢሮ ተደውሎለት ማውራት ጀመረ። የሷም ስልክ ጠራና ስታነሣው ክብሮም ነበር። ረቡዕ እንደሚገባ ያለውን የጉዞ ዝርዝር ነገራት። እሷም ክብሮም መሆኑን መላኩ እንዲያውቅ አሁንም አሁንም ስሙን እየጠራች ነበር ስታወራ የነበረው። መላኩም ክብሮም አዲስ አበባ ሊመጣ መሆኑ ስለገባው ነገሩ በጣም ሳያውቀው ቢረብሸውም ስሜቱን ለመደበቅ ታገለ። ስልኩን እንደዘጋች "ባክህ ክብሮም ነው። እሮብ ሊመጣ ነው። ለነገሩ አንተም አትፈልግም እንጂ ታየው ነበር። ሰሎሜን ሰርፕራይዝ ሊያደርጋት ነው። ፊቃዱን አጨናንቆ ነው የሚመጣው። እንዲያው መጥፎ አጋጣሚ ሆኖ እንጂ እኮ እንዴት ዐይነት ጥሩ ልጅ

መሰለህ?" አለች ከመላኩ ጋር እያወራች እንዳለች በከፊል ረስታ፡፡

"ኡፍ...ፍፍ አታድክሚኝ እስኪ ... አሁን እኔ ምንም ጊዜ የለኝም። አንቺም ለክብሮምሽ ተዘጋጂ... በቃ ስደርስ እደውላለሁ። እሺ, take care በቃ እኔም አሁን ልሂድና የቀሩኝን ነገሮች ልጨራርስ። ደግሞ ዳኒን ሰላም በይው።" ብሎ ውስጡ ያፈነው ስሜት ሳያመልጥ ስንክሳርን ተሰናብቶ ከቢሮ ያሉትን ዶክመንቶችና አንዳንድ የሚፈልጋቸውን ዕቃዎች ለመውሰድ ሄደ። ቢሮ እንደገባም በቀረችው ጥቂት ጊዜ ከፎዚያ ጋር ቁጭ ብለው ያለውን ሥራ አስረከባት።

"ምንም ችግር ቢኖር ኢሜይል አድርጊልኝ። እኔም በሳምንት ምናምን እደውላለሁ። እምም እንግዲህ የድሬደዋውን ፕሮጀክት አደራ። እንኪ እነዚህ የቢሮ ቁልፎቹ ናቸው። ሌላ የረሳሁት ነገር ይኖር ይሆን?" አለ እንደቆመ፡፡

"አይ አይመስለኝም። አትጨነቅ። የሚያስፈልግ ነገር ካለ እነግርሃለሁ እንዳልከው። አይዞህ አንተ ተረጋጋ፣ ደግሞ ትንሽ አረፍም በል። ያው አሳሀ ያውቃል ማራንም በተመለከተ።" አለች እጁን እንደ ጨበጠች፡፡

"እሺ ፎዚ በርቺ..." ብሎ ተከታትለው ወጡና መኪናው ድረስ ሸኘችው።

መላኩ ለነመዐዛም በድንገት ወደ አሜሪካ እንደሚሄድና አንድ ሁለት ወር እንደሚቆይ ነግሮአቸው በስልክ ተሰናበታቸው። ማታ ላይ አየር ማረፊያ ሶፊያና ማርቆስ አደረሱት። እሱን ካደረሱት በኋላ እነሱ አብረው አመሹ። ማርቆስ በማራ አደጋ ውስጡ በከፍተኛ ደረጃ ተናውጧል። ማርቆስ ለማራ የተለየ ፍቅር ነው ያለው። በጣም ታሳዝነዋለች። 'እንዴት ምንተስኖት ላይ እንደወደቀች ያልተፈታልኝ እንቆቅልሽ ነው' ነው ይላል። ነገሩን በይበልጥ ባሰላሰለው ቁጥር ደግሞ "ስፍር ቁጥር የሌላቸው ምንተስኖቶች ደግሞ ማራዎችን እንደማጥመድ የሚቀናቸው ነገር ሊኖር አይችልም። ሚዳቋና ነብር ማለት ናቸው። የወላጅ ትልቁ ኀላፊነት ልጅን ጨዋና ጉበዝ ተማሪ አርጎ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ብልጥና ጠንቃቃም ማድረግ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ልጆችን እየተሳሳቱ እንዲማሩ ዕድል መስጠት ያስፈልጋል። የራሳቸውን ውድቀት ደብቀው በልጆቻቸው ስሕተት ሁሉ ላይ አለንጋ የሚመዙ ወላጆች የራሳቸውን ስሕተት በልጆቻቸው ይደግማሉ።" ወደሚል ድምዳሜ ደርሷል።

ስንክሳር ከመላኩ እንደተለያዩ ብዙም ሳትቆይ ነበር የመላኩን በአደጋው ምክንያት ድንገት ወደ አሜሪካ መሄድ ለሰሎሜ የነገረቻት። ነገሩ በሰሎሜ ላይ ግርታ ቢፈጥርባትም፣ ብዙም ስሜት እንዳልሰጣት አድርጋ የወሬውን ርዕስ ቀየረችው። ከዚያም የባጥ የቆጡን አውርተው በዕቅዳቸው መሠረት መቀሌ ሐሙስ እንደሚገናኙ ተነጋግረው ስልኩን ዘጉት።

እሮብ ክብሮም አዲሳባ ሲገባ ስንክሳርም እሱን ተቀብላና ራት አብልታ ሆቴሉ ከገባ በኋላ ሰሎሜ ጋ ደወለች። የክብሮምን መምጣት ነግራት ፈጽሞ

ልታስደነግጣት አልፈለገችም። ምክንያቱም ከክብሮም ጋር ያላቸው ግንኙነት አሁንም ገና ያልተፈታ ስለሆነ ውጤቱ ጥሩ አይሆንም ብላ ስላሰበች ነው። ስለ ነገ ጉዞዋ እያወሩ እንዴት አድርጋ ነገሩን እንደምትነግራት ማሰቧን ቀጥላለች፡፡

"ሰሊ በጣም የማትጠብቂውን የሩቅ አገር እንግዳ ነው ይገርልሽ የምመጣው" ስትላት፣

"በናትሽ እኔ እንደዚህ ዐይነት ሰርፕራይዝ አልወድም ... ማነው?" አለች መላኩ እንደማይሆን ተስፋ እያደረገች።

"እስኪ ገምች... ካወቅሽ ትልቅ ቸኮሌት ነው ሽልማትሽ" አለች የካንገት በላይ ሣቋን እየሣቀች

"በናትሽ ስንኪ ... እኔ መገመት አልችልም ... ማነው? .. ከየት ..?"

"እሺ ፍንጭ ልስጥሽ ... ካሜሪካ.." ስትል ለቅጽበት ክብሮም ቢመጣባትም አያደርገውም ብላ ላፏ ያህል፡፡

"ማን ማሚዬ ናት?" አለች፡፡

"ደርሰሽበታል ... ከዚያው ነው... አላስለፍልፍሽ ...ክብሮም ነው። በቃ እኔ እንኳ መምጣቱ ብዙም አልታየኝም ነበር። እሱ ግን መተኛትም አልቻልኩም ... ከቤተ ሰቦቿም ጋር እንደዚህ መራራቁ አስጠልቶኛል። ስለዚህ ይቅርታ ልጠይቃት እፈልጋለሁ ብሎ ነው የመጣው። ምንም ብለው እምቢ አለኝ። አትንገሪያት ብሎ አስምሎኝ ስለነበር በቃ መንገሩም ከበደኝ። ሰርፕራይዝ ሊያደርግሽ ነው እሱ የፈለገው። ግን ሳስበው ጥሩ ስላልመሰለኝ ነው።" አለች።

ሰሎሜ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ፣ "ምን ዐይነት ነገር ነው በናትሽ አሁን ይሄ ምን ያደርጋል? ... በቃ ማን በሱ ላይ ቂም ያዘ። ምን ዐይነቱ ሙዝዝ ያለ ልጅ ነው ባካቹ? መቼም ይሄ ያንቺ ሥራ እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ" አለች እየናደዳትም ደግሞ ይህንን ሁሉ ርቀት አቋርጦ መምጣቱም እየሳዘናት። "አንቺ ምን ነካሽ! እንዴት እኔ እንደዚህ አደርጋለሁ? ማሰብሽ ራሱ ይገርማል። ላንቺ ሳልነግር እንዲህ አደርጋለሁ። አዝናለሁ እንደዚህ በማሰብሽ።" አለች ድምፅዋን እንዳዘነና እንደተቀየመ በማድረግ፡፡

"አይ ታዲያ ምን ልበል! አንቺ ራስሽ ሐሙስ እመጣለሁ ብለሽ የኔን ዕቅድ አጥብቀሽ ጠይቀሽኝ ነበር ትዝ ይልሻል? ተዪው ያው ስለ መሰለኝ ነው። ያስቀይምሻል ብዬ አይደለም። ግን በቃ የቸገረው ሰው የማያስበው ነገር የለም። ይቅርታ ስንኪ፣ እንዴትም እንደማስብ የማውቅ አይመስለኝም ባክሽ። አሁን ምን ይባላል? እና ነገ ነው የምትመጡት? ምን ዐይነት ጣጣ ነው ባካቹ።" አለች የምር ግራ ገብቷት፡፡

"በናትሽ ድክምክም ብሎት እንዴት ኗንዳሳዘነኝ። ተረኛ ሆኖ ውሎ አድሮ ነው በዚያው አውሮፕላኑ ውስጥ ተኝቶ የመጣው። አሁን እኮ ነው ሆቴሉ ጥዬው

የመጣሁት።" አለች ሰሎሜም እንድታዝንለት ስስ ልቧን እየኰረኰረች።

"ምን ይደረጋል አሁንማ እዚህ ድረስ መጥቶአል። ለመሆኑ ለነማሚና ለሕያው ነግሮአቸው ይሆን? ምን ይባላል አሁን። አንቺ ግን እዚህ እመጣለሁ ያልሽኝ ከሱ ጋር ያቀዳችሁት ዕቅድ ነው እንዴ? መቼም ጉዳዩን ዛሬ ነው ያወቅሁት እንደማትይኝ ነው?" አለች አሁንም ስንክሳር በነገሩ ከውጥኑም ጀምሮ ልትኖርበት እንደምትችል ልቧ እየተጠራጥረ።

" እኔ አንቺ ጋ መምጣቴ ከበፊትም የነበረኝ ሐሳብ ነው። ማለቴ የሱንም መምጣት ዛሬ አይደለም ያወቅሁት። በቃ ሙዝዝ አለ ካልመጣሁ ብሎ። እቤትስ ምን ይላሉ? ብለው ሳያውቁ ድንገተኛ ፈቃድ ወስጄ መምጣት እችላለሁ አለኝ። ገና ከመጀመሪያ ብነግርሽ ደግሞ ያው ደውልሽ ቅር ትይዋለሽ ወይም አይ ዶኖ ... በቃ አትንገሪያት ብሎ ስለለመነኝም ... መሰለኝ አሳዘነኝ፤ .. ደግሞም ሳታውቂ መቀሌ እንዲገኝ አልፈለግሁም ... ለዚህ ነው አሁንም ቢሆን የምነግርሽ ..." አለች ሰሎሜን የሚያነቃ ነገር እንዳይፈጠር እሷም ግራ የገባት በሚመስል ድምፅ፡፡

"አይ እንግዲህ ምንም አይደለም ... አሁንማ ምን ይደርጋል .. በቃ እንግዲህ አሁን እዚህ ከሆነ ምን ይደረጋል? እና ነገ ጠዋት አብራችሁ ነው የምትመጡት ማለት ነው? ሆቴልስ ?..." አለች መምጣቱን የተቀበለ በሚመስል ድምፅ፡፡

"እኔንጃ እዚያ የትኛው ነው አሪፉ ሆቴል? ከቻልሽ እስኪ ለኔም ለሱም አስይዢልን... እምን ነገ ጠዋት አራት ሰአት ላይ እንደርሳለን።" አለች ነገሩን ቀለል አድርጋ፡፡

"ኦኬይ ወይ አክሱም ወይ አብርሃ ካስትል ያርፋል። አንቺ እንኳን እዚሁ እያቴ ጋ ከኔ ጋር እንሆናለን።" አለች ሰሎሜ። ሰሎሜ ትንሽ ከተረጋጋችበት ሕይወት እንደገና የሚበጠብጣት ነገር እንዳይፈጠር ሥጋት አድሮባታል። ክብሮምን ለማግኘት ባትፈልግም፣ ባንድ በኩል ነገሩ ቢስተካከል ለሁሉም ጥሩ እንደሆነ አሰባለች። ሌሊቱን ብዙም እንቅልፍ ሳይዛት ነበር ያደረችው። ስትቃዥና የሚያስፈሩ ህልሞችን ስታይ ስላደረች ጠዋት ስትነሣ ደክሞአት ነበር የነቃችው።

መቀሌ ሰሎሜና ክብሮም መጀመሪያ ሲገናኙ ጭንቅ የሚል የዝምታ ድባብ በመካከላቸው ሰፍኖ ቆዩ። ሰላምታቸውም እንደነገሩ ነበር። እንቅልፉም ድንጋጤውም ግራ መጋባቱም የተጫነው ክብሮም ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለበት አላወቀም። ስንክሳር ነገሩን ቀለል ለማድረግ ያልሞከረችው ነገር አልነበረም። በመጨረሻም መቀሌ የምታውቀውን አንድ የወንድሟን ጓደኛ ደውላ ለመጠየቅ በሚል ሰበብ ለብቻቸው ተወቻቸው። ቀስ በቀስ የሆነውን ነገር ካወሩ በኋላ ክብሮምም ልባዊ ይቅርታውን ጠይቆ ትንሽ ቀለል ብሎአቸው ማውራት ጀመሩ።

ያደረገውን ሁሉ ባለማወቅና ከልቡ ስለሚወዳት ብቻ እንደሆነ ነግሮአት ከዚህ በኋላ ግን እንደዚህ ዐይነት ጥፋት እንደማይደገም እንባ ባቀረሩ ዐይኖቹ እያያት ነገራት። ነገሩ ልቧን ስለነካው እሷም ይቅርታዋን በሙሉ ልቧ ነው ያደረገችለት። ስላሳዘናትም ደስ እንዲለው የምትችለውን ሁሉ ማድረግ ጀመረች። መምጣቱን ለሕያውም ሆነ ለእናቷ አለመንገሩ ደስ ብሏታል።

ክብሮምና ሰሎሜ ወደ አዲስ አበባ ከመመለሳቸው በፊት ከትንሽ እኅቷ ጋር አክሱም ደርሰው ተመለሱ። ጉብኝታቸው ካሰበችው በላይ ነበር ያዝናናት። የአክሱም ሐውልቶችና የንግሥት ሳባ መዋኛ፣ የነገሥታቱ የካሌብና ገብረመስቀል የምድር ውስጥ መቃብር ሁሉ ምጥቀቱ ገርሟታል። ሳታስበው የመላኩን ጽሑፍ አስታወሳት። የሃ ሆቴል አፋፍ ላይ ሆኖ የአክሱምን ከተማ ማየት ራሱ አንዳች ፍሥሓን ይሰጣል። አዲስ የተሠራው ዩኒቨርስቲም ከከተማው ወጣ ብሎ ከባሻገር ይታያል። አክሱም ጽዮን ገብተው ሲያዩዋት፣ ከሩቅ ሲመለከቷዋትም የውበት ሁሉ መደምደሚያ ሆና ከተማውንም፣ እያሌ የቀድሞ ነግሥታትንም አንግሣ ትታያለች። የሙሴ ታቦት ላለፉት ብዙ መቶ ዓመታት መኖሪያው እዚህ እንደሆነ ይነገራል።

ከመቀሌ ተመልሰው አዲሳባ ሲደርሱ መጣላታቸው ቀርቶ ፍጹም ጓደኛሞች መስለው ነበር። አክስቷንና ዘመዶቿን ሁሉ የሕያው ጓደኛና አብሮ አደጋቸው ነው እያለች አስተዋወቀችው። ሶስና እምብዛም አልተጠጋችውም። ልጆች አዋቂዎች ሲያድጉ የሚጥሉት ያለመረጃ ሰውን የሚያውቁበት አንቴና አላቸው ይባላል። ስንክሳርም በበኩሏ ሶስናን ለመቅረብ ብዙ ብትሞክርም ያን ያህል አልቀረበቻትም። አዲሳባ ሁለት ቀን አድሮ ክብሮምም ወዳሜሪካ ደስ ብሎት ተመለሰ። እንደገባም በሰላም መግባቱን ደውሎላቸዋል። ስለ ሶፊያ ምንም አለመጠየቁ ሰሎሜን ቢከነክናትም፣ አለመጠይቁ እፎይታን ፈጥሮላታል። ስንክሳር ናት አውጥታ አውርዳ አለመጠየቁ እንደሚሻል የወሰነችው። ሰሎሜን ወደ መቀሌ ከመሸኘቷ በፊት የንግድ ሥራዋ ትንሽ እየተበላሸ እንደሆነና የሷን መኖር የሚጠይቁ አንዳንድ የምትፈርምባቸውም ነገሮች ስላሉ፣ ከአንድ ወይም ከሁለት ሳምንት በኋላ አሜሪካ መሄድ ሳይኖርባት እንደማይቀር ነገረቻት። ስንክሳር መሄዷን እንደምትጠላ ሆና ነው ነገሩን የነገረቻት። ሰሎሜም የሷ መሄድ እንዴት እንደሚያጎድላት ነግራት በሌላ በኩል ደግሞ ለነትዬ ሕይወት ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ ተነጋገሩ።

ያው እዚህ ካሉት ቤተ ሰቦቿም ጋር ስለተዋወቀ ማወቃቸው አይቀርምና ብላ የክብሮምን መምጣትና የሆነውንም ሁሉ ለእናቷዋ ነግራቸው ጉዳዩን በስፋት አጫወተቻቸው። ለምን ሳይነግራቸው እንደመጣም ምክንያቱን ልታስረዳቸው ሞከረች። አብረው አክሱም እንደሄዱ፣ አዲሳባም ከዘመድ ጋር አስተዋውቃው ሁሉም እንደወደዱትና ደስ ብሎት እንደተመለሰ ነገረቻቸው።

በልደቷ ቀንም የተፈጠረውን ነገር በተለይ የቀለበቱን ነገርና እንዴት እንደሳማት ስትገልጽላቸው፣ "አይ ጢጊዬ በርግጥ ልክ አይደለም። አንዳንዴ ግን ፍቅር የያዘው ሰው እኮ እውር ነው። አትፍረጂበት። አንዳንዴ ግን ዝም ብዬ ሳስበው እንደሱ የሚወድሽና እኛም የምናውቀው ጥሩ ሰው እኮ ማግኘቱ ቀላል አይደለም። እንዲያው አንቺ በሕይወትሽ ሌላ ሰው አለ? ወይስ በቃ ዝም ብለሽ ወንድሜ ነው እሱን አላገባም የሚለው ስሜት ነው እሱን እንድትገፊው የሚያደርግሽ?" አሉ ዕድሉን ካገኘሁ አይቀር ብለው ብዙ ጊዜ ያብሰለሰላቸውን ጥያቄ አውጥተው፡፡

"ማሚ ... እንዴት እንደምነግርሽ አላውቅም። በጣም የምወደው ልጅ ነበር እዚህ። ብዙ ነገሩ ሶለንን ነው የሚመስለው። መልኩ ሳይሆን አስተሳሰቡ፣ ደግነቱ በቃ ምን ልበልሽ! ከሱ ጋ ሳወራ ወይ ከዳዲ ጋር ወይ ከሶለን ጋር ያለሁ ነው የሚመስለኝ። እሱም ለኔ ተመሳሳይ ስሜት ያለው ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን አሁን ሳየው አልመሰለኝም። ይባስ ብሎ እኔ እዚያ ሆኜ ትዝ ይልሻል ያቺ የሶለን ጓደኛ የነበረችው ሶፊያ?" አለች ባትሪ እየጨረሰ ያለውን ስልኳን ከቻርጀሩ እየሰካች፡፡

"አዎን እንዴት ረሳታለሁ፣ ታዲያ እሷም እዚያው ኢትዮጵያ መጥታ የለም እንዴ?" አሉ ከምታወራላቸው ነገር ጋር ምን እንደሚያይዘው ግራ ገብቶአቸው።

"አዎን ... አንዳንድ ነገር እንዲረዳት ብዬ የሱንና የጓደኛውን ስልክ ሰጥቻት ነበር። በቃ ባጭሩ ከሷ ጋር እፍ ብለው በያገሩ መዞር ሁሉ ጀምረዋል። " አለች ስሜቷ ወደ ንዴት እያዘነበለ። ሰሎሜ ያልተረጋገጠ ወሬና በሰው ላይ መጥፎ ማውራት ፈጽሞ አትወድም። እስካሁንም ነገሩን ከማንም ጋር ላለማወራት የወሰነችው ከዚያ የተነሣ ነበር። አሁን ግን አልቻለችም። ልቧንና አጥንቷን የሰበረውን ነገር ነው ለናቷ የምትነግረው። ይሁን እንጂ እውነቱን አይቀይረውም፤ ይሄም መሠረቱ ቢስ ወሬ ማዛመት ነው። ብዙ ክፉ ወሬ የሚዛመተውና ሰዎች ባልሆነ ምክንያት ሌላውን የሚጠሉት በዚሁ በየዋሆች ወሬ ነው።

"እኔ እኮ የልጄ ሞት ምክንያት ከሆነች በኋላ አንቺ አልሽ እንጂ ቀልቤም አልወደዳትም። እሱም ደኅና ሰው ቢሆን እንዲህ ሊያደርግ አይችልም። ደግሞስ በምን ዐይነት ፍጥነት እዚህ ውስጥ ገቡ? አይ የዘንድሮ ልጆች!! እኔ የምለው ነገሩን ራስሽ አረጋግጠሽ ነው ወይስ የሰው ወሬ ሰምተሽ? ማለቴ አሁን የምትይኝ ነገር እውነት መሆኑን እንዴት አወቅሽ?" አሉ እሳቸውም እየተናደዱ፣ የተወሰነ ጥርጣሬም አድሮባቸው፡፡

"አይ በቃ እኮ ዘግቶኛል፣ ከመጣሁ እንኳ እንዴት ነሽ ለማለትም አልደወለልኝም። ለወንድሜም ልቅሶ አልደረሰም። ደግሞ ለስንክሳርም የሚነግራት ነገር ... በቃ ተይው እሱን ሳወራውም ነው ራሴን የሚያመኝ። የሱን ጉዳይ እንተወው። ግን ማሚዬ እንዲያው በናትሽ አትደብቂኝ፣ አንቺ ብትሆኚ አሁን በኔ ቦታ ምን ታደርጊያለሽ? እውነቱን ንገሪኝ" አለች የምር ግራ ገብቶአት፡፡

"ጢጊ .. መቼም እውነቱን ንገሪኝ ካልሽ ... እኔ ክብሮምን የመሰለ ፍቅሩ የማይለወጥ ታማኝና ደግ ሰው ብዙ ያለ አይመስለኝም። ደግሞ የተማረ፣ ቤተ ሰብ የሚወድና ትሑት ልጅ ነው። እኛም ከልጅነቱ ጀምሮ እናውቀዋለን። ያደረገውንም ሁሉ ያደረገው ስለሚወድሽ እንጂ ለክፋት ብሎ አይመስለኝም። ያው አንቺ ነሽ የምትወስኚው። እኔም ሆንኩ አባትሽና ሒያው ከዚህ የተለየ አናስብም።" ብለው ምኞታቸውን ለሰኑት። በርግጥ መጥፎ አለመሆን ጥሩ መሆን ነው ወይ? ጥሩስ መሆን ሁልጊዜ ትክክለኛ ያደርጋል? ይህ አመለካከት የሶለንን አመለካከት የሚመስል ሲሆን፣ የሰሎሜን ልብ ግን በመጠኑም ቢሆን ወደ ክብሮም ያዘፋት ይመስላል እናቷና ስንክሳር። ከእናቷ ጋር ካወራች በኋላ ሰሎሜና ክብሮምም መደዋወል ጀምረዋል ቀስ በቀስ። ስለ መላኩ ማሰብም አትፈልግም። ሆኖም ራሷን ሳታስበው ስለመላኩ ስታስብ ታገኘዋለች።

ስንክሳር ሶፊያን ብቻዋን ነው አሁን የምታገኛት። ሶፊያም በምትሠራው ሥራ የምትባክን ስለሆነ ብዙ ጊዜ አይገናኙም። ስንክሳር ወደ አሜሪካ በቻለችው ፍጥነት ሄዳ ያሰበችውን፣ መላኩን ወደሷ መሳቡን ሥራ መጀመር እንዳለባት አውጠንጥና ጨርሳለች። አሁን እርሱ በሥልጠና ምክንያት እሷ ከምትኖርበት ከተማ በጣምም ሩቅ በማይባል ከተማ ነው ያለው። እሱ እዚያ መኪና ስለማይነዳ ከሱ ጋር ብዙ ጊዜ ማጥፋት እንደምትችልና የመጨረሻዋን ግብ ለማስገባት ኳሷ በጇ እንደሆነች ርግጠኛ ሆናለች። ከዚያ በፊት ግን በተከላካይ መሥመር አስቸጋሪ የሆነ አጥርን ማለፍ እንዳለባትና ይህ ተከላካይ ተጫዋችም በጣም የምትፈራው፣ ያሸናፊነቷን ዋንጫ መንጠቅ የሚያስችል የማጥቃት ችሎታም ያለው እንደሆነ ታውቃለች።

ማርቆስን በቀይ ካርድ ከመላኩ ሕይወት ካስወጣች ሁሉ ሊሠምር እንደሚችል ነው ያመነችው። ስለዚህ ከሶፊያ ስልኩን ወስዳ ደጋግማ ደውላለት ልታገኘው ሞከረለች። ከሁለት ቀን በኋላ ቆይቶ ደወለላት። ላንድ ጥብቅ ጉዳይ እንደምትፈልገውና ምናልባት በቅርብ ጊዜ ውስጥ እሷም ወደ አሜሪካ ስለምትመለስ ሳትሄድ ብታገኘው መልካም እንደሆነ ጠየቀችው። በማግስቱ ለቁርስ ሊያገኛት መድሃኔዓለም አካባቢ ቃተኛ ተቀጣጠሩ። እሱም ሊያገኛት ሰበብ እየፈለገ ነበር። ሰሎሜንም መላኩንም እየቀረበች ልታስታርቃቸው ምንም ዐይነት ሙከራ እንዴት እንዳላደረገች ከንክኖታል። ያደረገችው ሙከራምካለ ማወቅ ፈልጎአል። ካልሆነም እሷ የምታውቀውን ነገር ከሷ ለማወቅ ሲመኝ ነበር። አንዳንዴ ምን የሆነች አይጥ የድመትን አፍንጫ ታሸታለች ይባላል።

የተነጋገሩበትን ጉዳይ ለመላኩ ሊነግረው ይችላል ብላ ስላሰበችና መላኩም የማያውቃቸውን ነገሮች ላለማውጣት በጣም መጠንቀቅ እንዳለባት ዐውቃለች። ማርቆስ ደግሞ ነጋዴ መሆኑን እንጂ ምን ዐይነት አስተሳሰብና ነገሮችን የመረዳት ችሎታ እንዳለው አታውቅም። እዚህ አገር ንግድ እንደምታስብና ምክር ፈላጊ መስላ ነው የቀረበችው። እሱም ያላትን ጥያቄ ሁሉ እየመለሰ ወደ ዋና ጉዳዩዋ አስባ

እስክትገባ ሳይጠብቅ ደንገት ሳታስበው

" ስለ መላኩና ስለ ሰሎሜ ምን ታስቢያለሽ?" አላት።

ያላሰበችው ነገር ስለሆነ፣ "እኔንጃ ሁለቱም በጣም ጥሩ ልጆች ናቸው። በተለይ መላኩን ለረጅም ጊዜ ነው የማውቀው። እሷን እንኳን እሱ ነው ያስተዋወቀኝ፣ ያን ያህልም ብዙ አላውቃትም። ነገር ግን ጥሩ ልጅ ነው የምትመስለው። ቤተ ሰቧማ በቃ እንዴት ጥሩ ሰዎች መሰሉህ! ሚቹን ወንድሟን በጣም ነበር የምትወደው። በመካከላቸው ምን እንደገባ አላውቅም፣ እሷም ስለሱ መስማት አትፈልግም፣ እሱም ስሟ ሲጠራበት ነው አንበሳ የሚሆነው። ስለዚህ እንጃ ምን ማሰብ ወይም ማድረግ እንዳለብኝም አላውቅም።" አለች የነገሩ አካሄድ ወዴት እንደሆነ ማወቅ እየከበዳት፡፡

"አይደል ... የሚገርም ነው! እንደሱ አስቤው አላውቅም ነበር ... እንዳልሽው በመካከላቸው የገባ ነገር ሊኖር ይችላል ማን ያውቃል..? አንቺ ለማስታረቅ ወይም ተገናኝተው እንዲያወሩ ለማድረግ የሞከርሽው ነገር ነበር?" ብሎ ዝም አለ። አካሄዱ ደስ አላላትም፡፡

"እንዳልኩህ ሁለቱም ሙዝዝ ብለው አታንሺብኝ ስላሉኝ ተስፋ ቆርጬ ተውኩት። በጣም ነው እኮ የሚያሳዝነው እንዴት ሁለት ጥሩ ሰው እንዲህ ሊሆን እንደሚችል። ግን አንተ የሞከርከው ነገር የለም ነገሩን ለመረዳት? ምናልባት እኮ አብረን ብንሞክር የተሻለ ይሆናል አንዳችን የማናውቀውን ሌላችን ልናውቅ ስለምንችል። እሱ ላንተም ምንም ያለህ ነገር የለም?" አለች የተጨነቀ በሚመስል ገጽታ፡፡

"እም ም ... ምንም ልክ አንቺ እንዳልሽው ነው... መስማትም መናገርም አይፈልግም። ግን ያንቺ አሳብና ግምት ምንድነው?" አለ ማርቆስ አሁንም አይን አይኗን እያየ። ሰዎች አይን አይናቸውን ሲያዩዋቸው መዋሸት ይከብዳቸዋል፣ ከዋሹም ያስታውቃሉ ይባላል። ቀላል ሰው እንዳላጋጠማት አውቃለች። ብዙ የማያወሩ ግን ብዙ የሚያስወሩ ሁሌም አስቸጋሪ ሰዎች እንደሆኑ ታውቃለች። መሳሳት ስላልፈለገች፡፡

"ምን አሳብና ግምት አለኝ ብለህ ነው ... ይሄ እኮ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው እነሱም የሚያውቁት አይመስለኝም" ስትል አሁንም ካፏ ቀበል ብሎ፡-

"የምትገርሚ ልጅ ነሽ። አስተያየቶችሽ ሁሉ ነገሩን እኔ አይቼው በማላውቀው አቅጣጫ ነው እንድረዳው ያደረጉኝ... ህም..." ብሎ ዝም ሲል ነገሩ በፈጠረባት ጉጉትና አንዳች የማይመች ስሜት፡-

"ምኑ? ማለቴ የቱ አስተሳሰብ?" ስትል፣

"ማለቴ እነሱም የሚያውቁት አይመስለኝም ያልሽው። እውነት እኮ ነው ... እነሱም ላያውቁት ይችላሉ። ግን ደግሞ ይህንን የሚያህል ገደል በመካከላቸው ሲፈጠር ቅድም እንዳልሽው የሆነ ነገር በመካከላቸው ገብቶ መሆን አለበት።" ብሎ በድጋሜ እያጤናት ዝም አለ። ማርቆስ ምን እደሚያስብ ለማወቅ አልቻለችም። ማርቆስን በሩቁ መያዝ ካልሆነ፣ ውጥኗን ሁሉ ፍርክስክስ ሊያደረግ የሚችል መዶሻ የያዘ ያህል ነው የፈራችው። ብዙም አላወሩም። ከዚያም ነገሩን እንደ ምንም እያላላች እያላላች ወደ ቢዝነሱ ሐሳብ አተኩራ ከመሄዷ በፊት እንደምታገኘውና ለሌላ ቀጠሮ እንደምትቸኩል ነግራው ተለያዩ። ማርቆስም የስንክሳር ድብስብስነትና ድሮውንም ለቧ ያለው ያልጠራ ስሜት ተጨማምሮ ምንም የማታውቅ መስሎ አልታየውም። ወደ አሜሪካ ደጋግማ መመላለሱዋም በነዝንተኛነቷ ምክንያት አልመስልህ ብሎታል። ቢዝነስ ብላ ልታማክረው ያነሳችውም ሐሳብ ልቧ ያለበት አለመሆኑን አውቆታል። በተለይ ሁለት የሚጋጩ ነገሮችን እየነገራት 'አይደል ... እኔም እንደሱ ነበር የማስበው' ስትለው ልቧ ሌላ ቦታ መሆኑን ተረድቶታል። የብልጎና የብልጣብልጥ ጦርነት የተጀመረ ይመስላል። በኋላም ሳትደውልለት በሶፊያ በኩል 'ይቅርታ በጣም ተወጣጥሬ ሳልደውልልህም ሳላገኝህም ሄድኩ' የሚል መልእክት ትታለት ወደ አሜሪካ ሄደች።

የሚቀጥለው አንድ ወር ያህል ጊዜ ብዙ ነገሮች የተለዋወጡበት ጊዜ ነበር። ሰሎሜ ከከብሮም ጋር ያላት ወዳጅነት ተሻሽሎአል። እናቷም ስንክሳርም የመከሩዋት ምክር ሥር ሰዶ ወደ አሜሪካ ለመመለስ ማሰብ ጀምራለች። ከከብሮም ጋር ብዙ ጊዜ ነው በስልክ የሚያወሩት። የከብሮምን ጥያቄ ስታስብበት እንደቆየችና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ዕድል ልትሰጠው እንደምትችል እያመነታች ነግራዋለች። የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ግን አብረው ትንሽ ጊዜ ማሳለፍ እንዳለባቸውና ጊዜ እንደሚያስፈልጋት ነው የነገረችው። ይህም እሱን ከልክ በላይ አስደስቶታል። ስንክሳር ይህን ስትሰማ በደስታ ሰከረለች። ከከብሮም ጋር ደስታቸውን ያከበሩት የሚቀጥለውን መላኩን በእጁ የማስገባት ድሏን ተመኝተው ነው።

አንዴ ካንሳስ አንዴም ሉዊቭል የሚመላለሰውን መላኩን የገንዘብም የብቸኝነትም ችግር እንዳያጋጥመው ስንክሳር የሚያስፈልገውን ሁሉ ታደርግለት ነበር። ካንሳስ ካልሄደ እሷ ጋ ኢንድያናፖሊስ ነድታ ትወስደውና አዝናንታ ሰኞ በጠዋት ትመልሰው ነበር። የአንድ ሰዓት ተኩል መንገድ ነው በመኪና። ሥልጠናውን ሊጨርስ ሳምንት ሲቀረው ከቅዳሜና ከእሁድ ጋር የአራት ቀን ዕረፍት ስለነበረው ወደ ካንሳስ መኪና እየነዳ ሊሄዱ ዐቅደው ስለነበር እሷ ጋ አደረ። በጠዋት ተነሥተው ጉዞ ስለጀመሩ አራት ሰዓት አካባቢ ጠዋት ነበር ሴንት ሊዊስ የደረሱት። እዚያ ትንሽ ቆይተው በሚሲሲፒ ወንዝ ዳርቻ ላይ የሚገኘውን ጌት ዌይ አርች ላይ ወጥተው አዩ። በ1963 በአውሮጳውያን አቆጣጠር ቢሆንም የተገነባው አሁንም ድረስ አሠራሩ ያስደንቃል። እላዩ ላይ የሚወጣባቸው የተለዩ አሳንሰሮች

ወደ ላይ ቀጥ ያለ ሳይሆን ከፊል ክብ ቅርጽ ባለው ደጋን ሐውልት ላይ የተሰሩና እያንዳንዳቸው አምስት ሰው አዝለው ወደ ጐን፣ ወደ ላይ እያዋዙ ሽቅብ ተወንጭፈው ጫፍ ላይ ስለሚያደርሱ እጅግ የሚያስገርሙ ናቸው።

እዚያው ከተማ ምሳ በልተው ወደ ከሰዓት ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ላይ ነው እነማራ ቤት የደረሱት። ማራ ከሆስፒታል ወጥታ እየገገመች ናት። ቁስሉ ሁሉ ባይድንም ከጠባሳ በቀር ምንም የአካል ጉድለት ወይም ቋሚ ጉዳት ስላልደረሰባት ሁሉም ደስ ብሎታል። ልጇ ግን አሁንም ከደረሰባት የአእምሮ መቃወስ ፈጽሞ አላገገመችም። ማታ ከራት በኋላ ማርቆስ ጋ ደውለው ብዙ አወሩት። ስንክሳር ሰላም ብላው ወዲያው ነበር ስልኩን ለመላኩ የሰጠችው። ይሄ ደግሞ ማርቆስን 'ሁለቱም ሳያውቁ የሆነ ነገር በመካከላቸው ገብቶ ሊሆን ይችላል' ብላ ራሷ የሰጠችውን የመላምት ሌንስ ወደሷ እንዲያዞር ሳይኰረኩረው አልቀረም።

ከካንሳስ ሲመለሱ እሑድ ከሰዓት ተነሥተው በዚያው በሴይንት ሊዊስ አድርገው ቀጥታ ነበር ሉውቪል የገቡት። እሱን ማረፊያው አድርሳ እሷም ወደ ቤቷ የዚያኑ ለት ማታ አቀናች። ከምሽቱ አራት ሰዓት ስለሆነ እደሪ ቢላትም አሻፈረኝ አለችው። ከሥልጠናው በኋላ ሁለት ሳምንት ማራ ጋ እንደሚቆይ ስለነገራት እሱን ተከትላ ወይም አብራው ወደ ኢትዮጵያ መሄዱ ሌላ እንዳይመስል ብላ ቀድማ ለመሄድ አስባለች። ነገሩን ቀድሞ የታሰበበት ለማስመሰልም ለሶፊያ በስልክ ነግራታለች። ማርቆስ ጆሮ እንዲገባ ብላ እንጂ ለሶፊያ የመንገር ምንም ሐሳብ አልነበራትም።

ሥልጠናውን ሲጨርስ መላኩን ሰርፕራይዝ ልታደርገው ላስቬጋስን ልታስጐበኘው ቲኬቱን ገዝታ ሁሉንም ነገር አመቻችታለች። ያንን የሳምንት መጨረሻ ሌላ ፕሮግራም እንዳይዝም ነግራዋለች። መላኩ የስንክሳር ደግነትና አብረው የሚያሳልፉት ጊዜ ብዛት ልቡን ሳይሸረሽረው አልቀረም። አንዳንዴ ረጅም ሰዓት አብረው እየተጓዙ ያወራሉ። በመጀመሪያም ጥላው አሜሪካ ስትገባ የልጅነት ልቧ አታሎአት ሊሆን እንደሚችል አስቦ ነገሩን አቅልሎ ለማየት እየሞከረ ነው። መልኳም ከመቼውም ይልቅ ያማረ መስሎ እየታየው ነው። የተዳፈነ እሳት ባይነድም አይጠፋም እንደሚባለው ቀድሞውንም ያለ ምክንያት አልወደዳትምና እሱም እያገረሸበት ሊሆን ይችላል።

ሰሎሜም ከክብሮም ጋር ከዕለት ዕለት እያደገ የመጣው ግንኙነታቸው ቀስ በቀስ መላኩን በከፊል ሳያስረሳት አልቀረም። አስቸጋሪ የሆነችባት ሶስና ናት። ብዙ የማይመለስ ጥያቄ አላት። አሜሪካ ስለ መሄድ ሲነገራትም መላኩስ ነው የምትለው። ሰሎሜም በዚህ ጊዜ የመቀሌውን ፕሮጀክት ለመጨረስ ብዙ አልቀራትም። የሶለን ግለታሪክ መጽሐፍ ግን ፊቀቅም አላለ። ከእናቷ ጋር ሲያወሩ እዚያው አሜሪካ ዐረፍ ብላ ልትጽፈው እንደምትችል ነው ያሰቡት። ሁሉ ነገር ከሠመረና ብዙም ሳይቆዩ ከክብሮም ጋር ለመጋባት እንደሚችሉም አውርተዋል። ይህንን ሁሉ ግን ለክብሮም አልነገረችውም። በጨዋታ መሃል ያንን የበፊቱን

ቀለበት ፈጽሞ እንዳልወደደችውና የምትወደው ዐይነትም ምን አይነት እንደሆነ እንደ ቀልድ እያደረገች ነግራዋለች። ክብሮም ዘንድሮ ሥልጠናውን ስለሚጨርስ እዚያው ቺካጎ ነው ለመኖር የሚያስበው። ቤት ለመግዛትም እያፈላለገ ነው፡፡

መላኩ ወደ አሜሪካ ሲሄድ የእጅ ስልኩን ማርቆስ ጋ ነበር ትቶ የሄደው። ምናልባት ከአፋር ስለ አባቱ ጉዳይ ቢደወል ብሎ በማሰብ። እሱ በሄደ በወር ተኩል አካባቢ ስልኩ ተደወለ። ስልኩን የደወሉት ሰው ከማርቆስ ጋር በቋንቋ የተነሣ በደንብ መግባባት ቢቸገሩም፣ የመላኩ አባት ለተወሰኑ ዓመታት ድሬዳዋ አካባቢ ይኖሩ እንደነበርና የሚተዳደሩትም በንግድ እንደነበር ገልጹለት። ሙሉ ስማቸው ሀሰን ሱሌማን እንደሆነም አዲስ መረጃ ሰጡት። ሆኖም በአሁኑ ሰዓት እዚያው ድሬደዋ መሆናቸውን በእርግጠኛነት እንደማያውቁ ገለጹለት። የተለያዩት ማርቆስ እንደሚደውልላቸው ነግሮአቸውና አመስግኖአቸው ነበር። መላኩ ነገሩን ማርቆስ ከነገረው በኋላ ደግሞ ደጋግሞ ቢደውልም፣ የሰውዬው ስልክ አልመልስ ብሎት ልቡ ስቅል ብሎ ከረመ። ፎዚያንም የድሬደዋ ልጅ ስለሆነችና ምናልባትም የሷም አባት በከተማው የታወቁ ነጋዴ ስለሆኑ ፍለጋው ላይ እንድትረዳው ደውሎ ነግሯታል። ስለዚህ እሷም ለቤተሰቧ ሁሉ ነግራ ፍለጋው ላይ በየአቅጣጫው ነው የተሰማሩት።

የመላኩ ሥልጠና ያለቀው በዚያው ሰሞን ነበር። ዕቃውን ሁሉ ከሉዊቪል በመኪና አጓጉዘው ስንክሳር ቤት አስቀምጠው ወዲያው ዐርብ ወደ ማታ ላይ ወደ ቬጋስ በረሩ። ወደ ላስ ቬጋስ እየበረሩ አውሮፕላን ውስጥ ብዙ ማውራት ችለው ነበር። ኢትዮጵያ የመመላለሷ ነገር አልገባ ያለው መላኩ፡-

"እንዴ አንቺ ምንድነው እንደዚህ አንዴ አዲሳባ አንዴ እዚህ? ትራንስፖርቱንስ እንዴት ነው የምትችይው?" አለ መላኩ ትንሽ ግራ ገብቶት።

"አይ ባለፈው ለማርቆስም ልመጣ ስል ነግሬው ነበር እዚህ ስልችት እያለኝ ነው። ከተቻለ ቢዝነስ እዚያ ጀምሬ እዚህ ቤቱንም ቢዝነሱንም ሸጬው ወደዚያ ለመግባትም እያሰብኩ ነው።" አለችው የምሯን ያሰበችበት በሚመስል የፊት ገጽታ፡፡

"ብራቮ ብራቮ! ... አንቺ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ከፈለግሽ ተስፋ አለን። በቃ ሁሉም ሰው ወዳገሩ መመለሻው እየደረሰ ነው ማለት ነው።" ብሎ ትከሻዋን እየነቀነቀ ቀለደባት፡፡

"ቀልድ መሰለሃል። እዚያ እኮ ሰላሙ፣ ረጋ ማለቱ በቃ ሁሉም ነገር ... እግዜርም ፊቱን ያዞረላት ይመስለኛል ያቺ አገር። በርግጥ ያው ብዙ ችግር አለ ሰው ተንኰለኛ ነው። ፊቱን እንጂ ልቡን አታውቀውም። እዚህ ስትኖር ደግሞ በቃ ብዙ ነገር ነው የምትማረው። የዋህነትህን ሰዎች ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ። ግን ያው እኛው ሄደን ነው የምንለውጠው።" ብላ ስትሰብከው ዐይኑን አፍጥጦ ነው ያያት። እሷና ንግግሯ ምን ያህል የተገላቢጦሽ እንደሆኑ ግን የልብ መነጽር ያለው ብቻ ነው የሚያውቀው።

ላስ ቬጋስ መላኩ ሁሌም መሄድ ይመኝ ነበር። 'ዘመናዊ ሰዶም' መስላ ነው የታየችው። ቁማሩ ገና ካውሮፕላን አየር ማረፊያ ውስጥ ነው የተቀበላቸው። የተከራዩትን መኪና ተረክበው ለማረፍ ወደ ያዙት ሆቴል ሄዱ። ያው የመላኩን ሕግ ስለምታውቅ ሁለት የተለያየ ክፍል ነበር የያዙት። ዐርብን ትልልቅ ሆቴሎች ባሉበት ስትሪፕ በሚባለው አካባቢ ላይ ለዐይን በሚያታክቱ በጣም ብልጭልጭና ወደ በሆኑ ሆቴሎችና የመቆመሪያ ካዚኖዎች ሲዞሩና ሲጎበኙ አመሹ።

ፓሪስ፣ ኒውዮርክ፣ ሞሮኮ፣ የግብጽ ፒራሚድ ምን የቀረ አለ... ሁሉንም በትንሽ በትንሹ ሠርተውታል። ከተማው ግን ሕይወት የሚያገኘው ጨለምለም ሲል ሲመሽ ነው። ከነዋሪው ቆማሪው ይበዛል። ጥሩ ራት በልተው ምሽቱን ሁሉ ሲዞሩና የሰዉን ጩኸትና ዕብደት ሲያዩ አለፉ። ግርግሩና ሁካታው ዐርብ ማታ ይብሳል። ባላጂዮ ሄደው በሙዚቃ የሚደንሰውን ፏፏቴ ሲያዩት የአዲስ አበባዋ የሸራተን እስክስተኛ ፏፏቴ ትንሽ ሆነችባቸው። በመጨረሻም ደክሞአቸው ስለነበር ሁለቱም ወደየመኝታቸው ሄዱ።

ቅዳሜ በሌሊት ተነሥተው ሳንዲያጎ ካሊፎርኒያ ነድተው ምሳ ሰዓት አካባቢ ላይ ደረሱ። ትልቁን የአራዊት መጠበቂያ ዙ ሲጎበኙ ቆይተው፣ ቀጥሎም ላሆላ የሚባለውን የሀብታም ሰፈር ጎብኝተው ሲጨርሱ ነበር ወደ ከተማዋ እምብርት የሄዱት። ሳንዲየጎ በውበቷም በአየሯም ምርጥ ከተማ ስለሆነች ነው ኑሮም ያንኑ ያህል የሚወደድባት። ራታቸውን በልተው በእግራቸው እየተንሸራሸሩ በባሕሩ ዳርቻ ብዙ ቆዩ። ሳይታወቃቸው እጅ ለጅ ተያይዘው በኋላም ተቃቅፈው ነበር በባሕሩ ዳር ሲዞሩና ሲቀመጡ የቆዩት። የሁለቱም ሰውነት መሞቅ ጀምሮአል። በተለይ እጅ ለእጅ መያያዙና እሱ በሷ አንገት ላይ፣ እሷ በሱ ወገብ ዙሪያ የጠመጠመቻቸው እጆች ደስ የሚል ጉልበትና ኀይል ወደየንዳንዳቸው ሰውነት ማንዘር ጀምረዋል።

አጠገብ ላጠገብ ወዳለው የሆቴል ክፍላቸው ከመግባታቸው በፊት መጀመሪያ ወደሱ ክፍል ውስጥ እያወሩ ገብተው ሶፋው ላይ ተቀመጡ። እሱ ቲቪ ሊከፍት ሲል፣ "መጣሁ መታጥቢያ ቤት ደርሼ በዚያውም ስላላበኝ ሻወር ነገር ወስጄ ፒጃ ቀይሬ ልምጣ" ብላ ወደ ክፍሏ ሄደች። እሱም የሞቀውን ሰውነቱን በረድ ለማድረግና ቀለል ቢለኝ ብሎ ሻወር ውስጥ ገባ። ሁለቱም ግን ሻወር ውስጥ ሆነው አንዳቸው ስለሌላቸው ማሰባቸው አልቀረም። ካንድ አርባ አምስት ደቂቃ በኋላ ስንክሳር መጣች። የለበሰችው ቀለልና ሳሳ ያለ ፒጃማ ሲሆን፣ የተቀባችውም ሽቶ ቀልብ የሚስብ ነበር።

"ዋው ... ሽቶሽ በጣም አሪፍ ነው" አለ መላኩ ባንዴ አካባቢውን ያወደውን ሽቶ ወደ ውስጥ እየሳበ

"ኦ ታንክ ዩ..." ብላ አጠገቡ መጥታ ተቀመጠች፡፡

ሳይታሰብ ትንሽ እየተጎነታተሉ መላፋት ጀመሩ። እሷ ሆዱን ስታሻሽ

እሱም ትንሽ ቦርጯን እየነካካ ሲቀልድባት የበለጠ ተቀራረቡ። ከዚያም ሳያስቡት አንዳቸው በሌላቸው እቅፍ ውስጥ ገብተው አተነፋፈሳቸውም ተቀየረ። አድራሻ የማይሳሳቱት ከናፍርት ድንገት ተገጣጠመው ነገሩ ወደ መሳሳም ሲቀየር እስቲማው ዘልላ ተነሣችና፣ "ይቅርታ መሌ ... የኔ ስሕተት ነው ... የኔ ስሕተት ነው። እንደዚህ ማድረግ የለብንም ... እኔ ነኝ ... በጣም አዝናለሁ ... ይቅርታ ... በጣም ይቅርታ" አለች ፊቷን በሁለት እጆቿ ይዛ። ከዚያም እሱ ቁጭ እንዳለ፣ እሷም ጉንቅላቱን እየነካካች በቆመችበት ቀረች። እሱም የሚለው ጠፍቶት... እንዳቀረቀረ ቆየና ድንገት ብድግ ብሎ ትከሻዎቿን በሁለት እጁ ያዝ አድርጎ ዕፍረት በተሞላው ገጽታ፣ "Oh goodness ... it is me ... am so sorry ... this is unbelievable... sorry ... እኔ ነኝ እንጂ አንቺማ ምን... ልክ ነሽ ... ልክ ነሽ ... Sorry!" ብሎ ትንሽ ፈንጠር ፈንጠር ብለው ተቀመጡ። ከተወሰነ የጸጥታ ጊዜ በኋላ ለአፍታ አጥለቅልቆአቸው የነበረው የስሜት አዙሪት ሲለቃቸው ሌላ ዙር ንዝረት ሳይመጣባቸው እንደምንም ብሎ ቆመ፡፡

ወዲያውም "በቃ ስንኪ... አሁን መተኛቱ ይሻላል... ነገ እናወራለን አሁን እንተኛ ..." አለ የማዱን። መለያየቱን ባይፈልግም፣ ባንድ በኩል ኀሊናው እንደ ጦር እየወጋው። ወጥታ ስትሄድ እሱ "ወይ አምላኬ ... ምን ውስጥ ነው የገባሁት...! " እያለ በጸጸትና በግራ መጋባት ክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ብሎ መጨረሻ ላይ ፊቱን በቀዝቃዛ ውሃ ታጥቦ በቀጥታ ሶፋው ላይ ዘፍ ብሎ ቁጭ አለ። አሁንም የስንክሳር መዐዛ አካባቢውን እንዳወደው ነው። ተነሥቶ ወደ መስኮቱ ተጠግቶ ወደ ውጪ እየተመለከተ ግራ እንደገባው በሐሳብ ነጎደ። ስንክሳር ደግሞ የበሯን ቁልፍ ቆልፋ እጇን እንደጨበጠች በድል አድራጊነት "yes! Yes! ስንኪ ... በቃ እኮ ልጁ በጅሽ ነው...፥ መሌ ... ከነጎፈሬው ያንቺ ሆኗል" ብላ ዘላ አልጋው ላይ ራሷን ዘረረችና በጀርባዋ ተንጋላ የሚሰማትን ተድላ እያጣጣመች "አንተ ምን ይሳንሃል .... ጌታዬ! ..." አለች የቱን ጌታ እንደሆነ ባይታወቅም።